ኢማም ነወዊ

ሪያዱ-ሷሊሒን

ከቁጥር 1-84 ሐዲስ

ቅጽ 1

ነጃሺ ኢስላሚክ አማራጭ
ስልክ 0[illegible] ፋክስ 0[illegible] ኦሮሚያ አዲስ
e-mail: najashi@[illegible]

ሪያዱ-ሷሊሒን

ከቁጥር 1 - 84 ሐዲስ

ቅጽ 1

አዘጋጅ
ኢማም ነወዊ

ትርጉም

ነጃሺ አሣታሚ ድርጅት

prepared to you by @Smatch81

የፊያዱ-ሷሲሒን ቅጽ 1 ማውጫ

ርዕስ	ገጽ
መቅድም	1
የደራሲው ማስታወሻ	3
ምዕራፍ 1 ቅንነትና ታማኝነት (ኢኽላስ)÷ እንዲሁም መልካም ተነሳሽነት (ኒያ) በማንኛውም ንግግርና ተግባር -ግልጽ ይሁን ድብቅ	8
ምዕራፍ 2 ተውበት (ዐፀት)	19
ምዕራፍ 3 ትዕግስት (ሶብር)	43
ምዕራፍ 4 እውነተኝነት	68
ምዕራፍ 5 የአላህን የበላይ ተቆጣጣሪነት ምንጊዜም አለመዘንጋት (ሙራቀበህ)	73
ምዕራፍ 6 ጥንቁቅነት (ተቅዋ)	83
ምዕራፍ 7 ጥልቅ ዕምነት (የቂን) እና በአላህ መመካት (ተወኩል)	86

መቅድም

"ሪያዱስ-ሷሊሒን" በታላቁ የሐዲስ ሊቅ ኢማም አን-ነወዊ ከበርካታ ምዕተ ዓመታት በፊት ተጠርሞ ለንባብ የሞለ እውቅ የሶሒሕ ሐዲሶች ስብስብ ነው። በዘመናቱ በመላው ዓለም ከፍተኛ ተቀባይነትን አግኝቷል። ከ1900 ያላነሱ ተአማኒ (ሶሒሕ) የሐዲስ ዘገባዎችን በውስጡ ይዟል።

ሰብዕናን ኢስላም በሚሻው መልኩ ለመቅረጽና ደራሲው ከመጽሐፉ መግቢያ ላይ እንደጠቆሙት፥ የደንጉችንና ምርጥ የአላህ አገልጋዮችን የሕይወት ስልት በመከተል በዚህችም ሆነ በቀጣዩ ዓለም ለስኬት ለመብቃት "ሪያዱስ-ሷሊሒን" እጅግ ጠቃሚ መጽሐፍ ነው።

መጽሐፉ ካለው ጠቀሜታና በሀገራችን እያገኘ ከመጣው እውቅና አንጻር ወደ አማርኛ መልሰነው ሕዝባችንን ከኒህ ታላቅ የሐዲስ ሊቅ የእውቀት ማዕድ ተቋዳሽ ብናደርግ እጅግ የላቀ ፋይዳ እንደሚኖረው ተሰማን። እናም ለትርጉም አበቃነው።

የተከተልነው የአተረጓጎም ስልት የቃል በቃል ትርጉም ነው። ቢሆንም ግን የአማርኛን የሰዋሰው ሥርዓት ላለማፋለስ የቻልነውን ሁሉ አድርገናል። የቃል በቃል ትርጉም ሥርዓትን በመከተል የሐዲሱን መልዕክት በትክክል ማስተላለፍ አዳጋች በሚሆንባቸው ቦታዎች ላይ የነጻ ትርጉምን ሥርዓት ለመከተል ተገደናል። የዐረብኛው አገላለጽ በውስጡ የሚያስቀራቸው ሐሳቦች በሚገጥሙን ወቅት ሐሳቦችን በቅንፍ አስቀምጠናል። የሰፋ ትርጉም ያላቸውን የዐረብኛ ቃላት በአማርኛ እንዳሉ ከትበናቸዋል። አንዳንድ አስፈላጊ የሆኑ ቃላትና ጽንሰ-ሐሳቦችን በቁጥር ተመልክተው በግርጌ ማስታወሻዎች ላይ ማብራሪያ ተሰጥቶባቸዋል።

"ከሐዲሱ የምንማራቸው ቁምነገሮች" በሚል ርዕስ ሥር ለየሐዲሶቹ ግርጌ ለተሰጡ አስተምህሮዎች መሠረት ያደረግነው ኑገዘቱል መትተቂን" የተሰኘውንና ዶ/ር ሙስጠፋ ስዒድ

አል-ኺን፣ ዶ/ር ሙስጠፋ አል-ቡጋ፣ ሙሐዲን ሙስተዋ፣ ዓሊይ ሸርበጂ እና ሙሐመድ አሚን ሉጥፊ በጋራ ያዘጋጁትን የ"የሪያዱስ-ሷሊሒን" ማብራሪያ (ሸርሕ) መጽሐፍ ነው።

ሥራው እጅግ አድካሚ ቢሆንም አጠናቀነዋል። የኛ የማጣቀም አቅምም ሆነ የአንባቢያን የመግዛት ችሎታ የሚፈቅድ ባለመሆኑ በአንድ ላይ ወይም በጥቂት ጥራዞች ብቻ ከፋፍለን ልናሳትመው አልቻልንም። በአያሌ ጥራዞች እየከፋፈልን ለማውጣት ተገደናል።

ሥራችን ከስህተት የራቀ፥ ከግድፈት የተጠበቀ እንዳልሆነ እናምናለን። ስህተቶችን ፈጽመን ሊሆን ይችላል። የማይሳሳተው አላህ ብቻ ነው። እናም የአንባቢያንን የእርምት አስተያየት በእጅጉ ያስፈልገናል። ስለዚህም ሆነ ስለሌሎች የትርጉም ሥራዎቻችን ያላችሁን አስተያየት ብትልኩልን በደስታ እናስተናግዳለን። ግድፈቶቻችንን አርመንና አስተካክለን የተሻለ ሥራ ለማቅረብ ይረዱናል። አስጀምሮ ላስጨረሰን አምላክ አላህ ምሥጋና ይግባው። ወደር የለሽ ምሥጋና።

አላሁ አክበር!
ወሊላሂል ሐምድ

ተርጓሚው

የደራሲው ማስታወሻ

ለአላህ ምሥጋና ይግባው። ብቸኛና ኃያል፥ መሐሪ የበላይ ለሆነው፥ የግንዛቤ ጽድቀትን የተቸሩ ሰዎች ያስታውሱና ትምህርት ይቀስሙ ዘንድ ሌትና ቀንን በማፈራረቅ አስደናቂ ተአምሩን ለሰው ዘር ግልጽ ላደረገ ጌታ።

አላህ ከባሮቹ የተወሰኑትን በመምረጥ የሕይወትን ያልተዛባ ግንዛቤ አስጨበጣቸው። እርሱ በመረጠው ፍኖት እንዲጓዙም አስቻላቸው። ሁልየም ትእዛዙን እንዲጠባበቁ፤ እርሱኑ ከማውሳት እንዳይዘናጉ፤ ራሳቸውን እንዲመረምሩና እንዲፈትሹ። እርሱን ከማምለክ እንዳይቆጠቡ፥ ለመጭው ዓለም ሕይወታቸው ዘወትር እንዲዘጋጁ፥ እርሱን ከሚያስቆጡና ለከፍተኛ ቅጣት ከሚያበቁ እኩይ ተግባራት እንዲርቁ፥ ምንጊዜም በዚህ ባሕሪያቸው ፀንተው እንዲገኙም አቅምና ችሎታውን ለገሣቸው።

ለአላህ ምስጋና አደርሳለሁ። እጅግ ሠፊና ጥልቅ፥ ምሉዕና ሁለንተናዊ የሆነ ምሥጋና። እጅግ በጣም ርኅሩኅና ቸር ከሆነው አላህ ውጭ ሌላ የሚመለክ ኃይል እንደሌለ እመሰክራለሁ። ነቢዩ ሙሐመድ የሰውን ዘር ወደ ቀጥተኛው ፍኖት እንዲመሩ፥ ትክክለኛውን ዲን እንዲያስተምሩ የተላኩ የአላህ መልዕክተኛ መሆናቸውን እናዘዛለሁ። በርሳቸው በቤተሰቦቻቸውና በሌሎች ጻድቅ ሰብዕናዎች ላይም የአላህ ረሕመትና ሰላም ይስፈን።

አላህ እንዲህ ሲል የአዋጅ ድምጹን አሰምቷል፦

﴿وما خلقت الجن والإنس إلا ليعبدون. مآ أريد منهم مـــن رزق ومآ أريد أن يطعمون﴾

"ጌንና ሰውንም ሊግዙኝ እንጂ ለሌላ አልፈጠርኳቸውም። ከነሱም ምንም ሲሳይ አልፈልግም፤ ሊመግቡኝም አልሻም።" (አል-ዛሪያት፡ 56-57)

ይህ አንቀጽ በግልጽ እንደሚያመለክተው የሰው ልጅ የተፈጠረለት ዓላማ ዒባዳ ነው። ሰዎች የተፈጠሩለትን ዓላማ ትኩረት ሊቸሩት ይገባል። ከዚህች ዓለም ጥቅማጥቅሞች በ"ዙህድ" ትጥቅ በመጠበቅ። ምክንያቱም ይህች ዓለም ጠፊ ናት። ዘልዓለም የሚኖሩባት ቦታ አይደለችም። ለዚህም ነው እጅግ ብልህና አስተዋይ የሆኑ የአላህ አገልጋዮች የዚህችን ዓለም ትክክለኛ ፋይዳ በመገንዘብና ለአጭበርባሪ ግርግሯ ባለመታለል የ"ዙህድ"ን ሕይወት የመረጡት። አላህ እንዲህ ሲል የዚህችን ዓለም ትክክለኛ ባሕሪ ገልጿል፦

﴿إنما مثل الحياة الدنيا كماء أنزلناه من السمآء فاختلط به نبـــات الأرض مما يأكل الناس والأنعام حتى إذا أخذت الأرض زخرفـــها وازينت وظن أهلها أنهم قادرون عليها أتاها أمرنا ليـــلا أو نـــهارا فجعلناها حصيدا كأن لم تغن بالأمس كذلك نفصل الآيات لقـــوم يتفكرون﴾

"የቅርቢቱ ሕይወት ምሳሌ (ጊዜዋ በማጠርና በመጥፋት) ከሰማይ እንዳወረድነው ውሃ፥ በርሱም ሰውና እንስሳዎች ከሚበሉት የምድር በቃይ ተቀላቅሎበት (እንደ ፋፋ፥) ምድርም ውብትዋን በያዘችና ባጌጠች ጊዜ፥ ባለቤቶችዋም በርሷ ላይ እነርሱ ቻዮች መኾናቸውን ባሰቡ ጊዜ፥ ትእዛዛችን ሌሊት ወይም ቀን መጥቶባት፥ ትላንት እንዳልነበረች የታጨደች እንዳደረግናት ብጤ ነው፤ እንደዚሁም ለሚያስተነትኑ ሕዝቦች አንቀጾችን እናብራራለን።" (ዩኑስ፥ 24)

ከላይ ከተጠቀሰው "እያ" መንፈስ ጋር የሚሄዱ የቁርአን አንቀጾች በርካታ ናቸው። አንድ ባለቅኔ እንዲህ ሲል ስንኝ ቋጥሯል፦

ጥንቁቅ አገልጋዮች አላህ ባሮች አሉት፤
ዱንያን የተዉ ፈተናዋን ስጋት፤
በጥልቅ መረመሯት፤
ፈተኟት፤
አጠኗት፤

የሕያውን ሀገር፤
የብልሆች መንደር፤
የአስተዋዮች ሠፈር፤
ፈጽሞ እንዳልሆነች በውል ተገንዝበው፤
እንደጥልቅ ውቅያኖስ እንዲ ባሕር ቆጥረው፤
በጽድቅ ከንውን ጀልባቸው ተሳፍረው፤
በመልካም ሥራ ስንቅ፤
በኸይር አድራጉት ጽድቅ፤
አለፏት ተሻግረው።

የዚህችን ዓለም ባሕሪና ትክክለኛ ፋይዳ፤ የሰው ዘርንም የሕይወት ግብ ከላይ በመግለጽ ለማስቀመጥ ሞክሪያለሁ። እናም እያንዳንዱ ሰው ትክክለኛውን ምርጫ ወስኖ ጉዞ መጀመር አለበት። የታላላቅ የአላህ አገልጋዮችን የስኬት ፈለግ መከተል ለጠቆምኩት ቁምነገር መዘጋጀት።

በዚህ ረገድ ትክክለኛው ስልት የነቢያት ፈርጥ ከሆኑት ነቢይ (ሶ.ዐ.ወ) የተገኙ አስተምህሮዎችን በገቢር ማዋል ነው። አላህ (ሱ.ወ) እንዲህ ብሏል፦

﴿وتعاونوا على البر والتقوى﴾

"...በበጐ ነገርና አላህን በመፍራት ተረዳዱ፤" (አል-ማኢዳህ፡ 2)

የአላህ መልዕክተኛም (ሶ.ዐ.ወ) እንዲህ ሲሉ መናገራቸው ተወስቷል፦

((والله في عون العبد ما كان العبد في عون أخيه))

"ባሪያው ወንድሙን መርዳት እስካላቆመ ድረስ አላህ ባሪያውን ከመርዳት አይቆጠብም።"

((من دل على خير فله مثل أجر فاعله))

"ወደ መልካም ተግባር ያመላከተ፡ ያን ተግባር የሠራው ሰው የሚያገኘውን ያክል ምንዳ ያገኛል።"

((من دعا إلى هدى كان له من الأجر مثل أجور مـــن تبعـــه لا ينقض ذلك من أجورهم شيئا))

"ወደ ጽድቅ ጥሪ ያደረገ ተከታዮቹ የሚያገኙትን ያክል ምንዳ ያገኛል፣ የነርሱ ምንዳ ቅንጣት ሳይቀነስ።"

መልዕክተኛው (ሶ.ዐ.ወ) ለዓሊይ (ረ.ዐ) እንዲህ ሲሉ መከረዋቸዋል፦

((فوالله لأن يهدي الله بك رجلا واحدا خير لك من حمر النعم))

"በአላህ ይሁንብኝ፣ አላህ በእንተ ሰበብ አንድን ሰው ወደ ትክክለኛው ፍናት መምራቱ ላንተ ከቀይ ግመል የተሻለ ዋጋ አለው።"

ሰዎች ወደ መጭው ዓለም ለሚያደርጉት ጉዞ ስኬት ጠቃሚ የሆኑ፥ ግልጽና ስውር የሆኑ ኢስላማዊ አደቦችን የሚጠቁም፥ ነፍስን ለማረምና ለመምራት፥ ሥነ-ምግባርን ለማረቅና ለመግራት፥ ልቦናን ለማጽዳትና ለማከም፥ የአካልን ደህንነት ለመጠበቅና ሌሎችንም የደጋግ የአላህ ባሮችን የሕይወት ግብ የሚጠቁሙ ሐዲሶችን ያካተተ አጠቃላይ የሶሒሕ ሐዲሶች ስብስብ ባዘጋጅ ጠቃሚ መስሎ ስለታየኝ ይህችን አነስተኛ መጽሐፍ አዘጋጅቻለሁ። እያንዳንዱን ምዕራፍ የከፈትኩት በቁርአን አናቅጽ ሲሆን፥ መብራራት አለባቸው ብዬ ያመንኩባቸውን ሐዲሶች ለማብራራት ሞክሪያለሁ። ከሐዲሱ ማሳረጊያ ላይ "ሙትተፊቅ" የሚል ቃል ሳስቀመጥ ቡኻሪና ሙስሊምን ማለመልከቴ እንደሆነ ይታወቅልኝ።

ይህች መጽሐፍ አንባብያንን ወደ መልካም ሁሉ የምትመራውና ከመጥፎ የምትከለክል ትሆንልኝ ዘንድ አላህን እማፀናለሁ።

ከዚህች መጽሐፍ ጥቂትም ቢሆን የተጠቀመ ወንድሜን ለኔ፣ ለወላጆቼ፣ ለታላላቅ መምህራኖቼና ለሌሎችም ወዳጆቼ፥ እንዲሁም ለሙስሊሞች ባጠቃላይ ዱዓ ያደርግ ዘንድ እጠይቀዋለሁ።

የምመካው በአላህ ነው። የምጠጋውም ወደርሱ ነው። እርሱ በቂዬ ነው። አስተማማኝ መመኪያ ነው አላህ። ኃያልና ጥበበኛ ከሆነው አላህ ውጭ ብልሃትም ኃይልም የለም።

ደራሲው

١- بَابُ الإخلاَصِ وإحضار النّية في جميع الأعمال والأقوال والأحوال البارزة والخفية

قَالَ اللهُ تعالى: ﴿وَمَا أُمِرُوا إِلاَّ لِيَعْبُدُوا اللهَ مُخْلِصِينَ لَهُ الدِّينَ حُنَفَاءَ وَيُقِيمُوا الصَّلاَةَ، وَيُؤْتُوا الزَّكَاةَ، وَذَلِكَ دِينُ الْقَيِّمَةِ﴾ وَقَالَ تَعَالَى: ﴿لَنْ يَنَالَ اللهَ لُحُومُهَا وَلاَ دِمَاؤُهَا وَلَكِنْ يَنَالُهُ التَّقْوَى مِنْكُمْ﴾ وَقَالَ تَعَالَى: ﴿قُلْ إِنْ تُخْفُوا مَا فِي صُدُورِكُمْ أَوْ تُبْدُوهُ يَعْلَمْهُ اللهُ﴾.

١- وَعَنْ أَمِيرِ الْمُؤْمِنِينَ أَبِي حَفْصٍ عُمَرَ بْنِ الْخَطَّابِ بْنِ نُفَيْلِ ابْنِ عَبْدِ الْعُزَّى بْنِ رِيَاحِ بْنِ عَبْدِ اللهِ بْنِ قُرْطِ بْنِ رَزَاحِ بْنِ عَدِيِّ ابْنِ كَعْبِ بْنِ لُؤَيِّ بْنِ غَالِبٍ الْقُرَشِيِّ الْعَدَوِيِّ ﷺ قَالَ: سَمِعْتُ رَسُولَ اللهِ ﷺ يَقُولُ: ((إِنَّمَا الأَعْمَالُ بِالنِّيَّاتِ وَإِنَّمَا لِكُلِّ امْرِئٍ مَا نَوَى. فَمَنْ كَانَتْ هِجْرَتُهُ إِلَى اللهِ وَرَسُولِهِ فَهِجْرَتُهُ إِلَى اللهِ وَرَسُولِهِ، وَمَنْ كَانَ هِجْرَتُهُ لِدُنْيَا يُصِيبُهَا أَوْ امْرَأَةٍ يَنْكِحُهَا فَهِجْرَتُهُ إِلَى مَا هَاجَرَ إِلَيْهِ)) مُتَّفَقٌ عَلَى صِحَّتِهِ.

ምዕራፍ 1

ቅንነትና ታማኝነት (ኢኽላስ) እንዲሁም መልካም ተነሳሽነት (ኒያ)፣ በማንኛውም ንግግርና ተግባር -ግልጽ ይሁን ድብቅ

አላህ እንዲህ ብሏል፦

"አላህን፥ ሃይማኖትን ለርሱ ብቻ እጥሪዎች፥ ቀጥተኞች ኾነው ሊግዘት፥ ሶላትንም አስተካክለው ሊሰግዱ፥ ዘካንም ሊሰጡ እንጅ ያልታዘዙ ሲኾኑ (ተለያዩ)። ይህም የቀጥተኛይቱ (ሃይማኖት) ድንጋጌ ነው።" (አል-በይነህ፥ 5)

"አላህን ሥጋዎቿም፥ ደሞቿም ፈጽሞ አይደርሰውም፤ ግን ከናንተ የኾነው ፍራቻ ይደርሰዋል።..." (አል-ሐጅ፥ 37)

"ከደረቶቻችሁ ውስጥ ያለውን ነገር ብትደብቁ፥ ወይም ብትገልጹት አላህ ያውቀዋል፥ (በል)።" (አል-ዒምራን፥ 29)

1- ዑመር ኢብን አል-ኸጣብ (ረ.ዐ) እንዳስተላለፉት የአላህ መልዕክተኛ (ሶ.ዐ.ወ) እንዲህ ብለዋል፦ "ሥራ የሚለካው በሐሳብ (ኒያ) ነው። ማንኛውንም ሰው ያሰበውን ያገኛል። ስደቱ ወደ አላህና መልዕክተኛው የሆነ ስደቱ ወደ አላህና መልዕክተኛው ነው። የስደቱ ግብ ዓለማዊ ጥቅም (ዱንያ) ከሆነ ያገኛታል፤ ሴትም ከሆነች ያገባታል። ስደቱ ለተሰደደበት ዓላማ ነው።"

(ቡኻሪና ሙስሊም)

ከሐዲሱ የምንማራቸው ቁምነገሮች

- አንድ ተግባር ከመከናወኑ በፊት መልካም ተነሳሽነት (ኒያ) አስፈላጊ እንደሆነ ዑለሞች ይስማሙበታል፥ የዚያን ተግባር ምንዳ ማግኘት ይቻል ዘንድ። ግና ማንኛውንም ተግባር ተቀባይነት ይኖረው ዘንድ የግድ ኒያ ያስፈልገዋል ወይስ አያስፈልገውም? በሚለው ነጥብ ላይ ተወዛግበዋል። የሻፊዒይ መዝሀብ ምሁራን፥ እንደ ውዱእ ባሉ የዒባዳ ዝግጅቶችም ሆነ እንደ ሶላት ባሉ ዒባዳዎች ላይ ኒያ ሸርጥ (ቅድመ-ግዳጅ) ነው ሲሉ፥ የሐነፊይ መዝሀብ ምሁራን ደግሞ በዒባዳዎች ላይ እንጂ ለዒባዳ በሚደረጉ ዝግጅቶች ላይ ኒያ እንደማያስፈልግ ይናገራሉ።
- የኒያ ማዕከል ቀልብ (ልቦና) ነው። አንድን ተግባር ለማከናወን በልቦና ማሰቡ ብቻ በቂ ነው። መናገሩ አያስፈልግም።
- ተግባርን ለአላህ ብቻ በ"ኢኽላስ" ማከናወን ለተቀባይነቱ ዋስትና ይሰጣል። አላህ ለርሱ ብቻ በቅንነትና በታማኝነት (ኢኽላስ) የተከናወነን ተግባር እንጅ አይቀበልም።

٢- وَعَنْ أُمِّ الْمُؤْمِنِينَ أُمِّ عَبْدِ اللهِ عَائِشَةَ رَضِيَ اللهُ عَنْهَا قَالَتْ: قَالَ رَسُولُ اللهِ ﷺ: يَغْزُو جَيْشٌ الْكَعْبَةَ، فَإِذَا كَانُوا بِبَيْدَاءَ مِنَ الأَرْضِ يُخْسَفُ بِأَوَّلِهِمْ وَآخِرِهِمْ. قَالَتْ: قُلْتُ: يَارَسُولَ اللهِ كَيْفَ يُخْسَفُ بِأَوَّلِهِمْ وَآخِرِهِمْ وَفِيهِمْ أَسْوَاقُهُمْ وَمَنْ لَيْسَ مِنْهُمْ؟ قَالَ: ((يُخْسَفُ بِأَوَّلِهِمْ وَآخِرِهِمْ ثُمَّ يُبْعَثُونَ عَلَى نِيَّاتِهِمْ)) مُتَّفَقٌ عَلَيْهِ. هَذَا لَفْظُ الْبُخَارِيِّ.

2- የሙእሚኖች እናት ዓኢሻ (ረ.ዐ) እንዲህ ሲሉ አስተላልፈዋል፦ የአላህ መልዕክተኛ (ሶ.ዐ.ወ)፦ "ከዕቦን ለማው ደም የሚተም አንድ ሠራዊት ይዘም ታል። ከአንድ ምድረ በዳ መሬት ላይ ሲደርስ ከመጀመሪያው እስከ መጨረሻው ያሉት ሁሉም በመሬት መሰን ጠቅ ይዋጣሉ። በማለት ተናገሩ። "እንዴት ከመጀመሪያው እስከ መጨረሻው (ሁሉም) በመሬት መሰንጠቅ እንዲዋጡ ይደረጋል? ከመካከላቸው የንግድ ሰዎችና ሌሎችም (ዓላማቸው ከዕቦን ማፍረስ ያልሆነ ሰዎች) እያሉ?" አልኳቸው። "ከመጀመሪያቸው እስከ መጨረሻቸው (ሁሉም) ይዋጣሉ። ከዚያም እንደየኒያቸው ይቀሰቀሳሉ።" በማለት ተናገሩ።
(ቡኻሪና ሙስሊም፥ የሐዲሱ ቃል የቡኻሪ ነው)

ከሐዲሱ የምንማራቸው ቁምነገሮች

- የአንድ ሰው ተግባር መልካምነት ወይም መጥፎነት መለኪያ መስፈርቱ ያን ተግባር ለማከናወን ያነሳሳው ዓላማ (ኒያው) ነው።

- ግፈኞችንና በአላህ ትእዛዝ ላይ ያመፁ ሰዎችን የመጉዳኘት አደገኛነት።
- ቅንና መልካም ሰዎችን የመጉዳኘት ጠቀሜታ።
- ነቢዩ (ሶ.ዐ.ወ) በዚህ የሐዲስ ዘገባ ላይ ትንቢት ተናግረዋል። ትንቢቱ በነገሩን መልኩ ተፈጸሚ እንደሚሆን እምኖ መቀበል ግዴታችን ነው። የንግግራቸው ምንጭ መለኮታዊ ራዕይ (ወሕይ) ነውና።

٣- وعَنْ عَائِشَةَ رضى الله عنها قَالَتْ: قَالَ النَّبِيُّ ﷺ ((لاَهِجْرَةَ بَعْدَ الْفَتْحِ، وَلَكِنْ جِهَادٌ وَنِيَّةٌ؛ وَإِذَا اسْتُنفِرْتُمْ فَانْفِرُوا)) مُتَّفَقٌ عَلَيْهِ.

3- ዓኢሻ (ረ.ወ) እንዳስተላለፉት የአላህ መልዕክተኛ (ሶ.ዐ.ወ) እንዲህ ብለዋል፦ "ከመካ (በድል) መከፈት በኋላ ስደት የለም። ግና ጂሃድና "ኒያ" ምንጊዜም ይኖራሉ። (ለጂሃድ) እንድትዘምቱ በምትጠየቁበት ጊዜ ዝመቱ።"

(ቡኻሪና ሙስሊም)

ከሐዲሱ የምንማራቸው ቁምነገሮች

- አንዲት ሀገር ኢስላማዊ (ዳረል ኢስላም) ከሆነች በኋላ ወደ ሌላ ሀገር መሰደድ አይፈቀድም።
- አንዲት ሀገር የኩፍር ሀገር (ዳረል-ኩፍር) እስከሆነችና መስሊሞች በዚያች ሀገር ላይ ኢስላምን ተግባራዊ ለማድረግ እስከተሳናቸው ድረስ ስደት ግዴታ እንደሆነ ይቆያል።
- ሁልየም ጂሃድን ማሰብና ለጂሃድ ተዝዉን ዝግጅት ማድረግ አስፈላጊ ተገቢ ነው፤ ወደ ጂሃድ ጥሪ በሚመጣበት ወቅት አፋጣኝ ምላሽ መስጠት ይቻል ዘንድ።

٤ - وَعَنْ أَبِي عَبْدِ اللهِ جَابِرِ بْنِ عَبْدِ اللهِ الأَنْصَارِيِّ رضى الله عنهما قَالَ: كُنَّا مَعَ النَّبِيِّ ﷺ فِي غَزَاةٍ فَقَالَ: ((إِنَّ بِالْمَدِينَةِ لَرِجَالاً مَا سِرْتُمْ مَسِيرًا، وَلاَ قَطَعْتُمْ وَادِيًا، إِلاَّ كَانُوا مَعَكُمْ حَبَسَهُمُ الْمَرَضُ)) وَفِي رِوَايَةٍ ((إِلاَّ شَرِكُوكُمْ فِي الأَجْرِ)) رَوَاهُ مُسْلِمٌ.
وَرَاهُ الْبُخَارِيُّ عَنْ أَنَسٍ ﷺ قَالَ:

4- ዐብደላህ ኢብን ጃቢር ዐብደላህ አል-አንሷሪይ (ረ.ዐ) እንዲህ ሲሉ አስተላልፈዋል፦ ከአንድ ዘመቻ ላይ ከነቢዩ (ሶ.ዐ.ወ) ጋር ነበርን። እንዲህ አሉ፦ "መዲና ውስጥ በሽታ (ከዘመቻ) ያስቀራቸው ሰዎች አሉ። መንገድን አልሄዳችሁም፣ ሸለቆንም አላቋረጣችሁም -ከናንተ ጋር ቢሆኑ እንጅ።"

በሌላ ዘገባ ደግሞ፦
"በምንዳ የተጋራችሁ ቢሆን እንጂ።" የሚል ተመልክቷል።

(ሙስሊም ዘግበውታል)

ቡኻሪ አነስን ጠቅሰው እንደዘገቡት፦

ከተቡክ ዘመቻ ተመለስን። ከነቢዩ (ሶ.ዐ.ወ) ጋር። "ከኋላችን መዲና ውስጥ ችግር (ውዝር) ከዘመቻ ያስቀራቸው ሰዎች አሉ። ጋራ ሸንተረሩን አላቆራረጥንም፥ ከኛ ጋር የሆኑ ቢሆኑ እንጂ።" በማለት ተናገሩ።

رَجَعْنَا مِنْ غَزْوَةِ تَبُوكَ مَعَ النَّبِيِّ ﷺ فَقَالَ: ((إِنَّ أَقْوَامًا خَلْفَنَا بِالْمَدِينَةِ مَاسَلَكْنَا شِعْبًا وَلاَ وَادِيًا إِلاَّ وَهُمْ مَعَنَا؛ حَبَسَهُمُ الْعُذْرُ)).

ከሐዲሱ የምንማራቸው ቁምነገሮች

- በአንዳች አስገዳጅ ምክንያት ከጂሃድ የቀረ ሰው መልካም ኒያና ፍላጉት እስካለው ድረስ ጂሃድ ያደረጉ ሰዎችን ምንዳ ያገኛል።

5- አቡ የዚድ መዕን ኢብን የዚድ ኢብን አል-አኽለስ (ረ.ዐ) -እርሳቸውም፥ አባታቸውም፥ አያታቸውም ሶሐባዎች ነበሩ- እንዲህ ሲሉ አስተላልፈዋል፦ አባቴ የዚድ ለምጽዋት የተወሰኑ ዲናሮችን አወጣና መስጊድ ውስጥ ለአንድ ሰው መፀወተ። መጣሁና አነሳኋቸው፥ ወደ ርሱም ይዣቸው መጣሁ። "በአላህ እምላለሁ፥ ለአንተ አላሰብኳቸውም ነበር።" አለ። ከመልዕክተኛው (ሶ.ዐ.ወ) ዘንድ ሞግትኩ። "የዚድ ሆይ! ለአንተ ያሰብከው አለህ፥ (የኒያህን ዋጋ ታገኛለህ)። መዕን ሆይ! ለአንተ ደግሞ የያዝከው አለህ።" አሉ።

(ቡኻሪና ሙስሊም)

٥-وَعَنْ أَبِي يَزِيدَ مَعْنِ بْنِ يَزِيدَ بْنِ الأَخْنَسِ ﷺ -وَهُوَ وَأَبُوهُ وَجَدُّهُ صَحَابِيُّونَ- قَالَ: كَانَ أَبِي يَزِيدُ أَخْرَجَ دَنَانِيرَ يَتَصَدَّقُ بِهَا، فَوَضَعَهَا عِنْدَ رَجُلٍ فِي الْمَسْجِدِ، فَجِئْتُ فَأَخَذْتُهَا فَأَتَيْتُهُ بِهَا. فَقَالَ: وَاللهِ مَا إِيَّاكَ أَرَدْتُ ، فَخَاصَمْتُهُ إِلَى رَسُولِ اللَّهِ ﷺ فَقَالَ: ((لَكَ مَانَوَيْتَ يَا يَزِيدُ، وَلَكَ مَا أَخَذْتَ يَا مَعْنُ)) رَوَاهُ الْبُخَارِيُّ.

ከሐዲሱ የምንማራቸው ቁምነገሮች

- ሱንና የሆነን ምጽዋት ለልጆች መስጠት ይፈቀዳል። ዘካን ግን ለልጆችም ሆነ ለወላጆች መስጠት አይፈቀድም።
- ሰደቃን በወኪል ማሠራጨት ይፈቀዳል።

6- ሰዕድ ኢብን አቢወቃስ (ረ.ዐ) -ጀነንት ከተመሰከረላቸው አሥር ሰዎች መካከል አንዱ ናቸው- እንዲህ ሲሉ አስተላልፈዋል፦ የመሰናበቻ ሐጅ ዓመት ወቅት ነቢዩ

٦- وَعَنْ أَبِي إِسْحَاقَ سَعْدِ بْنِ أَبِي وَقَّاصٍ مَالِكِ بْنِ أُهَيْبِ بْنِ عَبْدِ مَنَافِ بْنِ زُهْرَةَ بْنِ

كِلاَبِ بْنِ مُرَّةَ بْنِ كَعْبِ بْنِ لُؤَيٍّ الْقُرَشِيُّ الزُّهْرِيُّ ﷺ: أَحَدِ الْعَشَرَةِ الْمَشْهُودِ لَهُمْ بِالْجَنَّةِ ﷺ قَالَ: جَاءَنِي رَسُولُ اللهِ ﷺ يَعُودُنِي عَامَ حَجَّةِ الْوَدَاعِ مِنْ وَجَعٍ اشْتَدَّ بِي، فَقُلْتُ: يَارَسُولَ اللهِ إِنِّي قَدْ بَلَغَ بِي مِنَ الْوَجَعِ مَاتَرَى وَأَنَا ذُو مَالٍ وَلاَ يَرِثُنِي إِلاَّ ابْنَةٌ لِي أَفَأَتَصَدَّقُ بِثُلُثَيْ مَالِي؟ قَالَ: ((لاَ))، قُلْتُ: فَالشَّطْرُ يَارَسُولَ اللهِ؟ فَقَالَ: ((لاَ))، قُلْتُ: فَالثُّلُثُ يَارَسُولَ اللهِ؟ قَالَ: ((الثُّلُثُ، وَالثُّلُثُ كَثِيرٌ -أَوْ كَبِيرٌ- إِنَّكَ أَنْ تَذَرَ وَرَثَتَكَ أَغْنِيَاءَ خَيْرٌ مِنْ أَنْ تَذَرَهُمْ عَالَةً يَتَكَفَّفُونَ النَّاسَ، وَإِنَّكَ لَنْ تُنْفِقَ نَفَقَةً تَبْتَغِي بِهَا وَجْهَ اللهِ إِلاَّ أُجِرْتَ عَلَيْهَا حَتَّى مَايَجْعَلُ فِي امْرَأَتِكَ)). (قَالَ) فَقُلْتُ: يَارَسُولَ اللهِ، أُخَلَّفُ بَعْدَ أَصْحَابِي؟ قَالَ: ((إِنَّكَ لَنْ تُخَلَّفَ فَتَعْمَلَ عَمَلاً تَبْتَغِي بِهِ وَجْهَ اللهِ إِلاَّ ازْدَدْتَ بِهِ دَرَجَةً وَرِفْعَةً، وَلَعَلَّكَ أَنْ تُخَلَّفَ حَتَّى يَنْتَفِعَ بِكَ أَقْوَامٌ وَيُضَرَّ بِكَ آخَرُونَ. اللَّهُمَّ أَمْضِ لأَصْحَابِي هِجْرَتَهُمْ، وَلاَ تَرُدَّهُمْ عَلَى أَعْقَابِهِمْ، لَكِنِ الْبَائِسُ سَعْدُ بْنُ خَوْلَةَ)) يَرْثِي لَهُ رَسُولُ اللهِ ﷺ أَنْ مَاتَ بِمَكَّةَ: مُتَّفَقٌ عَلَيْهِ.

(ሶ.ዐ.ወ) . ሊጠይቁኝ መጡ። ብርቱ በሽታ አሞኝ ነበር። "በኔ ላይ የምታዩት በሽታ ደርሶብኛል። በርካታ ንብረት አለኝ። ከአንዲት ሴት ልጅ ሌላ ወራሽ የለኝም። የገንዘቤን ሁለት ሦስተኛ ልመጽውትን? አልኳቸው። "አይሆንም።" አሉኝ። "የአላህ መልዕክተኛ ሆይ! ግማሹንስ?" አልኳቸው። "አይሆንም።" አሉኝ። "የአላህ መልዕክተኛ ሆይ! ሲሶውንስ?" አልኳቸው። "ሲሶ፥ ሲሶም ብዙ -ወይም ትልቅ- ነው። ወራሾችህን ሃብታሞች አድርገህ ማለፍህ፥ ድሃዎችና የሰዎችን እጅ የሚያዩ አድርገሃቸው ከመሞትህ የበለጠ ነው። የአላህን ውዴታ በመሻት አንድንም ምጽዋት አትመፀውትም፥ ምንዳ ያገኘህበት ቢሆን እንጂ። ከባለቤትህ አፍ በምታስቀ ምጠው (ጉርሻ) እንኳ ቢሆን (ምንዳ ታገኛለህ)።" አሉ። "ከባልደረቦቼ ተነጥዬ ወደኋላ እቀራለሁን?" አልኳቸው። "ወደኋላ ተነጥለህ ቀርተህ የአላህን ውዴታ በመሻት መልካምን ተግባር አትፈጽምም፥ ደረጃንና ልዕልናን የጨመርክ ቢሆን እንጂ። ምናልባትም ከፊል ሰዎች እንዲጠ ቀሙብህ፥ ጠላቶች ደግሞ በአንተ (ሰበብ) እንዲጐዱ ወደኋላ ትቀር ይሆናል። አላህ ሆይ! የባልደረቦቼን ስደት አጽድቅ። ወደኋላ አትመልሳቸው።" አሉ። ነገር ግን የሚያሳዝነው ሰዕድ ኢብን ኸወይለህ ነው። መካ ውስጥ ነበር የሞተው። ነቢዩ (ሶ.ዐ.ወ) እጅግ ያዘኑለትና በሞት የመለየቱ ነገር ይሰማቸው ነበር።

(ቡኻሪና ሙስሊም)

ከሐዲሱ የምንማራቸው ቁምነገሮች

- ለመልካም ዓላማና ተግባር በሽታን ለሌሎች መናገር ክልክልነት የለውም። ለምሳሌ ፈውስን ወይም የወንድምን ዱዓ በመሻት።
- ገንዘብን ሐላል በሆነ መንገድ መሰብሰብ ይፈቀዳል። ባለሃብቱ ኃላፊነቱን በብቃት እስከተወጣ ድረስ ሃብት ማከማቸቱ ከጥፋት ሊቆጠርበት አይገባም።
- አንድ ሰው -ወራሽ እስካልፈቀደለት ድረስ- ከገንዘቡ ከአንድ ሦስተኛ በላይ ኑዛዜ ማድረግ አይፈቀድለትም።
- ሰዎች በመልካም ኒያና ተነሳሽነት ለሚፈጽሙት ተግባር ሁሉ ምንዳ ያገኛሉ። የቤተሰብን -ቁሳዊ ፍላጉት ማሟላትም- መልካም ኒያ ከታከለበት - ምንዳ ያስገኛል።

٧- وَعَنْ أَبِي هُرَيْرَةَ عَبْدِ الرَّحْمَنِ بْنِ صَخْرٍ ﷺ قَالَ: قَالَ رَسُولُ اللهِ ﷺ: ((إِنَّ اللهَ لاَيَنْظُرُ إِلَى أَجْسَامِكُمْ وَلاَ إِلَى صُوَرِكُمْ وَلَكِنْ يَنْظُرُ إِلَى قُلُوبِكُمْ)). رَوَاهُ مُسْلِمٌ.

7- አቡ ሁረይራ (ረ.ዐ) እንዳስተላለፉት የአላህ መልዕክተኛ (ሶ.ዐ.ወ) እንዲህ ሲሉ ተናግረዋል፡- "አላህ ውጫዊ ቅርጽና ውበታችሁን አይመለከትም። ልቦናችሁን ነው የሚመለከተው።"

(ሙስሊም ዘግቦውታል)

ከሐዲሱ የምንማራቸው ቁምነገሮች

- በሥራ መጠቀምና አጅር ማግኘት የሚቻለው ተግባሩ ከመልካም ኒያ ጋር የተቆራኘ እንደሆነ ብቻ ነው።
- ልቦናን የአላህ ቁጣ ሊያስከትሉ ከሚችሉት በሽታዎች ሁሉ ለማጽዳት ጥረት ማድረግ ከፍተኛ ትኩረት ሊሰጠው የሚገባ ነው።
- ልቦናን የማጽዳቱ ተግባር፡ ከሌሎች ተግባራት ይልቅ ቅድሚያ ትኩረት ሊቸረው ይገባል። ምክንያቱም ለማንኛውም ሥራና እንቅስቃሴ ተቀባይነት ማግኘት ወይም ውድቅ መሆን ወሳኙ የቀልብ ፀአዳነት ወይም መበከል ነውና።

٨ - وَعَنْ أَبِي مُوسَى عَبْدِ اللهِ بْنِ قَيْسٍ الأَشْعَرِيِّ ﷺ قَالَ: سُئِلَ رَسُولُ اللهِ ﷺ عَنِ الرَّجُلِ يُقَاتِلُ شَجَاعَةً وَيُقَاتِلُ حَمِيَّةً وَيُقَاتِلُ رِيَاءً أَيُّ ذَلِكَ فِي سَبِيلِ اللهِ فَقَالَ رَسُولُ اللهِ ﷺ: ((مَنْ قَاتَلَ لِتَكُونَ كَلِمَةُ اللهِ هِيَ الْعُلْيَا فَهُوَ

8- አቡ ሙሳ ዐብደላህ ኢብን ቀይስ አል-ዐሽዐሪይ (ረ.ዐ) እንዳስተላለፉት፡- የአላህ መልዕክተኛ (ሶ.ዐ.ወ) ለጀግንነት ስለሚዋጋ፣ ለዘር ክብር ስለሚዋጋና ለይዩልኝ (ለዝናና ክብር ሲል) ስለሚዋጋ ሰው -የትኛው በአላህ ጉዳና ላይ እንደሆነ- ተጠየቁ። "የአላህ ቃል የበላይ ትሆን ዘንድ የሚፋለም፣

በአላህ ጉዳና ላይ ያለ እርሱ ነው።" ሲሉ ተናገሩ። (ቡኻሪና ሙስሊም)

فِي سَبِيلِ اللهِ)) مُتَّفَقٌ عَلَيْهِ.

ከሐዲሱ የምንማራቸው ቁምነገሮች

- አንድ ተግባር ከአላህ ዘንድ ተቀባይነት ሊያገኝ የሚችለው በጥሩ ኒያ ከተፈፀመ ብቻ ነው። በአላህ መንገድ ላይ፥ የአላህን ቃል የበላይነት ለማስጠበቅ ሲፋለሙ ሰማእት የሆኑ ብቻ ናቸው በቁርአንና በሐዲስ የተጠቀሱ የሰማእታት እጣዎችን ሊጎናፀፉ የሚችሉት። ግና ከፍልሚያው መስክ ላይ የወደቀ ሁሉ እንደ ሰማእት ይቆጠራል። አይታጠብም፣ ከፈንም አይለብስም። እንዲሁ እንዳለ ከነደሙና ልብሱ ይቀበራል። የ"ኒያ" ጉዳይ ለአላህ የተተወ ነው።

٩- وَعَنْ أَبِي بَكْرَةَ نُفَيْعِ بْنِ الْحَارِثِ الثَّقَفِيِّ ﷺ أَنَّ النَّبِيَّ ﷺ قَالَ: ((إِذَا الْتَقَى الْمُسْلِمَانِ بِسَيْفَيْهِمَا فَالْقَاتِلُ وَالْمَقْتُولُ فِي النَّارِ)). قُلْتُ: يَارَسُولَ اللهِ هَذَا الْقَاتِلُ فَمَا بَالُ الْمَقْتُولِ، قَالَ: ((إِنَّهُ كَانَ حَرِيصًا عَلَى قَتْلِ صَاحِبِهِ)). مُتَّفَقٌ عَلَيْهِ.

9- አቡበክረት ኑፈይዕ ኢብን አል-ሐሪሥ ለቀፈይ (ረ.ዐ) እንዲህ ሲሉ አስተላልፈዋል፡- ነቢዩ (ሶ.ዐ.ወ) "ሁለት ሙስሊሞች ሾተል ከተማዘዙ ገዳይም፥ ሟችም እሳት ውስጥ ናቸው።" በማለት ተናገሩ። "የአላህ መልዕክተኛ ሆይ! ገዳይስ ይሁን፣ የሟች ጥፋት ምን ሆኖ ነው (ለቅጣት የበቃው)?" ስል ጠየቅኩ። "ወዳጁን ለመግደል ቋምጦ ነበር።" ሲሉ መለሱ። (ቡኻሪና ሙስሊም)

ከሐዲሱ የምንማራቸው ቁምነገሮች

- ወንጀል ለመፈፀምና የአላህን ሕግጋት ለመተላለፍ የቆረጠና ለውጊያ የሚያበቁ ቅደመ-ሁኔታዎችን ሁሉ ያሟላ -ወንጀሉን ፈፀመም አልፈፀመም- ከተጠያቂነት አያመልጥም።
- ሙስሊሞች እርስ በርስ መሻኮትና መገዳደል የለባቸውም። ጉልበታቸውም ያለ አግባብ እንዲባክንና እንዲደክሙ ከማድረጉ ባሻገር የአላህንም ቁጣ ያስከትላልና።

١٠- وَعَنْ أَبِي هُرَيْرَةَ ﷺ قَالَ: قَالَ رَسُولُ اللهِ ﷺ: ((صَلَاةُ الرَّجُلِ فِي جَمَاعَةٍ تَزِيدُ عَلَى صَلَاتِهِ فِي سُوقِهِ وَبَيْتِهِ بِضْعًا وَعِشْرِينَ دَرَجَةً وَذَلِكَ أَنَّ أَحَدَهُمْ إِذَا تَوَضَّأَ فَأَحْسَنَ الْوُضُوءَ ثُمَّ

10- አቡ ሁረይራ (ረ.ዐ) እንዳስተላለፉት የአላህ መልዕክተኛ (ሶ.ዐ.ወ) እንዲህ ብለዋል፡- "አንድ ሰው በጀመዐ የሚሰግዳት ሶላት ከሥራ ቦታው ወይም ከቤቱ ከሚሰግድባት ሶላት ከሃያ ሦስት እስከ ሰላሳ ደረጃ ብልጫ አላት። ይህም የሚሆነው በተሟላ መልኩ ውዱእ

أَتَـى الْمَسْجِدَ لاَ يُرِيدُ إِلاَّ الصَّلاَةَ لاَ يَـنْهَزُهُ إِلاَّ الصَّلاَةُ لَمْ يَخْطُ خطْوَةً إِلاَّ رُفِـعَ لَـهُ بِهَا دَرَجَةٌ وَحُطَّ عَنْهُ بِهَا خَطِيـئَةٌ حَـتَّى يَدْخُلَ الْمَسْجِدَ فَإِذَا دَخَـلَ الْمَسْجِدَ كَانَ فِي الصَّلاَةِ مَا كَانَت الصَّلاَةُ هِيَ تَحْبِسُهُ وَالْمَلاَئِكَةُ يُصَـلُّونَ عَـلَى أَحَدِكُـمْ مَادَامَ فِي مَجْلِسِهِ الَّذِي صَلَّى فِيهِ يَقُولُونَ اللَّهُمَّ ارْحَمْهُ اللَّهُمَّ اغْفِرْ لَهُ اللَّهُمَّ تُبْ عَلَيْهِ مَالَمْ يُؤْذِ فِيهِ مَالَمْ يُحْدِثْ فِيهِ)).

مُتَّفَقٌ عَلَيْهِ. وَهَذَا لَفْظُ مُسْلِمٍ.

ከፈፀመና ከዚያም ሶላትን እንጂ ሌላን ባለመሻት -ከቤቱ የወጣበት ዓላማ ሶላት ብቻ ሆኖ- ወደ መስጊድ ከመጣ ነው። ወደ መስጊድ በሚያደርገው ጉዞ በእያንዳንዱ እርምጃ አንድ ደረጃ ከፍ ይደረግለታል። በዚያችው እርምጃ አንድ ኃጢአት ይታበስለታል -መስጊድ እስኪገባ ድረስ። መስጊድ ከገባ በኋላም -መስጊድ ውስጥ ለመቆየቱ ምክንያት ሶላቱ ብቻ እስከሆነች ድረስ- ሶላት ውስጥ እንዳለ ይቆጠርለታል። ከናንተ አንዳችሁ የሰገደበትን ቦታ እስካል ለቀቀ፥ ሰዎችን እስካላወከና ውዱእ እስካልፈታ ድረስ መላኢኮች፦ "አላህ ሆይ! ምሕረትን ለግሰው፣ አላህ ሆይ ፀፀቱን ተቀበለው።" እያሉ ዱዓ ያደርጉለታል።" (ቡኻሪና ሙስሊም። የሐዲሱ ቃል የሙስሊም ነው)

ከሐዲሱ የምንማራቸው ቁምነገሮች

- ከሥራ ቦታ ላይ ሶላት መስገድ ይፈቀዳል። ምንም እንኳ ቀልብን ሰብስቦ ለመስገድ ስለማያስችል የሚጠላ ቢሆንም።
- መስጊድ ውስጥ በጀመዐ የሚሰገድ ሶላት ለብቻ ከሚሰገድ ሶላት በ25፣ 26 ወይም 27 ደረጃዎች ይበልጣል።
- ይህን ያህል የላቀ ምንዳ ለማግኘት ቅንነትንና ታማኝነት (ኢኽላስ) ወሳኝነት ይኖረዋል።
- ሶላት ከሌሎች መልካም ተግባራት ብልጫ አላት። ሶላት ውስጥ ላለ ሰው መላኢኮች ዱዓ እንደሚያደርጉ መወሳቱ ይህንኑ ይጠቁማል።
- ለሙእሚኖች ዱዓ ማድረግ ከመላኢኮች ተግባራት አንዱ ነው።

١١- وَعَـنْ أَبِي الْعَبَّاسِ عَبْدِ اللَّهِ بْنِ عَبَّاسِ بْنِ عَبْدِ الْمُطَّلِبِ رضى الله عنهما عَنْ رَسُـولِ الـلَّهِ ﷺ فِيمَا يَرْوِي عَنْ رَبِّهِ تَـبَارَكَ وَتَعَـالَى قَالَ: ((إِنَّ اللهَ كَتَبَ الْحَسَنَاتِ وَالسَّيِّئَاتِ ثُمَّ بَيَّنَ ذَلِكَ فَمَنْ

11- አቢ ዐብባስ ዐብደላህ ኢብን ዐብባስ ኢብን ዐብደል ሙጦሊብ (ረ.ዐ) እንዳስተላለፉት የአላህ መልዕክተኛ (ሶ.ዐ.ወ) በሐዲሰል ቁድሲ ተከታዩን ተናግረዋል፦ "አላህ መልካምና ክፉ ተግባራትን ጽፏል፣ ይህንኑ አብራርቷልም። አንዲትን መልካም ተግባር ለመፈፀም ያሰበና ያልፈፀማት ልዑልና ቅዱስ የሆነው

هَمَّ بِحَسَنَةٍ فَلَمْ يَعْمَلْهَا كَتَبَهَا اللَّهُ تَبَارَكَ وَتَعَالَى عِنْدَهُ حَسَنَةً كَامِلَةً وَإِنْ هَمَّ بِهَا فَعَمِلَهَا كَتَبَهَا اللَّهُ عَشْرَ حَسَنَاتٍ إِلَى سَبْعمِائَةِ ضِعْفٍ إِلَى أَضْعَافٍ كَثِيرَةٍ وَإِنْ هَمَّ بِسَيِّئَةٍ فَلَمْ يَعْمَلْهَا كَتَبَهَا اللَّهُ تَعَالَى عِنْدَهُ حَسَنَةً كَامِلَةً وَإِنْ هَمَّ بِهَا فَعَمِلَهَا كَتَبَهَا اللَّهُ سَيِّئَةً وَاحِدَةً)) مُتَّفَقٌ عَلَيْهِ.

አላህ ከርሱ ዘንድ አንድ ሙሉ መልካም ተግባር (የመልካም ተግባር ምንዳ) ይጽፍለታል። አስቦ ከፈፀማት ደግሞ ከአሥር እስከ ሰባት መቶ እጥፍ፥ ከዚያም በላይ መልካም ተግባራትን ይጽፍለታል። ክፉ ተግባር አስቦ ካልፈፀማት አላህ ከርሱ ዘንድ አንድ ሙሉ መልካም ተግባር ይጽፍለታል። ግና አስቦ ከፈፀማት አንድ ክፉ ተግባር ብቻ ይጽፍበታል።"

(ቡኻሪና ሙስሊም)

ከሐዲሱ የምንማራቸው ቁምነገሮች

- አንድን መልካም ተግባር ለመፈፀም የተነሳሳ ሰው -መፈፀም ባይችል እንኳ- አላህ ምንዳውን አይነሳውም። መልካም ተነሳሽነት የተግባር መሠረት ነው።
- አንድ ክፉ ተግባር ለመፈፀም ተነሳስቶ በሌላ ሰበብ ሳይሆን -ለአላህ ፍራቻ ሲል ብቻ- ከመፈፀም የተቆጠበ አላህ የአንድ መልካም ተግባር ምንዳ ይጽፍለታል። አላህን በመፍራት ከወንጀል መታቀብ በራሱ መልካም ተግባር ነው።

١٢- وَعَنْ أَبِي عَبْدِ الرَّحْمَنِ عَبْدِ اللهِ بْنِ عُمَرَ بْنِ الْخَطَّابِ ﷺ قَالَ سَمِعْتُ رَسُولَ اللهِ ﷺ يَقُولُ: ((انْطَلَقَ ثَلَاثَةُ نَفَرٍ مِمَّنْ كَانَ قَبْلَكُمْ حَتَّى آوَاهُمُ الْمَبِيتُ إِلَى غَارٍ فَدَخَلُوهُ فَانْحَدَرَتْ صَخْرَةٌ مِنَ الْجَبَلِ فَسَدَّتْ عَلَيْهِمُ الْغَارَ فَقَالُوا إِنَّهُ لَا يُنْجِيكُمْ مِنْ هَذِهِ الصَّخْرَةِ إِلَّا أَنْ تَدْعُوا اللهَ بِصَالِحِ أَعْمَالِكُمْ قَالَ رَجُلٌ مِنْهُمْ اللَّهُمَّ كَانَ لِي أَبَوَانِ شَيْخَانِ كَبِيرَانِ وَكُنْتُ لَا أَغْبِقُ قَبْلَهُمَا أَهْلًا وَلَا مَالًا فَنَأَى بِي طَلَبُ الشَّجَرِ

12- አቡ ዐብዱረሕማን ዐብደላህ ኢብን ዑመር ኢብን አል-ኸጣብ (ረ.ዐ)፥ የአላህ መልዕክተኛ (ሶ.ዐ.ወ) ተከታዩን ሲናገሩ አድምጫለሁ በማለት አስተላልፈዋል፦ "ከናንተ በፊት ከነበሩ ሰዎች መካከል ነበር። ሦስት ሰዎች ለጉዞ ተንቀሳቀሱ። ሲመሽባቸው ለአዳር ከአንድ ዋሻ ውስጥ ገቡ። ከተራራ ላይ የነበረ አንድ ቋጥኝ ተንከባሉ ዋሻውን ዘጋባቸው። "አላህን በመልካም ተግባራችሁ ካልለመናችሁት በቀር ከዚህ ቋጥኝ የሚያድናችሁ ነገር አይኖርም።" ተባባሉ። ከመካከላቸው አንዳቸው እንዲህ አለ፦ "አላህ ሆይ! አዛውንት ወላጆች ነበሩኝ። እነርሱ ከመጠጣቸው በፊት ቤተሰቤንም፥ ከብቶቼንም፥ ወተት አላጠጣም ነበር። እንጨት

يَوْمًا فَلَمْ أُرِحْ عَلَيْهِمَا حَتَّى نَامَا فَحَلَبْتُ لَهُمَا غَبُوقَهُمَا فَوَجَدْتُهُمَا نَائِمَيْنِ فَكَرِهْتُ أَنْ أُوقِظَهُمَا وَأَنْ أَغْبِقَ قَبْلَهُمَا أَهْلاً أَوْ مَالاً فَلَبِثْتُ وَالْقَدَحُ عَلَى يَدِي أَنْتَظِرُ اسْتِيقَاظَهُمَا حَتَّى بَرِقَ الْفَجْرُ وَالصِّبْيَةُ يَتَضَاغَوْنَ عِنْدَ قَدَمَيَّ فَاسْتَيْقَظَا فَشَرِبَا غَبُوقَهُمَا اللَّهُمَّ إِنْ كُنْتُ فَعَلْتُ ذَلِكَ ابْتِغَاءَ وَجْهِكَ فَفَرِّجْ عَنَّا مَا نَحْنُ فِيهِ مِنْ هَذِهِ الصَّخْرَةِ فَانْفَرَجَتْ شَيْئًا لاَ يَسْتَطِيعُونَ الْخُرُوجَ مِنْهُ قَالَ الآخَرُ اللَّهُمَّ إِنَّهُ كَانَتْ لِيَ ابْنَةُ عَمٍّ كَانَتْ أَحَبَّ النَّاسِ إِلَيَّ

وَفِي رِوَايَةٍ كُنْتُ أُحِبُّهَا كَأَشَدِّ مَا يُحِبُّ الرِّجَالُ النِّسَاءَ فَأَرَدْتُهَا عَلَى نَفْسِهَا فَامْتَنَعَتْ مِنِّي حَتَّى أَلَمَّتْ بِهَا سَنَةٌ مِنَ السِّنِينَ فَجَاءَتْنِي فَأَعْطَيْتُهَا عِشْرِينَ وَمِائَةَ دِينَارٍ عَلَى أَنْ تُخَلِّيَ بَيْنِي وَبَيْنَ نَفْسِهَا فَفَعَلَتْ حَتَّى إِذَا قَدَرْتُ عَلَيْهَا

وَفِي رِوَايَةٍ فَلَمَّا قَعَدْتُ بَيْنَ رِجْلَيْهَا قَالَتْ اتَّقِ اللَّهَ وَلاَ تَفُضَّ الْخَاتَمَ إِلاَّ بِحَقِّهِ فَانْصَرَفْتُ عَنْهَا وَهِيَ أَحَبُّ النَّاسِ إِلَيَّ وَتَرَكْتُ الذَّهَبَ الَّذِي أَعْطَيْتُهَا اللَّهُمَّ إِنْ كُنْتُ فَعَلْتُ ذَلِكَ ابْتِغَاءَ وَجْهِكَ فَافْرُجْ عَنَّا مَا نَحْنُ فِيهِ

ለቀማ ሩቅ ቦታ ሄድኩ። እስከ ተኙበት ጊዜ ድረስ አልተመለስኩም። ወተታቸውንም አለብኩላቸው። ተኝ ተው አገኘኋቸው። ልቀሰቅሳቸው አል ከጀልኩም። ከነርሱ በፊት ቤተሰቤንና ከብቶቼን ማጠጣትንም አልፈቀድ ኩም። ወተት የያዘውን ዋንጫ በእጄ እንደያዝኩ መንቃታቸውን ስጠባበቅ ጉህ እስኪቀድ ድረስ ቆየሁ። ሕጻናት ከእግሮቼ ሥር ይንጫጫሉ። ወላጆቼ ከእንቅልፋቸው ነቅተው ወተታቸውን ጠጡ። አላህ ሆይ! ይህንን ድርጊት የፈፀምኩት የአንተን ውዴታ ከጅዬ ከሆነ በዚህ ቋጥኝ ሰበብ ከደረሰብን መከራ አውጣን።" ቋጥኙ ትንሽ ከፈት አለ። መውጣት የማያስችላቸው ያክል። ሌላኛው ደግሞ እንዲህ አለ:- "የአጐት ልጅ ነበረችኝ። እጅግ አፈቅራት ነበር።" በሌላ ዘገባ እንደ ተደወሳው:- "አንድ ወንድ አንዲትን ሴት የሚያፈ ቅራትን የመጨረሻው የፍቅር እርከን ያክል አፈቅራታለሁ። ለወሲባዊ ተራክቦ ጠየቅኳት። ፈቃደኛ አልሆነችም። አንድ የድርቅ ዓመት ተከሠተ። (እርዳታዬን ፍለጋ) ከኔ ዘንድ መጣች። የምፈልገ ውን እንድፈጽም ቃል አስገብቼ አንድ መቶ ሃያ ዲርሃም ሰጠኋት። ቃሏን አከበረች፣ ያሻኝን ማረግ እስክችል ድረስ።" በሌላ ዘገባ ላይ እንደተወሳው ደግሞ:- "በጭኖቿ መሐል እንደገባሁ:- «አላህን ፍራ! ያለ አግባብ ክብረ-ንጽህናዬን አትገርስስ።» አለችኝ። ዘወር አልኩ። ምንም ነገር ሳልፈጽም። ከማንም አብልጬ እወዳታለሁ። የሰጠኋትንም ወርቅ ተውኩላት። አላህ ሆይ! ይህንን ተግባር የፈፀምኩት

فَانْفَـرَجَتْ الصَّـخْرَةُ غَيْـرَ أَنَّهُمْ لاَ يَسْتَطِيعُونَ الْخُرُوجَ مِنْهَا وَقَالَ الثَّالِثُ اللَّهُمَّ اسْـتَأْجَرْتُ أُجَرَاءَ وَأَعْطَيْتُهُمْ أَجْرَهُمْ غَيْرَ رَجُلٍ وَاحِدٍ تَرَكَ الَّذِى لَهُ وَذَهَبَ فَثَمَّرْتُ أَجْرَهُ حَتَّى كَثُرَتْ مِنْهُ الأَمْوَالُ فَجَاءَنِى بَعْدَ حِينٍ فَقَالَ يَاعَبْدَ اللهِ أَدِّ إِلَيَّ أَجْرِى فَقُلْتُ كُلُّ مَاتَرَى مِنْ أَجْرِكَ مِنَ الإِبِلِ وَالْبَقَرِ وَالْغَنَمِ وَالرَّقِيقِ فَقَالَ يَاعَبْدَ اللهِ لاَتَسْتَهْزِئْ بِى! فَقُلْتُ لاَأَسْتَهْزِئُ بِكَ فَأَخَذَهُ كُلَّهُ فَاسْتَاقَهُ فَلَمْ يَتْرُكْ مِنْهُ شَيْئًا اللَّهُمَّ إِنْ كُنْتُ فَعَلْتُ ذَلِكَ ابْتِغَاءَ وَجْهِكَ فَافْرُجْ عَنَّا مَانَحْنُ فِيـهِ! فَانْفَـرَجَتْ الصَّخْرَةُ فَخَرَجُوا يَمْشُونَ)). مُتَّفَقٌ عَلَيْهِ.

የአንተን ውዴታ ከጅዬ ከሆነ ካለንበት መከራ አውጣን።" ቋጥኙ ትንሽ ከፈት አለ። መውጣት ግን አይችሉም። ሦስተኛው እንዲህ አለ፦ "ሠራተኞችን ቀጠርኩ። ለሁሉም ያገልግሎት ክፍያቸውን ከፈልኳቸው፤ ከመካከላቸው አንዱ ሲቀር። ድርሻውን ከኔ ዘንድ ትቶ ሄደ። ትቶት የሄደውን ገንዘብ አባዛሁለት፤ ብዙ ሃብት እስኪሆን ድረስ፡ ከዘመናት በኋላ ከኔ ዘንድ መጣ። እንዲህም አለኝ፦ «ዐብደላህ ሆይ! ድርሻየኝ ስጠኝ» «ይህ የምትመለከተው ሁሉ -ግመሉም፣ ከብቱም፣ ፍየሉም፣ ባሪያውም- ድርሻህ ነው።» አልኩት። «ዐብደላህ ሆይ! አትቀልድብኝ።» አለኝ። «እየቀለድኩብህ አይደለም።» አልኩት። ሁሉንም ተረክቦ እየነዳ ወሰደ። አንዳችም ነገር አልተወም። አላህ ሆይ! ይህንን የፈፀምኩት ያንተን ውዴታ በመሻት ከሆነ ካለንበት መከራ አውጣን።" ቋጥኙ ተከፈተ። ወጥተው ጉዟቸውን ቀጠሉ።"
(ቡኻሪና ሙስሊም)

ከሐዲሱ የምንማራቸው ቁምነገሮች

- በመከራ ሰዓትና በሌላም ወቅት ዱዓ ማድረግ፣ እንዲሁም መልካም ተግባራትን እያወሱ አላህን መማፀን ይወደዳል።
- ለወላጆች በጐ መዋል፣ እነርሱን ማገልገልና ከልጅ፣ ከሚስት... ይበልጥ ለነርሱ ቅድሚያ መስጠት ጠቃሚ ተግባር ነው።
- ከሐራም መጠበቅ ብተለይም ማድረግ እየቻሉ ለአላህ ሲሉ ብቻ መቆጠብ እጅግ ድንቅ ተግባር ነው።
- ቃልኪዳንን መሙላትና አደራን ለባለቤቱ መመለስ፣ መልካም ማኅበራዊ ውሎ ጽድቅ ከንውኖች ይህና ሌሎችንም የቁርአንና የሐዲስ ዘገባዎች ያመለክታሉ።
- በጭንቅ ሰዓት በቅንነትና ታማኝነት (ኢኽላስ) የሚደረግ ዱዓ ተቀባይነት ይኖረዋል።
- አላህ የበጐ ሠሪዎችን ውለታ አያጠፋም።

ምዕራፍ 2

ተውበት (ፀፀት)

٢- بَابُ التَّوبَةِ

ዑለሞች እንደሚሉት፦ ከየትኛውም ኃጢአት መፀፀት (ተውበት) ግዴታ (ዋጂብ) ነው። የተፈፀመው ወንጀል በአላህና በሰውየው መካከል ብቻ ተወስኖ የሚቀርና ከሰው መብት (ሐቅ) ጋር ያልተነካካ ከሆነ ከእንዲህ ዓይነቱ ወንጀል ለመቶበት ሦስት ቅድመሁኔታዎች (ሸርጦች) መሟላት አለባቸው፦

(1) ሰውየው ወንጀሉን ማቆም አለበት።

(2) ለሠራው ኃጢአት፥ ለፈፀመው ጥፋት መቆጨት ይኖርበታል።

(3) ወደፊት እንዲህ ዓይነቱን ኃጢአት ዳግም ላለመፈፀም ቁርጥ ውሳኔ ማድረግ ይጠበቅበታል።

ከነኝህ ሦስት ቅድመሁኔታዎች አንዱ ከጐደለ ተውበቱ ተቀባይነት የለውም። ወንጀሉ ከሰዎች መብት (ሐቅ) ጋር የተያያዘ ከሆነ ደግሞ ለተውበት አራት ሸርጦች መሟላት አለባቸው። ከላይ የተጠቀሱት ሦስቱና ከሰውየው ሐቅ መጽዳት። ገንዘብ ወይም መሰል ነገር ከሆነ ይመልስለታል። በዝሙት ወይም በሐሜት ስሙን አጥፍቶ ከሆነ ተግቢውን ቅጣት ይቀበላል፥ ወይም ይቅርታውን ይጠይቃል...። አንድ ሰው ከሁሉም ኃጢአቶቹ የመቶበት ግዴታ አለበት። ከከፊሉ ብቻ ከቶበተም ከዚያ

قَالَ الْعُلَمَاءُ التَّوْبَةُ وَاجِبَةٌ مِنْ كُلِّ ذَنْبٍ فَإِنْ كَانَتِ الْمَعْصِيَةُ بَيْنَ الْعَبْدِ وَبَيْنَ اللَّهِ تَعَالَى لاَ تَتَعَلَّقُ بِحَقِّ آدَمِيٍّ فَلَهَا ثَلاَثَةُ شُرُوطٍ أَحَدُهَا أَنْ يُقْلِعَ عَنِ الْمَعْصِيَةِ وَالثَّانِي أَنْ يَنْدَمَ عَلَى فِعْلِهَا وَالثَّالِثُ أَنْ يَعْزِمَ أَنْ لاَ يَعُودَ إِلَيْهَا أَبَدًا فَإِنْ فُقِدَ أَحَدُ الثَّلاَثَةِ لَمْ تَصِحَّ تَوْبَتُهُ وَإِنْ كَانَتِ الْمَعْصِيَةُ تَتَعَلَّقُ بِآدَمِيٍّ فَشُرُوطُهَا أَرْبَعَةٌ هَذِهِ الثَّلاَثَةُ وَأَنْ يَبْرَأَ مِنْ حَقِّ صَاحِبِهَا فَإِنْ كَانَتْ مَالاً أَوْ نَحْوَهُ رَدَّهُ إِلَيْهِ وَإِنْ كَانَتْ حَدَّ قَذْفٍ وَنَحْوَهُ مَكَّنَهُ مِنْهُ أَوْ طَلَبَ عَفْوَهُ وَإِنْ كَانَ غِيبَةً اسْتَحَلَّهُ مِنْهَا وَيَجِبُ أَنْ يَتُوبَ مِنْ جَمِيعِ الذُّنُوبِ فَإِنْ تَابَ مِنْ بَعْضِهَا صَحَّتْ تَوْبَتُهُ عِنْدَ أَهْلِ الْحَقِّ مِنْ ذَلِكَ الذَّنْبِ وَبَقِيَ عَلَيْهِ الْبَاقِي وَقَدْ تَظَاهَرَتْ دَلاَئِلُ الْكِتَابِ وَالسُّنَّةِ وَإِجْمَاعِ الأُمَّةِ عَلَى وُجُوبِ التَّوْبَةِ

(قال الله تعالى) ﴿وَتُوبُوا إِلَى اللهِ جَمِيعًا أَيُّهَا الْمُؤْمِنُونَ لَعَلَّكُمْ تُفْلِحُونَ﴾ وقال تعالى ﴿اسْتَغْفِرُوا رَبَّكُمْ ثُمَّ تُوبُوا إِلَيْهِ﴾ وقال تعالى ﴿يَاأَيُّهَا الَّذِينَ آمَنُوا تُوبُوا إِلَى اللهِ تَوْبَةً نَصُوحًا﴾.

ኃጢአት መመለሱ ተቀባይነት ይኖረዋል። ሌሎች ወንጀሎች እንዳሉ ይቀራሉ። ተውበት ዋጂብ መሆኑን አያሌ የቁርአን አንቀጾችና የሐዲስ ዘገባዎች ያመለክታሉ። የዑለሞች ስምምነትም (ኢጅማዕ) ይህንኑ ያፀድቃል። አላህ እንዲህ ብሏል፦

"ምእምናኖች ሆይ! ትድኑ ዘንድ ሁላችሁም ወደ አላህ (በመመለስ) ተፀፀቱ።..." (አል-ኑር፥ 31)

"እላንተ ያመናችሁ ሆይ! ንጹሕ የሆነችን ፀፀት በመፀፀት ወደ አላህ ተመለሱ፤" (አል-ተሕሪም፥ 8)

١٣- وَعَنْ أَبِي هُرَيْرَةَ ﷺ قال: سَمِعْتُ رَسُولَ اللهِ ﷺ يَقُولُ: ((وَاللهِ إِنِّي لَأَسْتَغْفِرُ اللهَ وَأَتُوبُ إِلَيْهِ فِي الْيَوْمِ أَكْثَرَ مِنْ سَبْعِينَ مَرَّةً)) رَوَاهُ الْبُخَارِيُّ.

13- የአላህ መልዕክተኛ (ሶ.ዐ.ወ) ተከታዩን ሲናገሩ አድምጫለሁ በማለት አቡ ሁረይራ (ረ.ዐ) አስተላልፈዋል፦ "እኔ በየቀኑ ከሰባ ጊዜ በላይ አላህን ምሕረቱን እማፀናለሁ፤ ወደርሱም እመለሳለሁ።" (ቡኻሪና ሙስሊም)

ከሐዲሱ የምንማራቸው ቁምነገሮች

- መልዕክተኛው (ሶ.ዐ.ወ) ከወንጀል የተጠበቁና ከሰው ሁሉ በላጭ፥ እንዲሁም አላህ ጥቃቅን ግድፈታቸውን ሁሉ የማራቸው ከመሆናቸው ጋር በየቀኑ ከሰባ ባላነሰ ጊዜ አላህን ምሕረት ይለምናሉ፤ ወደርሱም በፀፀት ይመለሳሉ። ይህም በሙስሊሙ ጎብረተሰብ ላይ የተውበት ስሜት እንዲዳብር ግፊት ለማሳደር የተደረገ ነው።

١٤- وَعَنِ الأَغَرِّ بْنِ يَسَارٍ الْمُزَنِيِّ ﷺ قال: قَالَ رَسُولُ اللهِ ﷺ ((يَاأَيُّهَا النَّاسُ تُوبُوا إِلَى اللهِ وَاسْتَغْفِرُوهُ فَإِنِّي أَتُوبُ فِي الْيَوْمِ مِائَةَ مَرَّةٍ)) رَوَاهُ مُسْلِمٌ.

14- አል-አገር ኢብን የሳር አል-መደኒይ (ረ.ዐ) አንዳስተላለፉት የአላህ መልዕክተኛ (ሶ.ዐ.ወ) እንዲህ ብለዋል፦ "እናንተ ሰዎች ሆይ! ወደ አላህ በፀፀት ተመለሱ፤ (ተውበት አድርጉ)፤ ምሕረትንም ለምኑት፤ እኔ በየቀኑ መቶ ጊዜ ተውበት አደርጋለሁ።" (ሙስሊም እንደዘገቡት)

ከሐዲሱ የምንማራቸው ቁምነገሮች

ከላይ ከተጠቀሰው አስተምህሮ በተጨማሪ፦
- ምሕረትን መለመን እና ተውበትን ማብዛት አጽንኦት ለመስጠት ነው እዚህ ላይ የተፈለገው። ከዚህ ላይና ከላይ ከተጠቀሰው ሐዲስ የተወሰኑ ቁጥሮች ለገደብ ሳይሆን ብዛትን አመልካች ናቸው።

١٥- وَعَنْ أَبِي حَمْزَةَ أَنَسِ بْنِ مَالِكٍ الأَنْصَارِيِّ خَادِمِ رَسُولِ اللهِ ﷺ، ﷺ قَالَ: قَالَ رَسُولُ اللَّهِ ﷺ: ((اللهُ أَفْرَحُ بِتَوْبَةِ عَبْدِهِ مِنْ أَحَدِكُمْ سَقَطَ عَلَى بَعِيرِهِ وَقَدْ أَضَلَّهُ فِي أَرْضٍ فَلاَةٍ))

مُتَّفَقٌ عَلَيهِ. وَفِي رِوَايَةٍ لِمُسْلِمٍ

((اللهُ أَشَدُّ فَرَحًا بِتَوْبَةِ عَبْدِهِ حِينَ يَتُوبُ إِلَيْهِ مِنْ أَحَدِكُمْ كَانَ عَلَى رَاحِلَتِهِ بِأَرْضٍ فَلاَةٍ فَانْفَلَتَتْ مِنْهُ وَعَلَيْهَا طَعَامُهُ وَشَرَابُهُ فَأَيِسَ مِنْهَا فَأَتَى شَجَرَةً فَاضْطَجَعَ فِي ظِلِّهَا وَقَدْ أَيِسَ مِنْ رَاحِلَتِهِ فَبَيْنَمَا هُوَ كَذَلِكَ إِذْ هُوَ بِهَا قَائِمَةً عِنْدَهُ فَأَخَذَ بِخِطَامِهَا ثُمَّ قَالَ مِنْ شِدَّةِ الْفَرَحِ اللَّهُمَّ أَنْتَ عَبْدِي وَأَنَا رَبُّكَ أَخْطَأَ مِنْ شِدَّةِ الْفَرَحِ.))

15- የአላህ መልዕክተኛ (ሶ.ዐ.ወ) አገልጋይ አቡ ሐምዘት አነስ ኢብን ማሊክ አል-አንሷሪይ (ረ.ዐ) መልዕክተኛ (ሶ.ዐ.ወ) እንዲህ ሲሉ መናገራቸውን አስተላልፈዋል፦ "ከናንተ አንዳችሁ ምድረ በዳ መሬት ላይ ያጣትን ግመሉን በድንገት ሲያገኝ ከሚሰማው ደስታ የበለጠ አላህ በባሪያው ተውበት ይረካል።"

(ቡኻሪና ሙስሊም)

በሌላ ዘገባ ደግሞ በሚከተለው መልኩ ተወስቷል፦

"ከናንተ አንዳችሁ ምድረ በዳ መሬት ላይ ከግመሉ ላይ ነበር። አመለጠችው። ምግቡንም፣ መጠጡንም እንደያዘች። እንደማያገኛት ተስፋ ቆርጦ ከአንዲት ዛፍ ተደገፈ፣ ከጥላዋ ተጠለለ። ግመሉን እንደማያገኛት ተስፋ ቆርጧል። በእንዲህ ዓይነት ሁኔታ ላይ እያለ ግመሉ ከፊት ለፊቱ ቆማ አገኛት -በድንገት። ልጓሟን ያዘና እንዲህ አለ -ከደስታ ብዛት፦ "አላህ ሆይ፣ አንተ ባሪያዬ ነህ፣ እኔ ደግሞ ጌታህ።" ከደስታ ብዛት ስህተት ፈፀመ። አላህ በባሪያው ተውበት ከዚህ ሰው ደስታ ይበልጥ እርካታ ይሰማዋል።"

ከሐዲሱ የምንማራቸው ቁምነገሮች

- አላህ የባሮቹን ተውበት በመቀበል ምን ያህል ለነርሱ ፍቅርና ርኅራኄ እንዳለው ይህ ዘገባ ያመለክታል።
- ይህ ዘገባ ለተውበት ያነሳሳል።

- አንድን ነገር ይበልጥ ለማብራራትና ግልጽ ለማድረግ ምሳሌዎችን እየጠቀሱ ማስተማር ከነቢዩ (ሶ.ዐ.ወ) የማስተማር ስልቶች አንዱ ነው።
- አንድን ነገር በአጽንኦት ለመግለጽና ተዝዉው ትኩረት እንዲሰጠው ለማድረግ መሐላ መፈፀም ይፈቀዳል።

١٦- وَعَنْ أَبِي مُوسَى عَبْدِ اللهِ بْنِ قَيْسٍ الأَشْعَرِيِّ ﷺ عَنِ النَّبِيِّ ﷺ قَالَ: ((إِنَّ اللهَ تَعَالَى يَبْسُطُ يَدَهُ بِاللَّيْلِ لِيَتُوبَ مُسِيءُ النَّهَارِ وَيَبْسُطُ يَدَهُ بِالنَّهَارِ لِيَتُوبَ مُسِيءُ اللَّيْلِ حَتَّى تَطْلُعُ الشَّمْسُ مِنْ مَغْرِبِهَا)) رَوَاهُ مُسْلِمٌ.

16- አቡ ሙሳ ዐብደላህ ኢብን ቀይስ አል-ዐሽዐሪይ (ረ.ዐ) እንዳስተላለፉት ነቢዩ (ሶ.ዐ.ወ) እንዲህ ብለዋል፡- "አላህ በሌሊት እጁን ይዘረጋል፥ ቀን ጥፋት የፈፀመ ተውበት ያደርግ ዘንድ፣ በቀን እጁን ይዘረጋል፥ ሌሊት ጥፋት የፈፀመ ተውበት ያደርግ ዘንድ። ፀሐይ በመግቢያዋ እስከምትወጣበት ዕለት ድረስ።" (ሙስሊም እንደዘገቡት)

ከሐዲሱ የምንማራቸው ቁምነገሮች

- አላህ ለባሮቹ ያለው እዝነትና ይቅር ባይነቱ ሁሉንም ዘመናት የሚያጠቃልል ነው። ለተወሰነ ጊዜ ብቻ የተለየ አይደለም።
- በቀን ወይም በሌሊት ለተፈፀመ ጥፋት አፋጣኝ ተውበት ማድረግ ተገቢ እንደሆነ ይህ ዘገባ ያመለክታል።
- የተወበት በራፍ ክፍት እስከሆነ ድረስ ተውበት ምንጊዜም ተቀባይነት ይኖረዋል። የተውበት በራፍ የሚዘጋው ከቂያማ ታላላቅ ምልክቶች አንዱ የሆነው ፀሐይ በመግቢያዋ የመውጣት ክስተት እውን ሲሆን ነው።

١٧- وَعَنْ أَبِي هُرَيْرَةَ ﷺ قَالَ: قَالَ رَسُولُ اللهِ ﷺ: ((مَنْ تَابَ قَبْلَ أَنْ تَطْلُعَ الشَّمْسُ مِنْ مَغْرِبِهَا تَابَ اللهُ عَلَيْهِ)) رَوَاهُ مُسْلِمٌ.

17- አቡ ሁረይራ (ረ.ዐ) እንዳስተላለፉት የአላህ መልዕክተኛ (ሶ.ዐ.ወ) እንዲህ ሲሉ ተናግረዋል፡- "ፀሐይ በመግቢያዋ ከመ ውጣቷ በፊት ተውበት ያደረገ አላህ ተውበቱን ይቀበለዋል።" (ሙስሊም እንደዘገቡት)

ከሐዲሱ የምንማራቸው ቁምነገሮች

- አላህ የአንድን ሰው ተውበት፥ የተውበት ሸርጦች እስከተሟሉ ድረስ ይቀበላል። ፀሐይ በመግቢያዋ መውጣት ከመጀመሯ በፊት መሆኑ ከተውበት ሸርጦች አንዱ ነው።

١٨- وَعَنْ أَبِي عَبْدِ الرَّحْمَنِ عَبْدِ اللهِ بْنِ عُمَرَ بْنِ الْخَطَّابِ رضي الله عنهما عَنِ

18- አቡ ዐብዱረሕማን ዐብደላህ ኢብን ዑመር ኢብን አል-ኸጧብ (ረ.ዐ) እንዳስተላለፉት ነቢዩ (ሶ.ዐ.ወ) እንዲህ ብለዋል፡-

النَّبِيُّ ﷺ قَالَ: ((إِنَّ اللَّهَ عَزَّ وَجَلَّ يَقْبَلُ تَوْبَةَ الْعَبْدِ مَالَمْ يُغَرْغِرْ)).

رَوَاهُ التِّرْمِذِيُّ وقال حَدِيثٌ حَسَنٌ.

"የክብርና የልዕልና ባለቤት የሆነው አላህ አንድን ሰው ተውበት ይቀበላል፤ ሰውየው ከሞት አፋፍ ላይ እስካልሆነ ድረስ።"

(ቲርመዚይ ዘግበውታል፡ ሐዲሱ "ሐሰን" ነውም ብለዋል)

ከሐዲሱ የምንማራቸው ቁምነገሮች

- አንድ ሰው የሚሞትበት የመጨረሻ ቁርጥ ሰዓት ከመድረሱ በፊት ተውበት ማድረጉ ከተውበት ሸርጦች አንዱ ነው።

١٩- وَعَنْ زِرِّ بْنِ حُبَيْشٍ قَالَ أَتَيْتُ صَفْوَانَ بْنَ عَسَّالٍ ﷺ أَسْأَلُهُ عَنِ الْمَسْحِ عَلَى الْخُفَّيْنِ فَقَالَ مَاجَاءَ بِكَ يَازِرُّ؟ فَقُلْتُ: ابْتِغَاءَ الْعِلْمِ. فَقَالَ: إِنَّ الْمَلَائِكَةَ تَضَعُ أَجْنِحَتَهَا لِطَالِبِ الْعِلْمِ رِضًى بِمَا يَطْلُبُ. فَقُلْتُ: إِنَّهُ قَدْ حَكَّ فِي صَدْرِي الْمَسْحُ عَلَى الْخُفَّيْنِ بَعْدَ الْغَائِطِ وَالْبَوْلِ وَكُنْتَ امْرَأً مِنْ أَصْحَابِ النَّبِيِّ ﷺ فَجِئْتُ أَسْأَلُكَ هَلْ سَمِعْتَهُ يَذْكُرُ فِي ذَلِكَ شَيْئًا؟ قَالَ: نَعَمْ كَانَ يَأْمُرُنَا إِذَا كُنَّا سَفَرًا أَوْ مُسَافِرِينَ أَنْ لَانَنْزِعَ خِفَافَنَا ثَلَاثَةَ أَيَّامٍ وَلَيَالِيَهُنَّ إِلَّا مِنْ جَنَابَةٍ لَكِنْ مِنْ غَائِطٍ وَبَوْلٍ

19- ዚር ኢብን ሑበይሽ እንዲህ ሲሉ አስተላልፈዋል፦ በ"ኹፍ" ላይ ስለማበስ ልጠይቀው ከሶፍዋን ኢብን ዐሳል (ረ.ዐ) ዘንድ ሄድኩ። "ዚር ሆይ! ምን አመጣህ?" አለኝ። "እውቀት ፍለጋ ነው የመጣሁት።" አልኩት። "መላኢኮች ለእውቀት ፈላጊ ከንፋቸውን ይዘረጋሉ፤ በሚፈልገው ነገር በመርካት።" አለ። "ከሽንት ወይም ከመፀዳዳት በኋላ በ"ኹፍ" ላይ የማበስ ነገር (ይፈቀድ አይፈቀድ) ግራ ገብቶኛል። አንተ ደግሞ ከነቢዩ (ሶ.ዐ.ወ) ባልደረቦች አንዱ ነህ። ስለዚህ ጉዳይ ልጠይቅህ ነው የመጣሁት። ነቢዩ (ሶ.ዐ.ወ) ይህን አስመልክቶ አንዳች ነገር ሲሉ አድምጠሃልን?" አልኩት። "አዎ፤ በጉዞ ላይ (ሰፈር) በምንሆንበት ወቅት ሦስት ቀን ከነሌሊቱ ኹፍችን እንዳናወልቅ ያዙን ነበር፤ ለጀናባ ሲቀር። ለሽንት፣ ሰገራና መኝታ ግን አናወልቅም።" አለ። "ስለፍቅርስ አንዳች ነገር ሲሉ ሰምተሃልን?" አልኩት፤ "አዎ፤ በአንድ ጉዞ ላይ ከአላህ መልዕክተኛ (ሶ.ዐ.ወ) ጋር ነበርን። ከእርሳቸው ዘንድ እያለን አንድ በደዊን ድምፁን ከፍ አድርጉ

ጠራቸው። "ሙሐመድ ሆይ!" አላቸው። የአላህ መልዕክተኛ (ሶ.ዐ.ወ) እንደርሱ ድምጻቸውን ከፍ አድርገው "አለሁ፤ እዚሁ ነኝ።" በማለት መለሱለት። "ወዮልህ! ድምጽህን ዝቅ አድርገህ ተናገር። ከነቢዩ (ሶ.ዐ.ወ) ዘንድ ነው ያለኸው። እዚህ ላይ ድምጽህን ከፍ አድርገህ እንዳትናገር ተከልክለሃል።" አልኩት። "በአላህ ይሁንብኝ ድምጼን ዝቅ አላደርግም።" አለ። ከዚያም፡- "ሰውየው ሰዎችን በእጅጉ ያፈቅራል። ወደነርሱ የም ጥቀት ደረሻ የሚያዘልቅን መልካም ሥራ ግን አልሠራም።" አላቸው። ነቢዩ (ሶ.ዐ.ወ) "ሰውየው የቂያማ ዕለት ከሚወደው ጋር ነው።" አሉ። ንግግራቸውን በመቀጠልም በፀሐይ መግቢያ የሚገኝ አንድ በራፍ አወሱ። የጉን ስፋቱ አርባ ወይም ሰባ ዓመ ታት ያክል ነው። ወይም የጉን ስፋቱ ጋላቢን አርባ ወይም ሰባ ዓመታት ያስኬዳል።" ይህን ዘገባ ካስተላለፉት ሰዎች መካከል አንዱ የሆነው ሱፍያን እንደተናገሩት፡- "ይህ በራፍ የሚገኘው በሻም አቅጣጫ ነው። አላህ ሰማያትንና ምድርን የፈጠረ ዕለት ለተውበት ክፍት አድርጉ የፈጠረው ነው። ፀሐይ እርሱ ባለበት አቅጣጫ እስክትወጣ ድረስ አይዘጋም።" (ቲርመዚይና ሌሎችም ዘግበውታል፡ ሐዲሱን "ሐሰኑን ሶሒሕ" ነውም ብለዋል)

وَنَـوْمٍ. فَقُلْتُ: هَلْ سَمِعْتَهُ يَذْكُرُ فِي الْهَـوَى شَـيْئًا: قَالَ: نَعَمْ كُنَّـا مَعَ رَسُولِ اللهِ ﷺ فِي سَفَرٍ فَبَيْنَا نَحْنُ عِنْدَهُ إِذْ نَـادَاهُ أَعْرَابِيٌّ بِصَوْتٍ لَهُ جَهْوَرِيٍّ يَا مُحَمَّدُ. فَأَجَابَهُ رَسُولُ اللهِ ﷺ نَحْوًا مِنْ صَـوْتِهِ ((هَـاؤُمُ)) فَقُلْتُ لَهُ وَيْحَكَ اغْضُضْ مِنْ صَوْتِكَ فَإِنَّكَ عِنْـدَ النَّبِيِّ ﷺ وَقَدْ نُهِيتَ عَنْ هَذَا! فَقَالَ: وَاللهِ لاَ أَغْضُـضُ. قَالَ الأَعْرَابِيُّ: الْمَرْءُ يُحِبُّ الْقَوْمَ وَلَمَّا يَلْحَقْ بِهِمْ؟ قَالَ النَّبِيُّ ﷺ: ((الْمَـرْءُ مَـعَ مَـنْ أَحَـبَّ يَـوْمَ الْقِيَامَـةِ)) فَمَا زَالَ يَحَدِّثُنَا حَتَّى ذَكَرَ بَابًـا مِـنَ الْمَغْرِبِ مَسِيرَةُ عَرْضِهِ أَوْ يَسِـيرُ الرَّاكِبُ فِي عَرْضِهِ أَرْبَعِينَ أَوْ سَـبْعِينَ عَامًا. قَالَ سُفْيَانُ أَحَدُ الرُّوَاةِ: قِـبَلَ الشَّامِ خَلَقَهُ اللهُ تَعَالَى يَوْمَ خَلَقَ السَّـمَوَاتِ وَالأَرْضَ مَفْتُوحًا لِلتَّوْبَةِ لاَ يُغْلَقُ حَتَّى تَطْلُعَ الشَّمْسُ مِنْهُ.

رَوَاهُ التِّرْمِذِيُّ وَغَيْرُهُ وَقَالَ حَدِيثٌ حَسَنٌ صَحِيحٌ.

ከሐዲሱ የምንማራቸው ቁምነገሮች

- እውቀት የመፈለግ ጠቀሜታና እያንዳንዱ ሙስሊም ስለዲኑ ጉዳይ የማያውቀውን ለማወቅ ጥረት ማድረግ እንደሚጠበቅበት።
- በጉዞ ላይ ያለ (መሳፈር) ሦስት ቀን ከነሌሊቱ፡ ሀገር ቤት ውስጥ ያለ ደግሞ አንድ ቀን ከነሌሊቱ በ"ኹፍ" ላይ ማበስ ይፈቀድላቸዋል። የጊዜ አቆጣጠሩ

የሚጀምረው ኹፍን ካጠለቁ በኋላ ውዱእ ካፈረሱበት ወቅት ነው። በኹፍ ላይ ለማበስ ተከታዮቹ ቅድመ-ሁኔታዎች መሟላት የግድ ነው። ኹፉ ጡሃራ መሆን አለበት፣ ከተሟላ ንጽሕና በኋላ መለበስም ይኖርበታል። የእግርን ቁርጭምጭሚቶች የሚሸፍን ሊሆን ይገባል። በኹፍ ላይ ማበስ የሚቻለው ለውዱእ ብቻ ነው። ለጀናባ፣ ለሐይድ ወይም ለወሊድ (ኒፋስ) አይፈቀድም።

- ውለሞችና ደጋግ ሰዎችን በምናናግርበት ጊዜ፣ እንዲሁም ዒልም ከሚሰጥበት ቦታ ላይ ድምጽን ዝቅ አድርጉ መናገር አስላማዊ ሥነ-ሥርዓት (አደብ) ነው።
- የማያውቅን ሰው መልካም ሥነ-ምግባራትንና ጥሩ ማኅበራዊ ውሉን ማስተማር ተገቢ ነው።
- የነቢዩ (ሶ.ዐ.ወ) መልካም አርአያነት ከዚህ ዘገባ ላይ ተመልክቷል። መልካም ባሕሪያቸው፣ ሰዎችን በእውቀታቸውና በአዕምሮ ደረጃቸው ልክ ማናገራቸው።
- ከደጋግ ሰዎች ጋር አብሮ መዋል፣ እነርሱን ማክበርና መቅረብ፣ እንዲሁም መጥፎ ሰዎችን ከመቀላቀል መራቅና እነርሱን ከማፍቀር መቆጠብ።
- አፍቃሪ ወደ ተፈቃሪ የሕይወት መስመር መላብንና ለርሱ ታዛዥ እንዲሆን ማድረግ የፍቅር ዓይነተኛ ባሕሪ ነው።
- ሰዎችን በምናስተምርበትና በምንመክርበት ወቅት መጭውን ሕይወት በብሩህ ተስፋ እንዲመለከቱትና የሰዎችን ልቦና ሊስብ በሚችል ማራኪ አቀራረብ ምክሮችን መለገስ ይጠበቅብናል።
- የአላህን ርህራኄና ትሩፋት (ረሕመት) ስፋት፣ ለስኬት የሚያበቁ መስመሮችን ምን ያክል ቀላል እንዳደረጋቸውና የተውበትን በራፍ ወለል አድርጉ መክፈቱን ይህ ዘገባ በጉልህ ያሳያል።

20- አቡ ሰዒድ ኢብን ማሊክ ኢብን ሲናን አል-ኹድሪይ (ረ.ዐ) እንዳስተላለፉት የአላህ መልዕክተኛ (ሶ.ዐ.ወ) እንዲህ ሲሉ ተናግረዋል፦ "ከናንተ በፊት በነበረው ዘመን አንድ የዘጠና ዘጠኝ ሰዎችን ነፍስ ያጠፋ ሰው ነበር። ምድር ላይ ካሉ ሰዎች ሁሉ ይበልጥ ዐዋቂው ማን እንደሆነ ጠየቀ። ወደ አንድ መናኝ አመላከቱት። ከርሱ ዘንድ ሄደ። ዘጠና ዘጠኝ ነፍስ እንዳጠፋና ተውበት ቢያደርግ ተቀባይነት ያገኝ እንደሆነ ጠየቀው። "አታገኝም።" አለው -መናኙ። ገደለውና መቶ ሞላ። ከዚያም ምድር ላይ ካሉ ሰዎች ሁሉ ይበልጥ ዐዋቂው ማን እንደሆነ ጠየቀ ። ወደ አንድ ዐዋቂ ሰው አመላከቱት። አንድ

٢٠- وَعَنْ أَبِي سَعِيدٍ سَعْدِ بْنِ مَالِكِ بْنِ سِنَانٍ الْخُدْرِيِّ ﷺ أَنَّ نَبِيَّ اللهِ ﷺ قَالَ ((كَانَ فِيمَنْ كَانَ قَبْلَكُمْ رَجُلٌ قَتَلَ تِسْعَةً وَتِسْعِينَ نَفْسًا فَسَأَلَ عَنْ أَعْلَمِ أَهْلِ الأَرْضِ فَدُلَّ عَلَى رَاهِبٍ فَأَتَاهُ. فَقَالَ: إِنَّهُ قَتَلَ تِسْعَةً وَتِسْعِينَ نَفْسًا فَهَلْ لَهُ مِنْ تَوْبَةٍ؟ فَقَالَ: لاَ، فَقَتَلَهُ فَكَمَّلَ بِهِ مِائَةً ثُمَّ سَأَلَ عَنْ أَعْلَمِ أَهْلِ الأَرْضِ فَدُلَّ عَلَى رَجُلٍ عَالِمٍ

فَقَـالَ: إِنَّهُ قَتَلَ مِائَةَ نَفْسٍ فَهَلْ لَهُ مِنْ تَوْبَـةٍ؟ فَقَالَ: نَعَمْ، وَمَنْ يَحُولُ بَيْنَهُ وَبَيْـنَ التَّوبَةِ؟! انْطَلِقْ إِلَى أَرْضِ كَذَا وَكَـذَا فَـإِنَّ بِهَا أُنَاسًا يَعْبُـدُونَ اللهَ تَعَالَى فَاعْبُدِ اللهَ مَعَهُمْ وَلاَ تَرْجِعْ إِلَى أَرْضِكَ فَإِنَّهَا أَرْضُ سُوءٍ. فَانْطَلَقَ حَتَّى إِذَا نَصَـفَ الطَّـرِيقَ أَتَـاهُ الْمَوتُ فَاخْتَصَـمَتْ فِيـهِ مَلاَئِكَـةُ الرَّحْمَةِ وَمَلاَئِكَـةُ الْعَـذَابِ فَقَالَتْ مَلاَئِكَةُ الرَّحْمَةِ: جَاءَ تَائِبًا مُقْبِلاً بِقَلْبِهِ إِلَى اللهِ تَعَالَى، وَقَالَتْ مَلاَئِكَةُ الْعَذَابِ: إِنَّهُ لَمْ يَعْمَـلْ خَيْرًا قَـطُّ، فَأَتَاهُمْ مَلَكٌ فِي صُـورَةِ آدَمِـيٍّ فَجَعَلُوهُ بَيْنَهُمْ -أَيْ حَكَمًا- فَقَالَ قِيسُوا مَا بَيْنَ الأَرْضَيْنِ فَإِلَى أَيَّتِهِما كَانَ أَدْنَى فَهُوَ لَهُ فَقَاسُوا فَوَجَـدُوهُ أَدْنَى إِلَى الأَرْضِ الَّتِي أَرَادَ فَقَبَضَتْهُ مَلاَئِكَةُ الرَّحْمَةِ)) متفق عليه.

የመቶ ሰዎችን ሕይወት ያጠፋ ሰው ተውበት ቢያደርግ ተቀባይነት ያገኝ እንደሆነ ጠየቀው። "አዎ! (ተቀባይነት ያገኛል)፤ በርሱና በተውበቱ መካከል ግርዶ የሚፈጥረው ማን ነው?! እገሌ ወደ ተባለ ቦታ ሂድ። እዚያ ሥፍራ ላይ አላህን ብቻ የሚያመልኩ ሰዎች አሉ። ከነርሱ ጋር አብረህ አላህን አምልክ። ወደ ነበርክበት ሀገር አትመለስ። የከፉት ሥፍራ ነውና።" አለው -ዓሊሙ። ወደ ተጠቆመው ሀገር ተጓዘ። መንገዱን እንዳጋመሰ ሞት ነጠቀው። የእዝነት (ጀንነት) እና የቅጣት (ዐዛብ) መላኢኮች ተሟገቱ። "ቶብቶና ቀልቡን ወደ አላህ አዙሮ ነው የመጣው።" አሉ የጀንነት መላኢኮች። "በጉ ተግባር ፈጽሞ አያውቅም።" አሉ የዐዛብ መላኢኮች። አንድ መላኢካ በሰው ተመስሎ ወደ ነርሱ መጣ። ብይን ይሰጣቸው ዘንድ ጋበዙት። "ሁለቱ መሬቶች (የመጣበ ትንና የሚሄድበት) ከሞተበት ሥፍራ ያላቸውን ርቀት ለኩ። ለቀረበው ወገን ይሆናል።" አላቸው። ለኩ። መሄድ ወደ ጀመረበት ሥፍራ ቀረብ ብሎ አገኙት። የጀንነት መላኢኮች ወሰዱት።"
(ቡኻሪና ሙስሊም)

وَفِـي رِوَايَةٍ فِي الصَّحِيحِ ((فَكَانَ إِلَى الْقَرْيَةِ الصَّالِحَةِ أَقْرَبَ بِشِبْرٍ فَجُعِلَ مِنْ أَهْلِهَا.))

በሌላ "ሶሒሕ" በሆነ ዘገባ ላይ እንደሰፈረው፦
"መልካም ወደ ሆነችው ሀገር የአንዲት ስንዝር ያክል ቀርቦ ተገኘ። ከነዋሪዎቿ ጉራም ተመደበ።" የሚል ተመልክቷል።

በሌላ "ሶሒሕ" ዘገባ ደግሞ ተከታዩ ተወስቷል፦
"አላህ ለዚህችኛይቱ ሥፍራ እንድ ትቅ፥ ለዚያችኛይቱ ደግሞ እንድት

وَفِـــى رِوَايَةٍ فِى الصَّحِيحِ ((فَأَوْحَى اللهُ تَعَالَى إِلَى هَذِهِ أَنْ تَبَاعَدِى وَإِلَى هَذِهِ أَنْ تَقَـــرَبِى وَقَـــالَ قِيسُـــوا مَابَيْنَهُمَا فَوَجَـــدُوهُ إِلَى هَذِهِ أَقْرَبَ بِشِبْرٍ فَغُفِرَ لَهُ.))

وَفِى رِوَايَةٍ ((فَنَأَى بِصَدْرِهِ نَحْوَهَا.))

ቀርብ አዘዘ። ከዚያም፦ "ሁለቱ መሬቶች (ሰውየው ከሞተበት ሥፍራ) ያላቸውን ርቀት ለኩ።" አለ። ወደዚህችኛዋ በአንድ ስንዝር የቀረበ ሆኖ አገኙት። ምሕረት ተደረገለት።"

በሌላ ዘገባ ደግሞ፦

"(ከመሞቱ በፊት) ወደዚህችኛዋ ቦታ በደረቱ በመሳቡ ቀርበ ተገኘ።" የሚል ተወስቷል።

ከሐዲሱ የምንማራቸው ቁምነገሮች

- የመልዕክተኛው በተጨባጭ ምሳሌዎች የታጀበ ድንቅ የትምህርት አሰጣጥ ስልት ከዚህ ሐዲስ ተስተውሏል። ካለፉ ሕዝቦች ክንውኖች ከኢስላም ጋር የሚጣጣሙትን መዘከር ይፈቀዳል።
- መልካምን መንገድ ለመከተል ዝግጁነት ያላት ልቦና፥ በተወሰነ አጋጣሚ በስሜት በመሸነፍ የስኬትን ፍኖት ብትስትም፥ ወደ ትክክለኛ መሥመር የመመለስ ዕድሏ የሰፋ ነው።
- እውቀት (ዒልም) ከጥቂት ዒባዳ ጋር እንኳ ቢሆን፥ በብዙ ዒባዳዎች ከታጀበ ድንቁርና (ጀህል) ይበልጥ ጠቃሚ ነው። ምክንያቱም ጃሂል መልካም ተግባራትን የፈፀመ እየመሰለው ሊያጠፋና ሌሎችንም ለጥፋት ሊዳርግ ይችላል። ወዋቂዎች (ዓሊሞች) ግን በእውቀት ብርሃን እየተመሩ ትክክለኛውን መሥመር በመያዝ ለራሳቸው ተጠቅመው ሌሎችንም ይጠቅማሉ።
- የተውቡት ደጃፍ ክፍት ነው። ተውብት የሚያደርጉ ሰዎች ወንጀላቸው የቱን ያህል የበዛ ቢሆንም ተቀባይነት የማግኘት ዕድሉ አላቸው።
- አውቆ የሰው ነፍስ ያጠፋ ተውቡቱ ተቀባይነት ሊኖረው ይችላል። ከዚህ ሐዲስ እንደምንረዳው ሰውየው ሰዎችን የገደለው አውቆና በጠላትነት ስሜት ተነሳስቶ ነው። ይህ ግን ተውብቱ ከአላህ ዘንድ ተቀባይነት እንዲያጣ አላደረገውም።
- ወንጀለኞች ከወንጀላቸው እስካልታቀቡ ድረስ ከነርሱ ጋር የሚያኖርን ግንኙነት ማቆምና ማቋረጥ፥ እንዲሁም አላህን ከሚፈሩ ሰዎች ጋር ግንኙነትን ማጠናከር ተገቢ ነው።
- አላህ ባሪያዎቹ ወደርሱ በተውብት ሲመለሱ ከፍተኛ እርካታ ይሰማዋል። እጃቸውን ይዞ ለስኬት ያበቃቸዋል።
- ከደጋጎች ተርታ ለመሰለፍ፥ የነርሱን መልካም እርአያነት ለመከተል ከፍተኛ ጥረትና ትግል ማድረግ፥ በዚህ ሂደት የሚገጥሙ ፈተናዎችንና ችግሮችን መሸከም ለተውቡት ያለን ጉጉት የሚያሳይ ምልክት ነው።
- መላኢኮች የተለያየ ቅርጽ የመያዝ ችሎታ እንዳላቸው ዘገባው ያመለክታል። በሰው ተመስለው ብይን እንዲሰጡ መደረጉም የሰው ልጅ ከአላህ ዘንድ የተሰጠውን የላቀ ደረጃ ይጠቁማል።

٢١- وَعَنْ عَبْدِ اللهِ بْنِ كَعْبِ بْنِ مَالِك وَكَانَ قَائِدَ كَعْبٍ ﷺ مِنْ بَنِيهِ حِينَ عَمِيَ قَالَ سَمِعْتُ كَعْبَ بْنِ مَالِك ﷺ يُحَدِّثُ بِحَدِيثِهِ حِينَ تَخَلَّفَ عَنْ رَسُولِ اللهِ ﷺ فِي غَزْوَةِ تَبُوكَ قَالَ كَعْب لَمْ أَتَخَلَّفْ عَنْ رَسُولِ اللهِ ﷺ فِي غَزْوَةٍ غَزَاهَا قَطُّ إِلاَّ فِي غَزْوَةِ تَبُوكَ غَيْرَ أَنِّي قَدْ تَخَلَّفْتُ فِي غَزْوَةِ بَدْرٍ وَلَمْ يُعَاتَبْ أَحَدٌ تَخَلَّفَ عَنْهُ إِنَّمَا خَرَجَ رَسُولُ اللهِ ﷺ وَالْمُسْلِمُونَ يُرِيدُونَ عِيرَ قُرَيْشٍ حَتَّى جَمَعَ اللهُ تَعَالَى بَيْنَهُمْ وَبَيْنَ عَدُوِّهِمْ عَلَى غَيْرِ مِيعَادٍ. وَلَقَدْ شَهِدْتُ مَعَ رَسُولِ اللهِ ﷺ لَيْلَةَ الْعَقَبَةِ حِينَ تَوَاثَقْنَا عَلَى الإِسْلاَمِ وَمَا أُحِبُّ أَنَّ لِي بِهَا مَشْهَدَ بَدْرٍ وَإِنْ كَانَتْ بَدْرٌ أَذْكَرَ فِي النَّاسِ مِنْهَا. وَكَانَ مِنْ خَبَرِي حِينَ تَخَلَّفْتُ عَنْ رَسُولِ اللهِ ﷺ فِي غَزْوَةِ تَبُوكَ أَنِّي لَمْ أَكُنْ قَطُّ أَقْوَى وَلاَ أَيْسَرَ مِنِّي حِينَ تَخَلَّفْتُ عَنْهُ فِي تِلْكَ الْغَزْوَةِ واللهِ مَاجَمَعْتُ قَبْلَهَا رَاحِلَتَيْنِ قَطُّ حَتَّى جَمَعْتُهُمَا فِي تِلْكَ الْغَزْوَةِ وَلَمْ يَكُنْ رَسُولُ اللهِ ﷺ يُرِيدُ غَزْوَةً إِلاَّ وَرَّى بِغَيْرِهَا حَتَّى كَانَتْ تِلْكَ الْغَزْوَةُ فَغَزَاهَا رَسُولُ اللهِ ﷺ فِي حَرٍّ شَدِيدٍ وَاسْتَقْبَلَ

21- ዐብደላህ ኢብን ከዕብ ኢብን ማሊክ (ረ.ዐ) እንዲህ ሲሉ አስተላልፈዋል፦ ከዕብ ኢብን ማሊክ (ረ.ዐ) የተቡክ ዘመቻ ዕለት ከአላህ መልዕክተኛ (ሶ.ዐ.ወ) ተነጥለው ወደኋላ በቀሩበት ወቅት ስለተፈጠረ ክስተት እንዲህ በማለት ሲተርኩ አድምጫለሁ፦ "የአላህ መልዕክተኛ (ሶ.ዐ.ወ) ከዘመቷቸው ዘመቻዎች ውስጥ ከተቡክ ዘመቻ ውጭ ከአንዱም ተነጥዬ አላውቅም። በእርግጥ ከበድር ዘመቻ አልተሳተፍኩም። ምክንያቱም የአላህ መልዕክተኛ (ሶ.ዐ.ወ) እና ሙስሊሞች በወቅቱ የወጡት የቁረይሾችን ቅፍለት በመሻት ነበር። ግና ያለዕቅድና ጥላናቸው አላህ ከጠላቶቻቸው ጋር አጋፈጣቸው። ለኢስላም ቃል በተገባባንበት "የለይለተል-ዐቀባህ" ዕለት ከአላህ መልዕክተኛ (ሶ.ዐ.ወ) ጋር ነበርኩ። ምንም እንኳ በድር በሰዎች ዘንድ ይበልጥ የሚዘከር ቢሆንም የ"የለይለተል.ዐቀባህ" ዕለት መገኘቴን ግን በበድር ልለውጠውም አልወድም። የተቡክ ዘመቻ ዕለት ከአላህ መልዕክተኛ (ሶ.ዐ.ወ) ተነጥዬ በቀረሁበት ወቅት የሆነው ታሪኬ እንዲህ ነው፦ ያንዬ ከተቡክ ዘመቻ በቀረሁበት ዕለት ከነበርኩበት ይበልጥ በቂ የዘመቻ ዝግጅት ኖሮኝና ምቹ ሁኔታ ተፈጥሮልኝ አያውቅም። በአላህ ይሁንበኝ! ለዚያች ዘመቻ እንጅ ለሌላ ዘመቻ ሁለት ግመሎች ኖረውኝ አያውቁም። የአላህ መልዕክተኛ (ሶ.ዐ.ወ) ዘመቻ በሚያቅዱበት ወቅት የዘመቻውን ጉዳይ በሚስጥር መያዝ ልምዳቸው ነበር። የተቡክ ዘመቻ ዕለት ግን እንዲያ አላደረጉም። ብርቱ የሆነ ሙቀት በነበረበት

ወቅት ነበር የተቡክን ዘመቻ ለማድ ረግ የተነሱት። የሚሄዱበት ሀገር ሩቅና መንገዱም አስቸጋሪ ነበር። መልዕክተ ኛው (ሶ.ዐ.ወ) ለሙስሊሞች እቅዳቸ ውን ግልጽ አደረጉ -ተግቢውን የዘመቻ ዝግጅት ያደርጉ ዘንድ። መዘመት የሚፈልጉበትን አቅጣጫ በይፋ አስታ ወቁ። አኖሌ ሙስሊሞች ለዚህ ጥሪ አምንታዊ ምላሽ ሰጡ። ብዛታቸው መዝገብ የሚችለው አልነበረም። በዚህም የተነሳ ከዘመቻ ለመቅረት የሚያስቡ ሰዎች -ወሕይ እስካላጋለጣ ቸው ድረስ- ተለይተው የሚታወቁበት ሁኔታ እምብዛም አልነበረም። መልዕክተኛው (ሶ.ዐ.ወ) ለዚህ ዘመቻ የተነሱት አዝመራ በደረሰበት፣ ጥላው በሚያስጉመጅበት ወቅት ነበር። ይህ ሁኔታ እኔንም ልዩ መስህብ አሳድሮ ብኛል። የአላህ መልዕክተኛ (ሶ.ዐ.ወ) ዝግጅታቸውን ቀጠሉ። ሙስሊሞችም እንዲሁ። ከነርሱ ጋር ዝግጅት ለማድ ረግ እወጣና ምንም ሳላደርግ እመለሳ ለሁ። መወሰን አልቻልኩም። "በፈለግ ኩበት ቀን ማድረጉ አይሳነኝም።" በማለት አስባለሁ። ይህ ነገር በልቤ ውስጥ ይመላለሳል። ሰዎች ዝግጅታቸ ውን ተያይዘዋል። የአላህ መልዕክተኛ (ሶ.ዐ.ወ) ለዘመቻ በጧት ተንቀሳቀሱ። ሙስሊሞችም አብረዋቸው ተንቀሳቀሱ። አብሬ ስለመዘመቴ ጉዳይ መወሰን አልቻልኩም። በጧት ወጣሁና ተመለ ስኩ። መወሰን አልቻልኩም። ይህ ነገር ልቦናዬ ውስጥ ይመላለሳል። ሰዎች በፍጥነት ገስግሰዋል። ጓዜን ጭኜ፣ ስንቄን ሰንቄ ልከተላቸው አሰብኩ። ምንነው ይህንኑ አድርጌ በነበር። ግን አልቻልኩም። የአላህ መልዕክተኛ

سَفَرًا بَعِيدًا وَمَفَازًا وَاسْتَقْبَلَ عَدَدًا كَثِيرًا فَجَلَّى لِلْمُسْلِمِينَ أَمْرَهُمْ لِيَتَأَهَّبُوا أُهْبَةَ غَزْوِهِمْ فَأَخْبَرَهُمْ بِوَجْهِهِمْ الَّذِي يُرِيدُ وَالْمُسْلِمُونَ مَعَ رَسُولِ اللهِ ﷺ كَثِيرٌ وَلَا يَجْمَعُهُمْ كِتَابُ حَافِظٌ ((يُرِيدُ بِذَلِكَ الدِّيوَانَ)) قَالَ كَعْبٌ فَقَلَّ رَجُلٌ يُرِيدُ أَنْ يَتَغَيَّبَ إِلاَّ ظَنَّ أَنَّ ذَلِكَ سَيَخْفَى بِهِ مَالَمْ يَنْزِلْ فِيهِ وَحْيٌ مِنَ اللهِ وَغَزَى رَسُولُ اللهِ ﷺ تِلْكَ الْغَزْوَةَ حِينَ طَابَتِ الثِّمَارُ وَالظِّلَالُ فَأَنَا إِلَيْهَا أَصْعَرُ فَجَهَّزَ رَسُولُ اللهِ ﷺ وَالْمُسْلِمُونَ مَعَهُ وَطَفِقْتُ أَغْدُو لِكَيْ أَتَجَهَّزَ مَعَهُ فَأَرْجِعُ وَلَمْ أَقْضِ شَيْئًا وَأَقُولُ فِي نَفْسِي أَنَا قَادِرٌ عَلَى ذَلِكَ إِذَا أَرَدْتُ فَلَمْ يَزَلْ يَتَمَادَى بِي حَتَّى اسْتَمَرَّ بِالنَّاسِ الْجِدُّ فَأَصْبَحَ رَسُولُ اللهِ ﷺ غَادِيًا وَالْمُسْلِمُونَ مَعَهُ وَلَمْ أَقْضِ مِنْ جِهَازِي شَيْئًا ثُمَّ غَدَوْتُ فَرَجَعْتُ وَلَمْ أَقْضِ شَيْئًا فَلَمْ يَزَلْ يَتَمَادَى بِي حَتَّى أَسْرَعُوا وَتَفَارَطَ الْغَزْوُ فَهَمَمْتُ أَنْ أَرْتَحِلَ فَأُدْرِكَهُمْ فَيَالَيْتَنِي فَعَلْتُ، ثُمَّ لَمْ يُقَدَّرْ ذَلِكَ لِي، فَطَفِقْتُ إِذَا خَرَجْتُ فِي النَّاسِ بَعْدَ خُرُوجِ رَسُولِ اللهِ ﷺ يَحْزُنُنِي أَنِّي لَا أَرَى لِي أُسْوَةً إِلاَّ رَجُلاً مَغْمُوصًا عَلَيْهِ

فِي النِّفَاقِ أَوْ رَجُلاً مِمَّنْ عَذَرَ اللهُ تَعَالَى مِنَ الضُّعَفَاءِ وَلَمْ يَذْكُرْنِي رَسُولُ اللهِ ﷺ حَتَّى بَلَغَ تَبُوكَ، فَقَالَ وَهُوَ جَالِسٌ فِي الْقَوْمِ بِتَبُوكَ: ((مَا فَعَلَ كَعْبُ بْنِ مَالِكٍ؟)) فَقَالَ رَجُلٌ مِنْ بَنِي سَلِمَةَ: يَارَسُولَ اللهِ حَبَسَهُ بُرْدَاهُ وَالنَّظَرُ فِي عِطْفَيْهِ، فَقَالَ لَهُ مُعَاذُ بْنُ جَبَلٍ ﷺ: بِئْسَ مَاقُلْتَ! واللهِ يَا رَسُولَ اللهِ مَا عَلِمْنَا عَلَيْهِ إِلاَّ خَيْرًا فَسَكَتَ رَسُولُ اللهِ ﷺ. فَبَيْنَا هُوَ عَلَى ذَلِكَ رَأَى رَجُلاً مُبَيِّضًا يَزُولُ بِهِ السَّرَابُ فَقَالَ رَسُولُ اللهِ ﷺ: ((كُنْ أَبَا خَيْثَمَةَ)) فَإِذَا هُوَ أَبُو خَيْثَمَةَ الأَنْصَارِيُّ وَهُوَ الَّذِي تَصَدَّقَ بِصَاعِ التَّمْرِ حِينَ لَمَزَهُ الْمُنَافِقُونَ. قَالَ كَعْبٌ: فَلَمَّا بَلَغَنِي أَنَّ رَسُولَ اللهِ ﷺ قَدْ تَوَجَّهَ قَافِلاً مِنْ تَبُوكَ حَضَرَنِي بَثِّي فَطَفِقْتُ أَتَذَكَّرُ الْكَذِبَ وَأَقُولُ بِمَ أَخْرُجُ مِنْ سَخَطِهِ غَدًا؟ وَأَسْتَعِينُ عَلَى ذَلِكَ بِكُلِّ ذِي رَأْيٍ مِنْ أَهْلِي فَلَمَّا قِيلَ: إِنَّ رَسُولَ اللهِ ﷺ قَدْ أَظَلَّ قَادِمًا زَاحَ عَنِّي الْبَاطِلُ حَتَّى عَرَفْتُ أَنِّي لَمْ أَنْجُ مِنْهُ بِشَيْءٍ أَبَدًا، فَأَجْمَعْتُ صِدْقَهُ، وَأَصْبَحَ رَسُولُ اللهِ ﷺ قَادِمًا، وَكَانَ إِذَا قَدِمَ مِنْ سَفَرٍ بَدَأَ بِالْمَسْجِدِ

(ሶ.ዐ.ወ) ከወጡ በኋላ አደባባይ ስወጣ የተመለከትኩት ሁኔታ በጣም አሳዘነኝ። አቻዬን አላገኘሁም። በሙናፊቅነት የሚታዩ ወይም አላህ "ዑዝር" ከሰጣቸው ደካሞች የሆኑ ሰዎችን ብቻ ነበር የምመለከተው። የአላህ መልዕክተኛ (ሶ.ዐ.ወ) ተቡክ እስኪደርሱ ድረስ አላወሱኝም። ተቡክ እንደደረሱ ከሰዎች መካከል ተቀምጠው፡- "ከዕብ ኢብን ማሊክን ምን አገኘው?" በማለት ጠየቁ። የበኒ ሰለመህ ጉሳ አባል የሆነ አንድ ሰው፡- "የአላህ መልዕክተኛ ሆይ! ኩራት ነው ወደኋላ ያስቀረው።" ሲል ተናገረ። ሙዓዝ ኢብን ጀበል እንዲህ አለው -ለሰውየው "ምን ያህል ፀያፍ ቃል ነው የተናገርከው?! የአላህ መልዕክተኛ ሆይ! እስካሁን በርሱ (በከዕብ) ላይ ሰናይን እንጅ መጥፎ ነገር አናውቅበትም።" መልዕክተኛው (ሶ.ዐ.ወ) ዝም አሉ። በዚህ ሁኔታ ላይ እያሉ አንድ ነጭ ልብስ የለበሰ ሰው ከሩቅ ተመለከቱ። "አባ ኹሰይመህ በሆነ" ሲሉ ተመኙ። አንዲት ቁና (ሷዕ) ተምር ምጽዋት በመስጠቱ ሙናፊቆች ትችት ያደረሱበት አባ ኹሰይመተል አንሷሪይ ነበር።

የአላህ መልዕክተኛ (ሶ.ዐ.ወ) ከተቡክ ዘመቻ በመመለስ ላይ መሆናቸውን ስሰማ ከፍተኛ ሃዘንና ቁጭት ተሰማኝ። "ነገ ከቁጣቸው በምንድን ነው ልድን የምችለው?" የሚል ሞገ ቀት ያዘኝ። ለመዋሸት አሰብኩ። ቤተሰ ቦቼን በዚህ ጉዳይ ላይ አማከርኩ። መልዕክተኛው (ሶ.ዐ.ወ) መዲና መድ ረሳቸውን ስሰማ ከንቱ ሐሳቦቼ ሁሉ

فَرَكَعَ فِيهِ رَكْعَتَيْنِ ثُمَّ جَلَسَ لِلنَّاسِ، فَلَمَّا فَعَلَ ذَلِكَ جَاءَهُ الْمُخَلَّفُونَ يَعْتَذِرُونَ إِلَيْهِ وَيَحْلِفُونَ لَهُ، وَكَانُوا بِضْعًا وَثَمَانِينَ رَجُلاً، فَقَبِلَ مِنْهُمْ عَلاَنِيَتَهُمْ، وَبَايَعَهُمْ وَاسْتَغْفَرَ لَهُمْ وَوَكَلَ سَرَائِرَهُمْ إِلَى اللهِ تَعَالَى حَتَّى جِئْتُ. فَلَمَّا سَلَّمْتُ تَبَسَّمَ تَبَسُّمَ الْمُغْضَبِ ثُمَّ قَالَ: ((تَعَالَى)) فَجِئْتُ أَمْشِي حَتَّى جَلَسْتُ بَيْنَ يَدَيْهِ فَقَالَ لِي: ((مَا خَلَّفَكَ؟ أَلَمْ تَكُنْ قَدِ ابْتَعْتَ ظَهْرَكَ)) قَالَ: قُلْتُ: يَا رَسُولَ اللهِ، إِنِّي وَاللهِ لَوْ جَلَسْتُ عِنْدَ غَيْرِكَ مِنْ أَهْلِ الدُّنْيَا لَرَأَيْتُ أَنِّي سَأَخْرُجُ مِنْ سَخَطِهِ بِعُذْرٍ، لَقَدْ أُعْطِيتُ جَدَلاً وَلَكِنِّي وَاللهِ لَقَدْ عَلِمْتُ لَئِنْ حَدَّثْتُكَ الْيَوْمَ حَدِيثَ كَذِبٍ تَرْضَى بِهِ عَنِّي لَيُوشِكَنَّ اللهُ يُسْخِطُكَ عَلَيَّ، وَإِنْ حَدَّثْتُكَ حَدِيثَ صِدْقٍ تَجِدُ عَلَيَّ فِيهِ إِنِّي لأَرْجُو فِيهِ عُقْبَى اللهِ عَزَّ وَجَلَّ. وَاللهِ مَا كَانَ لِي مِنْ عُذْرٍ، وَاللهِ مَا كُنْتُ قَطُّ أَقْوَى وَلاَ أَيْسَرَ مِنِّي حِينَ تَخَلَّفْتُ عَنْكَ. قال: فَقَالَ رَسُولُ اللهِ ﷺ: ((أَمَّا هَذَا فَقَدْ صَدَقَ، فَقُمْ حَتَّى يَقْضِيَ اللهُ فِيكَ)). وَسَارَ رِجَالٌ مِنْ بَنِي سَلِمَةَ فَاتَّبَعُونِي فَقَالُوا لِي:

ተወገዱልኝ። ምንም ነገር ከቁጣቸው ሊያድነኝ እንደማይችል ተረዳሁ። እውነቱን ልነገራችሁ ቆረጥኩ። መልዕክተኛው (ሶ.ዐ.ወ) መዲና ገብተው እደሩ። ከጉዞ ሲመለሱ መጀመሪያ መስጊድ በመግባት ሁለት ረከዓዎችን ከሰገዱ በኋላ ፊታቸውን ወደ ሰዎች አቅጣጫ በመመለስ መቀመጥ ልምዳቸው ነበር። ይህንኑ እንዳደረጉ ከዘመቻው ተነጥለው የቀሩ ሰዎች ከርሳቸው ዘንድ ቀረቡ። የቀሩበትን ምክንያት ተናገሩ። መሐላም ፈፀሙ። ቁጥራቸው ከሰማንያ ሦስት እስከ ዘጠና ይደርሳል። መልዕክተኛው (ሶ.ዐ.ወ) ምክንያታቸውን ተቀበሉ። ቃልኪዳን (በይዐ) ተጋቧቸው። አላህን ምሕረት ለመኑላቸው። የውስጣቸውን ለአላህ በመተው።እኔ ከፊታቸው ስቀርብ ፈገግ አሉ -የቁጣ ፈገግታ። "ና" አሉኝ። ከፊት ለፊታቸው ተቀመጥኩ። "ምንድን ነው ተነጥለህ ወደኋላ እንድትቀር ያደረገህ? መጓጓዣ ገዝተህም አልነበረም?" በማለት ጠየቁኝ። "የአላህ መልዕክተኛ ሆይ! በአላህ ይሁንብኝ፥ ከርስዎ ሌላ ያሉ የዱንያ ሰዎች ፊት ብሆን ኖሮ የተቀመጥኩት ምክንያቶችን በመደርደር ከቁጣቸው መዳን እንደምችል ይታየኝ ነበር። አላማኝ የእንጋገር ስልትን ተክኛለሁ። ነገር ግን -በአላህ ይሁንብኝ- ዛሬ እርስዎን ሊያረካ የሚችል ሐሰት ነገር ብነግርዎት አላህ በኔ ላይ እንዲቆጡ ሊያደርግም ይችላል። እውነቱን ብነግርዎ ደግሞ በኔ ላይ ይቆጡ ይሆናል። ግና ልዑልና የበላይ የሆነው አላህ መጪሪሻውን ያማረ ያደርግልኝ ዘንድ ተስፋ ይናረኖል። በአላህ ይሁንብኝ! ምንም ምክንያት አልነበረኝም። ከርስዎ

واللهِ مَا عَلِمْنَاكَ أَذْنَبْتَ ذَنْبًا قَبْلَ هَذَا. لَقَدْ عَجَزْتَ فِي أَنْ لاَ تَكُونَ اعْتَذَرْتَ إِلَى رَسُولِ اللهِ ﷺ بِمَا اعْتَذَرَ إِلَيهِ الْمُخَلَّفُونَ، فَقَدْ كَانَ كَافِيَكَ ذَنْبَكَ اسْتِغْفَارُ رَسُولُ اللهِ ﷺ لَكَ. قال: فَوَ اللهِ مَازَالُوا يُؤَنِّبُونَنِي حَتَّى أَرَدْتُ أَنْ أَرْجِعَ إِلَى رَسُولِ اللهِ ﷺ فَأُكَذِّبَ نَفْسِي، ثُمَّ قُلْتُ لَهُمْ: هَلْ لَقِيَ هَذَا مَعِيَ مِنْ أَحَدٍ؟ قَالُوا: نَعَمْ، لَقِيَهُ مَعَكَ رَجُلاَنِ قَالاَ مِثْلَ مَاقُلْتَ، وَقِيلَ لَهُمَا مِثْلَ مَا قِيلَ لَكَ. قال: قُلْتُ: مَنْ هُمَا؟ قَالُوا: مُرَارَةُ بْنُ الرَّبِيعِ الْعَمْرِيُّ وَهِلاَلُ بْنُ أُمَيَّةَ الْوَاقِفِيُّ، قال: فَذَكَرُوا لِي رَجُلَيْنِ صَالِحَيْنِ قَدْ شَهِدَا بَدْرًا فِيهِمَا أُسْوَةٌ. قال فَمَضَيْتُ حِينَ ذَكَرُوهُمَا لِي. ونَهَى رَسُولُ اللهِ ﷺ عَنْ كَلاَمِنَا أَيُّهَا الثَّلاَثَةُ مِنْ بَيْنِ مَنْ تَخَلَّفَ عَنْهُ. قال: فَاجْتَنَبَنَا النَّاسُ - أَوْ قَالَ تَغَيَّرُوا لَنَا - حَتَّى تَنَكَّرَتْ لِي فِي نَفْسِي الأَرْضُ، فَمَا هِيَ بِالأَرْضِ الَّتِي أَعْرِفُ، فَلَبِثْنَا عَلَى ذَلِكَ خَمْسِينَ لَيْلَةً. فَأَمَّا صَاحِبَايَ فَاسْتَكَانَا وَقَعَدَا فِي بُيُوتِهِمَا يَبْكِيَانِ. وَأَمَّا أَنَا فَكُنْتُ أَشَبَّ الْقَوْمِ وَأَجْلَدَهُمْ، فَكُنْتُ أَخْرُجُ فَأَشْهَدُ

ተነጥዬ በቀረሁበት ዕለት እንደነበረው ዓይነት ምቹ ሁኔታ ከአሁን በፊት ገጥሞኝ አያውቁም።" "ይህ ሰው እውነቱን ነው የተናገረው። ቁም -አላህ ብይኑን እስኪሰጥ ድረስ።" አሉ። የበኒ ሰለማ ጉሳ አባል የሆኑ አያሌ ሰዎች ተከተሉኝ። እንዲህም አሉኝ- "ከዚህ በፊት ጥፋት ስትፈጽም አናውቅህም። ሌሎች እንዳንተ ወደኋላ የቀሩ ሰዎች እንደሰጡት ዓይነት ምክንያት ከአላህ መልዕክተኛ (ሶ.ዐ.ወ) ዘንድ ማቅረብ ትችል ነበር። በፈፀምከው ጥፋት የአላህ መልዕክተኛ (ሶ.ዐ.ወ) አላህን ምሕረት ቢለምኑልህ በቂህ ነበር።" ወደ አላህ መልዕክተኛ (ሶ.ዐ.ወ) ተመልሼ የውሸት ምክንያት በማቅረብ ያልኩትን ለመ ካድ እስካሰብ ድረስ ይተቹኝና ይወቅሱኝ ገቡ ። "እንደኔው እንዲህ ዓይነት ሁኔታ የገጠመው ይኖር ይሆን?" በማለት ጠየቅኳቸው። "ሁለት ሰዎች ያንተው ሁኔታ ገጥሟቸዋል።" አሉ። "እነርሱ እነማን ናቸው?" በማለት ጠየቅኳቸው። "ሙራረት ኢብን አር-ረቢዐ አል-ዐምሪይ እና ሂላል ኢብን ኡመየህ አል-ዋቂፊይ (ረ.ዐ) ናቸው።" አሉኝ። ሁለት ደጋግ ሰዎችን አወሱልኝ። በድር ዘመቻ ላይ የተገኙ አቻዎቼ ናቸው። በአቋሜ ፀናሁ። ከዘመቻው ተነጥለን ከቀረነው ሰዎች መካከል እኛን ሦስታችንን ሰዎች እንዳያናግሩን የአላህ መልዕክተኛ (ሶ.ዐ.ወ) ከለከሉ። ሰዎች እኛን ከማናገር ተቆጠቡ። ፍፁም ተቀየሩብን። ይህች ምድር የማውቃት ምድር አልመስልህ እስክትለኝ ድረስ። ቢዚህ ሁኔታ ለሀምሳ ቀናት ያክል ቆየን። ሁለቱ ባልደረቦቼ ከፍተኛ

الصَّـــلاَةَ مَـــعَ الْمُسْلِمِينَ وَأَطُوفُ فِي الأَسْوَاقِ، وَلاَ يُكَلِّمُنِي أَحَدٌ وَآتِي رَسُولَ اللهِ ﷺ فَأُسَلِّمُ عَلَيْهِ وَهُوَ فِي مَجْلِسِهِ بَعْدَ الصَّـــلاَةِ، فَـــأَقُولُ فِي نَفْسِي: هَلْ حَرَّكَ شَفَتَيْهِ بِرَدِّ السَّلاَمِ أَمْ لاَ؟ ثُمَّ أُصَلِّي قَرِيبًا مِـــنْهُ وَأُسَـــارِقُهُ النَّظَرَ، فَإِذَا أَقْبَلْتُ عَلَى صَلاَتِي نَظَرَ إِلَيَّ وَإِذَا التَفَتُّ نَحْوَهُ أَعْرَضَ عَنِّي، حَتَّى إِذَا طَالَ ذَلِكَ عَلَيَّ مِنْ جَفْوَةِ الْمُسْلِمِينَ مَشَيْتُ حَتَّى تَسَوَّرْتُ حِـــدَارَ حَائِطِ أَبِي قَتَادَةَ -وَهُوَ ابْنُ عَمِّي وَأَحَبُّ النَّاسِ إِلَيَّ- فَسَلَّمْتُ عَلَيْهِ، فَوَ اللهِ مَا رَدَّ عَـــلَيَّ السَّـــلاَمَ، فَقُلْتُ لَهُ: يَا أَبَا قَتَادَةَ أَنْشُـــدُكَ بِـــاللهِ هَـــلْ تَعْلَمُنِي أُحِبُّ اللهَ وَرَسُولَهُ ﷺ؟ فَسَكَتَ، فَعُدْتُ فَنَاشَدْتُهُ، فَسَـــكَتَ فَعُـــدْتُ فَنَاشَدْتُهُ. فَقَالَ: اللهُ وَرَسُـــولُهُ أَعْلَمُ. فَفَاضَتْ عَيْنَايَ وَتَوَلَّيْتُ حَتَّى تَسَوَّرْتُ الْجِدَارَ، فَبَيْنَا أَنَا أَمْشِي فِي سُـــوقِ الْمَدِيـــنَةِ إِذَا نَبَطِيٌّ مِنْ نَبَطِ أَهْلِ الشَّـــامِ مِمَّنْ قَدِمَ بِالطَّعَامِ يَبِيعُهُ بِالْمَدِينَةِ يَقُـــولُ: مَنْ يَدُلُّ عَلَى كَعْبِ بْنِ مَالِكٍ؟ فَطَفِقَ النَّاسُ يُشِيرُونَ لَهُ إِلَيَّ حَتَّى جَاءَنِي فَدَفَعَ إِلَيَّ كِتَابًا مِنْ مَلِكِ غَسَّانَ، وَكُنْتُ

ውርደትና ስቄት ተሰማቸው።ከቤታቸው ተቀምጠው ያለቅሱ ነበር። እኔ ግን ወጣ ትና ጠንካራ ስለነበርኩ ከቤቴ እወጣ ነበር። ከሙስሊሞች ጋር የጀመዐ ሶላት እሰግዳለሁ። የገበያ ቦታዎችን እየተዘዋ ወርኩ እጉበኛለሁ። አንድም የሚያናግ ረኝ አልነበረም። ከነቢዩ (ሶ.ዐ.ወ) ዘንድ በመቅረብ ሶላታቸውን አጠናቀው እንደተቀመጡ- ሰላምታ አቀርብላቸዋ ለሁ። ሰላምታ በመመለስ ከንፈራቸውን አንቀሳቅሰዋል ወይስ አልመለሱልኝም እያልኩ እጨነቃለሁ። ከዚያም ወደርሳ ቸው ቀረብ ብዬ እሰግዳለሁ። ሰረቅ እያደረግኩም እመለከታቸዋለሁ። ትኩ ረቴን ወደ ሶላት ሳደርግ ይመለከቱ ኛል። ወደርሳቸው ስዞር ፊታቸውን ከኔ ያዞራሉ። ሙስሊሞች እኔን ማግለላቸው እጅግ ሲረዝምብኝ ጊዜ የአቡ ቀታዳህን አጥር ዘልዬ ገባሁ። የአጐቴ ልጅ ነው። በእጅጉ እወደዋለሁ። ሰላምታ አቀረብኩለት። በአላህ ይሁንብኝ! አልመ ለሰልኝም። "አባ ቀታዳህ ሆይ! በአላህ እማፀንሃለሁ፤ አላህንና መልዕክተኛውን (ሶ.ዐ.ወ) እንደማፈቅር እታውቅምን?" አልኩት። ዝም አለ። እንደገና ተማፀን ኩት። መልስ አልሰጠኝም። አጥብቄ ተማፀንኩት። "አላህና መልዕክተኛው ያውቃሉ።" አለኝ። በአጥር ዘልዬ ተመለ ስኩ። በመዲና የገበያ ቦታዎች በመዘዋ ወር ላይ እያለሁ ከሻም ገበሬዎች አንዱን አገኘሁት። ምግብ ለመሸጥ ነው ወደ መዲና የመጣው። "ከዕብ ኢብን ማሊክን የሚያመላክተኝ ማን ነው?" እያለ ይጠይቃል። ሰዎች ወደኔ አመላክ ቱት። አንድ ደብዳቤ ሰጠኝ። ከመሊክ ገሳን የተላከ። ፀሐፊ ነበርኩ። አንብብ ኩት። ተከታዩ መልዕክት ሰፍሮበታል፡-

"ባልደረባህ እንዳገለለህ ደርሰናል፤ አላህ ከጥፋትና ከውርደት አገር እንድትኖር አልደነገገብህም። ከኛ ጋር ተቀላቀል። እንረዳሃለን።" "ይህም ሌላ ፈተና ነው።" አልኩ ደብዳቤውን አንብቤ ሳጠናቅቅ። አቃጠልኩት። በዚህ ሁኔታ አርባ ቀናት አለፉ። "ወሕይ" ዘገየ። "የአላህ መልዕክተኛ (ሶ.ዐ.ወ) ሚስትህን እንድታገል አዘውሃል።" የሚል መልዕክት አመጣ የመልዕክተኛው መልዕክተኛ። "ልፍታት ወይስ ምንድን ነው የማደርገው?" በማለት ጠየቅኩት። "አትፈታም። ግና አትቅረባት (ወሲባዊ ተራክቦ አትፈጽም)።" አለኝ። ለባልደረቦቼም ተመሳሳይ መልዕክት ደረሳቸው። "አላህ በዚህ ጉዳይ ላይ ብይኑን እስኪሰጥ ድረስ ወደ ቤተሰቦችሽ ሂጂ።" አልኳት ባለቤቴን። የሂላል ኢብን ኡመየህ ባልተቤት ከአላህ መልዕክተኛ (ሶ.ዐ.ወ) ዘንድ በመቅረብ እንዲህ አለች፦ "የአላህ መልዕክተኛ ሆይ! ሂላል ኢብን ኡመየህ ደካማ ሽማግሌ ነው። ረዳት አገልጋይ የለውም። እንዳገለግለው አይፈቀድልኝ ይሆን?" "እፈቅድልሻለሁ። ወሲባዊ ተራክቦ ግን እንዳይፈጽም።" አሏት። "እርሱ በአሁኑ ወቅት አንድም ነገር በሚከጅልበት ሁኔታ ላይ አይደለም። ይህ ነገር ከተከሠተበት ዕለት አንስቶ እስከ አሁን ድረስ በማልቀስ ላይ ነው።" አለቻቸው። ከቤተሰቦቼ አንዳንዶቹ "ሚስትህ (ታገለግልህ ዘንድ) የአላህን መልዕክተኛ (ሶ.ዐ.ወ) ጠይቅ። ለሂላል ኢብን ኡመየህ ሚስት ፈቅደውላታል።" አሉኝ። "የአላህን መልዕክተኛ (ሶ.ዐ.ወ)

كَاتِبًا. فَقَرَأْتُهُ فَإِذَا فِيهِ: أَمَّا بَعْدُ فَإِنَّهُ قَدْ بَلَغَنَا أَنَّ صَاحِبَكَ قَدْ جَفَاكَ، وَلَمْ يَجْعَلْكَ اللهُ بِدَارِ هَوَانٍ وَلاَ مَضْيَعَةٍ، فَالْحَقْ بِنَا نُوَاسِكَ فَقُلْتُ حِينَ قَرَأْتُهَا: وَهَذِهِ أَيْضًا مِنَ الْبَلاَءِ! فَتَيَمَّمْتُ بِهَا التَّنُّورَ فَسَجَرْتُهَا، حَتَّى إِذَا مَضَتْ أَرْبَعُونَ مِنَ الْخَمْسِينَ وَاسْتَلْبَثَ الْوَحْيُ إِذَا رَسُولُ رسولِ اللهِ ﷺ يَأْتِينِي فَقَالَ: إِنَّ رَسُولَ اللهِ ﷺ يَأْمُرُكَ أَنْ تَعْتَزِلَ امْرَأَتَكَ، فَقُلْتُ: أُطَلِّقُهَا أَمْ مَاذَا أَفْعَلُ؟ فقال: لاَ بَلْ اعْتَزِلْهَا فَلاَ تَقْرَبَنَّهَا. وَأَرْسَلَ إِلَى صَاحِبَيَّ بِمِثْلِ ذَلِكَ. فَقُلْتُ لاِمْرَأَتِي الْحَقِي بِأَهْلِكِ فَكُونِي عِنْدَهُمْ حَتَّى يَقْضِيَ اللهُ فِي هَذَا الأَمْرِ. فَجَاءَتِ امْرَأَةُ هِلاَلِ ابْنِ أُمَيَّةَ رَسُولَ اللهِ ﷺ فَقَالَتْ لَهُ: يَارَسُولَ اللهِ إِنَّ هِلاَلَ بْنِ أُمَيَّةَ شَيْخٌ ضَائِعٌ لَيْسَ لَهُ خَادِمٌ فَهَلْ تَكْرَهُ أَنْ أَخْدُمَهُ؟ قَالَ: لاَ، وَلَكِنْ لاَ يَقْرَبَنَّكِ. فَقَالَتْ إِنَّهُ وَاللهِ مَابِهِ مِنْ حَرَكَةٍ إِلَى شَيْءٍ، وَوَاللهِ مَازَالَ يَبْكِي مُنْذُ كَانَ مِنْ أَمْرِهِ مَاكَانَ إِلَى يَوْمِهِ هَذَا. فَقَالَ لِي بَعْضُ أَهْلِي: لَوِاسْتَأْذَنْتَ رَسُولَ اللهِ ﷺ فِي امْرَأَتِكَ فَقَدْ أَذِنَ لاِمْرَأَةِ هِلاَلِ بْنِ أُمَيَّةَ أَنْ تَخْدُمَهُ. فَقُلْتُ: لاَ أَسْتَأْذِنُ فِيهَا رَسُولَ

እንዲህ ዓይነቱን ጉዳይ አልጠይቃ ቸውም። ምን እንደሚሉኝ አላውቅም ፈቃድ ስጠይቃቸው። ወጣት ነኝ።" አልኳቸው። በዚህ ሁኔታ አሥር ቀናትን አሳለፍኩ። ሰዎች እንዲያነጋ ግሩን እቀባ ከተጣለብን ሐምሳ ቀናት ሙሉን ማለት ነው። በሐምሳኛው ቀን ጧት የፈጅርን ሶላት ከቤቶቻችን በአንድ ጣሪያ ላይ ሰገድኩ። አላህ በዘከረን ሁኔታ በጭንቀት ተውጬ እንደተቀመጥኩ የጩኸት ድምጽ ሰማሁ። "ሰልዕ" ጋራ ላይ። "ከዕብ ኢብን ማሊክ ሆይ! እንኳን ደስ ያለህ።" ይላል ብከፍተኛ ድምጽ። ሱጁድ ወረድኩ በደስታ። ከአላህ ዘንድ ብስራት መምጣቱን ተገነዘብኩ። የፈጅር ሶላት ተሰግዶ እንደተጠናቀቀ ነበር አላህ ፀፀታችንን መቀበሉን የአላህ መልዕክተኛ (ሶ.ዐ.ወ) ለሰዎች ያበሰሩት። ሰዎች እንኳን ደስ ያለህ ለማለት ይጉርፉ ጀመር። ወደ ሁለቱ ባልደረቦቼም እንዲሁ። አንድ ጋላቢ ወደኔ እየጋለበ መጣ። የአስለም ጉሳ አባል የሆነ አንድ ሰው በሩጫ ወደኔ አቅጣጫ ይሮጣል። ከተራራው ላይ ወጣ። ድምፁ ከፈረሱ ቀድሞ ደረሰ። ያ ድምፁን የሰማሁት ሰው "እንኳን ደስ ያለህ።" ሊለኝ ሲመጣ ልብሶቼን አወለቅኩና አለበስኩት። በጊዜው ከነሱ ውጭ ሌላ ልብስ አልነበረኝም። ሁለት ልብሶችን ተውሼ ለበስኩ። የአላህን መልዕክተኛ (ሶ.ዐ.ወ) በመከጀል ወጣሁ። ሰዎች በቡድን በቡድን ሆነው ይቀበሉኛል። ብስራት ያቀርቡልኛል። "አላህ ተውበትህን በመቀበሉ እንኳን ደስ ያለህ" ይሉኛል። መስጊድ ደረስኩ። የአላህ መልዕክተኛ (ሶ.ዐ.ወ)

اللهِ ﷺ وَمَا يُدْرِينِي مَاذَا يَقُولُ رَسُولُ اللهِ ﷺ إِذَا اسْتَأْذَنْتُهُ وَأَنَا رَجُلٌ شَابٌّ! فَلَبِثْتُ بِذَلِكَ عَشْرَ لَيَالٍ، فَكَمُلَ لَنَا خَمْسُونَ لَيْلَةً مِنْ حِينَ نُهِيَ عَنْ كَلَامِنَا، ثُمَّ صَلَّيْتُ صَلَاةَ الْفَجْرِ صَبَاحَ خَمْسِينَ لَيْلَةً عَلَى ظَهْرِ بَيْتٍ مِنْ بُيُوتِنَا، فَبَيْنَا أَنَا جَالِسٌ عَلَى الْحَالِ الَّتِي ذَكَرَ اللهُ تَعَالَى مِنَّا قَدْ ضَاقَتْ عَلَيَّ نَفْسِي وَضَاقَتْ عَلَيَّ الْأَرْضُ بِمَا رَحُبَتْ، سَمِعْتُ صَوْتَ صَارِخٍ أَوْفَى عَلَى سَلْعٍ يَقُولُ بِأَعْلَى صَوْتِهِ: يَا كَعْبُ ابْنَ مَالِكٍ أَبْشِرْ، فَخَرَرْتُ سَاجِدًا وَعَرَفْتُ أَنَّهُ قَدْ جَاءَ فَرَجٌ. فَأَذَنَ رَسُولُ اللهِ ﷺ النَّاسَ بِتَوْبَةِ اللهِ عَزَّ وَجَلَّ عَلَيْنَا حِينَ صَلَّى صَلَاةَ الْفَجْرِ، فَذَهَبَ النَّاسُ يُبَشِّرُونَنَا. فَذَهَبَ قِبَلَ صَاحِبَيَّ مُبَشِّرُونَ وَرَكَضَ رَجُلٌ إِلَيَّ فَرَسًا وَسَعَى سَاعٍ مِنْ أَسْلَمَ قِبَلِي وَأَوْفَى عَلَى الْجَبَلِ . وَكَانَ الصَّوْتُ أَسْرَعَ مِنَ الْفَرَسِ، فَلَمَّا جَاءَنِي الَّذِي سَمِعْتُ صَوْتَهُ يُبَشِّرُنِي نَزَعْتُ لَهُ ثَوْبَيَّ فَكَسَوْتُهُمَا إِيَّاهُ بِبِشَارَتِهِ، وَاللهِ مَا أَمْلِكُ غَيْرَهُمَا يَوْمَئِذٍ، وَاسْتَعَرْتُ ثَوْبَيْنِ فَلَبِسْتُهُمَا وَانْطَلَقْتُ أَتَأَمَّمُ رَسُولَ اللهِ ﷺ

يَتَلَقَّانِي النَّاسُ فَوْجًا فَوْجًا يُهَنِّئُونَنِي بِالتَّوْبَةِ وَيَقُولُونَ لِي: لِتَهْنِكَ تَوْبَةُ اللهِ عَلَيْكَ؛ حَتَّى دَخَلْتُ الْمَسْجِدَ فَإِذَا رَسُولُ اللهِ ﷺ جَالِسٌ حَوْلَهُ النَّاسُ، فَقَامَ طَلْحَةُ ابْنُ عُبَيْدِ اللهِ ﷺ يُهَرْوِلُ حَتَّى صَافَحَنِي وَهَنَّأَنِي، وَاللهِ مَاقَامَ رَجُلٌ مِنَ الْمُهَاجِرِينَ غَيْرُهُ، فَكَانَ كَعْبٌ لَايَنْسَاهَا لِطَلْحَةَ. قَالَ كَعْبٌ: فَلَمَّا سَلَّمْتُ عَلَى رَسُولِ اللهِ ﷺ قَالَ وَهُوَ يَبْرُقُ وَجْهُهُ مِنَ السُّرُورِ: ((أَبْشِرْ بِخَيْرِ يَوْمٍ مَرَّ عَلَيْكَ مُذْ وَلَدَتْكَ أُمُّكَ)). فَقُلْتُ: أَمِنْ عِنْدِكَ يَارَسُولَ اللهِ أَمْ مِنْ عِنْدِ اللهِ؟ قَالَ: ((لَا، بَلْ مِنْ عِنْدِ اللهِ عَزَّ وَجَلَّ))، وَكَانَ رَسُولُ اللهِ ﷺ إِذَا سُرَّ اسْتَنَارَ وَجْهُهُ حَتَّى كَأَنَّ وَجْهَهُ قِطْعَةُ قَمَرٍ، وَكُنَّا نَعْرِفُ ذَلِكَ مِنْهُ، فَلَمَّا جَلَسْتُ بَيْنَ يَدَيْهِ قُلْتُ: يَارَسُولَ اللهِ إِنَّ مِنْ تَوْبَتِي أَنْ أَنْخَلِعَ مِنْ مَالِي صَدَقَةً إِلَى اللهِ وَإِلَى رَسُولِهِ. فَقَالَ رَسُولُ اللهِ ﷺ: ((أَمْسِكْ عَلَيْكَ بَعْضَ مَالِكَ فَهُوَ خَيْرٌ لَكَ)) فَقُلْتُ: إِنِّي أُمْسِكُ سَهْمِيَ الَّذِي بِخَيْبَرَ. وَقُلْتُ: يَارَسُولَ اللهِ انَّ اللهَ تَعَالَى

ተቀምጠው አገኘኋቸው። ሰዎች ዙሪያቸውን ከበዋቸዋል። ጦልሐ ኢብን ዑብደላህ ተነስቶ በመቆም እየገሰገሰ መጥቶ ጨበጠኝ። "እንኳን ደስ ያለህ" ሲልም አበሰረኝ። ከሙሃጂሮች ውስጥ ከርሱ ውጭ እንድም ከተቀመጠበት የተነሳ አልነበረም። (ከዕብ ይህን የጦልሐን ድርጊት ምን ጊዜም አይዘነጋውም።) ለአላህ መልዕክተኛ (ሶ.ዐ.ወ) ሰላምታ በማቀርብላቸው ወቅት ፊታቸው በደስታ እየተፍለ ቀለቀ፡- "እናትህ ከወለደችህ ዕለት አንስቶ ካላለፍካቸው ቀናት ሁሉ በላጭ በሆነው ቀን" አሉኝ። "ብሥራቱ የመጣው ከርስዎ ዘንድ ነው ወይስ ከአላህ ዘንድ?" አልኳቸው። "ከኔ ዘንድ አይደለም! ልዑል ልና ኃያል ከሆነው አላህ ዘንድ ነው።" አሉኝ። የአላህ መልዕክተኛ (ሶ.ዐ.ወ) ደስታ በሚሰማቸው ወቅት ፊታቸው እጅግ ያበራ ነበር። የጨረቃ ቁራጭ እስኪመስል ድረስ ይፍለቀለቃል። ይህን ሁኔታ እናውቅባቸው ነበር። እንደተቀመጥኩ፡- "የአላህ መልዕክተኛ ሆይ! አላህ ተውቡቴን ስለተቀበለኝ ምሥጋናውን ለማድረስ ከገንዘቤ ለአላህና ለመልዕክተኛው (ዲን) አስተዋጽኦ ለማበርከት እከጅላለሁ።" አልኳቸው። "ከገንዘብህ ከፊሉን ብታስቀር መልካም ይሆንልሃል።" አሉኝ። "ለኸይበር ዘመቻ የተሳተፍኩበትን ዕጣዬን አስቀራለሁ።" አልኳቸው። "የአላህ መልዕክተኛ ሆይ! አላህ ነጻ ያወጣኝ እውነት ስለተናገርኩ ነው። አላህ ተውቡቴን ስለተቀበለኝ ምሥጋናውን

أَنَّمَا أَنْجَانِي بِالصِّدْقِ، وَإِنَّ مِنْ تَوْبَتِي أَنْ لاَ أُحَدِّثَ إِلاَّ صِدْقًا مَابَقِيتُ، فَوَ اللهِ مَاعَلِمْتُ أَحَدًا مَنَ الْمُسْلِمِينَ أَبْلاَهُ اللهُ تَعَالَى فِي صِدْقِ الْحَدِيثِ مُنْذُ ذَكَرْتُ ذَلِكَ لِرَسُولِ اللهِ ﷺ أَحْسَنَ مِمَّا أَبْلاَنِي اللهُ تَعَالَى، واللهِ مَاتَعَمَّدْتُ كِذْبَةً مُنْذُ قُلْتُ ذَلِكَ لِرَسُولِ اللهِ ﷺ إِلَى يَوْمِي هَذَا، وَإِنِّي لأَرْجُو أَنْ يَحْفَظَنِيَ اللهُ تَعَالَى فِيمَا بَقِيَ، قَالَ:

فَأَنْزَلَ اللهُ تَعَالَى: ﴿لَقَدْ تَابَ اللهُ عَلَى النَّبِيِّ وَالْمُهَاجِرِينَ والأَنْصَارِ الَّذِينَ اتَّبَعُوهُ فِي سَاعَةِ الْعُسْرَةِ﴾ حَتَّى بَلَغَ: ﴿إِنَّهُ بِهِمْ رَؤُوفٌ رَحِيمٌ. وَعَلَى الثَّلاَثَةِ الَّذِينَ خُلِّفُوا حَتَّى إِذَا ضَاقَتْ عَلَيْهِمُ الأَرْضُ بِمَا رَحُبَتْ﴾ حَتَّى بَلَغَ: اتَّقُوا اللهَ وَكُونُوا مَعَ الصَّادِقِينَ﴾.

قَالَ كَعْبٌ: واللهِ مَا أَنْعَمَ اللهُ عَلَيَّ مِنْ نِعْمَةٍ قَطُّ بَعْدَ إِذْ هَدَانِيَ اللهُ لِلإِسْلاَمِ أَعْظَمَ فِي نَفْسِي مِنْ صِدْقِي رَسُولَ اللهِ ﷺ أَنْ لاَ أَكُونَ كَذَبْتُهُ، فَأَهْلِكَ كَمَا هَلَكَ الَّذِينَ كَذَبُوا، إِنَّ اللهَ تَعَالَى قَالَ لِلَّذِينَ كَذَبُوا حِينَ أَنْزَلَ الْوَحْيَ شَرَّ مَا

ለማድረስ ሕይወቴ እስካለች ድረስ እውነትን እንጅ ሳልናገር ለራሴ ቃል ገብቻለሁ።" አልኪቸውም። ይህንን ነገር ለመልዕክተኛው ከዘከርኩላቸው ዕለት አንስቶ እውነትን በመናገር ለኔ የዋ ለልኝን ያህል ወሰን የለሽ ፀጋ አላህ የዋለለት አንድም ሰው የለም። ለአላህ መልዕክተኛ (ሶ.ዐ.ወ) ይህንን ነገር ካወሳሁላቸው በኋላ እስካሁኗ ዕለት ድረስ ሐሰት ለመናገር ያሰብኩበት ጊዜ የለም። በቀሪው ሕይወቴ በዚሁ እንድፀና አላህ እንደሚጠብቀኝ ተስፋ አደርጋለሁ። አላህ ተከታዩን የቁርአን አንቀጽ አወረደ፦

«በነቢዩ፥ በነዚያም በችግሪቱ ጊዜያት (በተቡክ ዘመቻ) ከነሱ የከፊሎቹ ልቦች (ለመቅረት) ሊዘነበሉ ከተቃረቡ በኋላ፥ በተከተሉት ሰደተኞችና ረዳቶች ላይ፥ አላህ በእርግጥ ፀፀታቸውን ተቀበለ፤ ከዚያም ከነርሱ ንስሓ መግባታቸውን ተቀበለ፤ እርሱ ለነርሱ ርኅሩህ፥ አዛኝ ነውና። በነዚያም በሦስቱ ሰዎች ላይ እስከተጠበቡ፥ ከአላህም ወደርሱ ቢሆን እንጂ ሌላ መጠጊያ እለመኖሩን እስከ አረጋገጡ ድረስ በተቆዩት ላይ፥ (አላህ ፀፀትን ተቀበለ)። ከዚያም ይፀፀቱ ዘንድ ወደ ፀፀት መራቸው፤ አላህ እርሱ ፀፀትን ተቀባይ፥ አዛኝ ነውና። እናንተ ያመናችሁ ሆይ፤ አላህን ፍሩ፤ ከውነተኞቹም ጋር ኹኑ።» (አል-ተውባህ፥ 117-119)

አላህ ለኢስላም ምሪት ካበቃኝ ዕለት ጀምሮ ለአላህ መልዕክተኛ (ሶ.ዐ.ወ) እውነትን ከመናገር የበለጠን ፀጋ ውሉልኝ አያውቅም። ካለመዋሸ ቴና እነዚያ የዋሹ ሰዎች የገጠማቸው ዓይነት ጥፋት ሳይገጥመኝ ከመቅረቱ

የበለጠ ፀጋ ውሉልኝ እያውቅም። አላህ ወሕይ ያወረደ ዕለት እነዚያን የዋሹ ሰዎችን አስከፊ በሆነ ቃላት አውስቷቸዋል። እንዲህ በማለት፦

قَالَ لأَحَد، فَقَالَ اللهُ تَعَالَى:﴿سَيَحْلِفُونَ بِاللهِ لَكُمْ اِذَا انْقَلَبْتُمْ إِلَيْهِمْ لِتُعْرِضُوا عَنْهُمْ، فَأَعْرِضُوا عَنْهُمْ اِنَّهُمْ رِجْسٌ وَمَأْوَاهُمْ جَهَنَّمُ جَزَاءًا بِمَا كَانُوا يَكْسِبُونَ. يَحْلِفُونَ لَكُمْ لِتَرْضَوا عَنْهُمْ فَإِنْ تَرْضَوا عَنْهُمْ فَإِنَّ اللهَ لاَيَرْضَى عَنِ الْقَوْمِ الْفَاسِقِينَ﴾.

«ወደነሱ በተመለሳችሁ ጊዜ፥ እንድትተውዋቸው ለናንተ በእርግጥ በአላህ ይምላሉ፤ እነሱንም ተውዋቸው፤ እነሱ እርኩሶች ናቸውና፤ ይሠሩትም በነበሩት ዋጋ መኖሪያቸው ገሃነም ነው። ከነሱ ትወዱላቸው ዘንድ፥ ለናንተ ይምሉላችኋል፤ ከነሱ ብትወዱም፥ አላህ ከአመጠኞች ሕዝቦች አይወድም።» (አል-ተውባህ፥ 95-96)

قَالَ كَعْبٌ: كُنَّا خُلِّفْنَا أَيُّهَا الثَّلاَثَةُ عَنْ أَمْرِ أُولَئِكَ الَّذِينَ قَبِلَ مِنْهُمْ رَسُولُ اللهِ ﷺ حِينَ حَلَفُوا لَهُ، فَبَايَعَهُمْ وَاسْتَغْفَرَ لَهُمْ، وَأَرْجَأَ رَسُولُ اللهِ ﷺ أَمْرَنَا حَتَّى قَضَى اللهُ تَعَالَى فِيهِ بِذَلِكَ،

قَالَ اللهُ تَعَالَى: ﴿وَعَلَى الثَّلاَثَةِ الَّذِينَ خُلِّفُوا﴾

وَلَيْسَ الَّذِي ذَكَرَ مِمَّا خُلِّفْنَا تَخَلُّفَنَا عَنِ الْغَزْوِ، وَإِنَّمَا هُوَ تَخْلِيفُهُ إِيَّانَا وَإِرْجَاؤُهُ أَمْرَنَا عَمَّنْ حَلَفَ لَهُ وَاعْتَذَرَ إِلَيْهِ فَقَبِلَ مِنْهُ. مُتَّفَقٌ عَلَيْهِ.

وَفِي رِوَايَةٍ ((إِنَّ النَّبِيَّ ﷺ خَرَجَ فِي غَزْوَةِ تَبُوكَ يَوْمَ الْخَمِيسِ، وَكَانَ يُحِبُّ أَنْ يَخْرُجَ يَوْمَ الْخَمِيسِ)).

እኛ ሦስት ሰዎች ጉዳያችን፥ ከነዚያ ምክንያታቸውን በመሐላ ሲገልጹ የአላህ መልዕክተኛ ምክንያታቸውን በመሐላ ሲገልጹ የአላህ መልክተኛ ምክንያታቸውን ተቀብለው ቃልኪዳን ከተጋቢቸውና የአላህንም ምሕረት ከለመኑላቸው ሰዎች፥ እንዲዘገይ ተደረገ። አላህ ብይኑን እስኪለግስ ድረስ መልዕክተኛው (ሶ.ዐ.ወ) ጉዳያችንን በይደር አቆዩት። አላህ «በነዚያ በሦስቱ በተቆዩት ሰዎች ላይ...» በማለት ውሳኔውን አሳለፈ። "በተቆዩት" ተብሉ መጠቀሱ ከተቡክ ዘመቻ ወደኋላ ተነጥለን መቅረታችንን ለማመልከት አይደለም። መልዕክተኛው (ሶ.ዐ.ወ) ጉዳያችንን ከነዚያ መሐላ በመፈፀም ምክንያታቸውን ከገለፁትና ከተቀበሏቸው ሰዎች፥ ማዘግየታቸውን ለመጠቆም ነው።" (ቡኻሪና ሙስሊም)

በሌላ ዘገባ እንደተወሳው፦

"የአላህ መልዕክተኛ (ሶ.ዐ.ወ) ለተቡክ ዘመቻ የተንቀሳቀሱት ሐሙስ

ቀን ነበር። ሐሙስ ቀን ጉዞ መውጣትን ይወዱ ነበር።"

وَفِـــي رِوَايَةٍ: ((وَكَانَ لاَيَقْدَمُ مِنْ سَفَرٍ إِلاَّ نَهَـــارًا فِـــي الضُّحَى، فَإِذَا قَدِمَ بَدَأَ بِالْمَسْجِدِ فَصَلَّى فِيهِ رَكْعَتَيْنِ ثُمَّ جَلَسَ فِيهِ)).

በሌላ ዘገባ ደግሞ ተከታዩ ተወስቷል፦

"ከጉዞ የሚመለሱት በቀን ረፋድ ወቅት ነው ላይ ነበር። ከጉዞ እንደተ መለሱ መስጊድ በመግባት ሁለት ረከዓ ከሰገዱ በኋላ መቀረመጥ ልምዳቸው ነበር።"

ከሐዲሱ የምንማራቸው ቁምነገሮች

- እውነተኛ የሙስሊሞች ግልጽነትና እውነተኝነት። ስህተታቸውን ያምናሉ ምክንያቶችን በመደርደር ስህተታቸውን ለመሸፋፈን አይሞክሩም።
- የመልዕክተኛው (ሶ.ዐ.ወ) ወታደራዊ ዕቅድና ፕላን፣ የዘመቻውን ሚስጥር መደበቃቸውና እርምጃቸውን ከሁኔታቸው ጋር ለማጣጣም የሚያደርጉት ጥረት፣ ሠራዊታቸውን አለማታለላቸውና ተጨባጩን ሁኔታ በመግለጽ እንዲዘጋጅ ማድረጋቸው።
- ሙስሊሞች የተለያዩ ችግሮች ቢኖራቸውም ለዘመቻ በከፍተኛ ጉጉትና ስሜት መትመማቸው።
- መልካም ተግባራትን ለመከወን አለማመንታትና ስንቆችንና ትጥቅን በማዘጋጀት በኩል ተገቢውን ርብርቦሽ ማድረግ።
- ሙስሊሞች ኃላፊነታቸውን ባለመወጣታቸው የሚሰማቸው ቁጭት ስሜትና ኮሙናፊቆች ወይም ወደኋላ ከሚያፈገፍጉ ሰዎች ተርታ ላለመሰለፍ የነበራቸው ፍርሃት።
- ሶሐቦች ብራሳቸውም ላይ እንኳ ቢሆን- ሐቅን በመናገር የነበራቸው ፍፁም ልዩ የሆነ ድንቅ ሰብዕና።
- ከሰዎች ጋር የሚኖረን ግንኙነት በውጫዊ ማንነታቸው ይወሰናል። ውስጣቸውን ለአላህ እንተወዋለን።
- "ሙናፊቅ" ምክንያት መደርደሩና ሐሰትን እውነት ለማስመሰል መጣሩ ከአላህ ቅጣትና ቁጣ አያድነውም።
- በሥነ-ምግባርም ሆነ በማኅበራዊ ውሉ መልካምነትና "ተቅዋ" የሌሉችን አርአያነት መከተል።
- የሙናፊቆችንና የሩሲቆችን ድርጊት አለመከታተልና ጊዜ ራሱ እስኪያጋልጣቸው ድረስ እንዲሁ መተው።
- ከወንጀለኞች ጋር ያለንን ግንኙነት መቁረጥ። ከነርሱ ጋር አለመቀላቀል፣ ሰላምታም አለማቅረብ፣ ወዘተ። የገቡትኝነትና ጥፋተኝነት ስሜት እንዲሰማቸውና ከወንጀላቸው መቆጠብ ተውብት እንዲያደርጉ ሚና ማሳደር።
- "ሙእሚን" ወንጀል በመሥራት ለፈፀመው ጥፋት ፀፀትና የሚሰማው ፀፀትና ቁጭት።

- ኢስላም በወንጀለኞች ላይ ያለው ቁጥር አቋም። ከጉብረተሰቡ በመገንጠልም እንኳ ቢሆን ይቀጣቸዋል። ለሌሎች ጠቃሚ ትምህርት እንዲሆናቸው።
- "ተውበት" ከሚገኝባቸው፣ "ረሕመት" ከሚዘንብባቸው፥ "ኢስቲግፋር" ከማይታጣባቸው አካባቢዎች መገኘት ተወዳጅ ነው።
- ያጠፋን ሰው ጥፋት ከተፈፀመበት አካል ጋር ለማቀራረብና ምክንያቶችን በመደርደር ግንኙነታቸውን ለማሻሻል መሞከር ጽድቅ ተግባር ነው።
- የመልዕክተኛው (ሶ.ዐ.ወ) ድንቅ ሰብዕናና ለተከታዮቻቸው የነበራቸው እዝነት። ሲደሱ ይደሳሉ፣ ሲከፉ ይከፋሉ።
- ሙእሚን በዲኑም በዱንያውም ፈተና ይገጥመዋል። አላህ መልካምን የሻለት ሰው ከአላህ ጋር ያለው ግንኙነት በእውነትና የአላህን ቃልኪዳን በመጠበቅ ጽኑ መሠረት ላይ የተገነባ ይሆናል።
- ሙእሚን ከማንም ከምንም ይልቅ ለአላህና ለረሱል በታዛዥነት ፀንቶ መገኘትን ይመርጣል።
- አንድ ሰው ወንጀል ከፈፀመና ወንጀሉ "ኒፋቅ" ወይም "ኩፍር" ውስጥ ይከተዋል ተብሎ የሚገመት ከሆነ ባልተቤቱ ለወሲባዊ ግንኙነት ፈቃደኛ ልትሆን አይፈቀድላትም።
- ብሥራትን መንገርና ለዚህ ተግባር መሽቀዳደም ተወዳጅ ነው።
- ሁሉንም ገንዘብ መመጽወት ይጠላል። ለድህነትና የሰው እጅ ለማየት ጥፋት ሊያበቃ ይችላልና።
- እውነት በዚህች ዓለምም ሆነ በመጭው ሕይወት ለስኬት ያበቃል።
- ተውበትን በመቀበሉና በሌሎችም ውለታዎቹ፥ እንዲሁም ወንጀለኞቹን ይቅር በማለቱ ለአላህ ምስጋና ማድረስ ተገቢ ነው።
- ቃልኪዳን መሙላትና ከወንጀል በኋላ መልካም ተግባርን መፈፀም ተገቢ ነው።
- ሙእሚን አላህ ተውብቱን ሲቀበለውና ለእውነተኛነትና ታማኝነት በመብቃቱ ደስታ ይሰማዋል።
- ይህ የሐዲስ ዘገባ አያሌ አስተምህሮዎችን አዝሏል። ግና ከዚህ ምዕራፍ መንፈስ ጋር የሚሄዱትን አስተምህሮዎች ብቻ ነው በአጭሩ ለማስፈር የሞከረው።

22- አቡ ኑጀይድ ዒምራን ኢብን አል-ሑሶይን አል-ኹዛዒይ (ረ.ዐ) እንዳስተላለፉት:- አንዲት የጁሐይና ጉሳ አባል የሆነች ሴት ከአላህ መልዕክተኛ (ሶ.ዐ.ወ) ዘንድ ቀረበች። በዝሙት አርግዛለች። "የአላህ መልዕክተኛ ሆይ! የአላህን ድንበር ጥሻለሁ። "ሐድ" (የግድያ ቅጣት) ይፈፀምብኝ" አለች። ነቢዩ (ሶ.ዐ.ወ) የቅርብ ወኪሏን ጠሩና "ተንከባከባት። ስትወልድ ይዘሃት ከኔ ዘንድ ና"

٢٢- وَعَنْ أَبِي نُجَيْد -بضم النون وفتح الجيم- عِمْرَانَ ابْنِ الْحُصَيْنِ الْخُزَاعِيِّ ﷺ أَنَّ امْرَأَةً مِنْ جُهَيْنَةَ أَتَتْ رَسُولَ اللهِ ﷺ وَهِيَ حُبْلَى مِنَ الزِّنَا، فَقَالَتْ: يَا رَسُولَ اللهِ أَصَبْتُ حَدًّا فَأَقِمْهُ عَلَيَّ، فَدَعَا نَبِيُّ اللهِ ﷺ وَلِيَّهَا فَقَالَ: ((أَحْسِنْ إِلَيْهَا، فَإِذَا وَضَعَتْ فَأْتِنِي)) فَفَعَلَ فَأَمَرَ

بِهَـا نَبِيُّ اللهِ ﷺ، فَشُدَّتْ عَلَيْهَا ثِيَابُهَا، ثُـمَّ أُمِرَ بِهَا فَرُجِمَتْ، ثُمَّ صَلَّى عَلَيْهَا، فَقَـالَ لَهُ عُمَرُ: تُصَلِّي عَلَيْهَا يَارَسُولَ اللهِ وَقَدْ زَنَتْ؟ قَالَ: ((لَقَدْ تَابَتْ تَوْبَةً لَوْ قُسِمَتْ بَيْنَ سَبْعِينَ مِنْ أَهْلِ الْمَدِينَةِ لَوَسِعَتْهُمْ، وَهَلْ وَجَدْتَ أَفْضَلَ مِنْ أَنْ جَادَتْ بِنَفْسِهَا لِلهِ عَزَّ وَجَلَّ؟!))

رَوَاهُ مُسْلِمٌ.

አሉት። የታዘዘውን አደረገ። ልብሷ ወደላይ ተሰብስቦ እንዲታሰር ተደረገ። ከዚያም (የግድያ) ትእዛዝ አስተላለፉ። በድንጋይ ተደብድባ ተገደለች። ዑመር (ረ.ዐ) ለመልዕክተኛው (ሶ.ዐ.ወ)፦"የአላህ መልዕክተኛ ሆይ! ዝሙት የፈፀመች ሆና እያለ የጀናዛ ሶላት ይሰገድባታል?" አላቸው። "ቢከፋፈል ለሰባ የመዲና ሰዎች የሚተርፍ የሆነን ተውበት ቶብታለች። ልዑልና ኃያል ለሆነው ጌታ አላህ ነፍሷን አሳልፋ ከሰጠች ሴት የበለጠ (ጻድቅ) አግኝተሃልን?" አሉት። (ሙስሊም ዘግበውታል)

ከሐዲሱ የምንማራቸው ቁምነገሮች

- አንድ ወንጀል ከፈፀሙ በኋላ በእጅጉ መፀፀትና መቆጨት፥ ራስን ከርክሰት ለማጽዳት መጓጓት የሙእሚኖች ድንቅ ባሕሪ ነው።
- በዚህች ዓለም ላይ የሚሰጥ ሸሪዓዊ ቅጣት ፀፀትና ቁጭት ከታከለበት ወንጀልን ያስምራል።
- እርጉዝ እስክትወልድ ድረስ የዝሙት ቅጣት አይፈፀምባትም። ቅጣቱ ግርፋት ከሆነ ከወሊድ ደም እስክትፀዳ ድረስ፥ ሞት ከሆነ ደግሞ ልጁ የርሷ ድጋፍ ከማያስፈልገው ደረጃ ላይ እስኪደርስ ድረስ እንዲዘገይ ይደረጋል።

٢٣- وَعَنْ ابْنِ عَبَّاسٍ رضى الله عنهما أَنَّ رَسُـولَ اللهِ ﷺ قَالَ: ((لَوْ أَنَّ لِابْنِ آدَمَ وَادِيًا مِنْ ذَهَبٍ أَحَبَّ أَنْ يَكُونَ لَهُ وَادِيَـانِ، وَلَنْ يَمْلَأَ فَاهُ إِلاَّ التُّرَابُ، وَيَتُوبُ اللهُ عَلَى مَنْ تَابَ)) مُتَّفَقٌ عَلَيْهِ.

23- ኢብን ዐብባስ አነስ ኢብን ማሊክ (ረ.ዐ.) እንዳስተላለፉት የአላህ መልዕክተኛ (ሶ.ዐ.ወ) እንዲህ ብለዋል፦ "የአደም ልጅ አንድ ሸለቆ ወርቅ ቢኖረው ሁለተኛ እንዲኖረው መመኘቱ አይቀርም። አፉን ከአፈር ውጭ የሚሞላው ነገር የለም። አላህ የተውበተኞችን ተውበት ይቀበላል"። (ቡኻሪና ሙስሊም)

ከሐዲሱ የምንማራቸው ቁምነገሮች

- የሰው ልጅ ሃብትን ለመሰብሰብና ለዚህች ዓለም ፀጋዎች ያለው ከፍተኛ ጉጉት። ይህ ዓይነቱ ስግብግብነት አላህን ከመግዛት የሚያዘናጋውና አዕምሮን ከአኼራ ይልቅ በዱንያዊ ሐሳብ ብቻ እንዲሞላ የሚያደርግ ከሆነ የተወገዘ ይሆናል።
- ከመጥፎ ባሕሪያት ተውበት ያደረገ ሰው አላህ ተውቡን ይቀበለዋል።

٢٤- وَعَنْ أَبِي هُرَيْرَةَ ﷺ أَنَّ رَسُولَ اللهِ ﷺ قَالَ: ((يَضْحَكُ اللهُ سُبْحَانَهُ وَتَعَالَى إِلَى رَجُلَيْنِ يَقْتُلُ أَحَدُهُمَا الآخَرَ يَدْخُلاَنِ الْجَنَّةَ، يُقَاتِلُ هَذَا فِي سَبِيلِ اللهِ فَيُقْتَلُ، ثُمَّ يَتُوبُ اللهُ عَلَى الْقَاتِلِ فَيُسْلِمُ فَيُسْتَشْهَدُ)) مُتَّفَقٌ عَلَيْهِ.

24- አቡ ሁረይራ (ረ.ዐ.) እንዳስተላለፉት የአላህ መልዕክተኛ (ሶ.ዐ.ወ) እንዲህ ብለዋል:- "ልዑልና ብዑእ የሆነው አላህ በሁለት ሰዎች ይረካል። አንዱ ሌላኛውን ይገድላል። ግና ሁለቱም ጀንነት ይገባሉ። አንደኛው በአላህ መንገድ ሲፋለም ይገደላል። አላህ የገዳይን ተውበት ይቀበላል። (ገዳይ) ኢስላምን ይቀበልና ሰማዕት (ሸሂድ) ይሆናል።"
(ቡኻሪና ሙስሊም)

ከሐዲሱ የምንማራቸው ቁምነገሮች

- ከወንጀል -የቱን ያህል ታላቅ ቢሆንም- መጥበትና ከአላህ እዝነትና ትሩፋት (ረሕመት) ተስፋ አለመቁረጥ።
- ኢስላም ኩፍር ውስጥ የተረፀመን ወንጀል ሁሉ ያብሳል። ተውበት የተረፀሙ ወንጀሎችንና ጥፋቶችን ሁሉ ታስረያለች።

ምዕራፍ 3

ትዕግስት (ሶብር)

٣- بَابُ الصَّبْرِ

"እላንተ ያመናችሁ ሆይ! ታገሱ፣ ተብራቱም፣" (አሊ-ዒምራን፣ 200)

"ከፍርሃትና ከረኃብም በጥቂት ነገር፣ ከገንዘቦችና ከነፍሶችም ከፍራፍሬዎችም በመቀነስ በእርግጥ እንሞክራችኋለን። ታጋሾችንም (በገነት) አብስር።" (አል-በቀራህ፣ 155)

"ታጋሾቹ ምንዳቸውን የሚሰጠጡት ያለ ግምት ነው።" (አል-ዙመር፣10)

"የታገሰና ምሕረት ያደረገም ሰው፣ ይህ ከምርጮቹ (ከተፈላጊዎቹ) ነገሮች ነው።" (አል-ሹራ፣ 43)

"እላንተ ያመናችሁ ሆይ በመታገስና በሶላት ተረዱ፣ አላህ (በእርዳታው) ከታጋሾች ጋር ነውና።" (አል-በቀራህ፣ 153)

"ከናንተም ታጋዮቹንና ታጋሾቹን እስከምናውቅ... እንሞክራችኋለን።" (መሐመድ፣ 31)

ስለትዕግስት ጥሪ የሚያደርጉ፣ የትዕግስትን የላቀ ደረጃ የሚገልጹ የቁርአን አንቀጾች በርካታ ናቸው።

قَالَ اللهُ تَعَالَى: ﴿يَا أَيُّهَا الَّذِينَ ءَامَنُوا اصْبِرُوا وَصَابِرُوا﴾ وَقَالَ تَعَالَى: ﴿وَلَنَبْلُوَنَّكُمْ بِشَيْءٍ مِنَ الْخَوْفِ وَالْجُوعِ وَنَقْصٍ مِنَ الأَمْوَالِ وَالأَنْفُسِ وَالثَّمَرَاتِ وَبَشِّرِ الصَّابِرِينَ﴾ وَقَالَ تَعَالَى: ﴿إِنَّمَا يُوَفَّى الصَّابِرُونَ أَجْرَهُمْ بِغَيْرِ حِسَابٍ﴾ وَقَالَ تَعَالَى: ﴿وَلَمَنْ صَبَرَ وَغَفَرَ إِنَّ ذَلِكَ لَمِنْ عَزْمِ الأُمُورِ﴾ وَقَالَ تَعَالَى: ﴿اسْتَعِينُوا بِالصَّبْرِ وَالصَّلَوةِ إِنَّ اللهَ مَعَ الصَّابِرِينَ﴾ وَقَالَ تَعَالَى: ﴿وَلَنَبْلُوَنَّكُمْ حَتَّى نَعْلَمَ الْمُجَاهِدِينَ مِنْكُمْ وَالصَّابِرِينَ﴾ والآيَاتُ فِي الأَمْرِ بِالصَّبْرِ وَبَيَانِ فَضْلِهِ كَثِيرَةٌ مَعْرُوفَةٌ.

25- Abu Malik al-Harith bin Asim al-Ash'ari (r.a) narrated that the Messenger of Allah (s.a.w) said: "Purity is half of faith, and Alhamdulillah fills the scale, and Subhanallah and Alhamdulillah fill what is between the heavens and the earth.

٢٥- وَعَنْ أَبِي مَالِكٍ الْحَارِثِ بْنِ عَاصِمٍ الأَشْعَرِيِّ ﷺ قَالَ: قَالَ رَسُولُ اللهِ ﷺ ((الطُّهُورُ شَطْرُ الإِيمَانِ وَالْحَمْدُ لِلَّهِ تَمْلأُ الْمِيزَانَ، وَسُبْحَانَ

25- አቡ ማሊክ ሐሪስ ኢብን ዓሊም አል-አሽዓሪይ (ረ.ዐ) እንዳስተላለፉት የአላህ መልዕክተኛ (ሶ.ዐ.ወ) እንዲህ ብለዋል፡- "ንጽሕና የእምነት (ኢማን) ግማሽ ነው። "አልሐምዱ ሊላህ" ያለችው

اللهِ وَالْحَمْدُ للهِ تَمْلآنِ –أَوْ تَمْلأُ– مَا بَيْنَ السَّمَوَاتِ وَالأَرْضِ، وَالصَّلاَةُ نُورٌ، وَالصَّدَقَةُ بُرْهَانٌ، وَالصَّبْرُ ضِيَاءٌ، وَالْقُرْآنُ حُجَّةٌ لَكَ أَوْ عَلَيْكَ. كُلُّ النَّاسِ يَغْدُو، فَبَائِعٌ نَفْسَهُ فَمُعْتِقُهَا، أَوْ مُوبِقُهَا)) رَوَاهُ مُسْلِمٌ.

ቃል ሚዛን ትሞላለች፣ "ሱብሐነላህ ወልሐምዱ ሊላህ" የሚሉት ቃላት በምድርና በሰማይ መካከል (ያለውን ቦታ) ይሞላሉ -ወይም ትሞላለች። ሶላት ብርሃን ነው። ምጽዋት (ሶደቃ) (የኢማን) ዋቢ ነው። ትዕግስት (ሶብር) ብርሃን ነው። ቁርአን ላንተ ወይም በአንተ ላይ አስረጅና መስካሪ ነው። ሁሉም ሰው ነፍሱን ነጻ ያወጣ ወይም ለጥፋት የዳረገ ሆኖ ዕለቱን ይጀምራል።" (ሙስሊም እንደዘገቡት)

ከሐዲሱ የምንማራቸው ቁምነገሮች

- ውዱእ የሶላት ቅድመ ግዳጅ (ሸርጥ) ነው።
- ሶላትን ማብዛት ከፍተኛ ጠቀሜታ አለው። ከመጥፎ እና አስፀያፊ አድራጉቶች ያቅባል። ወደ ቀጥተኛው ጉዳና ይመራል። ከጥፋት ያድናል።
- ሶደቃን የማብዛት ጠቀሜታ -የእንድን ሙእሚን እውነተኝነት፣ ታማኝነትና ቅንነት ያመለክታልና።
- የትዕግስት (ሶብር) ትሩፋት።
- ቁርአን ለሁሉም ሸሪዓዊ ብይኖች መነሻ መሠረት፥ የሙስሊሞች ብቸኛ ዋቢና የመመሪያ ምንጭ ነው።
- እያንዳንዱ ሰው ሥራዬ ብሎ የሚያከናውነው ነገር ሊኖረው እንደሚገባ።
- ሙስሊም እያንዳንዱን የሕይወቱን ሽርፍራፊ የአላህን ፈቃድ በመፈፀም ተግባር ላይ ለማዋል ጥረት ያደርጋል።

٢٦- وَعَنْ أَبِي سَعِيدٍ سَعْدِ بْنِ مالِكِ بْنِ سِنَانٍ الْخُدْرِيِّ رضى الله عنهما: أَنَّ نَاسًا مِنَ الأَنْصَارِ سَأَلُوا رَسُولَ اللهِ ﷺ فَأَعْطَاهُمْ، ثُمَّ سَأَلُوهُ فَأَعْطَاهُمْ، حَتَّى نَفِدَ مَا عِنْدَهُ، فَقَالَ لَهُمْ حِينَ أَنْفَقَ كُلَّ شَيْءٍ بِيَدِهِ: ((مَا يَكُنْ عِنْدِي مِنْ خَيْرٍ فَلَنْ أَدَّخِرَهُ عَنْكُمْ، وَمَنْ يَسْتَعْفِفْ يُعِفَّهُ اللهُ، وَمَنْ يَسْتَغْنِ يُغْنِهِ اللهُ، وَمَنْ يَتَصَبَّرْ

26- ሰዕድ ኢብን ሲናን አል-ኹድሪይ (ረ.ዐ) እንዳስተላለፉት:- ከአንሷር የሆኑ ሰዎች የአላህን መልዕክተኛ (ሶ.ዐ.ወ) (ስጦታ) ጠየቁ። ሰጧቸው። በድጋሚ ጠየቁ። ሰጧቸው፣ ከኻቸው ያለው እስኪያልቅ ድረስ። በኻቸው ያለውን ሰጥተው ከጨረሱ በኋላ እንዲህ አሏቸው:- "ከኔ ዘንድ አንዳች መልካም ነገር ካለ ከናንተ አልቆጥበውም። አላህን ቁጥብነትን (ሰዎችን ከመጠየቅ መቆጠብን) የለመነ አላህ ቁጥብነትን ይለግሰዋል። መብቃቃትን (ራስን በራስ መቻልን) የለመነም አላህ መብቃቃትን

ይሰጠዋል። አንድ ሰው ከትዕግስት (ሶብር) የበለጠ ሰፊና መልካም ስጦታ አልተሰጠም።" (ቡኻሪና ሙስሊም)

يُصَبِّرْهُ اللهُ. وَمَا أُعْطِيَ أَحَدٌ عَطَاءً خَيْرًا وَأَوْسَعَ مِنَ الصَّبْرِ)). مُتَّفَقٌ عَلَيْهِ.

ከሐዲሱ የምንማራቸው ቁምነገሮች

- የነቢዩ (ሶ.ዐ.ወ) ሊጋስነትና መልካም ሥነ-ምግባራቸው።
- የሃብት ክምችት ሃብታም አያሰኝም። እውነተኛ ሃብት የልቦና ሃብት ነው።
- ራስን በራስ መቻልና ሰዎችን ከመለመን መቆጠብ።
- መልካም ሥነ-ምግባራትና ድንቅ ባሕሪያት በትዕግስት (ሶብር) ይገኛሉ።

27- አቡ የሕያ ሱሐይብ ኢብኑ ሲናን (ረ.ዐ) እንዳስተላለፉት፦የአላህ መልዕክተኛ (ሶ.ዐ.ወ) ተከታዩን ተናግረዋል፦"የሙእሚን ጉዳይ እጅግ የሚደንቅ ነው። ሁለ ነገሩ ኸይር (ሰናይ) ነው። ይህ የሙእሚን (ዕጣ ፈንታ) እንጅ ለማንም (የተሰጠ) አይደለም። አስደሳች ነገር ከገጠመው ለአላህ ምሥጋና (ሹክር) ያደርሳል፤ መልካም ይሆንለታል። ጉዳት ካገኘውም (አስከፊ ነገር ከገጠመውም) ትዕግስት (ሶብር) ያደርጋል፤ ይህም ለርሱ መልካም ይሆንለታል።" (ሙስሊም እንደዘገቡት)

٢٧- وَعَنْ أَبِي يَحْيَى صُهَيْبِ بْنِ سِنَانٍ ﷺ قَالَ: قَالَ رَسُولُ اللهِ ﷺ: ((عَجَبًا لِأَمْرِ الْمُؤْمِنِ! إِنَّ أَمْرَهُ كُلَّهُ لَهُ خَيْرٌ، وَلَيْسَ ذَلِكَ لِأَحَدٍ إِلَّا لِلْمُؤْمِنِ، إِنْ أَصَابَتْهُ سَرَّاءُ شَكَرَ فَكَانَ خَيْرًا لَهُ، وَإِنْ أَصَابَتْهُ ضَرَّاءُ صَبَرَ فَكَانَ خَيْرًا لَهُ)) رَوَاهُ مُسْلِمٌ.

ከሐዲሱ የምንማራቸው ቁምነገሮች

- የሙስሊም ሕይወት -ክፉም አገኘው በጉ- ኸይር ነው። ከአላህ ዘንድ ምንዳ ያገኝበታል።
- ምሉዕ ኢማን ያለው ሰው መልካም ነገር ሲገጥመው አላህን በማመስገን መጥፎ ነገር ሲገጥመው ደግሞ ትዕግስት በማድረግ የሁለቱንም ዓለማት ሰናይ ነገሮች ሁሉ ያገኛል።
- እምነቱ ጉደሉ የሆነ ሰው ግን አንዳች ችግር ሲገጥመው፥ መከራ ሲያገኘው ይቆጣል፤ ይበሳጫል። መከራው አይለቀውም። ተጨማሪ ወንጀልም ይሸምታል። አላህ አንዳች ፀጋ (ኒዕማ) ሲውልለት በተገቢው መንገድ ማስተናገድ ይሳነዋል። ኒዕማው ወንጀል ያስከትልበታል።

28- አነስ (ረ.ዐ) እንዲህ ሲሉ አስተላልፈዋል፦ነቢዩ (ሶ.ዐ.ወ) ጣዕረ-ሞት በያዛቸው ጊዜ ፋጢማ፦ "አቤት የአባቴ ስቃይ!"

يَاأَبَتَاه إِلَى جِبْرِيلَ نَنْعَاهُ. فَلَمَّا دُفِنَ قَالَتْ فَاطِمَةُ رضي الله عنها: أَطَابَتْ أَنْفُسُكُمْ أَنْ تَحْثُوا عَلَى رَسُولِ اللهِ ﷺ التُّرَابَ؟ رَوَاهُ الْبُخَارِيُّ.

٢٨- وَعَنْ أَنَسٍ ﷺ قَالَ: لَمَّا ثَقُلَ النَّبِيُّ ﷺ جَعَلَ يَتَغَشَّاهُ الْكَرْبُ فَقَالَتْ فَاطِمَةُ رضى الله عنها: وَا كَرْبَ أَبَتَاهُ. فَقَالَ: ((لَيْسَ عَلَى أَبِيكِ كَرْبٌ بَعْدَ الْيَوْمِ)) فَلَمَّا مَاتَ قَالَتْ: يَاأَبَتَاهُ أَجَابَ رَبًّا دَعَاهُ، يَا أَبَتَاه جَنَّةُ الْفِرْدَوْسِ مَأْوَاهُ،

አለች። "ከዛሬ በኋላ አባትሽ ላይ ስቃይ የለም።" አሏት። የሞቱ ጊዜ:- "አላህ ዱዐውን ተቀበለው። አባቴ ሆይ! ጀንነተል-ፈርደውስ መኖሪያው ነው። አባቴ ሆይ! ለጂብሪል መርዶ እንንገር።" አለች። ሲቀበሩ ደግሞ:- "በአላህ መልዕክተኛ (ሶ.ዐ.ወ) (አካል) ላይ አፈር ለማልበስ ነፍሳችሁ ወደደችን?" አለች ፋጢማ (ረ.ዐ)።

(ቡኻሪ እንደዘገቡት)

ከሐዲሱ የምንማራቸው ቁምነገሮች

- ጣዕረ-ሞት ላይ ላለ ሰው በጥልቅ ማዘን እንደሚፈቀድ።
- የሚችን መልካም ባሕሪያት መግለጽ እንደሚፈቀድ።
- ነቢዩ (ሶ.ዐ.ወ) በጣዕረ-ሞታቸው ወቅት የደረሰባቸውን ስቃይ በትዕግስት ማሳለፋቸው።

٢٩- وَعَنْ أَبِي زَيْدٍ أُسَامَةَ بن زَيْدِ بْنِ حَارِثَةَ مَوْلَى رَسُولِ اللهِ ﷺ وَحِبِّهِ وَابْنِ حِبِّهِ، رضى الله عنهما، قَالَ : أَرْسَلَتْ بِنْتُ النَّبِيِّ ﷺ: إِنَّ ابْنِي قَدِ احْتُضِرَ فَاشْهَدْنَا، فَأَرْسَلَ يُقْرِئُ السَّلَامَ وَيَقُولُ: ((إِنَّ لله مَا أَخَذَ، وَلَهُ مَا أَعْطَى، وَكُلُّ شَيْءٍ عِنْدَهُ بِأَجَلٍ مُسَمًّى، فَلْتَصْبِرْ وَلْتَحْتَسِبْ)) فَأَرْسَلَتْ إِلَيْهِ تُقْسِمُ عَلَيْهِ لَيَأْتِيَنَّهَا. فَقَامَ وَمَعَهُ سَعْدُ بْنُ عُبَادَةَ، وَمُعَاذُ بْنُ جَبَلٍ، وَأُبَيُّ بْنُ كَعْبٍ، وَزَيْدُ بْنُ ثَابِتٍ، وَرِجَالٌ ﷺ، فَرُفِعَ إِلَى رَسُولِ اللهِ ﷺ الصَّبِيُّ فَأَقْعَدَهُ فِي حِجْرِهِ

29- የአላህ መልዕክተኛ (ሶ.ዐ.ወ) አገልጋይ፥ ወዳጅና ልጅ አቡ ዘይድ አሳማ ኢብን ዘይድ ኢብነል ሐሪሥ (ረ.ዐ) እንዲህ ሲሉ አስተላልፈዋል:- የነቢዩ (ሶ.ዐ.ወ) ሴት ልጅ! "ልጄን ጣዕረ-ሞት ይዞታልና በአስቸኳይ እንዲመጡ።" በማለት (ከነቢዩ ዘንድ) ላከች። መልዕክተኛው (ሶ.ዐ.ወ) ሰላምታ በማቅረብ እንዲህ የሚል መልዕክት ላኩላት:-"የወሰደውም፥ የለገሠውም የአላህ ነው። ከርሱ ዘንድ እያንዳንዱ ነገር በዕቅድና በፕላን ነው የሚከናወነው። ትዕግስት ይኑራት። ከአላህ ምንዳን ትከጅል።" እንዲመጡላት ምላ መልዕክት ላከች። ለመሄድ ተነሱ። ከርሳቸው ጋር ሰዕድ ኢብን ዑባደህ፣ ሙዓዝ ኢብን ጀበል፣ ኡበይ ኢብን ከዕብ፣ ዘይድ ኢብን ሣቢትና ሌሎችም ሶሐቦች (ረ.ዐ) ነበሩ። ሕጻኑ ለነቢዩ (ሶ.ዐ.ወ) ተሰጣቸው። ከጭናቸው ላይ አስቀመጡት። ነፍሱ በጭንቅ ተይዛለች። ዓይኖቻቸው ረጠቡ።

وَنَفْسُـهُ تَقْعْقَعُ، فَفَاضَتْ عَيْنَاهُ. فَقَالَ: سَـعْدٌ: يَارَسُـولَ اللهِ مَاهَذَا؟ فَقَالَ: ((هَـذِهِ رَحْمَةٌ جَعَلَهَا اللهُ تَعَالَى فِي قُلُوبِ عِبَادِهِ)).

"ኖአላህ መልዕክተኛ ሆይ! ይህ (እንባም) ምንድን ነው?" አሏቸው -(ባልደረቦቻቸው)። "ይህች አላህ ከባሮቹ ልቦናዎች ውስጥ የሚያስቀምጣት ርኅራሄ ናት" አሉ።

وَفِـي رِوَايَةٍ ((فِي قُلُوبِ مَنْ شَاءَ مِنْ عِبَادِهِ وَإِنَّمَـا يَرْحَمُ اللهُ مِنْ عِبَادِهِ الرُّحَمَاءَ)). مُتَّفَقٌ عَلَيْهِ.

በሌላ ዘገባ ደግሞ፦

"(ይህች አላህ) ከባሮቹ ልቦና ውስጥ ከሚፈልጋቸው የሚያስቀምጣት ርኅራሄ ናት። አላህ ከባሮቹ እዝነቱን የሚሰጥነው አዛኝ ለሆኑት ነው።" ማለታቸው ተወስቷል። (ቡኻሪና ሙስሊም)

ከሐዲሱ የምንማራቸው ቁምነገሮች

- ታላላቅና ደጋግ ሰዎች ጣዕረ-ሞት ላይ ባለ ሰው አጠገብ እንዲገኙ ማድረግ ይፈቀዳል፤ ትሩፋታቸውን (በረካቸውን) እና ዱዓቸውን በመሻት።
- የማለን ሰው መሐላ መሙላት እንደሚወደድ።
- ለአላህ ፍጡራን ማዘንና መራራት እንደሚገባ።
- ቀልበ ደረቅነትን፣ እገሌተ ቢስነትንና ርኅራሄ አልባነትን፥ እንዲሁም የማያነባ ዓይን ባለቤት መሆን ታላቅ ኪሳራ መሆኑ።
- ድምጽን ሳያሰሙ ማልቀስ እንደሚፈቀድ።
- አንዳች ችግር ያገኘውን፥ መከራ የገጠመውን ሰው ሐዘኑ እንዲቀልለት መጣርና ማጽናናት ጽድቅ ተግባር ነው።

٣٠- وَعَنْ صُهَيْبٍ ﷺ أَنَّ رَسُولَ اللهِ ﷺ قَـالَ: ((كَانَ مَلِكٌ فِيمَنْ قَبْلَكُمْ، وَكَـانَ لَـهُ سَـاحِرٌ، فَلَمَّا كَبِرَ قَالَ لِلْمَـلِكِ: إِنِّي قَدْ كَبِرْتُ فَابْعَثْ إِلَيَّ غُلَامًا أُعَلِّمْهُ السِّحْرَ، فَبَعَثَ إِلَيْهِ غُلَامًا يُعَـلِّمُهُ، وَكَانَ فِي طَرِيقِهِ إِذَا سَلَكَ رَاهِـبٌ، فَقَعَـدَ إِلَيْهِ وَسَمِعَ كَلَامَهُ فَأَعْجَبَـهُ، وَكَانَ إِذَا أَتَى السَّاحِرَ مَرَّ

30- ሱሐይብ (ረ.ዐ) እንዳስተላለፉት የአላህ መልዕክተኛ (ሶ.ዐ.ወ) ተከታዩን ተናግረዋል፦ "ከናንተ በፊት ከነበሩ ሰዎች መካከል አንድ ንጉሥ ነበር። አንድ ጠንቋይ ነበረው። ጠንቋዩ እርጅና ሲጫጫነው ለንጉሱ እንዲህ አለው፦"እኔ እንግዲህ እያረጀሁ ነው። ድግምት የማስተምረው ልጅ ላክልኝ።" ንጉሡ የሚያስተምረውን ልጅ ላከለት። ልጁ ወደ ጠንቋዩ በሚያልፍበት መንገድ ላይ አንድ መናኝ ነበር። ከርሱ ዘንድ አረፍ አለና ንግግሩን አዳመጠ። በእጅጉ አስደነቀው። ዘወትር ወደ ድግምተኛው

بِالرَّاهِبِ وَقَعَدَ إِلَيْهِ، فَإِذَا أَتَى السَّاحِرَ ضَرَبَهُ، فَشَكَا ذَلِكَ إِلَى الرَّاهِبِ فَقَالَ: إِذَا خَشِيتَ السَّاحِرَ فَقُلْ: حَبَسَنِي أَهْلِي، وَإِذَا خَشِيتَ أَهْلَكَ فَقُلْ: حَبَسَنِي السَّاحِرُ. فَبَيْنَمَا هُوَ عَلَى ذَلِكَ إِذْ أَتَى عَلَى دَابَّةٍ عَظِيمَةٍ قَدْ حَبَسَتِ النَّاسَ فَقَالَ: الْيَوْمَ أَعْلَمُ السَّاحِرُ أَفْضَلُ أَمِ الرَّاهِبُ أَفْضَلُ؟ فَأَخَذَ حَجَرًا فَقَالَ: اللَّهُمَّ إِنْ كَانَ أَمْرُ الرَّاهِبِ أَحَبَّ إِلَيْكَ مِنْ أَمْرِ السَّاحِرِ فَاقْتُلْ هَذِهِ الدَّابَّةَ حَتَّى يَمْضِيَ النَّاسُ، فَرَمَاهَا فَقَتَلَهَا وَمَضَى النَّاسُ، فَأَتَى الرَّاهِبَ فَأَخْبَرَهُ. فَقَالَ لَهُ الرَّاهِبُ: أَيْ بُنَيَّ أَنْتَ الْيَوْمَ أَفْضَلُ مِنِّي، قَدْ بَلَغَ مِنْ أَمْرِكَ مَا أَرَى، وَإِنَّكَ سَتُبْتَلَى، فَإِنِ ابْتُلِيتَ فَلاَ تَدُلَّ عَلَيَّ، وَكَانَ الْغُلاَمُ يُبْرِئُ الأَكْمَهَ وَالأَبْرَصَ، وَيُدَاوِي النَّاسَ مِنْ سَائِرِ الأَدْوَاءِ. فَسَمِعَ جَلِيسٌ لِلْمَلِكِ كَانَ قَدْ عَمِيَ، فَأَتَاهُ بِهَدَايَا كَثِيرَةٍ فَقَالَ: مَاهَهُنَا لَكَ أَجْمَعُ إِنْ أَنْتَ شَفَيْتَنِي، فَقَالَ: إِنِّي لاَ أَشْفِي أَحَدًا، إِنَّمَا يَشْفِي اللهُ تَعَالَى، فَإِنْ آمَنْتَ بِاللهِ تَعَالَى دَعَوْتُ اللهَ فَشَفَاكَ، فَآمَنَ بِاللهِ تَعَالَى فَشَفَاهُ اللهُ تَعَالَى، فَأَتَى

በሚሄድበት ወቅት ትንሽ አረፍ ይላል። ጠንቋዩ ዘንድ ሲደርስ ይደበድበዋል፤ ለምን ዘገየህ በሚል። ይህንን ችግሩን ለመናኙ አጫወተው። "ጠንቋዩን የም ትሰጋ ከሆነ ቤተሰቦቼ አዘግይተውኝ ነው የሚል ምክንያት ስጥ። ቤተሰብህን ከሰጋህ ደግሞ ጠንቋዩ ስላዘገየኝ ነው በል።" አለው። በእንዲህ ዓይነት ሁኔታ ላይ እያለ አንድ ቀን ግዙፍ አውሬ ያጋጥመዋል። የሰዎችን መተላለፊያ መንገድ ዘግቶ። "ከጠንቋዩና ከመናኙ ማን የላቀ ደረጃ እንዳላቸው የማው ቀው ዛሬ ነው።" አለ። ድንጋይ አነሳና፦ "አላህ ሆይ! የመናኙ ምግባር ከጠን ቋዩ ነገረ ሥራ ይበልጥ ከአንተ ዘንድ ተወዳጅ ከሆነ ሰዎች ማለፍ ይችሉ ዘንድ ይህን አውሬ ግደለው።" በማለት ድንጋዩን ወረወረው። እናም ገደለው። ሰዎች ማለፍ ቻሉ። መናኙ ዘንድ መጣና ሁኔታውን አጫወተው። "ልጄ ሆይ! አንተ ዛሬ ከኔ ልቀሃል። ጉዳይህ የምመለከተውን ያክል ደረጃ ደርሷል። ወደፊት ፈተናዎች ይገጥሙሃል። ፈተናው ሲገጥምህ ወደኔ አታመላ ክት፤ አታጋልጠኝ።" አለው መናኙ። ልጁ ዲዳዎችንና ለምጽ ያለባቸውን፥ እንዲሁም ሌሎች በሽታዎች ያሉባ ቸውን ሰዎች ፈውስ ያስገኝ ጀመር። አንድ የንጉሡ ችሎታ ባልደረባ ይህን የልጁን የመፈወስ ችሎታ ሰማ። እውር ነበር። አያሌ ስጦታዎችን ለልጁ አመ ጣለት። "ይህ ይዣው የመጣሁት ሁሉ ላንተ ነው፤ ከበሽታዬ ከፈወስከኝ።" አለውም። "እኔ ማንንም አልፈውስም፤ የሚፈውሰው አላህ ብቻ ነው። በአላህ ካመንክ ለአላህ ዱዓ አደርግልሃለሁ፤

الْمَـــلِكَ فَجَلَسَ إِلَيْهِ كَمَا كَانَ يَجْلِسُ فَقَالَ لَهُ الْمَلِكُ: مَنْ رَدَّ عَلَيْكَ بَصَرَكَ؟ قَالَ: رَبِّي. أَوَلَكَ رَبٌّ غَيْرِي؟ قَالَ: رَبِّي وَرَبُّكَ اللهُ، فَأَخَذَهُ فَلَمْ يَزَلْ يُعَذِّبُهُ حَتَّى دَلَّ عَلَى الْغُلَامِ، فَجِيءَ بِالْغُلَامِ فَقَالَ لَهُ الْمَـــلِكُ: أَيْ بُـــنَيَّ قَدْ بَلَغَ مِنْ سِحْرِكَ مَاتُبْرِئُ الأَكْمَهَ وَالأَبْرَصَ، وَتَفْعَلُ وَتَفْعَلُ فَقَـــالَ: إِنِّي لاَ أَشْفِي أَحَدًا، إِنَّمَا يَشْفِي اللهُ تَعَـــالَى، فَأَخَذَهُ فَلَمْ يَزَلْ يُعَذِّبُهُ حَتَّى دَلَّ عَـــلَى الـــرَّاهِبِ، فَجِيءَ بِالرَّاهِبِ فَقِيلَ لَهُ: ارْجِعْ عَنْ دِينِكَ، فَأَبَى، فَدَعَا بِالْمِنْشَـــارِ فَوُضِـــعَ الْمِنْشَارُ فِي مَفْرِقِ رَأْسِهِ، فَشَقَّهُ حَتَّى وَقَعَ شِقَّاهُ، ثُمَّ جِيءَ بِجَـــلِيسِ الْمَـــلِكِ فَقِيلَ لَهُ: ارْجِعْ عَنْ دِيـــنِكَ فَأَبَى فَوُضِعَ الْمِنْشَارُ فِي مَفْرِقِ رَأْسِهِ فَشَقَّهُ بِهِ حَتَّى وَقَعَ شِقَّاهُ، ثُمَّ جِيءَ بِالْغُلَامِ فَقِيلَ لَهُ: ارْجِعْ عَنْ دِينِكَ فَأَبَى، فَدَفَعَـــهُ إِلَـــى نَفَرٍ مِنْ أَصْحَابِهِ فَقَالَ: اذْهَبُوا بِهِ إِلَى جَبَلِ كَذَا وَكَذَا فَاصْعَدُوا بِـــهِ الْجَبَلَ، فَإِذَا بَلَغْتُمْ ذِرْوَتَهُ فَإِنْ رَجَعَ عَـــنْ دِيـــنِهِ وَإِلاَّ فَاطْرَحُوهُ. فَذَهَبُوا بِهِ

ትድናለህ።"አለው -ልጁ። በአላህ አመነ። አላህ ፈወሰው። ሰውየው ከንጉሡ ዘንድ መጣና ዘወትር እንደሚያደርገው ተቀ መጠ። "ዓይንህን ማን መለሰልህ?" አለው ንጉሡ። "ጌታዬ።" በማለት መለሰ። "ከኔ ውጭ ሌላ ጌታ አለህን?" ጠየቀው። "የኔም የአንተም ጌታ አላህ ነው።" መለሰለት። ይዞ ይቀጣውና ያሰቃየው ጀመር። ወደ ልጁ አመላከ ተው። ልጁ ተይዞ እንዲቀርብ ተደረገ። ንጉሡ- "ልጄ ሆይ! ድግምትህ ዲዳንና ለምጽ ያለባቸውን ሰዎች ለመፈወስ፥ ይህን፣ ሀን መከወን ደረሻ አብቅ ቶሃል።" አለው። "እኔ ማንንም አልፈ ወስኩም፣ ፈውስ የሚለግሰው አላህ ብቻ ነው።" አለው ልጁ። ይዞ ይቀ ጣውና ያሰቃየው ጀመር። ወደ መናኙ አመላከተ። "ከእምነትህ ተመለስ።" ተባለ መናኙ። አሻፈረኝ አለ። ንጉሡ መጋዝ እንዲቀርብለት አዘዘ። መጋዙን ከመሃል አናቱ ላይ በማስቀመጥ ከሁ ለት ሰነጠቀው። ከዚያ የንጉሡ ችሎት ባልደረባ እንዲቀርብ ተደረገ። "ከእምነ ትህ ተመለስ።" ተባለ። አሻፈረኝ አለ። መጋዙን ከመሐል አናቱ ላይ በማስቀ መጥ ከሁለት ሰነጠቀው። ከዚያም ልጁ እንዲቀርብ ተደረገ። "ከእምነትህ ተመለስ።" ተባለ። አሻፈረኝ አለ። ንጉሡ ለባለሟሎቹ አስረከበው።እንዲህ ሲልም አዘዛቸው፦ "እንዲህ እንዲህ ወደተባለችው ጋራ ይዛችሁት ሂዱ። ተራራው ላይ አውጡት። ከተራራው ጫፍ ላይ ስትደርሱ (ከእምነቱ ይመ ለስ እንደሆን ጠይቁት)፤ ከተመለሰ መልካም። ያለበለዚያ ግን ከላይ ወደ ታች ወርውሩት።" ወደተባለችው ተራራ

فَصَعِدُوا بِهِ الْجَبَلَ فَقَالَ: اللَّهُمَّ اكْفِنِيهِمْ بِمَا شِئْتَ، فَرَجَفَ بِهِمُ الْجَبَلُ، فَسَقَطُوا وَجَاءَ يَمْشِي إِلَى الْمَلِكِ، فَقَالَ لَهُ الْمَلِكُ: مَا فَعَلَ أَصْحَابُكَ؟ فَقَالَ: كَفَانِيهِمُ اللهُ تَعَالَى، فَدَفَعَهُ إِلَى نَفَرٍ مِنْ أَصْحَابِهِ فَقَالَ: اذْهَبُوا بِهِ فَاحْمِلُوهُ فِي قُرْقُورٍ وَتَوَسَّطُوا بِهِ الْبَحْرَ، فَإِنْ رَجَعَ عَنْ دِينِهِ وَإِلاَّ فَاقْذِفُوهُ، فَذَهَبُوا بِهِ فَقَالَ: اللَّهُمَّ اكْفِنِيهِمْ بِمَا شِئْتَ، فَانْكَفَأَتْ بِهِمُ السَّفِينَةُ فَغَرِقُوا، وَجَاءَ يَمْشِي إِلَى الْمَلِكِ. فَقَالَ لَهُ الْمَلِكُ: مَا فَعَلَ بِأَصْحَابِكَ؟ فَقَالَ: كَفَانِيهِمُ اللهُ تَعَالَى. فَقَالَ لِلْمَلِكِ: إِنَّكَ لَسْتَ بِقَاتِلِي حَتَّى تَفْعَلَ مَا آمُرُكَ بِهِ. قَالَ: مَاهُوَ؟ قَالَ: تَجْمَعُ النَّاسَ فِي صَعِيدٍ وَاحِدٍ، وَتَصْلُبُنِي عَلَى جِذْعٍ، ثُمَّ خُذْ سَهْمًا مِنْ كِنَانَتِي، ثُمَّ ضَعِ السَّهْمَ فِي كَبِدِ الْقَوْسِ ثُمَّ قُلْ: بِسْمِ اللهِ رَبِّ الْغُلاَمِ ثُمَّ ارْمِنِي، فَإِنَّكَ إِذَا فَعَلْتَ ذَلِكَ قَتَلْتَنِي. فَجَمَعَ النَّاسَ فِي صَعِيدٍ وَاحِدٍ، وَصَلَبَهُ عَلَى جِذْعٍ، ثُمَّ أَخَذَ سَهْمًا مِنْ كِنَانَتِهِ، ثُمَّ وَضَعَ السَّهْمَ فِي كَبِدِ الْقَوْسِ، ثُمَّ قَالَ: بِسْمِ

ወሰዱትና ከተራራው ጫፍ ላይ አወጡት።"አላህ ሆይ! በከጀልከው አኳኋን ከነኝህ ሰዎች ግፍ አድነኝ" አለ-ልጁ። ተራራው ተንቀጠቀጠባቸው። የንጉሡ ባለሟሎች ወደቁ። ልጁ ከንጉሡ ዘንድ መጣ። "ባልደረቦችህን ምን አገኛቸው?" ሲል ንጉሡ ጠየቀው። "አላህ ከነርሱ በቃኝ (ከተንኮላቸው አዳነኝ)።" አለው። ለሌሎች ረዳቶቹ አስረከበው። እንዲህ ሲልም አዘዛቸው። "በጀልባ አድርጋችሁ ወደ ባሕሩ እምብርት ውሰዱት። ከእምነቱ ከተመለሰ መል ካም፤ ካልተመለሰ ግን ባሕሩ ውስጥ ጣሉት።" ወሰዱት። "አላህ ሆይ! በከጀልከው አኳኋን ከነኝህ ሰዎች የጣፍ ተግባር አድነኝ።" አለ። ጀልባዋ ተገለበጠችባቸው። የንጉሡ ባለሟሎች ባሕር ውስጥ ሰጠሙ። ልጁ ከንጉሡ ዘንድ ተመልሶ መጣ። "ባልደረቦችህን ምን አገኛቸው?" አለው። "አላህ ከነርሱ (ተንኮል) በቃኝ (አዳነኝ)።" በማለት መለሰ። በመቀጠልም፡- "የማዝህን እስካ ልፈፀምክ ድረስ ልትገድለኝ አትች ልም።" አለው ለንጉሡ። "ምንድን ነው የምታዘዝኝ?" ንጉሡ ጠየቀው። "ሰዎችን በአደባባይ ላይ ትሰበስባለህ። ከአንዲት የተምር ዛፍ ላይ ታንጠለጥለኛለህ። አንድ ጦር ከሰገባዬ ውስጥ ውሰድ። ከቀስቱ ላይ ሰካ። ከዚያም፣ የዚህ ልጅ ጌታ በሆነው አላህ ስም፣ በል፣ ከዚያ ቀስቱን አነጣጥረህ ወርውር። ይህንን ካደረግክ ትገድለኛለህ።" ሰዎችን በአንድ አደባባይ ላይ ሰበሰበ። ከአንዲት የተምር ዛፍ ላይ አንጠለጠለው። ከሠገባው ውስጥ ጦር ወሰደ። ጦሩን ከቀስቱ ደጋን ላይ ሰካ። "የዚህ ልጅ ጌታ

اللهِ رَبِّ الْغُـــلَامِ. ثُمَّ رَمَاهُ فَوَقَعَ السَّهْمُ فِـــي صُـــدْغِه، فَوَضَعَ يَدَهُ فِي صُدْغِه فَمَاتَ. فَقَالَ النَّاسُ: آمَنَّا بِرَبِّ الْغُلَامِ، فَـــأُتِيَ الْمَلِكُ فَقِيلَ لَهُ: أَرَأَيْتَ مَا كُنْتَ تَحْذَرُ قَدْ وَاللهِ نَزَلَ بِكَ حَذَرُكَ. قَدْ آمَنَ الـــنَّاسُ. فَأَمَرَ بِالْأُخْدُودِ بِأَفْوَاهِ السِّكَكِ فَخُدَّتْ وَأُضْرِمَ فِيهَا النِّيرَانُ وَقَالَ: مَنْ لَمْ يَرْجِعْ عَنْ دِينِه فَأَقْحِمُوهُ فِيهَا أَوْ قِيلَ لَـــهُ إِقْتَحِمْ، فَفَعَلُوا حَتَّى جَاءَتِ امْرَأَةٌ وَمَعَهَـــا صَـــبِيٌّ لَهَا، فَتَقَاعَسَتْ أَنْ تَقَعَ فِيهَـــا، فَقَالَ لَهَا الْغُلَامُ: يَا أُمَّاهْ اصْبِرِي فَإِنَّكِ عَلَى الْحَقِّ.)) رَوَاهُ مُسْلِمٌ.

በሆነው አላህ ስም።" በማለት ቀስቱን ወረወረ። ጦሩ ከወጣቱ ጆሮ ግንድ ላይ ተሰካ። ወጣቱ ጆሮ ግንዱን ያዘ። ለሕልፈተ ሕይወትም በቃ። ሰዎች "በዚህ ልጅ ጌታ አምነናል።" አሉ። "ስትፈራው የነበረው ነገር ተከሰተ፤ በአላህ ይሁንብን የሰጋህበት ነገር ተፈጸሚ ሆኗል። ሰዎች አምነዋል።" ተባለ -ንጉሡ። መንገድ ዳር ጉድጓድ እንዲቆፍሩ ባለሟሎቹን አዘዘ -ንጉሡ። ጉድጓዶቹ ተቆፈሩ። እሳት እንዲቀጣጠል ልባቸውም ተደረገ። "ከእምነቱ የማይ መለሰን ከነኝህ ጉድጓዶች ውስጥ ማግዱት።" የሚል ትእዛዝ ንጉሡ አስተላለፈ። ባለሟሎቹ የታዘዙትን በመፈፀም ላይ እያሉ አንዲት ሕጻን ልጅ የያዘች ሴት መጣች። ለመግገድ አልደፈረችም፤ ፈራች። ልጁ እንዲህ አላት:- "እናቴ ሆይ! ትዕግስት (ሶብር) ይኑርሽ፤ አንች በሐቅ ላይ ነሽ።"

(ሙስሊም እንደዘገቡት)

ከሐዲሱ የምንማራቸው ቁምነገሮች

- የአላህ ወዳጆች (ወልዮች) ተአምራት (ከራማ) እንዳላቸው።
- በጦርነትና ሌሎችም ወቅቶች ነፍስን ከጥፋት ለማዳን መዋሸት እንደሚፈቀድ።
- ሙእሚን በእውነተኛ እምነቱና በሐቅ ጉዳና ላይ በመጽናቱ እያሌ ፈተናዎች ይደርሱብታል።
- በአላህ መንገድ የሚደረግ ደዕዋና ለሐቅ የበላይነት የሚፈፀም ትግል ከፍተኛ መስዋእትነትን ይጠይቃል።
- አላህ ሐቅን የበላይ ያደርጋል። የሐቅ ቤተሰቦችንም ይረዳል። ሐሰትን ያንኮታኩታል። የሐሰት ጠበቆችንም ለውርደት ያበቃል።
- ይህ ሐዲስ የቁርአንን ተአምር ያሳያል። ባለፉት ዘመናት ስለተፈፀሙ ክስተቶች መዘገቡን። "አል-ቡሩጅ" የተሰኘው የቁርአን ምዕራፍ የሚያሳየው ይህንኑ ታሪክ መሆኑ ተመልክቷል።
- ያለፉ ሕዝቦች ታሪክ ውድቀትና ስኬታቸውን እያወሱ ማስተማር እጅግ ጠቃሚ ነው። በማስተማር ሂደት ላይ ጥሩ ሚና ይጫወታል።

٣١- وَعَنْ أَنَسٍ ﷺ قَالَ: مَرَّ النَّبِيُّ ﷺ بِامْرَأَةٍ تَبْكِي عِنْدَ قَبْرٍ فَقَالَ: ((اتَّقِي اللهَ وَاصْبِرِي)) فَقَالَتْ: إِلَيْكَ عَنِّي؛ فَإِنَّكَ لَمْ تُصَبْ بِمُصِيبَتِي! وَلَمْ تَعْرِفْهُ، فَقِيلَ لَهَا: إِنَّهُ النَّبِيُّ ﷺ، فَأَتَتْ بَابَ النَّبِيِّ ﷺ، فَلَمْ تَجِدْ عِنْدَهُ بَوَّابِينَ. فَقَالَتْ: لَمْ أَعْرِفْكَ، فَقَالَ: ((إِنَّمَا الصَّبْرُ عِنْدَ الصَّدْمَةِ الأُولَى)) مُتَّفَقٌ عَلَيْهِ.

وَفِي رِوَايَةٍ لِمُسْلِمٍ: تَبْكِي عَلَى صَبِيٍّ لَهَا.

31- አነስ (ረ.ወ) እንዳስተላለፉት:- ነቢዩ (ሶ.ዐ.ወ) ከአንድ መቃብር ዘንድ በምታ ለቅስ ሴት አጠገብ አለፉ። "አላህን ፍሪ ትዕግስት ይኑርሽ" አሏት። "ዘወር በልልኝ እኔን የገጠመኝ መከራ አንተን አል ገጠመህም።" አለች። አላወቀቻቸውም ነበር። ነቢዩ (ሶ.ዐ.ወ) መሆናቸው ተነገራት። ከነቢዩ (ሶ.ዐ.ወ) በራፍ መጣች። በር ጠባቂ ዘበኞችን አላገኘችም። "አላወቅኩዎትም ነበር።" አለቻቸው ነቢዩ (ሶ.ዐ.ወ)፦ "ትዕግስት (ሶብር) የሃዘን በትር ባረፈበት ቅጽበት ላይ ነው።" አሏት።

(ቡኻሪና ሙስሊም)

በሌላ ዘገባ ላይ ደግሞ:-

"ለሞተባት ሕጻን ልጅዋ በማልቀስ ላይ እያለች" የሚል ተወስቷል።

ከሐዲሱ የምንማራቸው ቁምነገሮች

- ትዕግስት አልበኝነት ከፈሪሀ አላህነት ይቃረናል።
- ጽድቅ ሊቸረው የሚገባ ትዕግስት የመከራ በትር ባረፈበት ቅጽበት የተከሠተ እንጅ ነገሮች መረሳት በጀመሩበት ወቅት የሚከሰት አይደለም።
- ነቢዩ (ሶ.ዐ.ወ) ለአላዋቂዎች የነበራቸው እገዛነትና ትህትና።
- ሴቶች ቀብርን መጐብኘት ይፈቀድላቸዋል። ከልክል ቢሆን ኖሮ ነቢዩ (ሶ.ዐ.ወ) ይህችን ሴት ይከለክሉ ነበር።

٣٢- وعَنْ أَبِي هُرَيْرَةَ ﷺ أَنَّ رَسُولَ اللهِ ﷺ قَالَ: ((يَقُولُ اللهُ تَعَالَى: مَا لِعَبْدِي الْمُؤْمِنِ جَزَاءٌ إِذَا قَبَضْتُ صَفِيَّهُ مِنْ أَهْلِ الدُّنْيَا ثُمَّ احْتَسَبَهُ إِلاَّ الْجَنَّةَ.)) رَوَاهُ الْبُخَارِيُّ.

32- አቡ ሁረይራ (ረ.ወ) እንዳስተላለፉት የአላህ መልዕክተኛ (ሶ.ዐ.ወ) እንዲህ ሲሉ ተናግረዋል:- "አላህ:- "ዱንያ ውስጥ ካሉ ሰዎች መካከል ወዳጁን ወስጀበት ከኔ ዘንድ ምንዳን በመፈለግ (ትዕግስት ላደረገ) ሙእሚን ባሪያዬ የምሰጠው ሽልማት ጀንነት እንጅ ሌላ አይደለም።" ይላል።" (ቡኻሪ እንደዘገቡት)

ከሐዲሱ የምንማራቸው ቁምነገሮች

- የሰው ልጅ ከሚደርስበት መከራ ሁሉ የከፋው ወዳጅን ማጣት ነው።
- "ካፊር" የሉን ያህል መልካም ተግባራትን ቢያከናውን ኢማን ከሌለው ከአላህ ዘንድ ሥራው ዋጋ አይኖረውም።

33- ዓኢሻ (ረ.ዐ) እንዳስተላለፉት:- እርሳቸው የአላህን መልዕክተኛ (ሶ.ዐ.ወ) ስለ ወረርሽኝ ጠየቋቸው። አላህ በሻው ሰው ላይ የሚያደርሰው ቅጣት እንደነበርና ለሙእሚኖች ግን እዝነት (ረሕመት) እንዳደረገላቸው አሜወቷት። እንዲህም አሏት:- "አንድ ሙእሚን ወረርሽኝ አግኝቶት ትዕግስት አድርጉና የአላህን ምንዳ በመጠባበቅ አላህ ከጻፈበት ውጭ ምንም ነገር እንደማያገኘው ተገንዝቦ ከሀገሩ ሳይወጣ ከተቀመጠ፥ የመቱ ሰማዕታት (ሸሂዶች) ምንዳ ይሰጠዋል።" (ቡኻሪ እንደዘገቡት)

٣٣- وَعَنْ عَائِشَةَ رضى الله عنها أَنَّهَا سَأَلَتْ رَسُولَ اللهِ ﷺ عَنِ الطَّاعُونِ، فَأَخْبَرَهَا أَنَّهُ كَانَ عَذَابًا يَبْعَثُهُ اللهُ تَعَالَى عَلَى مَنْ يَشَاءُ، فَجَعَلَهُ اللهُ تَعَالَى رَحْمَةً لِلْمُؤْمِنِينَ، فَلَيْسَ مِنْ عَبْدٍ يَقَعُ فِي الطَّاعُونِ فَيَمْكُثُ فِي بَلَدِهِ صَابِرًا مُحْتَسِبًا، يَعْلَمُ أَنَّهُ لَا يُصِيبُهُ إِلَّا مَا كَتَبَ اللهُ لَهُ إِلَّا كَانَ لَهُ مِثْلُ أَجْرِ الشَّهِيدِ)) رَوَاهُ الْبُخَارِيُّ.

ከሐዲሱ የምንማራቸው ቁምነገሮች

- ኢብን ዐላን እንዳሉት:- "የአንድ ሙእሚን ዓላማ የአላህን ምንዳ ማግኘት፥ ቃል የገባውን ፀጋ መጐናፀፍ ከሆነና ወረርሽኝ ያገኘው በአላህ ፍላጐት፥ ወረርሽኝ ቢያስወግድለትም በርሱው ፍቃድና ፕሳን መሆኑን ከተገነዘበ፥ እንዲሁም ባገኘው መከራና ስቃይ ሳይበሳጭ በጤንነትም ሆነ በህመም ወቅት ወደ አላህ ከተጠጋ የሰማእት ምንዳን ያገኛል።"
- ወረርሽኝም ሆነ ሌላ ዓይነት በሽታ አግኝቶት ትዕግስት ያደረገ ከቀብር ጠያቂዎች ነጻ ይሆናል።
- አንድ ሰው ወረርሽኝ ከተከሠተበት ሀገር ውስጥ ከሆነ ወደ ሌላ ሀገር መውጣት የለበትም -ሌሎችንም አካባቢዎች እንዳይበክል።
- የሰማዕትነት ምንም በአላህ መንገድ ሲታገል የሞተን ብቻ አይደለም የሚመለከተው፥ ሌሎች ክፍሎችንም ያጠቃልላል።

34- የአላህ መልዕክተኛ (ሶ.ዐ.ወ) ተከታዩን ሲናገሩ አድምጫለሁ በማለት አነስ (ረ.ዐ) አስተላልፈዋል:- "አላህ:- "ባሪያዬን በሁለት ወዳጆች ፈተና አድርሽበት ትዕግስት ካደረገ የምሰጠው ለውጥ (ምትክ) ጀንነትን ነው።" ብሏል።" "ሁለት ወዳጆች" የሚለው ቃል የሚያመለክተው ሁለቱን ዓይኖቹን ነው።
(ቡኻሪ እንደዘገቡት)

٣٤- وَعَنْ أَنَسٍ ﷺ قَالَ: سَمِعْتُ رَسُولَ اللهِ ﷺ يَقُولُ: ((إِنَّ اللهَ عَزَّ وَجَلَّ قَالَ: إِذَا ابْتَلَيْتُ عَبْدِي بِحَبِيبَتَيْهِ فَصَبَرَ عَوَّضْتُهُ مِنْهُمَا الْجَنَّةَ يُرِيدُ عَيْنَيْهِ)) رَوَاهُ الْبُخَارِيُّ.

ከሐዲሱ የምንማራቸው ቁምነገሮች

- ነቢዩ (ሶ.ዐ.ወ) በዚህ ሐዲሳቸው ዓይኖችን ብቻ ለይተው የተናገሩት ከሰው ልጅ የአካል ክፍሉች መካከል እጅግ ውድ ዋጋ ያላቸው እነርሱ በመሆናቸው ነው።
- ጀንነት ታላቅ ለውጥ (ምትክ) ነው። ከዚህች ዓለም ላይ ለዘልዓለም እንጠቀምም። ጀንነት ግን ዘልዓለማዊ ናት።

٣٥- وَعَنْ عَطَاءِ بْنِ أَبِي رَبَاحٍ قَالَ: قَالَ لِي ابْنُ عَبَّاسٍ ﷺ: أَلاَ أُرِيكَ امْرَأَةً مِنْ أَهْلِ الْجَنَّةِ؟ فَقُلْتُ: بَلَى، فَقَالَ: هَذِهِ الْمَرْأَةُ السَّوْدَاءُ أَتَتِ النَّبِيَّ ﷺ فَقَالَتْ: إِنِّي أُصْرَعُ، وَإِنِّي أَتَكَشَّفُ فَادْعُ اللهَ تَعَالَى لِي قَالَ: ((وَإِنْ شِئْتِ صَبَرْتِ وَلَكِ الْجَنَّةُ، وَإِنْ شِئْتِ دَعَوْتُ اللهَ تَعَالَى أَنْ يُعَافِيَكِ)) فَقَالَتْ: أَصْبِرُ. فَقَالَتْ: إِنِّي أَتَكَشَّفُ، فَادْعُ اللهَ أَنْ لاَ أَتَكَشَّفَ، فَدَعَا لَهَا. مُتَّفَقٌ عَلَيْهِ.

35- ዐጧእ ኢብን አቢ ረባሕ (ረ.ዐ) እንዲህ ሲሉ አስተላልፈዋል፦ ኢብን ዐብባስ (ረ.ዐ) "ከጀንነት ሰዎች አንዷን ላመላክትን?" አሉኝ። "አዎ!" አልኳቸው። "ይህች ጥቁር ሴት ናት። ከነቢዩ (ሶ.ዐ.ወ) ዘንድ በመምጣት፥ "እኔ አውድቅ በሽታ አለብኝ፣ (ህመሙ ሲነሳብኝ) እራቆታ ለሁ። (ከበሽታዬ እፈወስ ዘንድ) አላህን ይማፀኑልኝ።" በማለት ነቢዩን (ሶ.ዐ.ወ) ጠየቀች። "ከፈለግሽ ትዕግስት (ሶብር) አድርጊና ጀንነት ይሰጥሻል። ከፈለግሽ ደግሞ ይፈውስሽ ዘንድ አላህን እለም ንልሻለሁ።" አሏት። "ትዕግስት አደርጋ ለሁ።" አለች፣ ከዚያም፦ "ስለምራቆት እንዳልራቆት አላህን ይማፀኑልኝ።" ስትል ጠየቀች። ዱዓ አደረጉላት።"

(ቡኻሪና ሙስሊም)

ከሐዲሱ የምንማራቸው ቁምነገሮች

- ዱንያ ውስጥ ለሚደርስ ስቃይና መከራ ትዕግስት (ሶብር) ማድረግ ጀንነትን ለመጐናፀፍ ያበቃል።
- አላህን በመማፀን በሽታን ማስወገድ ህክምና ከማድረግ ጋራ ተገቢ ነው።
- አቅመና ችሎታው እስካለ ድረስ ልዩ ፈቃዶችን (ሩኽሲ) ከመጠቀም ይልቅ ራስን የላቀ ምንዳ ከሚያስገኙ ጠበቅ ያሉ ሕግጋት (ዐዚመህ) ጋር ማላመዱ በላጭነት አለው።

٣٦- وَعَنْ أَبِي عَبْدِ الرَّحْمَنِ عَبْدِ اللهِ بْنِ مَسْعُودٍ ﷺ قَالَ: كَأَنِّي أَنْظُرُ إِلَى

36- አቡ ዐብዱረህማን ኢብን መስዑድ (ረ.ዐ) እንዲህ ሲሉ አስተላልፈዋል፦ ከነቢያት (ሶ.ዐ.ወ) መካከል ሕዝቦች ደብድበውት

رَسُـــلِ اللهِ ﷺ يَحْكِي نَبِيًّا، مِنَ الأَنْبِيَاءِ صَـــلَوَاتُ الـــلّٰهِ وَسَلاَمُهُ عَلَيْهِمْ، ضَرَبَهُ قَوْمُـــهُ فَـــأَدْمَوْهُ، وَهُوَ يَمْسَحُ الدَّمَ عَنْ وَجْهِـــهِ، يَقُولُ: ((اللّٰهُمَّ اغْفِرْ لِقَوْمِي فَإِنَّهُمْ لاَيَعْلَمُونَ.)) مُتَّفَقٌ عَلَيْهِ.

አድምተውት፥ ደሙን ከፊቱ ላይ እየ ጠረገ፡-"አላህ ሆይ! ለሕዝቦቼ ምሕረት አውርድ፣ እነርሱ አያውቁምና።" በማ ለት አላህን ይማፀን ስለነበር አንድ ነቢይ የአላህ መልዕክተኛ (ሶ.ዐ.ወ) የተረኩበት አኳኋን ዘወትር ከዓይኔ አይጠፋም። (ቡኻሪና ሙስሊም)

ከሐዲሱ የምንማራቸው ቁምነገሮች

- የነቢያት (ሶ.ዐ.ወ) ትዕግስትና ደዕዋቸውን ለሰዎች በማድረሱ ሂደት ላይ ይደርስባቸው የነበረው ስቃይና ፈተና።
- አላዋቂነትን በትዕግስትና በይቅር ባይነት ማስተናገድ ከነቢያት መልካም ሥነ-ምግባራት አንዱ ነው።
- ለአላዋቂዎች እኩይ ተግባር ተመሳሳይ ምላሽ አለመስጠት።
- የነቢዩን (ሶ.ዐ.ወ) የመልካም ሥነ-ምግባር አርአያነት መከተል። የኡሑድ ዕለት ግንባራቸውን ተመቱ። ደማቸው በፊታቸው ላይ ተንዠቀዠቀ። "አላህ ሆይ! ለሕዝቦቼ ምሕረት አውርድ፣ እነርሱ አያውቁምና።" ከማለት ውጭ ሌላ ያከሉት አልነበረም።

٣٧- وَعَنْ أَبِي سَعِيدٍ وَأَبِي هُرَيْرَةَ ﷺ عَنِ النَّبِيِّ ﷺ قَالَ: ((مَا يُصِيبُ الْمُسْلِمَ مِـــنْ نَصَـــبٍ وَلاَ وَصَبٍ وَلاَ هَمٍّ وَلاَ حَزَنٍ وَلاَ أَذًى وَلاَ غَمٍّ، حَتَّى الشَّوْكَةُ يُشَاكُهَا إِلاَّ كَفَّرَ اللهُ بِهَا مِنْ خَطَايَاهُ)) مُتَّفَقٌ عَلَيْهِ.

37- አቡ ሁረይራ (ረ.ዐ) እንዳስተላለፉት ነቢዩ (ሶ.ዐ.ወ) እንዲህ ብለዋል፡- "አንድን ሙስሊም አንድም ችግር ወይም በሽታ፥ ሐሳብ ወይም ቁጭት፥ የሚያውክ ነገር ወይም ሞንቀት አያገኘውም -በምትወጋው እሾህ እንኳ- አላህ በርሷ (ሰበብ) ወንጀሉትን ያበሰለት ቢሆን እንጅ!"
(ቡኻሪና ሙስሊም)

ከሐዲሱ የምንማራቸው ቁምነገሮች

- በሽታዎችና ሌሎችም ሙስሊምን የሚገጥሙት አዋኪ ነገሮች ወንጀሉን ያራግፉለታል።
- እውነተኛ ችግር የደረሰበት ሰው ማለት ምንዳን ያልተቸረ ሰው ነው።

٣٨- وَعَـــنْ ابْـــنِ مَسْعُودٍ ﷺ قَالَ: دَخَـــلْتُ عَـــلَى النَّبِيِّ ﷺ وَهُوَ يُوعَكُ فَقُلْتُ: يَارَسُولَ اللهِ إِنَّكَ لَتُوعَكُ وَعْكًا

38- ኢብን መስዑድ (ረ.ዐ) እንዲህ ሲሉ አስተላልፈዋል፡- ከነቢዩ (ሶ.ዐ.ወ) ዘንድ ገባሁ፣ አሟቸው ልጠይቃቸው። "የአላህ መልዕክተኛ ሆይ! ከፍተኛ

شَدِيدًا. قَالَ: ((أَجَلْ إِنِّي أُوعَكُ كَمَا يُوعَكُ رَجُلاَنِ مِنكُمْ)) قُلْتُ: ذَلِكَ أَنَّ لَكَ أَجْرَيْنِ؟ قَالَ: ((أَجَلْ ذَلِكَ كَذَلِكَ مَا مِنْ مُسْلِمٍ يُصِيبُهُ أَذًى، شَوْكَةٌ فَمَا فَوْقَهَا إِلاَّ كَفَّرَ اللهُ بِهَا سَيِّئَاتِهِ، وَحُطَّتْ عَنْهُ ذُنُوبُهُ كَمَا تَحُطُّ الشَّجَرَةُ وَرَقَهَا)) مُتَّفَقٌ عَلَيْهِ.

የህመም ስሜት ይሰማዎታል?" አል ኪቸው። "አዎ! ከናንተ ሁለት ሰዎች የሚሰማቸውን ያክል የህመም ስሜት ይሰማኛል።" አሉ። "ይህ ማለት እርስዎ እጥፍ ምንዳ ያገኛሉ ማለት ይሆን?" በማለት ጠየቅኪቸው። "አዎ! ነገሩ እንዲያ ነው። እሾህም ትሁን ከዚያ በላይ የሆነ አዋኪ ነገር የሚያገኘው አንድም ሙስሊም የለም፥ አላህ በርሷ (ስበብ) ወንጀሉን ያበስለት፣ ከዛፍ ላይ ቅጠል እንደሚረግፍ ሁሉ ኃጢአቱ የተራገፈለት ቢሆን እንጅ።" በማለት ተናገሩ። (ቡኻሪና ሙስሊም)

ከሐዲሱ የምንማራቸው ቁምነገሮች

- አንዳች ችግር በሚያጋጥም ወቅት ትዕግስት ከታከለበት ምንዳ እንደሚያስገኝ።
- ከሰው ሁሉ ይበልጥ ፈተናና ችግር የሚደርስባቸው ነቢያት ናቸው። ምክንያቱም እነርሱ ከማንም የላቀ የትዕግስት ችሎታና ፅናት አላቸውና። አላህም ለሰው ዘር አርአያ አድርጓቸዋል።

٣٩- وَعَنْ أَبِي هُرَيْرَةَ ﷺ قَالَ: قَالَ رَسُولُ اللهِ ﷺ: ((مَنْ يُرِدِ اللهُ بِهِ خَيْرًا يُصِبْ مِنْهُ)) رَوَاهُ الْبُخَارِيُّ.

39- አቡ ሁረይራ (ረ.ዐ) እንዳስተላለፉት የአላህ መልዕክተኛ (ሶ.ዐ.ወ) እንዲህ ሲሉ ተናግረዋል:- "አላህ ኸይር የሻለትን ሰው በአንዳች ችግር ይፈትነዋል።" (ቡኻሪ እንደዘገቡት)

ከሐዲሱ የምንማራቸው ቁምነገሮች

- ሙእሚን ፈተና፥ ችግርና መከራ አያጣውም። የሚያጋጥሙት ፈተናዎች ሁሉ ኸይር የሆኑለት ሰበብ በዚህች ዓለም ወደ አላህ ይበልጥ እንዲቃረብ ስለሚያደርጉትና ለመጭው ዓለም ደግሞ ወንጀሉ እንዲታበስለት ሰበብ ስለሚኑ ነው።

٤٠- وَعَنْ أَنَسٍ ﷺ قَالَ: قَالَ رَسُولُ اللهِ ﷺ: ((لاَ يَتَمَنَّيَنَّ أَحَدُكُمُ الْمَوْتَ لِضُرٍّ أَصَابَهُ، فَإِنْ كَانَ لاَبُدَّ فَاعِلاً فَلْيَقُلِ: اللَّهُمَّ أَحْيِنِي مَا كَانَتِ الْحَيَاةُ

40- አነስ (ረ.ዐ) እንዳስተላለፉት የአላህ መልዕክተኛ (ሶ.ዐ.ወ) እንዲህ ብለዋል:- "ከናንተ አንዳችሁ ባገኘው ጉዳት ሳቢያ ሞትን አይመኝ። መመኘቱ ከልቀረ

ደግሞ፦ "አላህ ሆይ! ሕይወት ለኔ ኸይር ከሆነችልኝ በሕይወት አቆየኝ፣ ሞቴ የተሻለ ከሆነ ደግሞ ሞትን ለግሠኝ።" ይበል።"

(ቡኻሪና መስሊም)

خَيْرًا لِي وَتَوَفَّنِي إِذَا كَانَتِ الْوَفَاةُ خَيْرًا لِي)) مُتَّفَقٌ عَلَيْهِ.

ከሐዲሱ የምንማራቸው ቁምነገሮች

- በሕይወት መቆየትን ወይም ሊሕልፈት መብቃትን በተመለከተ ምርጫውን ለአላህ መተው ተገቢ ነው።
- ከአላህ ጋር ለመገናኘት፣ በአላህ መንገድ ሲዋጉ ለመሞት ወይም ከተላቀ ሀገር ለመቀበር ባለ ጉጉት፣ እንዲሁም በዲን ላይ ችግር እንዳይደርስበት ሞትን መመኘት የተጠላ አይደለም።

41- አቡ ዐብደላህ ኸባብ ኢብን አል-አረት (ረ.ዐ) እንዲህ ሲሉ አስተላልፈዋል፦ የአላህ መልዕክተኛ (ሶ.ዐ.ወ) ከከዕባ ጥላ ሥር ብቻቸውን ተንተርሰው ሳሉ፦ "ከአላህ ዘንድ ድልን አይለምኑልንም? ዱዓስ አያደርጉልንም?" በማለት ስሞታ አቀረብንላቸው። "ከናንተ በፊት በነበረው ዘመን ሰውየው ይያዝና ጉድጓድ ተቆፍሮ ከውስጡ እንዲገባ ይደረጋል። መጋዝ ይቀርብና ከራሱ ላይ ተደርጉ ከሁለት ይሰነጠቃል። ሥጋውን ዘልቆ አጥንቱ ድረስ በሚገባ የብረት ሚደ ይላጋል። ይህ ሁኔታ ከዲኑ አያስተጓጉሉትም። በአላህ ይሁንብኝ! አላህ ይህን ጉዳይ ይሞላዋል፣ አንድ ተጓዥ ከሰንዓ እስከ ሐድረመውት ከአላህ ውጭ ምንንም የማይፈራ ሆኖ መጓዝ እስኪችል ድረስ። (ሌላው ቀርቶ) ተኩላ ፍየሉችን ይተናኮልብኛል የሚል ስጋት ሳያድርበት። ግና እናንተ ትቸኩላላችሁ።"

(ቡኻሪ እንደዘገቡት)

٤١- وَعَنْ أَبِي عَبْدِ اللهِ خَبَّابِ بْنِ الأَرَتِّ ﷺ قَالَ: شَكَوْنَا إِلَى رَسُولِ اللهِ ﷺ وَهُوَ مُتَوَسِّدٌ بُرْدَةً لَهُ فِي ظِلِّ الْكَعْبَةِ، فَقُلْنَا: أَلاَ تَسْتَنْصِرُ لَنَا أَلاَ تَدْعُو لَنَا؟ فَقَالَ: ((قَدْ كَانَ مَنْ قَبْلَكُمْ يُؤْخَذُ الرَّجُلُ فَيُحْفَرُ لَهُ فِي الأَرْضِ فَيُجْعَلُ فِيهَا، ثُمَّ يُؤْتَى بِالْمِنْشَارِ فَيُوضَعُ عَلَى رَأْسِهِ فَيُجْعَلُ نِصْفَيْنِ، وَيُمْشَطُ بِأَمْشَاطِ الْحَدِيدِ مَادُونَ لَحْمِهِ وَعَظْمِهِ، مَايَصُدُّهُ ذَلِكَ عَنْ دِينِهِ، وَاللهِ لَيُتِمَّنَّ اللهُ هَذَا الأَمْرَ حَتَّى يَسِيرَ الرَّاكِبُ مِنْ صَنْعَاءَ إِلَى حَضْرَمَوْتَ لاَيَخَافُ إِلاَّ اللهَ وَالذِّئْبَ عَلَى غَنَمِهِ، وَلَكِنَّكُمْ تَسْتَعْجِلُونَ)) رَوَاهُ الْبُخَارِيُّ.

በሌላ ዘገባ ደግሞ፦

"ኩታቸውን ተንተርሰው...፤ ከአጋ ሪዎች አያሌ ፈተናዎች ደርሶብናል።" የሚል ተወስቷል።

وَفِي رِوَايَةٍ: ((وَهُوَ مُتَوَسِّدٌ بُرْدَةً وَقَدْ لَقِينَا مِنَ الْمُشْرِكِينَ شِدَّةً.))

ከሐዲሱ የምንማራቸው ቁምነገሮች

- ለዲን ሲባል ስቃይና መከራን መሸከም የሚወደስ መሆኑ።
- ነቢዩ በዚህና በሌሎች አያሌ ሐዲሶቻቸው ስለ ኢስላም መስፋፋትና ሰላም ስለመስፈኑ የተነበዩት እውን ሆኖ መገኘቱ እውነተኛ የአላህ መልዕክተኛ መሆናቸውን ያሳያል።
- የነቢዩ (ሶ.ዐ.ወ) ባልደረቦች ለኢስላም ሲሉ መከራንና ስቃይን በትዕግስትና በፅናት ተቋቁመዋል። እዚህ ሐዲስ ላይ እንደተወሳው ለነቢዩ (ሶ.ዐ.ወ) ስሞታ ማሰማታቸው ከምሬት ተነሳስተው አይደለም። ይልቁንም ሰላም ቢሰፍን ሙሉ በሙሉ ትኩረታቸውን አላህን ወደ ማምለክ ለማዞርና ወደ በለጠ የምሉዕነት ምጥቀት ለመሸጋገር ካላቸው ከፍተኛ ጉጉት የተነሳ ነው።
- የታላላቅና ደጋግ ሰዎችን አርአያነት መከተል ተገቢ ነው። በዲን ሰበብ የሚደርስባቸውን አያሌ ፈተናዎች በትዕግስትና በፅናት ተቋቁመዋል።
- በዲን ሰበብ ፈተና መድረሱ አይቀሬ ነው። ሙእሚኖች በየትኛውም ቦታና ጊዜ ፈተናዎችን በትዕግስት ለማስተናገድ መጣር ይኖርባቸዋል።
- ኢስላም የሰላም እምነት ነው።

٤٢- وَعَنْ ابْنِ مَسْعُودٍ ﷺ قَالَ: لَمَّا كَانَ يَوْمُ حُنَيْنٍ آثَرَ رَسُولُ اللهِ ﷺ نَاسًا فِي الْقِسْمَةِ، فَأَعْطَى الأَقْرَعَ بْنَ حَابِسٍ مِائَةً مِنَ الإِبِلِ، وَأَعْطَى عُيَيْنَةَ بْنَ حِصْنٍ مِثْلَ ذَلِكَ، وَأَعْطَى نَاسًا مِنْ أَشْرَافِ الْعَرَبِ وَآثَرَهُمْ يَوْمَئِذٍ فِي الْقِسْمَةِ. فَقَالَ رَجُلٌ: وَاللهِ إِنَّ هَذِهِ قِسْمَةٌ مَا عُدِلَ فِيهَا، وَمَا أُرِيدَ فِيهَا وَجْهُ اللهِ، فَقُلْتُ: واللهِ لأُخْبِرَنَّ رَسُولَ اللهِ ﷺ، فَأَتَيْتُهُ فَأَخْبَرْتُهُ بِمَا قَالَ، فَتَغَيَّرَ وَجْهُهُ حَتَّى كَانَ كَالصَّرْفِ. ثُمَّ قَالَ: ((فَمَنْ يَعْدِلُ إِذَا

42- ኢብን መስዑድ (ረ.ዐ) እንዳስተላለፉት፦ የሑነይን ዘመቻ ዕለት ነበር። የአላህ መልዕክተኛ (ሶ.ዐ.ወ) በምርኮ አከፋፈል ላይ ለተወሰኑ ሰዎች ከሌሎች ብልጫ ያለው ድርሻ ሰጡ። ለአቅረዕ ኢብን ሐቢብ መቶ ግመሎችን ለገሡ። ለሉዐይነህ ኢብን ሐሰንም እንዲሁ። ከዐረብ ታላላቅ ሰዎች ለተወሰኑትም ድርሻቸውን ሰጡ። በጊዜው ከሌሎች ብልጫ ያለው ድርሻ ነበር የሰጧቸው። "በእውነቱ ይህ ክፍፍል ፍትህ የጐደለውና የአላህ ውዴታ ያልተከጀለበት ክፍፍል ነው።" ሲል አንድ ሰው ተና ገረ። "በአላህ ይሁንብኝ ይህንን ቃልህን ለአላህ መልዕክተኛ (ሶ.ዐ.ወ) እነግራቸ ዋለሁ።" አልኩት። ከርሳቸው ዘንድ በመ ቅረብ ያለውን ነገርኳቸው። ፊታቸው

لَـمْ يَعْـدِلِ اللهُ وَرَسُولُهُ؟)) ثُمَّ قَالَ: ((يَـرْحَمُ اللهُ مُوسَى قَدْ أُوذِيَ بِأَكْثَرَ مِـنْ هَذَا فَصَبَرَ.)) فَقُلْتُ: لَأَحْرَمَ لَا أَرْفَعُ إِلَيْهِ بَعْدَهَا حَدِيثًا. مُتَّفَقٌ عَلَيْهِ.

ተለዋወጠ። ፍም መሰለ። "አላህና መልዕክተኛው ፍትሃዊ ካልሆኑ ማን ነው ፍትሃዊ ሊሆን የሚችለው?" ካሉ በኋላ፥ "ለሙሳ አላህ ይዘንለት። ከዚህ ይበልጥ መከራ ደርሶበት በትዕግስት አሳልፎታል።" አሉ። "ከእንግዲህ እንዲህ ዓይነቱን ወሬ አላደርስላቸውም።" አልኩ። (ቡኻሪና ሙስሊም)

ከሐዲሱ የምንማራቸው ቁምነገሮች

- ለአላህ፣ ለመልዕክተኛውና ለሙእሚኖች ታማኝ ሆኖ መገኘት።
- ምግባረ ብልሹነትንና ጥፋትን በይቅርታ ማለፍ የነቢያት ባሕሪ ነው።
- መልዕክተኛው (ሶ.ዐ.ወ) የሰዎችን ልቦናዎች ለማዋሃድና ለማጣጣም ይጠቀሙበት የነበረውን ጥበብ የተሞላበት ስልትና ትዕግስታቸውን ይህ ዘገባ በጉልህ ያሳያል።
- መልዕክተኛው (ሶ.ዐ.ወ) የነቢያት ወንድሞቻቸው አርአያነት መከተላቸው።
- መልዕክተኛው (ሶ.ዐ.ወ) ሰው እንደመሆናቸው ለሰዎች የሚሰማቸው የደስታ፥ የሀዘን ወዘተ ስሜቶች ይሰሟቸዋል።

٤٣- وَعَنْ أَنَسٍ ﷺ قَالَ: قَالَ رَسُولُ اللهِ ﷺ ((إِذَا أَرَادَ اللهُ بِعَـبْدِهِ خَيْـرًا عَجَّلَ لَهُ الْعُقُوبَةَ فِي الدُّنْيَا، وَإِذَا أَرَادَ اللهُ بِعَبْدِهِ الشَّرَّ أَمْسَكَ عَنْهُ بِذَنْبِهِ حَتَّى يُوَافِيَ بِهِ يَوْمَ الْقِيَامَةِ)) وَقَالَ النَّبِيُّ ﷺ: ((إِنَّ عِظَمَ الْجَزَاءِ مَعَ عِظَمِ الْبَلَاءِ وَإِنَّ اللهَ تَعَالَى إِذَا أَحَبَّ قَوْمًا ابْتَلَاهُمْ فَمَنْ رَضِـيَ فَلَهُ الرِّضَى، وَمَنْ سَخِطَ فَلَهُ السُّخْطُ)) رَوَاهُ التِّرْمِذِيُّ وَقَالَ حَدِيثٌ حَسَنٌ.

43- አነስ (ረ.ዐ) እንዳስተላለፉት የአላህ መልዕክተኛ (ሶ.ዐ.ወ) እንዲህ ብለዋል፦"አላህ ለባሪያው ደግን ነገር ሲያፀድቅለት ቅጣቱን በዚህች ዓለም ላይ ያደርግለታል። ለባሪያው መጥፎ ነገር ካፀደቀበት ደግሞ ኃጢአቱን ሁሉ በመያዝ ቅጣቱን እስከ ቂያማ ዕለት ያዘገይበታል።" እንዲህም ብለዋል፦ "ታላቅ ምንዳ ከታላቅ ፈተና ጋር ነው። አላህ ሰዎችን የወደዳቸው ጊዜ ይፈትናቸዋል። የረካ የአላህን እርካታ ይጐናፀፋል። የተበሳጨ የአላህን ቁጣ ያተርፋል።" (ቲርመዚይ ዘግቦታል፣ ሐዲሱ "ሐሰን" ነውም ብለዋል)

ከሐዲሱ የምንማራቸው ቁምነገሮች

- ሰዎች በእምነታቸው ልክ ነው ፈተናዎች የሚደርሱባቸው።
- መከራ ወይም በሽታዎች በሚደርሱበት ወቅት በትዕግስት ማሳለፍ ኃጢአትን ያራግፋል።

- አላህ ባሪያውን መሞኩሩ የማፍቀሩ ምልክት ነው።
- ሙእሚን ፈተናዎች ሲደርሱበት ተስፋ አለመቁረጥ፣ አለመበሳጨትና በትዕግስት ለመቋቋም መሞከር ይኖርበታል።
- የመከራ ጊዜ ትዕግስት ማድረግ ወንጀል የመማሩ ምልክት ነው።

٤٤- وَعَنْ أَنَسٍ ﷺ قَالَ: كَانَ ابْنٌ لأَبِي طَلْحَةَ ﷺ يَشْتَكِي، فَخَرَجَ أَبُو طَلْحَةَ، فَقُبِضَ الصَّبِيُّ، فَلَمَّا رَجَعَ أَبُو طَلْحَةَ قَالَ: مَا فَعَلَ إِبْنِي؟ قَالَتْ أُمُّ سُلَيْمٍ -وَهِيَ أُمُّ الصَّبِيِّ-: هُوَ أَسْكَنُ مَا كَانَ، فَقَرَّبَتْ إِلَيهِ الْعَشَاءَ فَتَعَشَّى، ثُمَّ أَصَابَ مِنْهَا، فَلَمَّا فَرَغَ قَالَتْ: وَارُوا الصَّبِيَّ، فَلَمَّا أَصْبَحَ أَبُو طَلْحَةَ أَتَى رَسُولَ اللهِ ﷺ فَأَخْبَرَهُ، فَقَالَ: ((أَعَرَّسْتُمْ اللَّيْلَةَ؟)) قَالَ: نَعَمْ، قَالَ: ((اللَّهُمَّ بَارِكْ لَهُمَا))؛ فَوَلَدَتْ غُلَامًا، فَقَالَ لِي أَبُو طَلْحَةَ: احْمِلْهُ حَتَّى تَأْتِيَ بِهِ النَّبِيَّ ﷺ، وَبَعَثَ مَعَهُ بِتَمَرَاتٍ، فَقَالَ: ((أَمَعَهُ شَيْءٌ؟)) قَالَ: نَعَمْ، تَمَرَاتٌ، فَأَخَذَهَا النَّبِيُّ ﷺ فَمَضَغَهَا، ثُمَّ أَخَذَهَا مِنْ فِيهِ فَجَعَلَهَا فِي فِي الصَّبِيِّ ثُمَّ حَنَّكَهُ وَسَمَّاهُ عَبْدَ اللهِ.

مُتَّفَقٌ عَلَيْهِ.

وَفِي رِوَايَةٍ لِلْبُخَارِيِّ قَالَ ابْنُ عُيَيْنَةَ: فَقَالَ رَجُلٌ مِنَ الأَنْصَارِ: فَرَأَيْتُ تِسْعَةَ أَوْلَادٍ كُلُّهُمْ قَدْ قَرَؤُوا الْقُرْءَانَ، يَعْنِي

44- አነስ (ረ.ዐ) እንዲህ ሲሉ አስተላልፈዋል፦ አቡ ጦልሃ ሀመም የሚያጣድፈው ልጅ ነበራቸው። ለጉዞ ሲወጡ ሕጻኑ ልጃቸው ሞተ። ከጉዞ ተመለሱና፦ "ልጄን ምን አገኘው?" ሲሉ ጠየቁ። ኡሙ ሰለመህ -የህፃኑ እናት-፦ "ከበፊቱ በረድ ብሎለታል።" ስትል መለሰች። ራት አቀረበችላቸው። ተመገቡ። ወሲባዊ ግንኙነት ፈጽመው ሲያጠናቅቁ፦"ሕጻኑን ይቅበሩት፦" አለቻቸው። ሲነጋ ከአላህ መልዕክተኛ (ሶ.ዐ.ወ) ዘንድ በመቅረብ የሆነውን ሁሉ አጫወታቸው -አባጦልሓ። "ወሲባዊ ግንኙነት ፈፀማችሁን?" ሲሉ መልዕክተኛው ጠየቁ። "አዎ!" አባጦልሃ መለሱ። "አላህ ሆይ! ባርክላቸው።" ሲሉ ዱዓ አደረጉ -መልዕክተኛው። ወንድ ልጅ ወለደች። "ከነቢዩ ዘንድ ውሰደው።" አሉኝ -አባጦልሃ። ተምሮችንም አብረው ላኩ። "ከርሱ ጋር የመጣ ነገር አለለ?" ሲሉ መልዕክተኛው ጠየቁ። "አዎ! ተምሮች አልሉ" አሉ። ነቢዩ (ሶ.ዐ.ወ) አንዷን ተምር ያዙና አላመጧት። ከአፋቸው አወጡና ከሕጻኑ አፍ ውስጥ ከተቱት። የአፉን ውስጥም በተምሯ ፈገፈጉት። ዐብደላህ ብለው ሰየሙትም።

(ቡኻሪና ሙስሊም)

ቡኻሪ ባስፈሩት ሌላ ዘገባ እንደተወሳው፦

ኢብን ዑየይነህ እንዲህ ብለዋል። አንድ የአንሷር ሰው፦ "ዘጠኝ ልጆችን አይቻለሁ። ሁሉም ቁርአንን በሕሊናቸው መቅረጽ (መሐፈዝ) ችለዋል።"

ብሏል። የተወለደውን የዐብደላህን ልጆች ማለቱ ነው።

مِنْ أَوْلَادِ عَبْدِ اللهِ الْمَوْلُودُ.

በመክሊም ዘገባ ላይ ደግሞ የሚከተለው ሰፍሯል፦

ከኡሙ ሰለመህ የተወለደ የአባ ጦልሃ ልጅ ሞተ። "አባጦልሐን ስለልጁ ሞት እኔ ከመንገሬ በፊት አትንገሩት።" በማለት ኡሙ ሰለመህ ቤተሰቦቿን አስጠነቀቀች። አባ ጦልሐ መጡ። ራት አቀረበችላቸው። በሉ፥ ጠጡ። ከዚያን ዕለት በፊት ከምታደርገው የበለጠ ሁኔታ ተጋጊጣና ተውባ ቀረበችላቸው። ወሲባዊ ግንኙነት ፈፀሙ። መጥገባቸውንና በወሲብ መርካታቸውን ስትገነዘብ፦ "አባ ጦልሐ ሆይ! ሰዎች ለአንድ ቤተሰብ አባላት ትውሰት አዋሱና እንዲመለስላቸው ጠየቁ። ሊከለክሏቸው ይገባልን?" በማለት ጠየቀች። "በፍፁም!" ሲሉ መለሱላት። "እንግዲያውስ የልጅዎን ሞት አውቀው ምንዳውን ከአላህ ይከጅሉ።" በማለት አረዳቻቸው። ተቆጡ። "(ወሲብ) እስክፈጽም ድረስ ዘግይተሽ ነው እንዴ የልጄን ሞት የምታረጂኝ?!" ሲሉም አማረሩ። ከቤታቸው በመውጣት ከነቢዩ (ሶ.ዐ.ወ) ዘንድ ሄዱ። የሆነውን ሁሉ አጫወቷቸው። "በዛሬው ሌሊት የፈፀማችሁትን ወሲብ አላህ ይባርክላችሁ።" አሏቸው -ነቢዩ። ኡሙ ሰለመህ አረገዘች። የአላህ መልዕክተኛ (ሶ.ዐ.ወ) ጉዞ ላይ ነበሩ። እርሷም ከርሳቸው ጋር ነበረች። የአላህ መልዕክተኛ (ሶ.ዐ.ወ) ወደ መዲና ሲመለሱ በምሽት መግባት ልማዳቸው አልነበረም። መዲና ሲቃረቡ ምጥ ያዛቸው -ኡሙ ሰለመህ። አቡ ጦልሐ ከርሷ ጋር ወደኋላ

وَفِي رِوَايَةٍ لِمُسْلِمٍ: مَاتَ ابْنٌ لأَبِي طَلْحَةَ مِنْ أُمِّ سُلَيْمٍ، فَقَالَتْ لأَهْلِهَا: لاَتُحَدِّثُوا أَبَا طَلْحَةَ بِابْنِهِ حَتَّى أَكُونَ أَنَا أُحَدِّثُهُ، فَجَاءَ فَقَرَّبَتْ إِلَيْهِ عَشَاءً فَأَكَلَ وَشَرِبَ، ثُمَّ تَصَنَّعَتْ لَهُ أَحْسَنَ مَاكَانَتْ تَصَنَّعُ قَبْلَ ذَلِكَ، فَوَقَعَ بِهَا، فَلَمَّا أَنْ رَأَتْ أَنَّهُ قَدْ شَبِعَ وَأَصَابَ مِنْهَا قَالَتْ: يَا أَبَا طَلْحَةَ، أَرَأَيْتَ لَوْ أَنَّ قَوْمًا أَعَارُوا عَارِيَتَهُمْ أَهْلَ بَيْتٍ فَطَلَبُوا عَارِيَتَهُمْ، أَلَهُمْ أَنْ يَمْنَعُوهُمْ؟ قَالَ: لاَ، فَقَالَتْ: فَاحْتَسِبْ ابْنَكَ. قَالَ: فَغَضِبَ، ثُمَّ قَالَ: تَرَكْتُنِي حَتَّى إِذَا تَلَطَّخْتُ ثُمَّ أَخْبَرْتِنِي بِابْنِي؟! فَانْطَلَقَ حَتَّى أَتَى رَسُولَ اللهِ ﷺ فَأَخْبَرَهُ بِمَا كَانَ، فَقَالَ رَسُولُ اللهِ ﷺ ((بَارَكَ اللهُ فِي لَيْلَتِكُمَا)) قَالَ: فَحَمَلَتْ، قَالَ: وَكَانَ رَسُولُ اللهِ ﷺ فِي سَفَرٍ وَهِيَ مَعَهُ، وَكَانَ رَسُولُ اللهِ ﷺ إِذَا أَتَى الْمَدِينَةَ مِنْ سَفَرٍ لاَ يَطْرُقُهَا طُرُوقًا فَدَنَوا مِنَ الْمَدِينَةِ، فَضَرَبَهَا الْمَخَاضُ، فَاحْتَبَسَ عَلَيْهَا أَبُو طَلْحَةَ، وَانْطَلَقَ رَسُولُ اللهِ ﷺ. قَالَ: يَقُولُ أَبُو طَلْحَةَ: إِنَّكَ لَتَعْلَمُ يَارَبِّ أَنَّهُ يُعْجِبُنِي أَنْ

أَخْـرُجَ مَعَ رَسُولِ اللهِ ﷺ إِذا خَرَجَ، وَأَدْخُـلَ مَعَهُ إِذَا دَخَلَ، وَقَد احْتَبَسْتُ بِمَا تَرَى! تَقُولُ أُمُّ سُلَيْمٍ: يَا أَبَا طَلْحَةَ مَـا أَجِـدُ الَّذِي كُنْتُ أَجِدُ، انْطَلِقْ، فَانْطَلَقْنَا، وَضَرَبَهَا الْمَخَاضُ حِينَ قَدِمَا فَوَلَدَتْ غُلَامًا. فَقَالَتْ لِي أُمِّي: يَا أَنَسُ لَايُرْضِـعُهُ أَحَـدٌ حَتَّى تَغْدُوَ بِهِ عَلَى رَسُـولِ اللهِ ﷺ، فَلَمَّا أَصْبَحَ احْتَمَلْتُهُ فَانْطَلَقْتُ بِهِ إِلَى رَسُولِ اللهِ ﷺ. وَذَكَرَ تَمَامَ الْحَدِيثِ.

ሲቀሩ፥ የአላህ መልዕክተኛ (ሶ.ዐ.ወ) ተንቀሳቀሱ። "ጌታዬ ሆይ! የአላህ መልዕክተኛ ሲገቡ መግባት እንደሚያ ስደስተኝ ታውቃለህ። በምትመለከተው ነገር ተይገፍ ወደኋላ ቀርቻለሁ።" አሉ -አቡ ጦልሐ።

"አባ ጦልሐ ሆይ! ይሰማኝ የነበ ረው የምጥ ስሜት ተወግዷል፤ ተንቀ ሳቀስ።" አለች ኡሙ ሰለመህ። ተንቀ ሳቀስን። መዲና ስትደርስ ምጥ ያዛት። ወንድ ልጅ ተገላገለች። እናቴ እንዲህ አለችኝ- "ከአላህ መልዕክተኛ ዘንድ በጧት ከመውሰድህ በፊት ማንም ሰው እንዳያጠባው።" "ሲነጋ ተሸከም ኩትና ከአላህ መልዕክተኛ (ሶ.ዐ.ወ) ዘንድ ወሰድኩት።" ከዚያም ቀሪውን የሐዲስ ክፍል አወሱ።

ከሐዲሱ የምንማራቸው ቁምነገሮች

- የሙስሊም ሴትና የመልካም ሚስት አርቆ አስተዋይነትና ብስለት ተጨባጭ ምሳሌ ከዚህ የሐዲስ ዘገባ ውስጥ ቀርቧል።
- ኡሙ ሰለመህ ልጅዋ ሲሞት ያሳየችው የትዕግስት ፅናት ሙስሊም ሴቶች በአርአያነት ሊከተሉት የሚገባ ነው።
- አንድ ችግር ወይም ሞት ሲደርስ በተቻለ መጠን አለዝቦ ለማቅረብ መሞከር ተገቢ ነው።
- የትዳር ጓደኛን ለሐዘን ከማብቃት ይልቅ ማስደሰትን መምረጥ ለትዳር ጓደኛ ያለን ታማኝነትና ፍቅር ያመለክታል።
- ሴት ልጅ በሺሃድ ላይ ተሳትፎ ማድረግ መቻሏና ከሙጃሂዶች ምንዳም እንደምትከፈል።
- ሶሐባዎች ለነቢዩ (ሶ.ዐ.ወ) የነበራቸው ፍቅርና ከርሳቸው ላለመለየት፥ እርሳቸውን ለማማከርና ትሩፋታቸውን ለማግኘት ምን ያህል ጉጉት እንደነበራቸው።
- የትዳር ጓደኞች አንዱ የሌላውን ችግር ለማቃለል፥ አንዱ ለሌላው ውብ ሆኖ ለመገኘት ጥረት ማድረጋቸው ሱንና ነው። ፍቅራቸውን ያደረጃል። የቁርኝት ገመዳቸውን ይበልጥ ያጠነክራል።
- ለልጆች ማራኪ ስም መምረጥ ተገቢ ነው። ከስሞች ሁሉ ብልጫ ያለው "ዐ ብደላህ" የተሰኘው ስም መሆኑ ተነግሯል።
- አንድን ነገር ለአላህ ብሎ የተወ ሰው አላህ የተሻለ ለውጥ ይለግሰዋል።

45- አቡ ሁረይራ (ረ.ዐ) እንዳስተላለፉት የአላህ መልዕክተኛ (ሶ.ዐ.ወ) እንዲህ ሲሉ ተናግረዋል፦ "ኃይል ማለት ተፎካካሪ ዎቹን ታግሎ የሚያሸንፍ ሳይሆን፥ በቁጣ ወቅት ራሱን መቆጣጠር የሚችል ነው።" (ቡኻሪና ሙስሊም)

٤٥- وَعَنْ أَبِي هُرَيْرَةَ ﷺ أَنَّ رَسُولَ اللهِ ﷺ قَالَ: ((لَيْسَ الشَّدِيدُ بِالصُّرْعَةِ إِنَّمَا الشَّدِيدُ الَّذِي يَمْلِكُ نَفْسَهُ عِنْدَ الْغَضَبِ)) مُتَّفَقٌ عَلَيْهِ.

ከሐዲሱ የምንማራቸው ቁምነገሮች

- ኢስላም በዘመነ-ድንቁርና (ጃሂሊያ) ኃይል ተሰጥቶት የነበረውን የተሳሳተ ትርጓሜ ውብ ወደሆነ ሥነ-ምግባራዊ ማኅበራዊ ትርጓሜ ለውጦታል።
- ራስን ታግሎ ማሸነፍ፥ መቆጣጠርና መምራት መቻል ጠላትን ከማንበርከክ ይበልጥ አስቸጋሪ ፈታኝ ነው።
- ከቁጣ መራቅ ተገቢ ነው። አካላዊ፣ አዕምሯዊና ማኅበራዊ ጉዳቶችን ስለሚያስከትል።

46- ሱለይማን ኢብን ሱረድ (ረ.ዐ) እንዲህ ሲሉ አስተላልፈዋል፦ ከነቢዩ (ሶ.ዐ.ወ) ጋር ተቀምጬ ነበር። ሁለት ሰዎች ይሰዳደባሉ። አንደኛው ፊቱ ቀልቷል። የደም ሥሩ ተግተርትሯል። "አንዲት አባባል አውቃለሁ። እርሷን ቢናገር ቁጣው ይበርድለታል። "ከተረገመው ሰይጣን በአላህ እጠበቃለሁ።" ቢል ቁጣው ይወገድለታል።" አሉ የአላህ መልዕክተኛ (ሶ.ዐ.ወ)። "ነቢዩ (ሶ.ዐ.ወ)፦ "ከተረገመው ሰይጣን በአላህ ተጠበቅ።" ብለውሃል።" አሉት (ሰዎች)። (ቡኻሪና ሙስሊም)

٤٦- وَعَنْ سُلَيْمَانَ بْنِ صُرَدٍ ﷺ قَالَ: كُنْتُ جَالِسًا مَعَ النَّبِيِّ ﷺ، وَرَجُلَانِ يَسْتَبَّانِ، وَأَحَدُهُمَا قَدِ احْمَرَّ وَجْهُهُ، وَانْتَفَخَتْ أَوْدَاجُهُ. فَقَالَ رَسُولُ اللهِ ﷺ: ((إِنِّي لَأَعْلَمُ كَلِمَةً لَوْ قَالَهَا لَذَهَبَ عَنْهُ مَا يَجِدُ، لَوْ قَالَ: أَعُوذُ بِاللهِ مِنَ الشَّيْطَانِ الرَّجِيمِ ذَهَبَ مِنْهُ مَا يَجِدُ.)) فَقَالُوا لَهُ: إِنَّ النَّبِيَّ ﷺ قَالَ: تَعَوَّذْ بِاللهِ مِنَ الشَّيْطَانِ الرَّجِيمِ. مُتَّفَقٌ عَلَيْهِ.

ከሐዲሱ የምንማራቸው ቁምነገሮች

- ይህ የሐዲስ ዘገባ ከሰባተኛው የቁርአን ምዕራፍ የ200ኛውን አንቀጽ መንፈስ ያንፀባርቃል። ቁጣን የሚያሞረው ሰይጣን ነው። በዲንም ሆነ በዱንያ የሚያስከትለውን ጉዳት ስለሚያውቅ። ስለዚህ ከዚህ የሰይጣን ተንኮል የአላህን ጥበቃ በመሻት መከላከል ያስፈልጋል።
- ነቢዩ (ሶ.ዐ.ወ) በእያንዳንዱ አጋጣሚ፣ ክስተትና ሁኔታ ተከታዮቻቸውን አቅጣጫ ለማስያዝና ለመምራት የነበራቸውን ጉጉት ይህ ዘገባ ያሳያል።

٤٧- وَعَنْ مُعَاذِ بْنِ أَنَسٍ ﷺ، أَنَّ النَّبِيَّ ﷺ قَالَ: ((مَنْ كَظَمَ غَيْظًا، وَهُوَ قَادِرٌ عَلَى أَنْ يُنفِذَهُ، دَعَاهُ اللهُ سُبْحَانَهُ وَتَعَالَى عَلَى رُؤُوسِ الْخَلَائِقِ يَوْمَ الْقِيَامَةِ حَتَّى يُخَيِّرَهُ مِنَ الْحُورِ الْعِينِ مَا شَاءَ)).

47- ሙዓዝ ኢብን አነስ (ረ.ዐ) እንዳስተላለፉት ነቢዩ (ሶ.ዐ.ወ) እንዲህ ሲሉ ተናግረዋል፦ "መበቀል እየቻለ ቁጣውን የተቆጣጠረ ሰው አላህ የቂያማ ዕለት ከሰዎች መካከል ጥሪ ያቀርብለታል። ከሑረል-ዓይን ያሻውን እንዲመርጥም ይጋብዘዋል።" (አቡ ዳውድና ቲርመዚይ ዘግበውታል፡ ሐዲሱን "ሐሰን" ነውም ብለዋል)

ከሐዲሱ የምንማራቸው ቁምነገሮች

- ቁጣን የመቆጣጠር አስፈላጊነትና ጠቀሜታ።
- መበቀል እየቻሉ በይቅርታ ማለፍ ከፍተኛ ማምት ይሰጠዋል።

٤٨- وَعَنْ أَبِي هُرَيْرَةَ ﷺ، أَنَّ رَجُلاً قَالَ لِلنَّبِيِّ ﷺ: أَوْصِنِي، قَالَ: ((لاَ تَغْضَبْ)) فَرَدَّدَ مِرَارًا قَالَ: ((لاَ تَغْضَبْ)). رَوَاهُ الْبُخَارِيُّ.

48- አቡ ሁረይራ (ረ.ዐ) እንዳስተላለፉት አንድ ሰው ነቢዩን (ሶ.ዐ.ወ)፦ "ምክር ይለግሱኝ።" አላቸው። "አትቆጣ።" አሉት። በተደጋጋሚ ጠየቃቸው። "አትቆጣ።" የሚል ተደጋጋሚ ምላሽ ሰጡት።
(ቡኻሪ እንደዘገቡት)

ከሐዲሱ የምንማራቸው ቁምነገሮች

- የቁጣ አጥፊነትና የሚያስከትለው ጉዳት።
- የቁጣ ውጉዝነትና ከቁጣ የመራቅ አስፈላጊነት።
- የተወገዘው ቁጣ ከዓለማዊ ጥቅምና ፍላጐት ጋር የተያያዘ እንደሆነ ብቻ ነው። ለአላህና ለዲኑ ሲባል የሚከሠት ቁጣ ሊወደስና ሊበረታታ ይገባል። ነቢዩ (ሶ.ዐ.ወ) የአላህ ክልክሉች ሲደፈሩ ይቆጡ እንደነበር ይነገራል።

٤٩- وَعَنْ أَبِي هُرَيْرَةَ ﷺ قَالَ: قَالَ رَسُولُ اللهِ ﷺ: ((مَا يَزَالُ الْبَلاَءُ بِالْمُؤْمِنِ وَالْمُؤْمِنَةِ فِي نَفْسِهِ وَوَلَدِهِ وَمَالِهِ حَتَّى يَلْقَى اللهَ تَعَالَى وَمَا عَلَيْهِ خَطِيئَةٌ)) رَوَاهُ التِّرمِذِيُّ وَقَالَ حَدِيثٌ حَسَنٌ صَحِيحٌ.

49- አቡ ሁረይራ (ረ.ዐ) እንዳስተላፉት የአላህ መልዕክተኛ (ሶ.ዐ.ወ) እንዲህ ብለዋል፦ "በራሱ፣ በልጁና በገንዘቡ በኩል በሙእሚን ላይ መከራዎች ከመውረድ አይበገሱም፣ ከወንጀል የፀዳ ሆኖ አላህን እስኪገናኝ ድረስ።"
(ቲርመዚይ ዘግበውታል፡ ሐዲሱን "ሐሰን ሶሒሕ" ብለውታል)

ከሐዲሱ የምንማራቸው ቁምነገሮች

- ሙእሚን በተለያዩ ችግሮችና መከራዎች ይፈተናል።
- ይህ ዘገባ መከራ ለሚደርስበት ምእሚን ብስራትን አዝሏል።

٥٠- وَعَنْ ابْنِ عَبَّاسٍ ﷺ قَالَ: قَدِمَ عُيَيْنَةُ بْنُ حِصْنٍ فَنَزَلَ عَلَى ابْنِ أَخِيهِ الْحُرِّ بْنِ قَيْسٍ، وَكَانَ مِنَ النَّفَرِ الَّذِينَ يُدْنِيهِمْ عُمَرُ ﷺ ، وَكَانَ الْقُرَّاءُ أَصْحَابَ مَجْلِسِ عُمَرَ ﷺ وَمُشَاوَرَتِهِ كُهُولاً كَانُوا أَوْ شُبَّانًا، فَقَالَ عُيَيْنَةُ لِابْنِ أَخِيهِ: يَا ابْنَ أَخِي لَكَ وَجْهٌ عِنْدَ هَذَا الأَمِيرِ فَاسْتَأْذِنْ لِي عَلَيْهِ، فَاسْتَأْذَنَ فَأَذِنَ لَهُ عُمَرُ. فَلَمَّا دَخَلَ قَالَ: هِيَ يَا ابْنَ الْخَطَّابِ، فَوَ اللهِ مَا تُعْطِينَا الْجَزْلَ وَلاَ تَحْكُمُ فِينَا بِالْعَدْلِ، فَغَضِبَ عُمَرُ ﷺ حَتَّى هَمَّ أَنْ يُوقِعَ بِهِ، فَقَالَ الْحُرُّ: يَا أَمِيرَ الْمُؤْمِنِينَ إِنَّ اللهَ تَعَالَى قَالَ لِنَبِيِّهِ ﷺ: ﴿خُذِ الْعَفْوَ وَأْمُرْ بِالْعُرْفِ وَأَعْرِضْ عَنِ الْجَاهِلِينَ﴾ وَإِنَّ هَذَا مِنَ الْجَاهِلِينَ، واللهِ مَا جَاوَزَهَا عُمَرُ حِينَ تَلاَهَا، وَكَانَ وَقَّافًا عِنْدَ كِتَابِ اللهِ تَعَالَى. رَوَاهُ الْبُخَارِيُّ.

50- ኢብን ዐብባስ (ረ.ዐ) እንዲህ ሲሉ አስተላልፈዋል፦ ዑየይነት ኢብን ሒስን (ረ.ዐ) (ወደ መዲና) በመምጣት ከወንድሙ ልጅ ከሑር ኢብን ቀይስ ዘንድ አረፈ። ሑር ዑመር (ረ.ዐ) ከሚያቀርባቸው ሰዎች አንዱ ነበር። የቁርአንን መልዕክት የመረዳት የላቀ ችሎታ ያላቸው ሰዎች -ወጣቶችም ይሁኑ ሽማግሌዎች- የዑመር (ረ.ዐ) ችሎት አባላትና አማካሪዎችም ነበሩ። "የወንደሜ ልጅ ሆይ! ከዚህ አሚር ዘንድ ተደማጭነት ያለህ ሰው ነህና ከፊቱ መቅረብ እችል ዘንድ ፈቃድ ጠይቅልኝ።" በማለት ዑየይነህ የወንድሙን ልጅ ይጠይቃል። ፈቃድ ጠየቀለት። ዑመር (ረ.ዐ) ፈቀዱለት። ከዑመር ዘንድ በቀረበ ጊዜ፦ "በአላህ ይሁንብኝ የኸጣብ ልጅ! በርከት ያለ ስጦታ አትሰጠንም፣ በፍትህ አትፈርድልንም።" በማለት ተናገረ። ዑመር (ረ.ዐ) አለቅጥ ተቆጡ። ሊቀጡት እስኪከጅሉ ድረስ። ሑር እንዲህ አላቸው፦ "የሙእሚኖች አሚር ሆይ! አላህ ለነቢዩ (ሶ.ዐ.ወ)፦ "ገርን ጠባይ ያዝ፣ በመልካም እዘዝ፣ ባለጌዎችንም ተዋቸው።" ብሏቸዋል። ይህ ሰው ደግሞ ከባለጌዎች አንዱ ነው።" ሑር ይህንን የቁርአን አንቀጽ ባነበበት ወቅት ዑመር ቁጣቸው በረደ። ዑመር (ረ.ዐ) የአላህ መጽሐፍ (መመሪያ) ቅንጣት የማይተላለፉ ሰው ነበሩ።

(ቡኻሪ እንደዘገቡት)

ከሐዲሱ የምንማራቸው ቁምነገሮች

- የቁርአንን መልዕክትና መንፈስ የተረዱ ሰዎች የላቀ ደረጃ እዚህ ሐዲስ ላይ ተጠቁሟል። ይህንን የክብር ደረጃ የተቸሩት የቁርአንን መልዕክት ተረድተው ወደ ተግባር የለወጡት ውለምች እንጅ ቁርአንን ለዓለማዊ ጥቅም ማከሸሻ ያረጉት ክፍሎች አይደሉም።

- መሪዎችና አስተዳዳሪዎች መልካም አማካሪዎችን መያዝ እንዳለባቸው ይህ ሐዲስ ይጠቁማል።

٥١- وَعَنْ ابْنِ مَسْعُودٍ ﷺ أَنَّ رَسُولَ اللهِ ﷺ قَالَ: ((إِنَّهَا سَتَكُونُ بَعْدِي أَثَرَةٌ وَأُمُورٌ تُنْكِرُونَهَا! قَالُوا: يَارَسُولَ اللهِ فَمَا تَأْمُرُنَا؟ قَالَ: تُؤَدُّونَ الْحَقَّ الَّذِي عَلَيْكُمْ، وَتَسْأَلُونَ اللهَ الَّذِي لَكُمْ)) مُتَّفَقٌ عَلَيْهِ.

51- ኢብን መስዑድ (ረ.ዐ) እንዳስተላለፉት የአላህ መልዕክተኛ (ሶ.ዐ.ወ)፦ "ከኔ በኋላ አድሏዊነትና ተቀባይነት የሌላቸው የተሳሳቱ ጉዳዮች የሚከሰቱበት ሁኔታ ይኖራል።" በማለት ተናገሩ። "የአላህ መልዕክተኛ ሆይ! እንዲህ ዓይነት ሁኔታዎች በሚገጥሙን ወቅት ምን እንድናደርግ ያዙናል?" በማለት ጠየቋቸው። "ግዴታችሁን በመወጣት መብታችሁን ከአላህ ትጠይቃላችሁ።" ሲሉ መለሱ።

ከሐዲሱ የምንማራቸው ቁምነገሮች

(ቡኻሪና ሙስሊም)

- በአላህ ዕቅድና ፕላን የተፈፀሙ ሁኔታዎችን በፀጋ መቀበልና ማስተናገድ እንደሚገባ።
- ለአላህ ፍላጐት ተገዥነት።
- በኢስላማዊው ሥርዓት ውስጥ በታሪክ አጋጣሚ የሚከሠቱ ከኢስላም መንፈስ ያፈነገጡ የሙስሊም ጎብረተሰብ መሪዎችን ክስልጣናቸው በአመጽ ለማውረድ መሞከር የባሰ ጥፋት የሚያስከትል ሆኖ ከተገኘ ችግሩን በሰላማዊ መንገድ ለመፍታት ጥረት ማድረግና አላህንም ነገርቼን መልካም በሆነ መልኩ ያስኬዳቸው ዘንድ መማፀን ተገቢ ነው።

٥٢- وَعَنْ أَبِي يَحْيَى أُسَيْدُ بْنِ حُضَيْرٍ ﷺ أَنَّ رَجُلاً مِنَ الأَنْصَارِ قَالَ: يَا رَسُولَ اللهِ أَلاَ تَسْتَعْمِلُنِي كَمَا اسْتَعْمَلْتَ فُلاَنًا؟ فَقَالَ: ((إِنَّكُمْ سَتَلْقَوْنَ بَعْدِي أَثَرَةً، فَاصْبِرُوا حَتَّى تَلْقَوْنِي عَلَى الْحَوْضِ)) مُتَّفَقٌ عَلَيْهِ.

52- አቡ ያሕያ አኽይድ ኢብን ሑደይር (ረ.ዐ) እንዳስተላለፉት አንድ አንሷር ሰው፦ "የአላህ መልዕክተኛ ሆይ! ለእገሌ ሹመት እንደሰጡት ለኔም ሹመት አይሰጡኝም?!" ሲል ጠየቃቸው። "ከኔ በኋላ አድሏዊነት ይገጥማችኋል። "ሐውድ"[1] ላይ እስክታገኙኝ ድረስ ትዕግስት ይኑራችሁ።" አሉት።

(ቡኻሪና ሙስሊም)

[1] "ሐውድ" አላህ ለነቢዩ (ሶ.ዐ.ወ) ብቻ ጀነት ውስጥ ታል የገባላቸው ምንጭ ነው።

ከሐዲሱ የምንማራቸው ቁምነገሮች

- የነቢዩ (ሶ.ዐ.ወ) ተአምር፣ ወደፊት ስለሚከሰቱ ሁኔታዎች መናገራቸው።
- ችሎታው ያለውና ለቦታው ብቁ የሆነ ተቀናቃኝ የሌለበት ሁኔታ እስካልሆነ ድረስ ሹመትን አለመፈለግ በላጭነት እንዳለው።
- የነቢዩ (ሶ.ዐ.ወ) አርቆ አስተዋይነትና ለቦታው ብቃት የሌላቸው ሰዎች አለመሾማቸው።
- ብቃት የሌላቸው ሰዎች ከሥልጣን ኮርቻዎች ላይ በሚወጡበትና ነገሮች በሚበላሹበት ወቅት ትዕግስት እጅግ ጠቃሚ ነው።

٥٣- وعن ابي إبراهيم عبد الله بن أوفى رضي الله عنهما أن رسول الله ﷺ في بعض أيامه التي لقي فيها العدو، انتظر حتى إذا مالت الشمس قام فيهم فقال: ((يا أيها الناس لا تتمنوا لقاء العدو، واسألوا الله العافية، فإذا لقيتموهم فاصبروا، واعلموا أن الجنة تحت ظلال السيوف)) ثم قال النبي ﷺ: ((اللهم منزل الكتاب ومجري السحاب، وهازم الأحزاب، اهزمهم وانصرنا عليهم)) متفق عليه وبالله التوفيق.

53- አቡ ኢብራሂም ዐብደላህ ኢብን አቢ አውፍ (ረ.ዐ) እንዳስተላለፉት የአላህ መልዕክተኛ (ሶ.ዐ.ወ) ጠላትን ለመግጠም ከወጡባቸው ቀናት በአንዷ ፀሐይ ወደ ምዕራብ ዘንበል እስክትል ድረስ ከጠበቁ በኋላ ከሰዎች መካከል በመቆም፦"እናንተ ሰዎች ሆይ! ከጠላት መግጠምን አትመኙም፣ አላህን ሰላምን ለምኑት። ከገጠማችኋቸው ደግሞ ትዕግስት ይኑራችሁ። ጀንነት ከሾተል ጥላ ሥር መሆኑን እወቁ።" ካሉ በኋላ፦ "ኪታብን ያወረድክ፥ ደመናን የምትነዳ፥ የከሐዲያንን ጥርቅም በታኝ የሆንከው አላህ ሆይ! በትናቸው፣ እርዳታህንም ለግሰን።" ሲሉ አላህን ተማፀኑ።

(ቡኻሪና ሙስሊም)

ከሐዲሱ የምንማራቸው ቁምነገሮች

- ለጂሃድ ምንጊዜም ዝግጁ ሆኖ መገኘት። ኃይልን ማደራጀትና ጠላትን ፊት ለፊት መግጠም፥ ከኃጢአት መጽዳት፣ እውነተኛ ተውበትና ከልብ ወደ አላህ መመለስ ከጂሃድ ዝግጅት ውስጥ የሚካተቱ ናቸው።
- በጭንቅ ወቅት፥ በመከራ ሰዓት ዱዓ ማድረግ ሸሪዐዊ መሆኑ።
- ነቢዩ (ሶ.ዐ.ወ) ለባልደረቦቻቸውና ለተከታዮቻቸው የነበራቸው ርኅራኄ።
- ከጠላት ጋር መግጠምን መመኘትን ነቢዩ (ሶ.ዐ.ወ) መከልከላቸው።
- ጥንቁቅነትን፣ ቅንጅትንና ቁርጠኝነትን ችላ በማለት በቁሳዊ ኃይል ብቻ አለመመካት።
- "ሶብር" ለጂሃድ ከሚያስፈልጉ ትጥቆችና መሣሪያዎች አንዱና ዓይነተኛው ነው።

ምዕራፍ 4

٤- بَابُ الصِّدْقِ

እውነተኝነት

قَـالَ اللهُ تَعَالَى ﴿يَاأَيُّهَا الَّذِينَ ءَامَنُوا اتَّقُوا اللهَ وَكُونُوا مَعَ الصَّادِقِينَ﴾ وَقَالَ تَعَـالَى ﴿وَالصَّـادِقِينَ وَالصَّادِقَاتِ﴾ وَقَـالَ تَعَالَى ﴿فَلَوْ صَدَقُوا اللهَ لَكَانَ خَيْرًا لَهُمْ﴾ وَأَمَّا الأَحَادِيثُ:

አላህ እንዲህ ሲል ተናግሯል፦
"እላንተ ያመናችሁ ሆይ! አላህን ፍሩ፤ ከእውነተኞቹም ጋር ኹኑ።"
(አል-ተውባህ፡ 119)

"...እውነተኞች ወንዶችና እውነተኞች ሴቶችም፥..." (አል-አሕዛብ፡ 35)

"...እውነተኞች በኾኑ ኖሮ፥ ለነሱ የተሻለ በኾነ ነበር።" (ሙሐመድ፡ 21)

٥٤- فَالأَوَّلُ: عَنِ ابْنِ مَسْعُودٍ ﷺ عَنِ النَّبِيِّ ﷺ قَالَ: ((إِنَّ الصِّدْقَ يَهْدِي إِلَى الْبِرِّ، وَإِنَّ الْبِرَّ يَهْدِي إِلَى الْجَنَّةِ، وَإِنَّ الـرَّجُلَ لَيَصْدُقُ حَتَّى يُكْتَبَ عِنْدَ اللهِ صِـدِّيقًا، وَإِنَّ الْكَـذِبَ يَهْدِي إِلَى الْفُجُورِ، وَإِنَّ الْفُجُورَ يَهْدِي إِلَى النَّارِ، وَإِنَّ الرَّجُلَ لَيَكْذِبُ حَتَّى يُكْتَبَ عِنْدَ اللهِ كَذَّابًا)) مُتَّفَقٌ عَلَيْهِ.

54- ኢብን መስዑድ (ረ.ዐ.) እንዳስተላለፉት የአላህ መልዕክተኛ (ሶ.ዐ.ወ) እንዲህ ብለዋል፦ "እውነት ወደ መልካም ተግባር፥ መልካም ተግባር ደግሞ ወደ ጀንነት ይመራል። አንድ ሰው እውነት ይናገራል -ከአላህ ዘንድ እውነተኛ በሚል እስኪጻፍ ድረስ። ሐሰት ደግሞ መጥፎ ተግባር፥ መጥፎ ተግባር ደግሞ ወደ ጀሀንነም ይመራል። አንድ ሰው ሐሰትን ይናገራል -ከአላህ ዘንድ ሐሰተኛ ተብሎ እስኪጻፍ ድረስ።"
(ቡኻሪና ሙስሊም)

ከሐዲሱ የምንማራቸው ቁምነገሮች

- እውነት የመናገር ጠቃሚነት -የመልካም ነገሮች ሁሉ ምክንያት ነውና። ከሐሰት መጠንቀቅ -የመጥፎ ነገሮች ሁሉ ምንጭ ነውና። እንድን ባሕሪ የተላበሰ ሰው በዚያው ባሕሪው ሊጠራ ይገባል።
- ምንዳ ወይም ቅጣት የሰው ልጅ በሚሠራው መልካም ወይም መጥፎ ተግባር ላይ የተንተራሰ ነው።

55- አቡ ሙሐመድ ሐሰን ኢብን ዐሊይ ኢብን አቢ ጧሊብ (ረ.ዐ) እንዲህ ሲሉ አስተላልፈዋል፦ ከአላህ መልዕክተኛ (ሶ.ዐ.ወ) ጠቃሚ ምክር ይዣለሁ፦ "የሚያጠራጥርህን ነገር በመተው የማያጠራጥርህን ያዝ። እውነት ውስጣዊ ሰላምና ስክነት ሲሆን፥ ሐሰት ደግሞ ጥርጣሬና የልቦና አለመረጋጋት ነው።" (ቲርሙዚይ ዘግበውታል፡ ሐዲሱን "ሐሰን" ነውም ብለዋል)

٥٥- السِّنَانِي: عَنْ أَبِي مُحَمَّدٍ الْحَسَنِ ابْنِ عَلِيِّ بْنِ أَبِي طَالِبٍ، رضي الله عنهما، قَالَ: حَفِظْتُ مِنْ رَسُولِ اللهِ ﷺ: ((دَعْ مَا يَرِيبُكَ إِلَى مَا لاَ يَرِيبُكَ؛ فَإِنَّ الصِّدْقَ طُمَأْنِينَةٌ، وَالْكَذِبَ رِيبَةٌ))

رَوَاهُ التِّرْمِذِيُّ وَقَالَ: حَدِيثٌ صحيحٌ.

ከሐዲሱ የምንማራቸው ቁምነገሮች

- አሻሚ ነገሮችን በመተው ሐላል ወደሆኑ ነገሮች መዘንበል እጅግ ጠቃሚ ነው። ከአሻሚ ነገሮች የራቀ ዲኑንም፥ ክብሩንም ጠብቋልና።

56- አቡ ሱፍያን ሶኽር ኢብን ሐርብ (ረ.ዐ) ስለ ሂረቅል በተረኩት ረዥም ትረካቸው እንዳወሱት፦ ሂረቅል፦ "የሚያዛችሁ ነገር ምንድንነው?" ሲል ጠየቃቸው -ነቢዩን (ሶ.ዐ.ወ) መሆኑ ነው። "እንዲህ አልኩት" ይላል አቡ ሱፍያን፦"አላህን ብቻ አምልኩ። በርሱ ላይ ማንንም አታጋሩ። አባቶቻችሁ የሚሉትን ነገር ተዉ፣" ይላል። "ሶላት እንድንሰግድ፥ እውነት እንድንናገር፥ ሐራም ከሆኑና ክብርን ከሚያጐድፉ ፀያፍ ተግባራት እንድንቆጠብና ዝምድናን እንድንቀጥል ያዘናል።"

(ቡኻሪና ሙስሊም)

٥٦- الثالث: عَنْ أَبِي سُفْيَانَ صَخْرِ بْنِ حَرْبٍ ﷺ فِي حَدِيثِهِ الطَّوِيلِ فِي قِصَّةِ هِرَقْلَ، قَالَ هِرَقْلُ: فَمَاذَا يَأْمُرُكُمْ؟ - يَعْنِي النَّبِيَّ ﷺ- قَالَ أَبُو سُفْيَانَ: فَقُلْتُ: يَقُولُ: ((اعْبُدُوا اللهَ وَحْدَهُ لاَ تُشْرِكُوا بِهِ شَيْئًا، وَاتْرُكُوا مَا يَقُولُ آبَاؤُكُمْ، وَيَأْمُرُنَا بِالصَّلاَةِ، وَالصِّدْقِ، وَالْعَفَافِ، وَالصِّلَةِ)) مُتَّفَقٌ عَلَيْهِ.

ከሐዲሱ የምንማራቸው ቁምነገሮች

- የአላህ መልዕክተኛ (ሶ.ዐ.ወ) እውነተኝነት ባሕሪያቸው እንደሆነና በዚህ ባሕሪያቸው ከሰዎች ዘንድ እንደሚታወቁ፣ ጣላትም እንደመሰከረላቸው ይህ ዘገባ ያመለክታል።
- የዚህ "ዲን" መሠረት አላህን በብቸኝነት ማምለክና በርሱ ላይ የትኛውንም አካል አለማሻረክ ነው። ይህ ነው የመልካም ሥነ-ምግባራት ሁሉ በላጭ።
- ሌሎችን በጭፍኑ የመከተል አደገኛነት ብተለይም በዲን ጉዳይ ላይ።

57- አቡ ዛቢት ሰህል ኢብን ሑነይፍ (ረ.ዐ) አቡ ሰዒድ አቡል ወሊድም ይባላሉ። በድር ዘመቻ ላይ የተካፈሉ ሰው ናቸው። እንዳስተላለፉት ነቢዩ (ሶ.ዐ.ወ) እንዲህ ብለዋል፡- "ሰማዕትነትን አላህን በእውነት የተማፀነ፥ አላህ ወደ ሰማዕታት ደረጃ ያዘልቀዋል፤ ከፍራሹ ላይ ቢሞትም እንኳ።" (ሙስሊም እንደዘገቡት)

٥٧- الـرابع: عَنْ أَبِي ثَابِتٍ، وَقِيلَ: أَبِي سَعِيدٍ، وَقِيلَ: أَبِي الْوَلِيدِ، سَهْلِ بْنِ حُنَيْفٍ، وَهُـوَ بَدْرِيٌّ ﷺ أَنَّ النَّبِيَّ ﷺ قَالَ: ((مَنْ سَأَلَ اللهَ تَعَالَى الشَّهَادَةَ بِصِدْقٍ بَلَّغَهُ اللهُ مَنَازِلَ الشُّهَدَاءِ، وَإِنْ مَاتَ عَلَى فِرَاشِهِ))

ከሐዲሱ የምንማራቸው ቁምነገሮች

- ወደ ታላቅ ደረጃ ለመዝለቅ የቀልብ እውነተኝነት ወሳኝ ነው። እንድን መልካም ተግባር ለመፈፀም ከልብ የተመኘ በተለያዩ ምክንያቶች መፈፀም ቢሳነውም እንኳ ምንዳውን ያገኛል።
- ሰማዕትነትን ከልብ መመኘት የተወደደ መሆኑ።

58- አቡ ሁረይራ (ረ.ዐ) እንዳስተላለፉት የአላህ መልዕክተኛ (ሶ.ዐ.ወ) እንዲህ ሲሉ ተናግረዋል፡- "ከአላህ ነቢያት አንዱ (ሶ.ዐ.ወ) ለዘመቻ ተንቀሳቀሰ። "ቤት አሞቶ ጋብቻውን ያልፈፀመ፥ ቤት ሠርቶ ጣሪያውን ያልከደነ፥ ያረገዘች ፍየል ወይም ግመል ገዝቶ መውለዷን የሚጠባበቅ ሰው አይከተለኝ።" በማለት ተከታዮቹን አዘዘ ። ለዘመቻ ወጣ ። ዐስር ወቅት ላይ ወይም አዚያው አካባቢ ከአንዲት መንደር ደረሱ። "እኔም አንችም ታዛዦች ነን።" አላት -ለፀሐይዋ። "አላህ ሆይ! እንዳትጠልቅ አዘግይልን።" በማለትም አላህን ለመነ። አላህ ድልን እስኪያቀዳጀው ድረስ ፀሐይዋ ሳትጠልቅ ቆየች። ምርኮውን ሰበሰበ። እሳቷ ልትበላው መጣች። አልበላችውም። "ከመካከ ላችሁ ምርኮ ደብቆ ያስቀረ ሰው አለ። ከአያንዳንዱ ጐሳ አንዳንድ ሰው እየመጣ ከኔ ጋር ቃልኪዳን ይጋባ።" አለ። የአንድ ሰው እጅ ከእጁ ላይ ተጣብቆ ቀረ። "ከናንተ መሐከል

٥٨- الخـامس: عَنْ أَبِي هُرَيْرَةَ ﷺ قَالَ: قَالَ رَسُولُ اللهِ ﷺ: ((غَزَا نَبِيٌّ مِنَ الأَنْبِيَاءِ صَلَوَاتُ اللهِ وَسَلاَمُهُ عَلَيْهِمْ، فَقَالَ لِقَوْمِهِ: لاَ يَتْبَعُنِّي رَجُلٌ مَلَكَ بُضْعَ امْرَأَةٍ. وَهُوَ يُرِيدُ أَنْ يَبْنِيَ بِهَا وَلَمَّا يَبْنِ بِهَا، وَلاَ أَحَدٌ بَنَى بُيُوتًا لَمْ يَرْفَعْ سُقُوفَهَا، وَلاَ أَحَدٌ اشْتَرَى غَنَمًا أَوْ خَلِفَاتٍ وَهُوَ يَنْتَظِرُ أَوْلاَدَهَا. فَغَزَا فَدَنَا مِنَ الْقَرْيَةِ صَلاَةَ الْعَصْرِ أَوْ قَرِيبًا مِنْ ذَلِكَ، فَقَالَ لِلشَّمْسِ: إِنَّكِ مَأْمُورَةٌ وَأَنَا مَأْمُورٌ، اللَّهُمَّ احْبِسْهَا عَلَيْنَا، فَحُبِسَتْ حَتَّى فَتَحَ اللهُ عَلَيْهِ، فَجَمَعَ الْغَنَائِمَ، فَجَاءَتْ -يَعْنِي النَّارَ- لِتَأْكُلَهَا فَلَمْ تَطْعَمْهَا، فَقَالَ: إِنَّ فِيكُمْ غُلُولاً، فَلْيُبَايِعْنِي مِنْ كُلِّ قَبِيلَةٍ رَجُلٌ، فَلَزِقَتْ يَدُ رَجُلٍ بِيَدِهِ فَقَالَ: فِيكُمُ الْغُلُولُ، فَلْتُبَايِعْنِي قَبِيلَتُكَ، فَلَزِقَتْ يَدُ

ምርኮ የደበቀ አለ። የጐሣህ አባላት ከኔ ጋር ቃልኪዳን ይጋቡ።" አለው። የሁለት ወይም የሦስት ሰው እጆች ከእጁ ጋር ተጣብቀው ቀሩ። "ምርኮ ደብቃችኋል።" አላቸው። የሦስት ሰው እራስ የሚያክል ወርቅ ይዘው ወጡ። ከምርኮው ጋር ቀላቀላቸው። እሳት ወረደችና ምርኮውን በላች። ከኛ በፊት ለማንም ምርኮ ሐላል አልነበረም። ከዚያም አላህ ደካማነታችንን በመገንዘብ ለኛ ሐላል አደረገልን።"

(ቡኻሪና ሙስሊም)

رَجُلَيْنِ أَوْ ثَلاَثَةً بِيَدِهِ، فَقَالَ: فِيكُمُ الْغُلُولُ. فَجَاؤُوا بِرَأْسٍ مِثْلِ رَأْسِ بَقَرَةٍ مِنَ الذَّهَبِ. فَوَضَعَهَا فَجَاءَتِ النَّارُ فَأَكَلَتْهَا. فَلَمْ تَحِلِّ الْغَنَائِمُ لأَحَدٍ قَبْلَنَا، ثُمَّ أَحَلَّ اللهُ لَنَا الْغَنَائِمَ لَمَّا رَأَى ضَعْفَنَا وَعَجْزَنَا فَأَحَلَّهَا لَنَا)) مُتَّفَقٌ عَلَيْهِ.

ከሐዲሱ የምንማራቸው ቁምነገሮች

- ቁርጠቢይ እንዳሉት፦ "ይህ ነቢይ ከተከታዮቹ በተጠቀሱት ሦስት ሁኔታዎች ሥር የሚገኙትን እንዳይከተሉት ከልክሏል። ምክንያቱም እነኝህ ሰዎች ልቦናቸው በነኝህ ጉዳዮች የተንጠለጠለ በመሆኑ ወደኋላ እየተጉተተ ያስቸግራቸዋል። ለትግልና መስዋዕትነት የሚያስፈልገው ቆራጥነትና ብርታት ይጐድላቸዋል።

- የኒህ ነቢይ አባባል ግልጽ ነው። በጂሃድ የሚንቀሳቀስ ሰው ከሌሎች ሐሳቦችና እንቅፋቶች ነጻ መሆን ይኖርበታል። በእውነተኛ ስሜትና ቆራጥነት መንቀሳቀስ እንዲችል።

- ግዑዛን ነገሮችና እንስሳት አንድን ነገር የመፈፀም ወይም ያለመፈፀም ምርጫ የላቸውም። በአላህ ትእዛዝ ሥር ብቻ ነው የሚንቀሳቀሱት። የሰው ልጆች ግን ለእንቅስቃሴያቸው ነጻነት ተሰጥቷቸዋል። ለእያንዳንዱ ድርጊታቸውም በኃላፊነት ይጠየቃሉ።

- ነቢያት ተአምራትን የመፈፀም ችሎታ አላቸው።

- ባለፉት ዘመናት የአንድ ምርኮ ከአላህ ዘንድ ተቀባይነት ማግኘት ምልክቱ እሳት ከሰማይ ወርዳ ያን ምርኮ መብላቷ ነበር። በኢስላም ግን አላህ ምርኮን ለነቢዩ (ሶ.ዐ.ወ) ተከታዮች የተፈቀደ አድርጐታል። ይህ ለነቢዩ ሙሐመድ (ሶ.ዐ.ወ) ከተሰጡ ልዩ ዕድሎች አንዱ ነው።

٥٩- السَّادِسُ: عَنْ أَبِي خَالِدٍ حَكِيمِ ابْنِ حِزَامٍ ﷺ قَالَ: قَالَ رَسُولُ اللهِ ﷺ: ((الْبَيِّعَانِ بِالْخِيَارِ مَالَمْ يَتَفَرَّقَا، فَإِنْ صَدَقَا وَبَيَّنَا بُورِكَ لَهُمَا فِي بَيْعِهِمَا،

59- አቡ ኻሊድ ሐኪም ኢብን ሐዝማ (ረ.ዐ) እንዳስተላለፉት የአላህ መልዕክተኛ (ሶ.ዐ.ወ) እንዲህ ብለዋል፡- "ሻጭና ገዥ -እስካልተለያዩ ድረስ- (ግብይቱ) በም ርጫቸው (ተፈጻሚ ይሆናል)። እውነት ከተናገሩና (መገለፅ ያለበትን ነገር) ግልጽ ካደረጉ ግብይታቸው የተባረከ

ይሆንላቸዋል። (ሐቅን) ከደበቁና ከዋሹ ግብይታቸው በረከተ-አልባ ይሆናል።"
(ቡኻሪና ሙስሊም)

وَإِنْ كَذَبَا وَكَتَمَا مُحِقَتْ بَرَكَةُ بَيْعِهِمَا)) مُتَّفَقٌ عَلَيْهِ

ከሐዲሱ የምንማራቸው ቁምነገሮች

- ሻጭና ገዥ ስምምነታቸውን ለማጽደቅ ወይም ለማፍረስ የሚናራቸው የጊዜ ገደብ ከተገበያዩ በኋላ ተለያይተው እስካልሄዱ ድረስ ይሆናል።
- በሸቀጥ ላይ ያለን ጉድለት በግልጽ መናገር ግዴታ ነው። ጉድለቱ ከታወቀ ስምምነቱን ለማጽደቅ ወይም ለማፍረስ የሚናረው ምርጫ ትክክለኛ ይሆናል።
- ሐሰት በረከት (በረካ) እንዳይኖር ዓይነተኛ ምክንያት ነው።
- አንድ ገበያተኛ በሸቀጡ ላይ ውሸት ካልጨመረ ንብረቱ የተባረከ እንደሚሆንለት ሁሉ፥ አንድ ሙእሚን ከአላህ ጋር ያለው ግንኙነት በእውነት የደመቀ ከሆነ፥ ግዴታ የሆነበትን ዓባዳዎች ይዩልኝ ይስሙልኝ ሳያክልበት በታማኝነትና በቅንነት ለአላህ ብሎ ከፈፀመ በረካ ይሆኑለታል። ምንዳውንም ከአላህ ያገኛል።

ምዕራፍ 5

٥- بَابُ الْمُرَاقَبَة

የአላህን የበላይ ተቆጣጣሪነት ምንጊዜም አለመዘንጋት (ሙራቀበህ)

قَالَ اللهُ تَعَالَى ﴿الَّذِي يَرَاكَ حِينَ تَقُومُ وَتَقَلُّبَكَ فِي السَّاجِدِينَ﴾ وَقَالَ تَعَالَى ﴿وَهُوَ مَعَكُمْ أَيْنَمَا كُنْتُمْ﴾ وقال تَعَالَى ﴿إِنَّ اللهَ لاَ يَخْفَى عَلَيْهِ شَيْءٌ فِي الأَرْضِ وَلاَ فِي السَّمَاءِ﴾ وَقَالَ تَعَالَى ﴿إِنَّ رَبَّكَ لَبِالْمِرْصَادِ﴾ وَ قَالَ تَعَالَى ﴿يَعْلَمُ خَائِنَةَ الأَعْيُنِ وَمَا تُخْفِي الصُّدُورُ﴾ وَالآيَاتُ فِي الْبَابِ كَثِيرَةٌ مَعْلُومَةٌ وَأَمَّا الأَحَادِيثُ.

"በዚያ ለሶላት በምትቆም ጊዜ፥ በሚያ ይህ፤ በሰጋጆች ውስጥ መዘዋወርህንም፥ (በሚያየው ጌታህ ላይ ተጠጋ)፤"
(አል-ሹዐራ፥ 217-218)

"...እርሱም የትም ብትኾኑ ከናንተ ጋር ነው፤" (አል-ሐዲድ፥ 4)

"አላህ፥ በምድርም በሰማይም ምንም ነገር በርሱ ላይ አይሰወርም።"
(አሊ-ዒምራን፥ 5)

"ጌታህ በመጠባበቂያ ላይ ነውና።"
(አል-ፈጅር፥ 14)

"(አላህ) የዓይኖችን ክዳት፥ ልቦችም የሚደብቁትንም ሁሉ ያውቃል።"
(አል-ሙእሚን፥ 19)

٦٠- فَالأَوَّلُ: عَنْ عُمَرَ بْنِ الْخَطَّابِ ﷺ قَالَ؛ ((بَيْنَمَا نَحْنُ جُلُوسٌ عِنْدَ رَسُولِ اللهِ ﷺ ذَاتَ يَوْمٍ إِذْ طَلَعَ عَلَيْنَا رَجُلٌ شَدِيدُ بَيَاضِ الثِّيَابِ شَدِيدُ سَوَادِ الشَّعْرِ، لاَ يُرَى عَلَيْهِ أَثَرُ السَّفَرِ، وَلاَ يَعْرِفُهُ مِنَّا أَحَدٌ حَتَّى جَلَسَ إِلَى النَّبِيِّ ﷺ فَأَسْنَدَ رُكْبَتَيْهِ إِلَى رُكْبَتَيْهِ، وَوَضَعَ كَفَّيْهِ عَلَى فَخِذَيْهِ، وَقَالَ: يَامُحَمَّدُ أَخْبِرْنِي عَنِ

60- ዑመር ኢብን አል-ኸጣብ (ረ.ዐ) እንዲህ ሲሉ አስተላልፈዋል፦ ከዕለታት አንድ ቀን ከአላህ መልዕክተኛ (ሶ.ዐ.ወ) ዘንድ ተቀምጠን እያለ አንድ በጣም ነጭ የሆነ ልብስ የለበሰ፥ ፀጉሩ በጣም ጥቁር የሆነ፥ የጉዞ ምልክት የማይታይ በት፥ ከመካከላችንም ማንም የማያው ቀው አንድ ሰው ብቅ አለ። ጉልበቱን ከነቢዩ (ሶ.ዐ.ወ) ጉልበት ጋር አሳክቶ ተቀመጠ። መዳፎቹን ደግሞ ታፋዎቹ ላይ አደረገ። "ሙሐመድ ሆይ! ስለ

الإِسْلاَمِ، فَقَالَ رَسُولُ اللهِ ﷺ: الإِسْلاَمُ أَنْ تَشْهَدَ أَنْ لاَإِلَهَ إِلاَّ اللهُ وَأَنَّ مُحَمَّدًا رَسُولُ اللهِ، وَتُقِيمَ الصَّلاَةَ، وَتُؤْتِيَ الزَّكَاةَ، وَتَصُومَ رَمَضَانَ، وَتَحُجَّ الْبَيْتَ إِنِ اسْتَطَعْتَ إِلَيْهِ سَبِيلاً. قَالَ: صَدَقْتَ. فَعَجِبْنَا لَهُ يَسْأَلُهُ وَيُصَدِّقُهُ، قَالَ: فَأَخْبِرْنِي عَنِ الإِيمَانِ. قَالَ: أَنْ تُؤْمِنَ بِاللهِ، وَمَلاَئِكَتِهِ، وَكُتُبِهِ، وَرُسُلِهِ، وَالْيَوْمِ الآخِرِ، وَتُؤْمِنَ بِالْقَدَرِ خَيْرِهِ وَشَرِّهِ. قَالَ: صَدَقْتَ. قَالَ فَأَخْبِرْنِي عَنِ الإِحْسَانِ. قَالَ: أَنْ تَعْبُدَ اللهَ كَأَنَّكَ تَرَاهُ، فَإِنْ لَمْ تَكُنْ تَرَاهُ فَإِنَّهُ يَرَاكَ. قَالَ فَأَخْبِرْنِي عَنِ السَّاعَةِ. قَالَ: مَاالْمَسْئُولُ عَنْهَا بِأَعْلَمَ مِنَ السَّائِلِ. قَالَ: فَأَخْبِرْنِي عَنْ أَمَارَتِهَا. قَالَ: أَنْ تَلِدَ الأَمَةُ رَبَّتَهَا، وَأَنْ تَرَى الْحُفَاةَ الْعُرَاةَ الْعَالَةَ رِعَاءَ الشَّاءِ يَتَطَاوَلُونَ فِي الْبُنْيَانِ. ثُمَّ انْطَلَقَ فَلَبِثْتُ مَلِيًّا ثُمَّ قَالَ: يَاعُمَرُ، أَتَدْرِي مَنِ السَّائِلُ؟ قُلْتُ: اللهُ وَرَسُولُهُ أَعْلَمُ. قَالَ: فَإِنَّهُ جِبْرِيلُ أَتَاكُمْ يُعَلِّمُكُمْ أَمْرَ دِينِكُمْ.)) رَوَاهُ مُسْلِمٌ.

ኢስላም ንገሩኝ።" ሲልም ጠየቀ። "ኢስላም ከአላህ ሌላ አምላክ የሌለ መሆኑን እና ሙሐመድ የአላህ መልዕክተኛ መሆናቸውን መመስከር፡ ሶላትን አስተካክለህ መስገድህ፡ ዘካን መስጠትህ፡ የረመዷንን ፆም መፆምህና ወደ ሐጅ ለመጓዝ ችሎታው ያለህ ከሆነ ሐጅ ማድረግህ ነው።" ሲሉ የአላህ መልዕክተኛ (ሶ.ዐ.ወ) መለሱለት። "እውነት ብለዋል።" አላቸው። ገረመን። ይጠይቃቸዋል፡ እውነት መናገራቸውንም ይናዘዛል። "ስለ ኢማን (እምነት) ይንገሩኝ።" አላቸው። "በአላህ፣ በመላእክታን፣ በመጻሕፍት፣ በመልዕክተኞች፣ በዕለተ-ትንሳኤና ክፉም ሆነ በጎ በአላህ ዕቅድና ፕላን ማመን ነው።" አሉት። "እውነት ብለዋል" አላቸው። "ስለ ኢሕሳን ይንገሩኝ።" አላቸው። "አላህን እንደምታየው አድርገህ ማምለክህ ነው፤ አንተ ባታየው እርሱ ያይሃል።" አሉት። "ስለ ፍርዱ ቀን ንገሩኝ።" አላቸው። "የሚጠየቀው ሰው ከጠያቂው የበለጠ ዕውቀት የለውም።" ሲሉ መለሱለት። "እሺ ስለ ምልክቶቿ ንገሩኝ።" አለ። "የሴት ባሪያ እመቤቷን ትወልዳለች። ጫማ የሌላቸው፣ የታረዙ፣ ድሆችና የፍየል እረኞች (የነበሩ ሰዎች) ታላላቅ ሕንጻዎችን በመገንባት ሲፎካከሩ ትመለከታለህ።" አሉት። ከዚያ ወጥቶ ሄደ። ትንሽ ቆየሁ። "ዑመር ሆይ! ጠያቂው ማን እንደሆነ አወቅከውን?" አሉኝ መልዕክተኛው (ሶ.ዐ.ወ)። "አላህና መልዕክተኛው ያውቃሉ።" አልኩ። "ጂብሪል ነው። ሃይማኖታችሁን ሊያስተምራችሁ ከናንተ ዘንድ መጥቶ ነው።" አሉ።

(ሙስሊም እንደዘገቡት)

ከሐዲሱ የምንማራቸው ቁምነገሮች

- አላህ ሙእሚኖችን እርስ በርሳቸው በሚጠራሩት ዓይነት ነቢዩንም እንዳይጠሩ በቁርአኑ (24፡ 62) ቢከለክልም መላእኩ ጂብሪል (ዐ.ሰ) ነቢዩን ስማቸውን መጥራቱ ማንነቱን ለመደበቅ ወይንም መላኢኮች ይህ ቁርአናዊ ትእዛዝ የማይመለከታቸው በመሆኑ ነው።
- ኢማን ማለት፡ የዲኑን መሠረቶች አምኖ መቀበል ሲሆን፡ ኢስላም ደግሞ ሸሪዐዊ ትዕዛዛትን መተግበር ነው። ሁለቱም ተያያዥነት ያላቸው ጽንሰ-ሐሳቦች ናቸው። ኢማን ያለ ኢስላም፡ ኢስላም ደግሞ ያለ ኢማን ተቀባይነት የላቸውም። በተወራራሽነት የሚሠሩበትም ቦታ ይስተዋላል።
- አንድ ሰው ሙስሊም ለመባል ቃለ-ተውሒድን በምላሱ መናገር ችሎታው ካለው ግዴታ ይሆንበታል።
- በነቢዩና ጂብሪል መካከል፡ በተደረገው ቃለ ምልልስ የውውይትና የቃለ-ምልልስ ሥነ-ሥርዓት፡ እንዲሁም የማስተማር ስልት ተንፀባርቋል።
- ጂብሪል ከነቢዩ (ሶ.ዐ.ወ) ፊት ለፊት መቀመጡ ዒልም የሚሰጥበትን ቦታ ማክበርና ከዒልም ቦታ ላይ መጠበቅ የሚገባቸውን ሥነ-ሥርዓቶች ያመለክታል።
- የ"ፍርዱ ቀን" መቼ እንደሚሆን ትክክለኛ ወቅቱን አላህ ለማንም አልገለፀም። ግና የ"ፍርዱ ቀን" መድረሱን የሚጠቁሙ አያሌ ምልክቶች አሉ። ከነኝህም መሐከል ከዚህ ሐዲስ ውስጥ የተጠቀሱት ይገኙበታል። ለምሳሌ፦ የሚሳና የደኸል መምጣት፣ ፀሐይ በመግቢያዋ የመውጣቷ ክስተት፣ ወዘተ።
- ሰዎች ምንጊዜም ቢሆን የአላህን የበላይ ተቆጣጣሪነት መዘንጋት የለባቸውም።
- ይህ ሐዲስ እንደሚጠቁመው የኃላፊነት ቦታዎች አግባብነት ለሌላቸው ሰዎች መያዛቸውንና በወላጆች ላይ የሚፈፀም ግፍ መበራከቱ የፍርዱ ቀን መቃረቡን ይጠቁማሉ።
- ሙስሊም የዲኑን መሠረቶች ሊጠብቅና ከአላህ የተጠያቂነት ስሜት አድሮበት እያንዳንዱን ተግባር አላህን በመፍራት ስሜት ሊያከናውን ይገባል።

٦١- الثَّانِي: عَنْ أَبِي ذَرٍّ جُنْدُبِ بْنِ جُنَادَةَ وَأَبِي عَبْدِ الرَّحْمَنِ مُعَاذِ بْنِ جَبَلٍ ﷺ عَنْ رَسُولِ اللهِ ﷺ قَالَ: ((اتَّقِ اللهَ حَيْثُمَا كُنْتَ وَأَتْبِعِ السَّيِّئَةَ الْحَسَنَةَ تَمْحُهَا، وَخَالِقِ النَّاسَ بِخُلُقٍ حَسَنٍ)) رَوَاهُ التِّرْمِذِيُّ وَقَالَ حَدِيثٌ حَسَنٌ.

61- አቡ ዘር ጁንደብ ጁናዳህ እና አቡ ዐብዱረሕማን መዓዝ ኢብን ጀበል (ረ.ዐ) እንዳስተላለፉት የአላህ መልዕክተኛ (ሶ.ዐ.ወ) እንዲህ ሲሉ ተናግረዋል፦ "ምንጊዜም ቢሆን አላህን ፍራ። ኃጢአትን በመልካም ተግባር አስከትል፣ ታብላለችና። ሰዎችን በመልካም ሥነ-ምግባር ተዳደር።" (ቲርመዚይ ዘግቧታል። ሐዲሱን "ሐሰን" ነውም ብለዋል)

ከሐዲሱ የምንማራቸው ቁምነገሮች

- መልካም ተግባር ኃጢአትን ያብሳል። ይህ ትናንሽ ወንጀሎችን ብቻ እንደሚመለከት ተወስቷል። ታላላቅ ወንጀሎች የግድ ሸርጡን ያሟላ ተውበት ያስፈልጋቸዋል። ወንጀሉ ከሰዎች ሐቅ ጋር ተያያዥነት ያለው መሆን እንደሌለበትም ተመልክቷል።

- ብሩህ ገጽታ፣ እንቅፋትን ማስወገድ፣ መልካም ነገርን ለመፈፀም በጉ ፈቃደኝነት፣ ከሰዎች ጋር የሚኖርን ግንኙነት መልካም ማድረግ ከጥሩ ሥነ-ምግባር የሚካተቱ ናቸው።

٦٢- السَّائِلُ: عَنِ ابْنِ عَبَّاسٍ ﷺ قَالَ: كُنْتُ خَلْفَ النَّبِيِّ ﷺ يَوْمًا فَقَالَ: ((يَا غُلَامُ إِنِّي أُعَلِّمُكَ كَلِمَاتٍ: احْفَظِ اللهَ يَحْفَظْكَ، احْفَظِ اللهَ تَجِدْهُ تُجَاهَكَ، إِذَا سَأَلْتَ فَاسْأَلِ اللهَ، وَإِذَا اسْتَعَنْتَ فَاسْتَعِنْ بِاللهِ، وَاعْلَمْ أَنَّ الأُمَّةَ لَوِ اجْتَمَعَتْ عَلَى أَنْ يَنْفَعُوكَ بِشَيْءٍ لَمْ يَنْفَعُوكَ إِلاَّ بِشَيْءٍ قَدْ كَتَبَهُ اللهُ لَكَ، وَإِنْ اجْتَمَعُوا عَلَى أَنْ يَضُرُّوكَ بِشَيْءٍ لَمْ يَضُرُّوكَ إِلاَّ بِشَيْءٍ قَدْ كَتَبَهُ اللهُ عَلَيْكَ رُفِعَتِ الأَقْلاَمُ وَجَفَّتِ الصُّحُفُ!)) رَوَاهُ التِّرْمِذِيُّ وَقَالَ حَدِيثٌ حَسَنٌ صَحِيحٌ.

وَفِي رِوَايَةٍ: غَيْرِ التِّرْمِذِيِّ ((احْفَظِ اللهَ تَجِدْهُ أَمَامَكَ، تَعَرَّفْ إِلَى اللهِ فِي الرَّخَاءِ يَعْرِفْكَ فِي الشِّدَّةِ، وَاعْلَمْ أَنَّمَا أَخْطَأَكَ لَمْ يَكُنْ لِيُصِيبَكَ، وَمَا أَصَابَكَ لَمْ يَكُنْ لِيُخْطِئَكَ: وَاعْلَمْ أَنَّ النَّصْرَ مَعَ الصَّبْرِ، وَأَنَّ الْفَرَجَ مَعَ الْكَرْبِ، وَأَنَّ مَعَ الْعُسْرِ يُسْرًا.))

62- ኢብን ዐብባስ (ረ.ዐ) እንዲህ ሲሉ አስተላልፈዋል፦ ከዕለታት አንድ ቀን ከነቢዩ (ሶ.ዐ.ወ) ኋላ ነበርኩ። እንዲህ አሉኝ፦ "አንተ ልጅ ሆይ! ጥቂት ቃላቶችን አስተምርሃለሁ። የአላህን ትእዛዝ ጠብቅ፣ እርሱም ይጠብቅሃል። አላህን ጠብቅ፣ ከፊት ለፊትህ ታገኘዋለህ። ስትጠይቅ አላህን ብቻ ጠይቅ። እርዳታ ስትፈልግ በአላህ ብቻ ተረዳ። ሕዝቦች ሁሉ ሊጠቅሙህ ቢሰበሰቡ በእርግጥ አይጠቅሙህም -አላህ በእርግጥ የወሰነልህ ነገር ሲቀር። ሊጉዱህ ቢሰበሰቡም ሊጉዱህ አይችሉም -አላህ በእርግጥ የወሰነብህ ነገር ቢሆን እንጅ። ብዕሮች ተነስተዋል፣ ገጾችም ደርቀዋል።"

(ቲርመዚይ ዘግበውታል፦ "ሐሰኑን ሶሒሕ" ብለውታልም)

ከቲርመዚይ ውጭ ካሉ ሌሎች ዘገባዎች ላይ ደግሞ፦

"አላህን ጠብቀው፣ ከፊትህ ታገኘዋለህ። ከአላህ ጋር በሰላም ጊዜ ተዋወቅ፣ በችግር ጊዜ ዕውቅና ይሰጥሃልና። ያላጋጠመህ ነገር ሊደርስብህ፣ ያልነበረና የደረሰብህም ነገር የሚያልፍህ እንዳልነበር ተረዳ። ድል ከትዕግስት ጋር፣ እርዳታ ከጭንቅ ጋር፣ ችግርም ከምቾት ጋር መኖሩን እወቅ" የሚል ተወስቷል።

ከሐዲሱ የምንማራቸው ቁምነገሮች

- ከአላህ ውጭ ማንም ማድረግ የማይችላቸውን ነገሮች ከአላህ ውጭ ያለን ፍጡር መጠየቅ ሐራም ነው። ሰዎችን በሚችሉት ጉዳይ ላይ እርዳታቸውን መሻት ግን የተከለከለ አይደለም።
- በአላህ እውቀት ሥር ያለ ማናቸውንም ነገር የፀደቀ ነው። አይዘገይም። አይሻርም። ያለፉትንም ይሁን ወደፊት የሚከሠቱ ነገሮች ሁሉ በአላህ እውቀት ሥር ናቸው። ከአላህ ዕውቀት ውጭ የሚከሠት አንድም ነገር የለም።
- እርካታ ከሞንቀት፥ ምኞት ከችግር ጋር የመቆራኘት ሚስጥር አንድ ሰው ችግር በሚበረታበት ወቅት ከአላህ ውጭ ባለ ማንኛውም ኃይል ላይ ያለው ተስፋ ይሟጠጣል። ልቦናው ከአላህ ጋር ብቻ የተቆራኘ ይሆናል። እውነተኛው "ተወኩል" ይህ ነው።
- ይህ ሐዲስ ስለ "ሙራቀበህ" የአላህን መብት ስለመጠበቅ፣ ለትእዛዙ ስለ ማደር፣ በርሱ ስለ መመካት፣ ብቸኛ አምላክነቱን ስለ መናዘዝና ፍጡራን አንዳችም ነገር ለመሥራት ችሎታው የሌላቸውና የአላህን እርዳታ እንደሚሹ የሚያሳይ መሠረታዊ ዘገባ ነው።

٦٣- الرَّابِعُ: عَنْ أَنَسٍ ﷺ قَالَ: ((إِنَّكُمْ لَتَعْمَلُونَ أَعْمَالاً هِيَ أَدَقُّ فِي أَعْيُنِكُمْ مِنَ الشَّعْرِ كُنَّا نَعُدُّهَا عَلَى عَهْدِ رَسُولِ اللهِ ﷺ مِنَ الْمُوبِقَاتِ)) رَوَاهُ الْبُخَارِيُّ.

63- አነስ (ረ.ዐ) እንዲህ ሲሉ አስተላልፈዋል:- "በናንተ ዓይን ከፀጉር የቀጠኑ ኢምንት፥ ግና በአላህ መልዕክተኛ (ሶ.ዐ.ወ) ዘመን ከአጥፊ የወንጀል ክን ውኖች እንቆጥራቸው የነበሩ ሥራዎችን ትሠራላችሁ።" (ቡኻሪ እንደዘገቡት)

ከሐዲሱ የምንማራቸው ቁምነገሮች

- ወንጀልን አቅልሎ መመልከት "ተቅዋ" አለመኖሩን ያመለክታል። እያንዳንዱ ጥቃቅን ወንጀል እንደ ትልቅ ጥፋት መመልከት ደግሞ የላቀ "ተቅዋ"ና "ሙራቀባ" እንዳለ ይጠቁማል።
- ከነቢያት ቀጥሎ አላህን ከምንም ይበልጥ የሚያውቁትንና የሚፈሩት የነቢዩ (ሶ.ዐ.ወ) ባልደረቦች ናቸው። ጥቃቅን ጥፋቶችን ሁሉ እንደ አጥፊ ወንጀሎች ይመለከቱ ነበር፣ የአላህን ታላቅነት፣ ልዕልናና ግዝፈት በጥልቅ ስለሚረዱ።

٦٤- الْخَامِسُ: عَنْ أَبِي هُرَيْرَةَ ﷺ عَنِ النَّبِيِّ ﷺ قَالَ: ((إِنَّ اللهَ تَعَالَى يَغَارُ، وَغَيْرَةُ اللهِ تَعَالَى أَنْ يَأْتِيَ الْمَرْءُ مَا حَرَّمَ اللهُ عَلَيْهِ)) مُتَّفَقٌ عَلَيْهِ.

64- አቡ ሁረይራ (ረ.ዐ) እንዳስተላለፉት የአላህ መልዕክተኛ (ሶ.ዐ.ወ) እንዲህ ሲሉ ተናግረዋል:- "ልዑል የሆነው አላህ ይቀናል። የአላህ ቅናት አንድ ሰው (አላህ) ውጉዝ (ሐራም) ያደረገውን ነገር ሲፈጽም ነው።" (ቡኻሪና ሙስሊም)

ከሐዲሱ የምንማራቸው ቁምነገሮች

- ሐራም የሆኑ ተግባራትን ከመፈፀም መቆጠብ -የአላህን ቁጣ ያስከትላሉና።

٦٥- السَّادِسُ: عَنْ أَبِي هُرَيْرَةَ ﷺ أَنَّهُ سَمِعَ النَّبِيَّ ﷺ يَقُولُ: ((إِنَّ ثَلَاثَةً مِنْ بَنِي إِسْرَائِيلَ أَبْرَصَ وَأَقْرَعَ وَأَعْمَى أَرَادَ اللهُ أَنْ يَبْتَلِيَهُمْ، فَبَعَثَ إِلَيْهِمْ مَلَكًا فَأَتَى الأَبْرَصَ فَقَالَ: أَيُّ شَيْءٍ أَحَبُّ إِلَيْكَ؟ قَالَ: لَوْنٌ حَسَنٌ، وَجِلْدٌ حَسَنٌ، وَيَذْهَبُ عَنِّي الَّذِي قَدْ قَذِرَنِيَ النَّاسُ، فَمَسَحَهُ فَذَهَبَ عَنْهُ قَذَرُهُ وَأُعْطِيَ لَوْنًا حَسَنًا. فَقَالَ: فَأَيُّ الْمَالِ أَحَبُّ إِلَيْكَ؟ قَالَ: الإِبِلُ -أَوْ قَالَ الْبَقَرُ- شَكَّ الرَّاوِي، فَأُعْطِيَ نَاقَةً عُشَرَاءَ فَقَالَ: بَارَكَ اللهُ لَكَ فِيهَا. فَأَتَى الأَقْرَعَ فَقَالَ: أَيُّ شَيْءٍ أَحَبُّ إِلَيْكَ؟ قَالَ: شَعْرٌ حَسَنٌ، وَيَذْهَبُ عَنِّي هَذَا الَّذِي قَذِرَنِي النَّاسُ، فَمَسَحَهُ فَذَهَبَ عَنْهُ وَأُعْطِيَ شَعْرًا حَسَنًا. قَالَ: فَأَيُّ الْمَالِ أَحَبُّ إِلَيْكَ؟ قَالَ: الْبَقَرُ، فَأُعْطِيَ بَقَرَةً حَامِلاً وَقَالَ: بَارَكَ اللهُ لَكَ فِيهَا. فَأَتَى الأَعْمَى فَقَالَ: أَيُّ شَيْءٍ أَحَبُّ إِلَيْكَ؟ قَالَ: أَنْ يَرُدَّ اللهُ إِلَيَّ بَصَرِي فَأُبْصِرَ النَّاسَ،

65- ነቢዩ (ሶ.ዐ.ወ) ተከታዩን ሲናገሩ ማድመጣቸውን አቡ ሁረይራ (ረ.ዐ) አስተላል ፈዋል:- "ከበኒ ኢስራኤሎች መካከል ሦስት ሰዎች -አንደኛው ለምጻም፣ ሌላኛው በራ፣ ሦስተኛው ደግሞ እውር- አላህ ሊፈትናቸው ፈለገ። መላኢካ ላከባቸው። ለምጽ ያለበትን ሰው መጣና:- "በጣም የምትወደው ነገር ምንድን ነው?" ሲል ጠየቀው። "መልካም መልክና መልካም ቆዳ። ሰዎች እኔን እንዲጠየፉኝ ምክንያት የሆነው በሽታዬም እንዲወገድልኝ።" ሲል መለሰ። አበሰው -መላኢካው። አስፀያፊው ሁኔታም ተወገደለት። መልካም መልክ ተሰጠ። "ከገንዘብ የትኛው ነው ካንተ ዘንድ ይበልጥ ተወዳጅ?" በማለት ጠየቀው። "ግመል ወይም ላም።" መለሰለት። እርጉዝ ግመል ተሰጠው። "አላህ ይባርክልህ።" ሲልም መረቀው። ወደ በራው ሰውዬ በመሄድም:- "እጅግ የምትወደው ነገር ምንድን ነው?" አለው። "መልካም ፀጉር፣ ሰዎች እንዲፀየፉኝ ምክንያት የሆነው በራዬም እንዲወገድ።" አለ። አበሰው። በራው ተወገደለት። ማራኪ ፀጉርም ተሰጠው። "ከገንዘብ የትኛው ነው ካንተ ዘንድ ይበልጥ ተወዳጅ?" ሲልም ጠየቀው። "ላም።" አለ። ያረገ ዘች ላም ተሰጠው። "አላህ ይባርክ ልህ።" አለው። ከእውሩም ዘንድ በመም ጣት:- "ይበልጥ የምትወደው ነገር ምንድን ነው?" ሲል ጠየቀው። "አላህ

فَمَسَحَهُ فَرَدَّ اللهُ إِلَيْهِ بَصَرَهُ. قَالَ: فَأَيُّ الْمَالِ أَحَبُّ إِلَيْكَ؟ قَالَ: الْغَنَمُ، فَأُعْطِيَ شَاةً وَالِدًا، فَأَنْتَجَ هَذَانِ وَوَلَّدَ هَذَا، فَكَانَ لِهَذَا وَادٍ مِنَ الإِبِلِ، وَلِهَذَا وَادٍ مِنَ الْبَقَرِ، وَلِهَذَا وَادٍ مِنَ الْغَنَمِ. ثُمَّ إِنَّهُ أَتَى الأَبْرَصَ فِي صُورَتِهِ وَهَيْئَتِهِ فَقَالَ: رَجُلٌ مِسْكِينٌ قَدِ انْقَطَعَتْ بِيَ الْحِبَالُ فِي سَفَرِي، فَلاَ بَلاَغَ لِيَ الْيَوْمَ إِلاَّ بِاللهِ ثُمَّ بِكَ أَسْأَلُكَ بِالَّذِي أَعْطَاكَ اللَّوْنَ الْحَسَنَ، وَالْجِلْدَ الْحَسَنَ، وَالْمَالَ، بَعِيرًا أَتَبَلَّغُ بِهِ فِي سَفَرِي، فَقَالَ: الْحُقُوقُ كَثِيرَةٌ. فَقَالَ: كَأَنِّي أَعْرِفُكَ أَلَمْ تَكُنْ أَبْرَصَ يَقْذَرُكَ النَّاسُ فَقِيرًا فَأَعْطَاكَ اللهُ؟ فَقَالَ: إِنَّمَا وَرِثْتُ هَذَا الْمَالَ كَابِرًا عَنْ كَابِرٍ. فَقَالَ: إِنْ كُنْتَ كَاذِبًا فَصَيَّرَكَ اللهُ إِلَى مَا كُنْتَ. وَأَتَى الأَقْرَعَ فِي صُورَتِهِ وَهَيْئَتِهِ فَقَالَ لَهُ مِثْلَ مَا قَالَ لِهَذَا، وَرَدَّ عَلَيْهِ مِثْلَ مَا رَدَّ هَذَا، فَقَالَ: إِنْ كُنْتَ كَاذِبًا فَصَيَّرَكَ اللهُ إِلَى مَا كُنْتَ. وَأَتَى الأَعْمَى فِي صُورَتِهِ وَهَيْئَتِهِ فَقَالَ: رَجُلٌ مِسْكِينٌ وَابْنُ سَبِيلٍ انْقَطَعَتْ بِيَ

የዓይኔን ብርሃን መልሶልኝ ሰዎችን መመልከት መቻል።" በማለት መለሰለት። አበሰው። አላህ የዓይኑን ብርሃን መለሰለት። "ከገንዘብ የትኛውን ነው ይበልጥ የምትወደው?" ሲልም ጠየቀው። "ፍየል።" አለ። ወላድ የሆነች ፍየል ተሰጠው። ሁሉም ተራብቡ፣ ተበራከቱ። አንደኛው የአንድ ሸለቆ ግመል፣ ሌላኛው የአንድ ሸለቆ ከብት፣ ሦስተኛው ደግሞ የአንድ ሸለቆ ፍየል ባለሃብቶች ሆኑ። በሌላ ወቅት መላኢካው ድሮ በነበረው መልክና አኳኋን ሆኖ ለምጻም ወደነበረው ሰው መጣና:- "ችግር የደረሰብኝ መንገደኛ ነኝ። አላህና አንተ ከምትለግሱኝ ችግር በስተቀር ጉዞዬን ለመቀጠል የሚያስችለኝ ስንቅ የለኝም። ለመዳረሻዬ የሚሆነኝ ስንቅ ታቀብለኝ ዘንድ መልካም መልክ፣ መልካም ቆዳና ይህን ሁሉ ግመል በለገሰህ አምላክ ስም እማፀንሃለሁ።" አለው። "አያሌ ጉዳዮች አሉብኝ፣ ልረዳህ አልችልም።" አለው። "የማውቅህ ይመስለኛል። ሰዎች የሚፀየፉህ ለምጻምና ድሃ አልነበርክም? አላህ ጥሩ መልክና ቆዳ እንዲሁም ሃብት ለገሰህ።" አለው። "ከአያት ቅድመ አያቶቼ የወረስኩት ነው።" አለ። "ሐሰት ከተናገርክ (አላህ) ድሮ ወደነበርክበት ሁኔታ ይመልስህ።" አለው። መላጣ ወደነበረው ሰው በጥንቱ መልክና አኳኋን ሆኖ በመም ጣትም ለዚያኛው ያለውን አለው። ይህኛውም ያኛው የሰጠውን ዓይነት ምላሽ መለሰለት። "ሐሰት ከተናገርክ ድሮ ወደነበርክበት ሁኔታህ አላህ ይመልስህ።" አለው። በጥንቱ መልክና

الْجِبَالُ فِي سَفَرِي، فَلاَ بَلاَغَ لِيَ الْيَوْمَ إِلاَّ بِـاللهِ ثُـمَّ بِكَ، أَسْأَلُكَ بِالَّذِي رَدَّ عَلَيْكَ بَصَرَكَ شَاةً أَتَبَلَّغُ بِهَا فِي سَفَرِي؟ فَقَـالَ: قَدْ كُنْتُ أَعْمَى فَرَدَّ اللهُ إِلَيَّ بَصَـرِي فَخُذْ مَاشِئْتَ وَدَعْ مَاشِئْتَ، فَـوَ اللهِ مَا أَجْهَدُكَ الْيَوْمَ بِشَيْءٍ أَخَذْتَهُ لِـلَّهِ عَزَّ وَجَلَّ. فَقَالَ: امْسِكْ مَالَكَ، فَإِنَّمَـا ابْتُلِيـتُمْ، فَقَدْ رَضِيَ اللهُ عَنْكَ وَسَخِطَ عَلَى صَاحِبَيْكَ)) مُتَّفَقٌ عَلَيْهِ.

አኺትን እውር ከነበረው ሰው ዘንድ መጣና:- "በጉዞ ላይ እያለሁ ስንቅ የተቋረጠብኝና ችግር የደረሰብኝ መንገደኛ ነኝ። ከአንተና ከአላህ ከማገኛቸው ችሮታ ውጭ ለመዳረሻዬ የሚሆነኝ ስንቅ የለኝም። ለመዳረሻዬ የሚሆነኝ እንዲት ፍየል ትሰጠኝ ዘንድ የዓይንህን ብርሃን በመለሰልህ አምላክ (ስም) እማፀንሃለሁ።" አለው። "እውር ነበርኩ፣ አላህ ዓይኔን መለሰለኝ። ያሻህን ትተህ ያሻህን ውሰድ። በአላህ ይሁንብኝ! ልዑ ልና ኃያል ለሆነው አላህ ስል ዛሬ የምትወስደውን ነገር መልስ ብዬ አላስቸግርህም።" አለው። "ገንዘብህን ያዝ። እናንተን ለመፈተን ነው የመጣሁት። አላህ በአንተ ረክቶ በሁለቱ ወዳጆችህ ተቆጥቷል።" አለው።"

(ቡኻሪና ሙስሊም)

ከሐዲሱ የምንማራቸው ቁምነገሮች

- ንፍጉት እጅግ አስፀያፊ ባሕሪ ነው። እንኳህን ሁለት ሰዎች አላህ በለገሣቸው ፀጋ የዋለላቸውን ውለታ ለመርሳትና ለመክዳት አብቅቷቸዋል።
- ስስትና ሐሰት መናገር የአላህን ቁጣ ያስከትላሉ። ከላይ በተወሱት ሁለት ሰዎች ላይ እንደተስተዋለው።
- ሊጋሾችና እውነት ተናጋሪዎች መልካም ከሆኑ ባሕሪያት ውስጥ ናቸው። እውሩ ሰው እንኳህ ባሕሪያት ይንፀባረቁበት ነበር። አላህ ለለገሰው ፀጋ ውለታውን እንዳይዘነጋና ቸር እንዲሆን አበቁት። የአላህን እርካታ አጉናፀፉት።
- አላህ ለሰዎች ምንዳ የሚሰጠው በሥራቸው መጠንና እንደየኒያቸው ነው።
- ስለ በኒ ኢስራኢሉች መተረክ ይቻላል። ለሌሎች ትምህርት እንዲሆን።
- በትረካ መልክ ትምህርት መቅረቡ ጠቀሜታ እንዳለው ይህ ዘገባ ይጠቁማል። በትረካ መልክ የሚቀርቡ ትምህርቶች ይበልጥ ከሰዎች ልቦና ውስጥ የመግባት ባሕሪ አላቸው።
- ሙእሚን የእውነተኝነትንና ሊጋስነትን መልካም ባሕሪያት መላበስ እንዲሁም አላህ ለለገሠው ፀጋ በንግግሩም ሆነ በተግባሩ ውለታውን መመለስ ይጠበቅበታል።

66- አቡ የዕላ ሸዳድ ኢብን አውስ (ረ.ዐ)
እንዳስተላለፉት የአላህ መልዕክተኛ (ሶ.ዐ.ወ)

እንዲህ ብለዋል፦ "ብልህ ሰው ስሜታዊ ዝንባሌውን መቆጣጠርና መምራት የቻለ ሲሆን፥ ደካማ ደግሞ ለስሜታዊ ዝንባሌው ተገዥ የሆነ፥ (አንዳች የሚፈ ይድ ነገር ሳይሠራ መልካምን ነገር) የሚመኝና ከአላህ የሚጠብቅ ነው።"
(ቲርሙዚይ ዘግበውታል፡ "ሐሰን" ብለውታልም።)

٦٦- السَّابِعُ:عَنْ أَبِي يَعْلَى شَدَّادِ بْنِ أَوْسٍ ﷺ عَنِ النَّبِيِّ ﷺ قَالَ:((اَلْكَيِّسُ مَنْ دَانَ نَفْسَهُ وَعَمِلَ لِمَا بَعْدَ الْمَوْتِ، وَالْعَاجِزُ مَنْ أَتْبَعَ نَفْسَهُ هَوَاهَا وَتَمَنَّى عَلَى اللهِ الأَمَانِيَّ)) رَوَاهُ التِّرْمِذِيُّ وَقَالَ حَدِيثٌ حَسَنٌ.

ከሐዲሱ የምንማራቸው ቁምነገሮች

- ራስን መቆጣጠርና መምራት፥ ማረምና መግታት፥ ኃላፊነትን በአግባቡ መወጣት እጅግ አስፈላጊ ነው። ባዶ ምኞትና የማይጨበጥ ሕልም ለጥፋት ይዳርጋል። አላህ ለሰዎች ምንዳ የሚለግሰው በተመኙት ሳይሆን በሠሩት ነው።

67- አቡ ሁረይራ (ረ.ዐ) እንዳስተላለፉት የአላህ መልዕክተኛ (ሶ.ዐ.ወ)፦ "አንድ ሰው የማይመለከተውን ነገር መተው የሰውየው ኢስላም የመዋቡ (የመስተካከሉ) ምልክት ነው።"
(ቲርሙዚይና ሌሎችም ዘግበውታል)

٦٧- السَّامِنُ: عَنْ أَبِي هُرَيْرَةَ ﷺ قَالَ: قَالَ رَسُولُ اللهِ ﷺ ((مِنْ حُسْنِ إِسْلاَمِ الْمَرْءِ تَرْكُهُ مَالاَيَعْنِيهِ)) حَدِيثٌ حَسَنٌ رَوَاهُ التِّرْمِذِيُّ وَغَيْرُهُ.

ከሐዲሱ የምንማራቸው ቁምነገሮች

- ለዚህ ወይም ለመጭው ዓለም ጠቃሚ በሆነ ተግባር መጠመድና በማያስፈልጉ ጉዳዮች ውስጥ እየገቡ ጊዜን አለማባከን፥ እንዲሁም በሌሎች ሰዎች ጉዳይ ውስጥ እየገቡ ፀብ ያለመጫር ከሙስሊሞች መልካም ባሕሪያት ውስጥ ይካተታሉ። እንዲህ ዓይነቱ ባሕሪ ትክክለኛውን መሥመር የመያዝ ምልክት ነው።

68- ዑመር (ረ.ዐ) እንዳስተላለፉት ነቢዩ (ሶ.ዐ.ወ)፦"ሰውየው ሚስቱን ለምን እንደመታት አይጠየቅም።" ብለዋል።
(አቡዳውድና ሌሎችም)

٦٨- التاسع: عَنْ عُمَرَ ﷺ عَنِ النَّبِيِّ ﷺ قَالَ: ((لاَ يُسْأَلُ الرَّجُلُ فِيمَا ضَرَبَ امْرَأَتَهُ)) رَوَاهُ أَبُو دَاوُدَ وَغَيْرُهُ.

ከሐዲሱ የምንማራቸው ቁምነገሮች

- የባለትዳሮችን የግል ሚስጥር መጠበቅ ተገቢ ነው።
- ባል ሚስቱን ለምን እንደመታ አይጠየቅም። ምክንያቱም ለዚህ ያበቃቸው ጉዳይ መነገሩ የሚያላፍር ወይም መደበቅ ያለበት ሊሆን ስለሚችል። ጉዳዩ ለባልና በአላህ ተቆጣጣሪነት ላይ ላለው እምነት የሚተው ይሆናል። ሚስቱን ሥርዓት እንዲያስይዝ ታዟል። ግና ጉዳዩ ችሎት ፊት ከቀረበና መጠየቁ አስፈላጊ ሆኖ ከተገኘ እንዲያ ማድረጉ ይፈቀዳል። ፍትህን ለማስከበርና በመካከላቸው የተፈጠረውን ችግር ለመፍታት ሲባል።

ምዕራፍ 6

٦- بَابُ التَّقْوَى

ጥንቁቅነት (ተቅዋ)

قَالَ اللهُ تَعَالَى: ﴿يَاأَيُّهَا الَّذِينَ ءَامَنُوا اتَّقُوا اللهَ حَقَّ تُقَاتِهِ﴾ وَقَالَ تَعَالَى: ﴿فَاتَّقُوا اللهَ مَااسْتَطَعْتُمْ﴾ وهَذِهِ الآيَةُ مُبَيِّنَةٌ لِلْمُرَادِ مِنَ الأُولَى. وَقَالَ اللهُ تَعَالَى: ﴿يَاأَيُّهَا الَّذِينَ ءَامَنُوا اتَّقُوا اللهَ وَقُولُوا قَوْلاً سَدِيدًا﴾ والآيَاتُ فِي الأَمْرِ بِالتَّقْوَى كَثِيرَةٌ مَعْلُومَةٌ، وَقَالَ تَعَالَى: ﴿وَمَنْ يَتَّقِ اللهَ يَجْعَلْ لَهُ مَخْرَجًا وَيَرْزُقْهُ مِنْ حَيْثُ لاَيَحْتَسِبُ﴾ وَقَالَ تَعَالَى: ﴿إِنْ تَتَّقُوا اللهَ يَجْعَلْ لَكُمْ فُرْقَانًا وَيُكَفِّرْ عَنْكُمْ سَيِّئَاتِكُمْ وَيَغْفِرْ لَكُمْ وَاللهُ ذُو الْفَضْلِ الْعَظِيمِ﴾ والآيَاتُ فِي الْبَابِ كَثِيرَةٌ مَعْلُومَةٌ وَأَمَّا الأَحَادِيثُ.

"እላንተ ያመናችሁ ሆይ! አላህን ተገቢውን መጠንቀቅ ተጠንቀቁ፤" (አሊ-ዒምራን፡ 102)

"አላህንም የቻላችሁትን ያክል ፍሩት፤" (አል-ተጋቡን፡ 16)

"አላህንም የሚፈራ ሰው ሰርሱ መውጫን ያደርግለታል። ከማያስበውም በኩል ሲሳይን ይሰጠዋል፤" (አል-ጦላቅ፡ 2-3)

"እላንተ ያመናችሁ ሆይ! አላህን ብትፈሩ፡ የውነት መለያን ብርሃን ያደርግላችኋል፤ ከፉ ሥራዎቻችሁንም ከናንተ ላይ ያብስላችኋል፤ ለናንተም ይምራችኋል፤ አላህም የታላቅ ችሮታ ባለቤት ነው።" (አል-አንፋል፡ 29)

"ተቅዋን የሚመለከቱ የቁርአን አንቀጾች በርካታ ናቸው። ከሐዲስ ደግሞ ተከታዮቹን እናገኛለን፦

٦٩- فَالأَوَّلُ: عَنْ أَبِي هُرَيْرَةَ ﷺ قَالَ: قِيلَ يَارَسُولَ اللهِ، مَنْ أَكْرَمُ النَّاسِ؟ قَالَ: ((أَتْقَاهُمْ)) فَقَالُوا: لَيْسَ عَنْ هَذَا نَسْأَلُكَ، قَالَ: ((فَيُوسُفُ نَبِيُّ اللهِ ابْنُ نَبِيِّ اللهِ ابْنِ خَلِيلِ اللهِ)) قَالُوا: لَيْسَ عَنْ هَذَا نَسْأَلُكَ، قَالَ:((فَعَنْ مَعَادِنِ الْعَرَبِ تَسْأَلُونِي؟

69- አቡ ሁረይራ (ረ.ዐ) እንዳስተላለፉት፡ "የአላህ መልዕክተኛ ሆይ! ከሰዎች ሁሉ የተላቀው ማን ነው?" ተብለው መልዕክተኛው ተጠየቁ። "ይበልጥ ተቅዋ ያለው" ሲሉ መለሱ። "ስለዚህ አይደለም የጠየቅንዎት፤" ተባሉ። "ዩሱፍ -የአላህ ነቢይ፡ የአላህ ነቢይ ልጅ፡ የአላህ ወዳጅ ልጅ።" አሉ። "ስለዚህም አይደለም የጠየቅንዎት።" ተባሉ። "ከዐረብ ጉሣዎች

ውስጥ ነው የምትጠይቁኝ? ከመካከላችሁ በዘመነ-ድንቁርና (ጃሂሊያ) ምርጦች የነበሩት በኢስላምም ከናንተ መካከል ምርጦች ይሆናሉ፤ ኢስላምን ከተረዱት።" አሉ። (ቡኻሪና ሙስሊም)

خِيَارُهُمْ فِي الْجَاهِلِيَّةِ خِيَارُهُمْ فِي الإِسْلاَمِ إِذَا فَقُهُوا)) مُتَّفَقٌ عَلَيْهِ.

ከሐዲሱ የምንማራቸው ቁምነገሮች

- የሰው ልጅ በ"ተቅዋ" አማካይነት ከአላህ ዘንድ የላቀ ደረጃን ይጐናፀፋል።
- "ተቅዋ" ያለው ሰው በዱንያ መልካም ነገሮች ይጠቀማል። በአኼራም የከብር ደረጃን ይቸራል።
- አንድ ሰው አያት ቅድመ አያቶቹ የ"ተቅዋ" ባለሃብቶች ከሆኑና እርሱም የነርሱን ፈለግ ከተከተለ ለክብር ይበቃል።

70- አቡ ሰዒድ አል-ኹድሪይ (ረ.ዐ) እንዳስተላለፉት ነቢዩ (ሶ.ዐ.ወ) እንዲህ ሲሉ ተናግረዋል፦ "ይህች ዓለም (ዱንያ) ጣፋጭና አረንጓዴ ናት ። አላህ በዚህች ዓለም ውስጥ ወኪሉ አድርጓችኋል። ይህንን ተግባራችሁን (ኃላፊነታችሁን እንዴት እንደምትወጡ) ይመለከታል። ዱንያንና ሴትን ልጅ ተጠንቀቁ። የበኒ ኢስራኢል የመጀመሪያ ፈተና ሴት ልጅ ነበረች።" (ሙስሊም እንደዘገቡት)

٧٠- السَّابِعُ: عَنْ أَبِي سَعِيدٍ الْخُدْرِيِّ ﷺ عَنِ النَّبِيِّ ﷺ قَالَ: ((إِنَّ الدُّنْيَا حُلْوَةٌ خَضِرَةٌ، وَإِنَّ اللهَ مُسْتَخْلِفُكُمْ فِيهَا فَيَنْظُرُ كَيْفَ تَعْمَلُونَ، فَاتَّقُوا الدُّنْيَا وَاتَّقُوا النِّسَاءَ فَإِنَّ أَوَّلَ فِتْنَةِ بَنِي إِسْرَائِيلَ كَانَتْ فِي النِّسَاءِ)). رَوَاهُ مُسْلِمٌ.

ከሐዲሱ የምንማራቸው ቁምነገሮች

- ባዕድ ከሆኑ የወሲብ ስሜትን ሊያጭር ከሚችል ልቅ የሆነ የሁለቱ ፆታዎች ግንኙነትና ወሲብን ሊቀሰቅስ የሚችልን የሰውነት ክፍል ከማየት፣ ሚስት ከሆነች ደግሞ ከርሷ ጋር የሚደረገው ግንኙነት ከኃላፊነት እንዳይዘናጋ መጠንቀቅ። በሴቶች ከመፈተን ራስን መጠበቅ ያስፈልጋል።
- ካለፉት ሕዝቦች መማር ያስፈልጋል። በኒ ኢስራኢሉች ላይ የደረሰው ውድቀት ሁኔታዎች ከተሟሉ በሌሎች ሕዝቦች ላይም የማይከሰትበት ምክንያት አይኖርም።

71- ኢብን መስዑድ እንዳስተላለፉት (ረ.ዐ) የአላህ መልዕክተኛ (ሶ.ዐ.ወ)፦ "አላህ ሆይ! ምሪትን፣ ተቅዋን፣ ከሐራም መቆጠብንና ክብረትን እጠይቅሃለሁ።" ይሉ ነበር። (ሙስሊም እንደዘገቡት)

٧١- الثَّالِثُ: عَنِ ابْنِ مَسْعُودٍ ﷺ أَنَّ النَّبِيَّ ﷺ كَانَ يَقُولُ: ((اللَّهُمَّ إِنِّي أَسْأَلُكَ الْهُدَى وَالتُّقَى وَالْعَفَافَ وَالْغِنَى)) رَوَاهُ مُسْلِمٌ.

ከሐዲሱ የምንማራቸው ቁምነገሮች

- በማንኛውም ሁኔታ ወደ አላህ መመለስና እርሱን ብቻ መለመን ይገባል።
- አላህን ከማንም በላይ የሚያውቁትና የሚፈሩትን ነቢይ (ሶ.ዐ.ወ) ከአላህ የጠየቋቸው እነኛህ ማራኪ ባሕሪያት እጅግ ጠቃሚ እንደሆኑ ዘገባው ያስረዳል።

72- አቡ ጦሪፍ ዐዲይ ኢብን ሓቲም አጥ-ጧኢይ (ረ.ዐ) የአላህ መልዕክተኛ (ሶ.ዐ.ወ) ተከታዩን ሲናገሩ አድምጫለሁ በማለት አስተላልፈዋል፦ "መሐላን የፈፀመና መሐላው ከመሙላት መቆጠቡ አላህን ይበልጥ ያረካዋል የሚል እምነት ካደረበት የማለበትን ነገር ከመፈፀም ይቆጠብ።" (ሙስሊም እንደዘገቡት)

٧٢- الرَّابِعُ: عَنْ أَبِي طَرِيفٍ عَدِيِّ بْنِ حَاتِمٍ الطَّائِيِّ ﷺ قَالَ: سَمِعْتُ رَسُولَ اللهِ ﷺ يَقُولُ: ((مَنْ حَلَفَ عَلَى يَمِينٍ ثُمَّ رَأَى أَتْقَى لِلَّهِ مِنْهَا فَلْيَأْتِ التَّقْوَى)) رَوَاهُ مُسْلِمٌ.

ከሐዲሱ የምንማራቸው ቁምነገሮች

- "ተቅዋ" ግዴታ ነው።
- አንድን ኃጢአት ለመሥራት የቆረጠ ቢምል ቢገዘት እንኳ- ቅጣት (ከፋራ) በመክፈል መሐላውን ያብስ እንጂ ወንጀሉን መፈፀም ፈጽሞ የለበትም።

73- አቡ አማመት ሱደይ ኢብን ዐጅላን አል-ባሂሊይ (ረ.ዐ) የአላህ መልዕክተኛ የመሰናበቻ ሐጅ ዕለት ተከታዩን ንግግር ሲያሰሙ አድምጫለሁ በማለት አስተላልፈዋል፦ "ከጌታችሁ ጀንነት ትገቡ ዘንድ አላህን ፍሩ፣ አምስት ወቅት ሶላቶችን ስገዱ፣ ወር ረመዷንን ፁሙ፣ ከገንዘባችሁ ዘካን ስጡ። መሪዎቻችሁን ታዘዙ፣" (ቲርሙዚይ ዘግበውታል። "ሐሰኑን ሶሒሕ" ነው ብለውታል)

٧٣- الْخَامِسُ: عَنْ أَبِي أُمَامَةَ صُدَيِّ بْنِ عَجْلَانَ الْبَاهِلِيِّ ﷺ قَالَ: سَمِعْتُ رَسُولَ اللهِ ﷺ يَخْطُبُ فِي حَجَّةِ الْوَدَاعِ فَقَالَ: ((اتَّقُوا اللهَ، وَصَلُّوا خَمْسَكُمْ، وَصُومُوا شَهْرَكُمْ، وَأَدُّوا زَكَاةَ أَمْوَالِكُمْ، وَأَطِيعُوا أُمَرَاءَكُمْ، تَدْخُلُوا جَنَّةَ رَبِّكُمْ.)) رَوَاهُ التِّرْمِذِيُّ وَقَالَ حَدِيثٌ حَسَنٌ صَحِيحٌ.

ከሐዲሱ የምንማራቸው ቁምነገሮች

- እነኛህን ተግባራት ማከናወን አላህን የመፍራት ምልክት ነው። "ተቅዋ" ጀንነትን ለመጉናፀፍ ዓይነተኛ መሣሪያ ነው። በዚህች ዓለም ውስጥ ለአላህ መገበርከክና ለፍላጐቱ ማደር በመጭው ዓለም ለስኬት ያበቃል።
- በኢስላማዊ ሥርዓት የሚያስተዳድሩ የኢስላማዊ መንግስት መሪዎችን በወንጀል እስካላዘዙ ድረስ መታዘዝ ግዴታ ነው።

ምዕራፍ 7

ጥልቅ እምነት (የቂን) እና በአላህ መመካት (ተወኩል)

٧- بَابُ الْيَقِينِ وَالتَّوَكُلِ

አላህ እንዲህ ብሏል:-
"አማኞቹም አሕዛብን ባዩ ጊዜ፥ ይህ አላህና መልክተኛው የቀጠሩን ነው፤ አላህና መልክተኛውም እውነትን ተናገሩ፥ (የተናገሩት እውነት መሆኑ ተገለጠ) አሉ። (ይህ) እምነትንና መታዘዝንም እንጅ አልጨመረላቸውም።" (አል-አሕዛብ፥ 22)

"እነዚያ ሰዎቹ፥ ለነርሱ- ሰዎች ለናንተ (ጦርን) አከማችተዋልና ፍሩዋቸው ያሏቸው ና (ይህም) እምነትን የጨመረላቸው፤ በቂያችንም አላህ ነው፥ ምን ያምርም መጠጊያ! ያሉ ናቸው። ከአላህም በኾነ ፀጋና ችሮታ ክፉ ነገር ያልነካቸው ኾነው ተመለሱ፤ የአላህንም ውዴታ ተከትተሉ። አላህም የታላቅ ችሮታ ባለቤት ነው።" (አሊ-ዒምራን፥ 173-174)

"በዚያም በማይሞተው ሕያው አምላክ ላይ ተመካ፤" (አል-ፉርቃን፥ 58)

"...በአላህም ላይ ብቻ ምእምናን ይመኩ።" (አሊ-ዒምራን፥ 160)

"ቁርጥ ሐሳብም ባደረግህ ጊዜ በአላህ ላይ ተመካ።" (አሊ-ዒምራን፥ 159)

"...በአላህም ላይ የሚጠጋ ሰው፥ እርሱ በቂው ነው፤" (አል-ጦላቅ፥ 3)

قَالَ اللهُ تَعَالَى: ﴿وَلَمَّا رَأَى الْمُؤْمِنُونَ الأَحْزَابَ قَالُوا: هَذَا مَاوَعَدَنَا اللهُ وَرَسُولُهُ، وَصَدَقَ اللهُ وَرَسُولُهُ وَمَا زَادَهُمْ إِلاَّ إِيمَانًا وَتَسْلِيمًا﴾ وَقَالَ تَعَالَى: ﴿الَّذِينَ قَالَ لَهُمُ النَّاسُ: إِنَّ النَّاسَ قَدْ جَمَعُوا لَكُمْ فَاخْشَوْهُمْ فَزَادَهُمْ إِيمَانًا وَقَالُوا: حَسْبُنَا اللهُ وَنِعْمَ الْوَكِيلُ. فَانْقَلَبُوا بِنِعْمَةٍ مِنَ اللهِ وَفَضْلٍ لَمْ يَمْسَسْهُمْ سُوءٌ وَاتَّبَعُوا رِضْوَانَ اللهِ وَاللهُ ذُو فَضْلٍ عَظِيمٍ﴾ وَقَالَ تَعَالَى: ﴿وَتَوَكَّلْ عَلَى الْحَيِّ الَّذِي لاَ يَمُوتُ﴾ وَقَالَ تَعَالَى: ﴿وَعَلَى اللهِ فَلْيَتَوَكَّلِ الْمُؤْمِنُونَ﴾ وَقَالَ تَعَالَى: ﴿فَإِذَا عَزَمْتَ فَتَوَكَّلْ عَلَى اللهِ﴾ وَالآيَاتُ فِي الأَمْرِ بِالتَّوَكُلِ كَثِيرَةٌ مَعْلُومَةٌ وَقَالَ تَعَالَى: ﴿وَمَنْ يَتَوَكَّلْ عَلَى اللهِ فَهُوَ حَسْبُهُ﴾ وَقَالَ تَعَالَى: ﴿إِنَّمَا

"ፍፁም ምእምናን፡ እነዚያ አላህ በተ ወሳ ጊዜ ልቦቻቸው የሚፈሩት፤ በነሱም ላይ አንቀጾቻችን በተነበቡ ጊዜ እምነትን የሚጨምሩላቸው፡ በጌታቸው ላይ ብቻ የሚመኩት ናቸው።" (አል-አንፋል፡ 2)

الْمُؤْمِنُونَ الَّذِينَ إِذَا ذُكِرَ اللهُ وَجِلَتْ قُلُوبُهُمْ وَإِذَا تُلِيَتْ عَلَيْهِمْ آيَاتُهُ زَادَتْهُمْ إِيمَانًا، وَعَلَى رَبِّهِمْ يَتَوَكَّلُونَ.﴾ والآيَاتُ فِي فَضْلِ التَّوَكُّلِ كَثِيرَةٌ مَعْرُوفَةٌ وَأَمَّا الأَحَادِيثُ.

በአላህ ላይ መመካትን (ተወኩልን) አስመልክቶ የተነገሩ የቁርአን አንቀ ጾች በርካታ ናቸው። ከሐዲስ ደግሞ ተከታዮቹ ተወስተዋል፡-

٧٤- فَالأَوَّلُ: عَنْ ابْنِ عَبَّاسٍ ﷺ قَالَ: قَالَ رَسُولُ اللهِ ﷺ: ((عُرِضَتْ عَلَيَّ الأُمَمُ، فَرَأَيْتُ النَّبِيَّ وَمَعَهُ الرُّهَيْطُ وَالنَّبِيَّ وَمَعَهُ الرَّجُلُ وَالرَّجُلاَنِ وَالنَّبِيَّ وَلَيْسَ مَعَهُ أَحَدٌ إِذْ رُفِعَ لِي سَوَادٌ عَظِيمٌ، فَظَنَنْتُ أَنَّهُمْ أُمَّتِي، فَقِيلَ لِي: هَذَا مُوسَى وَقَوْمُهُ، وَلَكِنِ انْظُرْ إِلَى الأُفُقِ، فَنَظَرْتُ فَإِذَا سَوَادٌ عَظِيمٌ، فَقِيلَ لِي: انْظُرْ إِلَى الأُفُقِ الآخَرِ فَإِذَا سَوَادٌ عَظِيمٌ فَقِيلَ لِي هَذِهِ أُمَّتُكَ وَمَعَهُمْ سَبْعُونَ أَلْفًا يَدْخُلُونَ الْجَنَّةَ بِغَيْرِ حِسَابٍ وَلاَ عَذَابٍ)) ثُمَّ نَهَضَ فَدَخَلَ مَنْزِلَهُ، فَخَاضَ النَّاسُ فِي أُولَئِكَ الَّذِينَ يَدْخُلُونَ الْجَنَّةَ بِغَيْرِ حِسَابٍ وَلاَ عَذَابٍ، فَقَالَ بَعْضُهُمْ: فَلَعَلَّهُمُ الَّذِينَ صَحِبُوا رَسُولَ اللهِ ﷺ وَقَالَ بَعْضُهُمْ: فَلَعَلَّهُمُ الَّذِينَ وُلِدُوا فِي الإِسْلاَمِ فَلَمْ

74- ኢብን ዐብባስ (ረ.ዐ) እንዳስተላለፉት የአላህ መልዕክተኛ (ሶ.ዐ.ወ) እንዲህ ብለዋል፡- "ሕዝቦችህ ተገለውልኝ፣ አንዱን ነቢይ ከጥቂት ተከታዮች ጋር፣ ሌላውን ነቢይ ከአንድ ወይም ሁለት ሰዎች ጋር፣ ሌላኛውን ደግሞ አንድም ተከ ታይ የሌለው ሆኖ ብቻውን ተመለከ ትኩ። የኔ ተከታዮች እንደሆነ ገመ ትኩ። "ይህ ሙሳና ተከታዮቹ ናቸው። ነገር ግን ወደ ሌላኛው አድማስ ተመልከት።" ተባልኩ። በርካታ አባላትን ያቀፈ አንድ የሰዎች ስብስብ ተመለከትኩ። "ወደ ሌላኛው አድማስ ተመልከት።" ተባልኩ። በርካታ አባላ ትን ያቀፈ የሰዎች ስብስብ ተመለከ ትኩ። "እነኝህ ተከታዮችህ ናቸው። ከነርሱ መሐከል ያለምንም ጥያቄና ቅጣት ጀንነት የሚገቡ ሰዎች አሉ።" ተባልኩ።" ነቢዩ (ሶ.ዐ.ወ) ይህን እንደ ተናገሩ ተነስተው ወደ ቤታቸው ገቡ። ስለነዚያ ያለምንም ጥያቄና ቅጣት ጀንነት ስለሚገቡ ሰዎች ታዳሚው ይነጋገር ጀመር። ከፊሎቹ፡- "የነቢዩ (ሶ.ዐ.ወ) ባልደረቦች ሊሆኑ ይችላሉ።" የሚል አስተያየት ሰጡ። ከፊሎቹ ደግሞ፡- "ምናልባትም በዘመነ ኢስላም

يُشْرِكُوا بِاللهِ شَيْئًا -وَذَكَرُوا أَشْيَاءَ- فَخَرَجَ عَلَيْهِمْ رَسُولُ اللهِ ﷺ فَقَالَ: ((مَا الَّذِي تَخُوضُونَ فِيهِ؟)) فَأَخْبَرُوهُ فَقَالَ: ((هُمُ الَّذِينَ لاَ يَرْقُونَ، وَلاَ يَسْتَرْقُونَ، وَلاَ يَتَطَيَّرُونَ، وَعَلَى رَبِّهِمْ يَتَوَكَّلُونَ)) فَقَامَ عُكَّاشَةُ بْنُ مِحْصَنٍ فَقَالَ ادْعُوا اللهَ أَنْ يَجْعَلَنِي مِنْهُمْ، فَقَالَ: ((أَنْتَ مِنْهُمْ)) ثُمَّ قَامَ رَجُلٌ آخَرُ فَقَالَ: ادْعُ اللهَ أَنْ يَجْعَلَنِي مِنْهُمْ، فَقَالَ: ((سَبَقَكَ بِهَا عُكَّاشَةُ)) مُتَّفَقٌ عَلَيْهِ.

የተወለዱና በአላህ አንዳችም ነገር ያላጋሩ።" ሊሆኑ እንደሚችሉ ገመቱ። ሌሎች ግምቶችም ተሰነዘሩ። በዚህ ወቅት የአላህ መልዕክተኛ (ሶ.ዐ.ወ) ከነበሩበት ክፍል በመውጣት፡- "ስለምን እየተነጋገራችሁ ነው?" ሲሉ ታዳሚዎችን ጠየቁ። የሚነጋገሩበትን ጉዳይ ነገሯቸው። "እነዚያ (ያለምንም ጥያቄና ቅጣት ጀንነት የሚገቡ ሰባ ሺህ ሰዎች) የማይደግሙና የማያስደግሙ፣ በገድ የማያምኑና በአላህ ብቻ የሚመኩ ናቸው።" አሉ። ዑካሸህ ኢብን ሚሕሶን፡- "ከነርሱ ያደርገኝ ዘንድ አላህን ይማፀኑልኝ።" አላቸው። "አንተ ከነርሱ ነህ።" አሉት። ሌላ ሰው ቆመና፡- "እኔንም ከነርሱ ያደርገኝ ዘንድ አላህን ይማፀኑልኝ።" አላቸው። "ዑካሸህ ቀድሞሃል።" አሉት። (ቡኻሪና ሙስሊም)

ከሐዲሱ የምንማራቸው ቁምነገሮች

- ይህ መገለጽ የነቢዩን (ሶ.ዐ.ወ) ልቅና ያመለክታል። በሕልማቸው ሊሆን ይችላል የተገለፀላቸው። የነቢያት ሕልም እውነት ነው። ወይንም የኢስራእ ጉዞ ባደረጉበት ሌሊት በእውን አለያም በሌላ መልኩ ሊሆን ይችላል። አላህ ለነቢያት ከሌሎች ሰዎች የተለዩ ነገሮችን አድርጉላቸዋል።
- አላህ ነቢዩን (ሶ.ዐ.ወ) ከሌሎች ነቢያት ማላቁ እዚህ ዘገባ ላይ ተመልክቷል። ተከታዮቻቸው ከየትኛውም ነቢይ ተከታይ ይበልጥ በርካታ ናቸው።
- በአላህ መመካት (ተወኩል) ያለው ጠቀሜታና አላህ በርሱ ለሚመኩ ሰዎች ያዘጋጀውን የላቀ ምንዳ ከዚህ ዘገባ ላይ ተወስቷል።
- የደረሰን ክፉ ነገር ለማስወገድ ወይም ይደርሳል ተብሉ የሚታሰበውን እንዳይደርስ ለመከላከል ከነቢዩ (ሶ.ዐ.ወ) የተገኘውን ስልትና የቁርአን አንቀጾችን መጠቀም በኢስላም ሕጋዊ (መሸሩዕ) ነው። ግና የኢማንን ጥራትና የተወከሉን ምሉዕነት የሚከውን የጃሂሊያ አጉል ልማድና ድግምት ግን ኢስላም ፈጽሞ አይፈቅድም።
- በገድ ማመን የተከለከለ ነው።

٧٥- الثَّانِي: عَنِ ابْنِ عَبَّاسٍ رضي الله عنهما أَيْضًا أَنَّ رَسُولَ اللهِ ﷺ كَانَ يَقُولُ: ((اللَّهُمَّ

75- ኢብን ዐብባስ (ረ.ዐ) እንዳስተላለፉት የአላህ መልዕክተኛ (ሶ.ዐ.ወ) ተከታዩን ይሉ ነበር፡- "አላህ ሆይ! ለአንተ እጅ

ሰጥቻለሁ፣ ባንተ አምኛለሁ፣ በአንተ ላይ ተመክቻለሁ፣ ወዳንተው ተመልሻለሁ። (ጠላቶችህን) ስለ አንተው ተሟግቻለሁ። አላህ ሆይ! ከአንተ ሌላ አምላክ የለም፣ እንዳታጠመኝ በኃይልህና በሥልጣንህ እጠበቃለሁ። አንተ ራስክን የቻልክና የማትሞት ሕያው አምላክ ነህ። ሰዎችና አጋንንቶች ግን ይሞታሉ።" (ቡኻሪና ሙስሊም)

لَكَ أَسْلَمْتُ، وَبِكَ آمَنْتُ، وَعَلَيْكَ تَوَكَّلْتُ، وَإِلَيْكَ أَنَبْتُ، وَبِكَ خَاصَمْتُ، اللَّهُمَّ إِنِّي أَعُوذُ بِعِزَّتِكَ؛ لَا إِلَهَ إِلَّا أَنْتَ، أَنْ تُضِلَّنِي، أَنْتَ الْحَيُّ الَّذِي لَا يَمُوتُ وَالْجِنُّ وَالْإِنْسُ يَمُوتُونَ)) مُتَّفَقٌ عَلَيْهِ وَهَذَا لَفْظُ مُسْلِمٍ وَاخْتَصَرَهُ الْبُخَارِيُّ.

ይህ ከሙስሊም ዘገባ ላይ የተወሰደ ነው። ቡኻሪ አሳጥረው አስፍረውታል።

ከሐዲሱ የምንማራቸው ቁምነገሮች

- በአላህ መመካትና ጥበቃን ከርሱ ብቻ መሻት ግዴታ ነው። አላህ የምሉዕ ባሕሪያት ባለሃብት በመሆኑ እርሱ ብቻ ነው ሊመኩበት የሚገባ። ፍጡራን ሁሉ አቅመቢስና ደካማ፥ ሟችችም እንደመሆናቸው መመኪያ ሊሆኑ አይችሉም።
- በነኝህ የእምነት ፅናትና ጥልቀት የሚገልጹ አጠቃላይ ማራኪ ቃላት ዱዓ በማድረግ የነቢዩን (ሶ.ዐ.ወ) አርአያነት ልንከተል ይገባል።

٧٦- الثالث: عَنِ ابْنِ عَبَّاسٍ ﷺ أَيْضًا قَالَ: ((حَسْبُنَا اللهُ وَنِعْمَ الْوَكِيلُ)) قَالَهَا إِبْرَاهِيمُ ﷺ حِينَ أُلْقِيَ فِي النَّارِ، وَقَالَهَا مُحَمَّدٌ ﷺ حِينَ قَالُوا: إِنَّ النَّاسَ قَدْ جَمَعُوا لَكُمْ فَاخْشَوْهُمْ، فَزَادَهُمْ إِيمَانًا وَقَالُوا: ((حَسْبُنَا اللهُ وَنِعْمَ الْوَكِيلُ)) رَوَاهُ الْبُخَارِيُّ

76- ኢብን ዐባስ (ረ.ዐ) እንዲህ ሲሉ አስተላልፈዋል፦ "ሐስቢየላህ ወኒዕመል ወኪል" (አላህ በቂያችን ነው፣ በርሱ መመካት ምን አማረ!) የሚለውን ቃል ነቢዩ ኢብራሂም (ሶ.ዐ.ወ) እሳት ውስጥ የተጣሉ ዕለት ብለውታል። ነቢዩ ሙሐመድ (ሶ.ዐ.ወ) "ሰዎች ጦር አከማችተውላችኋልና ፍሯቸው።" ባሏቸው ጊዜ ሁኔታው ኢማናቸውን ጨመረላቸው፣ "ሐስቢየላህ ወኒዕመል ወኪል" አሉም። (ቡኻሪ እንደዘገቡት)

وَفِي رِوَايَةٍ لَهُ عَنِ ابْنِ عَبَّاسٍ ﷺ قَالَ: كَانَ آخِرَ قَوْلِ إِبْرَاهِيمَ ﷺ حِينَ أُلْقِيَ فِي النَّارِ: ((حَسْبِيَ اللهُ وَنِعْمَ الْوَكِيلُ)) رَوَاهُ الْبُخَارِيُّ.

ኢብን ዐባስን (ረ.ዐ) ጠቅሰው ቡኻሪ ባሰፈሩት ሌላ ዘገባ ላይ ደግሞ፦

"ኢብራሂም ወደ እሳት በተወረወሩበት ዕለት የተናገሩት የመጨረሻ

ቃል "ሐስቢየሏህ ወኒዕመል ወኪል" ነበር።" የሚል ተወስቷል።

ከሐዲሱ የምንማራቸው ቁምነገሮች

- በአላህ መመካት ያለው ትሩፋትና በጭንቅ ሰዓት አስፈላጊነቱ።
- በአላህ ላይ በመመካት የነቢያትንና የአላህ ወዳጆችን እርአያነት መከተል።

77- አቡ ሁረይራ (ረ.ዐ) እንዳስተላለፉት የአላህ መልዕክተኛ (ሶ.ዐ.ወ)፦ "ልቦናዎ ቻቸው እንደ በራሪ አዕዋፋት ልቦና የሆኑ አያሌ ሰዎች ጀንነት ይገባሉ።" ብለዋል። (ሙስሊም እንደዘገቡት)

٧٧- الـرَّابِعُ: عَنْ أَبِي هُرَيْرَةَ ﷺ عَنِ النَّـبِيِّ ﷺ قَالَ: ((يَدْخُلُ الْجَنَّةَ أَقْوَامٌ أَفْئِدَتُهُمْ مِثْلُ أَفْئِدَةِ الطَّيْرِ)) رَوَاهُ مُسْلِمٌ.

"በአላህ ላይ የሚመኩ" ሰዎችን ለማመልከት እንደሆነ ተወስቷል። "ልቦናቸው በአላህ ፍርሃት የለሰለሰ" የሚል ትርጓሜም ተሰጥቶታል።

ከሐዲሱ የምንማራቸው ቁምነገሮች

- በአላህ የመመካትና የልቦና ልስላሴ ጠቀሜታ ጀንነትን ለመጐናፀፍ ከሚያስችሉ ምክንያቶቹ ውስጥ ናቸውና።

78- ጃቢር (ረ.ዐ) እንዳስተላለፉት፦ እሳቸው (ጃቢር) ከአላህ መልዕክተኛ (ሶ.ዐ.ወ) ጋር ወደ "ነጅድ" አቅጣጫ ዘመቱ። መልዕክተኛው (ሶ.ዐ.ወ) ከዘመቻ ሲመለሱ እሾሃማ ከሆነ ሸለቆ አካባቢ ሲደርሱ የእኩለ ቀን የእረፍት ሰዓት (ቀይሉላ) ደረሰባቸው። እዚሁ ሥፍራ ላይ ሰፈሩ። ሰዎች በየዛፎቹ ጥላ ሥር ተጠለሉ። የአላህ መልዕክተኛ ከአንድ እሾሃማ ዛፍ ሥር አረፉ፣ ጦራቸውን ከዛፉ ላይ አንጠልጥለው። እንቅልፍ አሸለበን። ብዙም ሳይቆይ የአላህ መልዕክተኛ ጠሩን። አንድ "አዕራቢይ" ከጉናቸው አለ። "ይህ ሰው ተኝቼ እያለሁ በኔ ላይ ጉራዴ

٧٨- الْخَـامِسُ: عَنْ جَابِرٍ ﷺ أَنَّهُ غَزَا مَـعَ النَّـبِيِّ ﷺ قِبَلَ نَجْد، فَلَمَّا قَفَلَ رَسُـولُ اللهِ ﷺ قَفَلَ مَعَهُمْ فَأَدْرَكَتْهُمُ الْقَائِـلَةُ فِـي وَادٍ كَثِيرِ الْعِضَاهِ، فَنَزَلَ رَسُولُ اللهِ ﷺ وَتَفَرَّقَ النَّاسُ يَسْتَظِلُّونَ بِالشَّـجَرِ، وَنَزَلَ رَسُولُ اللهِ ﷺ تَحْتَ سَمُرَةٍ، فَعَلَّقَ بِهَا سَيْفَهُ وَنِمْنَا نَوْمَةً فَإِذَا رَسُـولُ اللهِ ﷺ يَدْعُونَـا وَإِذَا عِـنْدَهُ أَعْرَابِيٌّ، فَقَالَ: ((إِنَّ هَذَا اخْتَرَطَ عَلَيَّ

سَيْفِي وَأَنَا نَائِمٌ، فَاسْتَيْقَظْتُ وَهُوَ فِي يَدِهِ صَلْتًا، قَالَ: مَنْ يَمْنَعُكَ مِنِّي؟ قُلْتُ: اللهُ -ثَلاَثًا- وَلَمْ يُعَاقِبْهُ وَجَلَسَ))

مُتَّفَقٌ عَلَيْهِ.

وَفِي رِوَايَةٍ:- قَالَ جَابِرٌ: كُنَّا مَعَ رَسُولِ اللهِ ﷺ بِذَاتِ الرِّقَاعِ، فَإِذَا أَتَيْنَا عَلَى شَجَرَةٍ ظَلِيلَةٍ تَرَكْنَاهَا لِرَسُولِ اللهِ ﷺ فَجَاءَ رَجُلٌ مِنَ الْمُشْرِكِينَ وَسَيْفُ رَسُولِ اللهِ ﷺ مُعَلَّقٌ بِالشَّجَرَةِ فَاخْتَرَطَهُ فَقَالَ: تَخَافُنِي؟ قَالَ: لاَ، قَالَ: فَمَنْ يَمْنَعُكَ مِنِّي؟ قَالَ: ((اللهُ)).

وَفِي رِوَايَةٍ أَبِي بَكْرٍ الإِسْمَاعِيلِيِّ فِي صَحِيحِهِ قَالَ: مَنْ يَمْنَعُكَ مِنِّي؟ قَالَ: اللهُ. فَسَقَطَ السَّيْفُ مِنْ يَدِهِ، فَأَخَذَ رَسُولُ اللهِ ﷺ السَّيْفَ، فَقَالَ: مَنْ يَمْنَعُكَ مِنِّي؟ فَقَالَ: كُنْ خَيْرَ آخِذٍ. فَقَالَ: تَشْهَدُ أَنْ لاَ إِلَهَ إِلاَّ اللهُ وَأَنِّي رَسُولُ اللهِ؟ قَالَ: لاَ، وَلَكِنِّي أُعَاهِدُكَ أَنْ لاَ أُقَاتِلَكَ وَلاَ أَكُونَ مَعَ قَوْمٍ يُقَاتِلُونَكَ. فَخَلَّى سَبِيلَهُ فَأَتَى أَصْحَابَهُ فَقَالَ: جِئْتُكُمْ مِنْ عِنْدِ خَيْرِ النَّاسِ.

መዘዘ። ሾተሌን ከአፎቱ መዞ አየሁት፦ "ከኔ ማን ያድንሃል?" አለኝ። "አላህ" አልኩት -ሦስት ጊዜ።" ካሉ በኋላ ተቀመጡ። አልተቆጡትም።

(ቡኻሪና ሙስሊም)

በሌላ ዘገባ ደግሞ ጃቢር እንዲህ ሲሉ ግስጥላለፋቸው ተወስቷል፦

"'ዛተ ሪቃዕ" ዘመቻ ወቅት ከአላህ መልዕክተኛ (ሶ.ዐ.ወ) ጋር ነበርን። ጥላማ ከሆነ ዛፍ ደረስን። ለአላህ መልዕክተኛ (ሶ.ዐ.ወ) ተውንላቸው። አንድ ሙሽሪክ ሰውዬ መጣ። የአላህ መልዕክተኛ (ሶ.ዐ.ወ) ጉራዴ ከዛፉ ላይ ተንጠልጥሏል። ጉራዴውን በመልዕክተኛው ላይ አነጣጠረና፦ "ትፈራኛለህ?" አላቸው። "አልፈራህም" ሲሉ መለሱለት። "ከኔ ማን ያድንሃል?" አላቸው። "አላህ" አሉ።"

አቡበክር ኢስማዒል ባስተላለፉት "ሶሒሕ" ዘገባ ደግሞ፦

"ከኔ ማን ያድንሃል?" አላቸው። "አላህ" አሉት። ጉራዴው ከእጁ ወደቀ፣ የአላህ መልዕክተኛ (ሶ.ዐ.ወ) ጉራዴውን ያዙና፦ "ከኔ ማን ያድንሃል?' አሉ። "ክፉን በክፉ የማይመልስ ደግ ወዳጅ ሁን።" አላቸው። "ከአላህ ሌላ አምላክ አለመኖሩንና እኔ የአላህ መልዕክተኛ መሆኔን ትመሰክራለህን?" አሉት። "ይህንን አልፈጽምም። ግና ካንተ ጋር ላልዋጋና አንተን ከሚወጉህ ሰዎች ጋር ላላብር ቃል እገባልሃለሁ።" አላቸው። ከባልደረቦቹ ዘንድ ሄደና፦ "ከሰው ሁሉ ይበልጥ ደግ ከሆነ ሰው ዘንድ ነበርኩ።" አላቸው።

ከሐዲሱ የምንማራቸው ቁምነገሮች

- ነቢዩ (ሶ.ዐ.ወ) በአደጋ ወቅት የነበራቸው ጀግንነትና ፅናት፥ በአላህ ላይ የነበራቸው እምነትና እውነተኛ ተወኩላቸው፣ ወደ አላህ የመመለስ ችሎታቸውም።
- በአደጋ ወቅት በአላህ መመካት የሚያስገኘው መልካም ውጤት።
- የነቢዩ ይቅር ባይነትና መልካም ባሕሪያቸው፥ ከብቀላ የራቁ አስተዋይ መሆናቸው። እንዲሁም የሰዎችን ልቦና ከሐቅ ጋር ለማስተዋወቅ ይፈጽሙት የነበረ ብስለት የተሞላበት ከንውን።

٧٩- السَّادِس: عَنْ عُمَرَ ﷺ قَالَ: سَمِعْتُ رَسُولَ اللهِ ﷺ يَقُولُ:((لَوْ أَنَّكُمْ تَتَوَكَّلُونَ عَلَى اللهِ حَقَّ تَوَكُّلِهِ لَرَزَقَكُمْ كَمَا يَرْزُقُ الطَّيْرَ تَغْدُوا خِمَاصًا وَتَرُوحُ بِطَانًا)). رَوَاهُ التِّرْمِذِيُّ وَقَالَ حَدِيثٌ حَسَنٌ.

79- የአላህ መልዕክተኛ (ሶ.ዐ.ወ) ተከታዩን ሲናገሩ አድምጫለሁ በማለት ዑመር (ረ.ዐ) አስተላልፈዋል፦ "በአላህ ላይ እውነተኛ መመካትን ብትመኩ ኖሮ፥ በራሪ አዕዋፍን እንደሚመግብ እናንተንም ይመግብ ነበር። ማለዳ ባዶ ሆዷን ትወጣለች። ሆዷን ሞልታ ትመላለች።" (ቲርመዚይ ዘግበውታል፣ "ሐሰን" ነውም ብለዋል)

ከሐዲሱ የምንማራቸው ቁምነገሮች

- በእያንዳንዱ ጉዳይ ላይ በአላህ መመካት እንደሚገባ።
- "ሪዝቅ" ለማግኘት ሰበብ የሚሆኑ ነገሮችን አለመዘንጋት፣ በአላህ ከመመካት ጋር፣ እንደ በራሪ አዕዋፋት። እንዲሁ አይቀመጡም። ምግባቸውን ለማግኘት ይንቀሳቀሳሉ።

٨٠- السابع: عَنْ أَبِي عُمَارَةَ الْبَرَاءِ ابْنِ عَازِبٍ ﷺ قَالَ: قَالَ رَسُولُ اللهِ ﷺ: ((يَافُلَانُ إِذَا أَوَيْتَ إِلَى فِرَاشِكَ فَقُلْ: اللَّهُمَّ أَسْلَمْتُ نَفْسِي إِلَيْكَ، وَوَجَّهْتُ وَجْهِي إِلَيْكَ، وَفَوَّضْتُ أَمْرِي إِلَيْكَ، وَأَلْجَأْتُ ظَهْرِي إِلَيْكَ، رَغْبَةً وَرَهْبَةً إِلَيْكَ، لَامَلْجَأَ وَلَا مَنْجَا مِنْكَ إِلَّا إِلَيْكَ، آمَنْتُ بِكِتَابِكَ الَّذِي أَنْزَلْتَ،

80- አቡ ዒማረህና በራእ ኢብን ዓዚብ (ረ.ዐ) እንዳስተላለፉት የአላህ መልዕክተኛ (ሶ.ዐ.ወ) እንዲህ ሲሉ ተናግረዋል፦ "እገሌ ሆይ! ወደ መኝታህ በምትሄድበት ወቅት፦ "አላህ ሆይ! ነፍሴን ለአንተ አስረክቤያለሁ። ሁለ ነገሬን ወደ አንተ አስጠግቼያለሁ። ጀርባዬን ወደ አንተ መልሻለሁ። (ትሩፋትህን) በመከጀልና (ቁጣህን) በመፍራት። ከአንተ (ቅጣት) ነጃ መውጫና መመለሻ ከአንተ ውጭ ሌላ ጋይል የለም። ባወረድከው መጽሐፍ አምኛለሁ። በላክከው ነቢይም አምኛለሁ።" በል። ይህንን ባልከበት

وَنَبِيِّكَ الَّذِى أَرْسَلْتَ، فَإِنَّكَ إِنْ مِتَّ مِنْ لَيْلَتِكَ مِتَّ عَلَى الْفِطْرَةِ وَإِنْ أَصْبَحْتَ أَصَبْتَ خَيْرًا)) مُتَّفَقٌ عَلَيْهِ.

وَفِى رِوَايَةٍ فِى الصَّحِيحَيْنِ عَنِ الْبَرَاءِ قَالَ: قَالَ لِى رَسُولُ اللهِ ﷺ: ((إِذَا أَتَيْتَ مَضْجَعَكَ فَتَوَضَّأْ وُضُوءَكَ لِلصَّلَاةِ، ثُمَّ اضْطَجِعْ عَلَى شِقِّكَ الْأَيْمَنِ وَقُلْ)) وَذَكَرَ نَحْوَهُ ثُمَّ قَالَ: ((وَاجْعَلْهُنَّ آخِرَ مَاتَقُولُ)).

ሌሊት ብትሞት በተፈጥሮ ማንነትህ (ፊጥራህ) ላይ ሞትክ። በሕይወት ከነጋህም በመልካም ሁኔታ አነጋህ።"
(ቡኻሪና ሙስሊም)

በሌላ ቡኻሪና ሙስሊም በራእን ጠቅሰው ባስፈሩት ዘገባ ላይ እንደተወሳው የአላህ መልዕክተኛ (ሶ.ዐ.ወ) እንዲህ ብለዋል፦

"ወደ መኝታህ በምትመጣበት ወቅት ለሶላት የምታደርገውን ዓይነት ውዱእ አድርግ። ከዚያም በቀኝ ጉንህ ተጋደምና እንዲህ በል።" በማለት ከላይ የተጠቀሰውን "ዱዓ" (ዚክር) አወሱ። ከዚያም፦ "እነኝህን ቃላት የንግግርህ መጭሻ አድርጋቸው።" አሉ።

ከሐዲሱ የምንማራቸው ቁምነገሮች

- በማንኛውም ጉዳይ ወደ አላህ የመመለስ አስፈላጊነት።
- በየቀኑ ከአላህ ጋር ያለን ቃልኪዳን ማደስና ከኢስላም ጋር የሚኖረን ግንኙነት በንግግርም፥ በተግባርም ማጠናከር።
- እነኝህ ከላይ የተጠቀሱ አባባሎችን ሁልየም ወደ መኝታ ሲሄዱ ማለትና የንግግርም መጭሻ ማድረግ። የኢማንንና የየቂንን ትርጓሜ ያካተቱ፥ ከአላህ ጋር ያለ ግንኙነት መልካም መሆኑን የሚያመለክቱ አባባሎች ናቸው።
- ወደ መኝታ ሲሄዱ ውዱእ ማድረግ ተገቢ ነው፤ በምሉዕ ንጽሕና ለተመኛት።

٨١- الثامن: عَنْ أَبِى بَكْرٍ الصِّدِّيقِ ﷺ عَبْدِ اللهِ ابْنِ عُثْمَانَ بْنِ عَامِرِ بْنِ عُمَرَ بْنِ كَعْبِ بْنِ سَعْدِ بْنِ تَيْمِ بْنِ مُرَّةَ بْنِ كَعْبِ بْنِ لُؤَيِّ ابْنِ غَالِبٍ الْقُرَيْشِيِّ التَّيْمِيِّ ﷺ -وَهُوَ وَأَبَوَاهُ وَأُمُّهُ صَحَابَةٌ- ﷺ قَالَ: نَظَرْتُ إِلَى أَقْدَامِ الْمُشْرِكِينَ وَنَحْنُ فِى الْغَارِ وَهُمْ عَلَى رُءُوسِنَا، فَقُلْتُ: يَارَسُولَ اللهِ، لَوْ أَنَّ أَحَدَهُمْ نَظَرَ تَحْتَ قَدَمَيْهِ لَأَبْصَرَنَا. فَقَالَ: ((مَاظَنُّكَ يَا أَبَا بَكْرٍ بِاثْنَيْنِ اللهُ ثَالِثُهُمَا)) مُتَّفَقٌ عَلَيْهِ.

81- አቡበክር አስ-ሲዲቅ (ረ.ዐ) -እርሳቸውና አባታቸውና እናታቸው የነቢዩ ባልደረቦች ነበሩ- እንዲህ ሲሉ አስተላልፈዋል፦ "(እኔና የአላህ መልዕክተኛ (ሶ.ዐ.ወ)) ዋሻ ውስጥ እያለን ሙሽሪኮችን አየኋቸው። በላያችን ላይ ነበሩ። "የአላህ መልዕክተኛ ሆይ! ከመካከላቸው አንዱ ወደ እግሮቹ አቅጣጫ ቢመለከት ሊያየን ይችላል።" አልኳቸው። "አቡበክር ሆይ! አላህ አብሯቸው ባልለ ሁለት ሰዎች ላይ ምን ዓይነት ጥርጣሬና ስጋት ነው የሚያድርብህ?" አሉኝ።"
(ቡኻሪና ሙስሊም)

ከሐዲሱ የምንማራቸው ቁምነገሮች

- ተገቢውን የጥንቃቄ እርምጃ ከወሰዱ በኋላ የአላህን ጥበቃና እንክብካቤ መማፀን ግዴታ (ዋጂብ) መሆኑ።
- አቡበክር ለረሱል (ሶ.ዐ.ወ) የነበራቸው ከፍተኛ ፍቅርና በጠላት እጅ ወድቀገሮው ተልዕኳቸው በእንጭጩ እንዳይቀጭ የነበራቸው ከፍተኛ ስጋት።
- አላህ ለነቢያትና ፈለጋቸውን ለተከተሉ ሁሉ የሚያደርገው ጥበቃ፥ ለድልና ስኬት ማብቃቱ።
- የመልዕክተኛው (ሶ.ዐ.ወ) ጀግንነት!

٨٢- التاسع: عَنْ أُمِّ الْمُؤْمِنِينَ أُمِّ سَلَمَةَ -واسْمُهَا هِنْدٌ بِنْتُ أَبِي أُمَيَّةَ حُذَيْفَةَ الْمَخْزُومِيَّةَ رَضِيَ اللهُ عَنْهَا أَنَّ النَّبِيَّ ﷺ كَانَ إِذَا خَرَجَ مِنْ بَيْتِهِ قَالَ: ((بِاسْمِ اللهِ تَوَكَّلْتُ عَلَى اللهِ، اللَّهُمَّ إِنِّي أَعُوذُ بِكَ أَنْ أَضِلَّ أَوْ أُضَلَّ، أَوْ أَزِلَّ أَوْ أُزَلَّ، أَوْ أَظْلِمَ أَوْ أُظْلَمَ أَوْ أَجْهَلَ أَوْ يُجْهَلَ عَلَيَّ)) حَدِيثٌ صَحِيحٌ رَوَاهُ أَبُو دَاوُدَ وَالتِّرْمِذِيُّ وَغَيْرُهُمَا بِأَسَانِيدَ صَحِيحَةٍ قَالَ التِّرْمِذِيُّ حَدِيثٌ حَسَنٌ صَحِيحٌ وَهَذَا لَفْظُ أَبِي دَاوُدَ.

82- የሙእሚኖች እናት ኡሙ ሰለመህ (ረ.ዐ) ሕማቸው ሂንድ ቢንት አቡ ኡመየህ ሁዘይፈተል መኽዙምየህ ነው- እንዳስተላለፉት፥ ነቢዩ (ሶ.ዐ.ወ) ከቤታቸው በሚወጡበት ወቅት:- "በአላህ ስም! በአላህ ተመካሁ። አላህ ሆይ! ሌሎችን ከማጥመም፥ በሌሎች ከመጥመም፣ ሌሎችን ከማሳሳት፥ በሌሎች ከመሳሳትም፣ ሌሎችን ከመበደል፥ በሌሎች ከመበደልም፣ ክፉ ከመፈፀም፥ ከማስፈፀምም በአንተ እጠበቃለሁ።" ይሉ ነበር።
(ሶሒሕ የሐዲስ ዘገባ ነው። አቡዳውድ፣ ቲርመዚይና ሌሎችም ዘግበውታል። ቲርመዚይ:- "ሐሰኑን ሶሒሕ" ብለውታል። የዘገቡው ቃል የአቡ ዳውድ ነው)

ከሐዲሱ የምንማራቸው ቁምነገሮች

- ከቤት በሚወጡበት ወቅት ይህንን ዱዓ ማድረግ የተወደደ ነው። የነቢዩን አርአያነት ለመከተል፣ መልካም ሁኔታም ለመገጠም፣ ከጥመት፣ ከስህተት፣ ከበደልና ከጥፋት መታቀብ ይቻል ዘንድም ራስን ለመምከር።
- ከስህተትና ጥፋት፥ የሐቅን ፍኖት ከመሳት ለመዳን የአላህን ጥበቃ በመሻት ወደ አላህ መመለስ ተገቢ ነው።

٨٣- العاشر: عَنْ أَنَسٍ ﷺ قَالَ: قَالَ رَسُولُ اللهِ ﷺ: ((مَنْ قَالَ -يَعْنِي إِذَا خَرَجَ مِنْ بَيْتِهِ- بِسْمِ اللهِ، تَوَكَّلْتُ عَلَى اللهِ، وَلَا حَوْلَ وَلَا قُوَّةَ إِلَّا بِاللهِ يُقَالُ لَهُ: هُدِيتَ وَكُفِيتَ وَوُقِيتَ،

83- አነስ (ረ.ዐ) እንዳስተላለፉት የአላህ መልዕክተኛ (ሶ.ዐ.ወ) ተከታዩን ተናግረዋል:- "(ከቤቱ በሚወጣበት ወቅት)፡- "በአላህ ስም! በአላህ ተመካሁ። ብልሃትም፥ ኃይልም የለም -በአላህ ቢሆን እንጂ!" ያለ፥ "ቅኑን መንገድ ተመራህ፣ ከምትፈልገው ሁሉ በቂ መጠጊያ

አገኘህ፣ ከክፉ ነገር ተጠበቅክ።" ይባላል። ሰይጣን ከርሱ ይገለላልም።"
(አቡ ዳውድ፣ ቲርሙዚይ፣ ነሳኢይና ሌሎችም ዘግበውታል። ቲርሙዚይ፦ "ሐሰን" ብለውታል።

وَكَنَحَّى عَنْهُ الشَّيْطَانُ)) رَوَاهُ أَبُو دَاوُد وَالتِّرْمِذِيُّ وَالنَّسَائِيُّ وَغَيْرُهُمْ، وَقَالَ التِّرْمِذِيُّ: حَدِيثٌ حَسَنٌ زَادَ أَبُو دَاوُدَ: فَيَقُولُ: -يَعْنِي الشَّيْطَانَ- لِشَيْطَانٍ آخَرَ: كَيْفَ لَكَ بِرَجُلٍ قَدْ هُدِيَ وَكُفِيَ وَوُقِيَ؟

አቡዳውድ ተከታዩን አክለዋል፦
"እንዱ ሰይጣን ለሌላው ሰይጣን፦ "ቀጥተኛውን መንገድ የያዘውን፣ በቂ መጠጊያ ያገኘውን፣ ከክፉ የተጠበቀውን ሰው በየት ብለህ ታጠቃዋለህ።" ይለዋል።"

ከሐዲሱ የምንማራቸው ቁምነገሮች

- በአላህ መመካትና በንግግርም ሆነ በተግባር ወደ አላህ መመለስ ከፍተኛ ጠቀሜታ አለው። ሙእሚን ከየትኛውም ክፉ ነገር እንዲጠበቅ ያበቃዋል።
- ከቤት ሲወጡ ከዘገባው ላይ የጠቀስነውን ዱዓ ማለት እጅግ ጠቃሚ ነው። የተገለፀውን መልካም ነገር ለማግኘት ይረዳል።

٨٤- وَعَنْ أَنَسٍ ﷺ قَالَ: كَانَ أَخَوَانِ عَلَى عَهْدِ النَّبِيِّ ﷺ وَكَانَ أَحَدُهُمَا يَأْتِي النَّبِيَّ ﷺ والآخَرُ يَحْتَرِفُ، فَشَكَا الْمُحْتَرِفُ أَخَاهُ لِلنَّبِيِّ ﷺ فَقَالَ: ((لَعَلَّكَ تُرْزَقُ بِهِ)) رَوَاهُ التِّرْمِذِيُّ بِإِسْنَادٍ صَحِيحٍ عَلَى شَرْطِ مُسْلِمٍ.

84- አነስ (ረ.ዐ) እንዲህ ሲሉ አስተላልፈዋል፦ በነቢዩ (ሶ.ዐ.ወ) ዘመን ሁለት ወንድማማቾች ነበሩ። አንደኛው ከነቢዩ (ሶ.ዐ.ወ) ዘንድ (ትምህርት ሲቀስም)፥ ሌላኛው ደግሞ በሥራ ተጠምዶ ይውሳሉ። ሠራተኛው ወንድሙን ከነቢዩ (ሶ.ዐ.ወ) ዘንድ ከሰሰ። ነቢዩም (ሶ.ዐ.ወ) "ምናልባትም "ሪዝቅ" የምታገኘው በርሱ ሰበብ ሊሆን ይችላል።" አሉት።
(ቲርሙዚይ "ሶሒሕ" በሆነ ሰነድ ዘግቦውታል)

ከሐዲሱ የምንማራቸው ቁምነገሮች

- የአላህን ዲንና ሸሪዐ ለመጠበቅ ሲል እውቀትን ፍለጋና ኢስላምን ለመረዳት የሚባክን አላህ መሠረታዊ ፍላጐቶቹን የሚያሟሉበትን መንገድ ያመቻችለታል።
- እውቀት ፈላጊዎችን መርዳት ተወዳጅ እንደሆነ።
- አንድ ሰው "ሪዝቅ" የሚያገኘው በሥሩ ባሉ ቤተሰቦቹ ሰበብ ነው።

رياض الصالحين

تأليف

الإمام أبي زكريا يحيى بن شرف النووي الدمشقي

٦٣١-٦٧٦هـ



مكتبة مؤسسة المحاشي

ص.ب: ٥٧٧٣٩٧ فاكس: ٥٧٧٣٩٦

البريد الكتروني: mgashi@tedata.net.jo